
# ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን

## ክፍል አንድ



በመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ
የሐዲስ ኪዳን ትርጓሜ መምህር፣በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የነገረ መለኮት የመጀመሪያ ዲግሪ ምሩቅ እና በፊሎሶፊ የማስተርስ ዲግሪ (BTH,MA)

2002 ዓ/ም

www.ethiopianorthodox.org

© መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

የጸሐፊው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved

ኹለተኛ እትም
የካቲት 2003 ዓ.ም

የአዘጋጁ አድራሻ
0 911 01 36 67 (0911-644726)
31274 Addis Ababa, Ethiopia
E-mail:rodastadese@yahoo.com

ከ ______________________

ማስታወሻ ______________________

______________________

______________________

______________________

______________________

ለ ______________________

ቀን ______________________



## መታሰቢያነቱ

እጅጉን ለምወዳቸውና ለማከብራቸው በሕይወተ ሥጋ ከዚህ ዓለም ለተለዩት ለእናቴ ለወ/ሮ በላይነሽ መንገሻ (መዐዛ ድንግል) እና ለሕፃን አቅሌስያ መስፍን (ወለተ ብርሃን)፤ በተጨማሪም ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን የአብነት መምህራንና ሰባክያነ ወንጌል ይኹንልኝ።

## ምስጋና

ከኹሉ በማስቀደም ይኽነን ሃይማኖታዊ መጽሐፍ እንዳዘጋጅ ያነሣሣኝ እንድፈጽመውም የረዳኝን በአንድነቱ ምንታዌ በሦስትነቱ ርባዔ የሌለበትን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስን አመሰግናለኹ። ዳግመኛም የነገረ ማርያም መጽሐፍን በማዘጋጅበት ጊዜ ኹሉ እርዳታዋ ያልተለየኝን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን አመሰግናለኹ።

በተጨማሪም የዚኽን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ በተለይም መልክአ ፊደላትን በትክክለኛ ቅርጻቸው እንዲቀመጡ በማድረግ ከጐኔ ያልተለዩትን የስዋስውና የጸዋትወ ዜማ ሊቅ የኾኑትን መምህር ዐምደ ወርቅ እስጢፋኖስን፤ የመጻሕፍተ ሐዲሳትና የመጻሕፍተ ሊቃውንት መምህር የኾኑት የሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር መልአከ ፀሐይ ታፈሰ ደሳለኝን፤ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ የቀሳውስትና የመምህራን ማሰልጠኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የሐዲሳት መምሕር መጋቤ ሐዲስ ደምፀ አንበርብርን፤ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ የሐዲሳት መምህር መጋቤ ሐዲስ ደጉ ዓለም ካሣን እና ለሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ የሐዲሳት መምሕር ለመጋቤ ሐዲስ እሸቱ ዓለምአየኹ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለኹ።

እንዲኹም ዲ/ን ቤተ ማርያምን፣መ/ር ሰሎሞን መንግሥቱን፣ መ/ር ኤርምያስ ዘመነን፣ ወ/ሮ መስታወት አክሊሉን፣ ወ/ት ምስርን፣ ወ/ት ቅድስት ሰሎሞንን ፣ወ/ሮ ገነት ዓለሙን፣ እኅቴ ብርሃናዊትን፣ሲ/ር አብረኸትን፣ ወጣት ነጻነትንና ስማቸውን ላልጠቀስኋቸው ጓደኞቼ ኹሉ ምስጋናዬን አቀርባለኹ።



www.ethiopianorthodox.org

- ደብተራ ኦሪት ........ 119
- ልብሰ አሮን ........ 122
- የወርቅ ማዕጠንት ........ 123
- ጣፋጭ ሽቱ ........ 125
- የሙሴ ጽላት ........ 126
- ገራህተ ሙሴ ........ 133


## ክፍል ሦስት


ነገረ ማርያም በኦሪት ዘኊልቊ

- የወይን ሐረግ ........ 137
- የአሮን የወርቅ ማዕጠንት ........ 139
- የአሮን በትር ........ 140


## ክፍል አራት


ነገረ ማርያም በኦሪት ዘዳግም

- ንጽሕት መሰክ ........ 143


## ምዕራፍ ኹለት


ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ኢያሱ እና በመጽሐፈ መሳፍንት ........ 146


## ክፍል አንድ


ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ኢያሱ

- የካሌብ ርስት ........ 146
- ምድረ ርስት ........ 148
- የኢያሱ የምስክር ሐውልት ........ 150


## ክፍል ኹለት


ነገረ ማርያም በመጽሐፈ መሳፍንት

- የባርቅ ኀይል ........ 152




www.ethiopianorthodox.org


- የማር ወለላ፤ ኅቱም መንሰከ አድግ፤ የሶምሶን ሹሩባ ........ 154
- የጌዴዎን ፀምር ........ 161


## ምዕራፍ ሦስት


ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ሳሙኤል ........ 163

- ታቦተ ጽዮን ........ 163
- የሳሙኤል የሽቱ ዕቃ ........ 172
- የዳዊት መሰንቆ ........ 173
- አውቴዝራማ ........ 174
- የኦርና ዐውድማ ........ 176


## ምዕራፍ አራት


ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ነገሥት ........ 179

- የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ........ 179
- የሰሎሞን ዙፋን (አትሮንስ) ........ 183
- የቀርሜሎስ መሠዊያ፤ የኤልያስ ደመና ........ 185
- የኤልያስ የወርቅ መሶብና የወገቡ መታጠቂያ ........ 187
- የኤልሳዕ ማሰሮና ማድጋ ........ 189
- ዐጽቀ በለስ ........ 192
- ማጠቃለያ ........ 194

ዋቢ መጻሕፍት ........ 198

# ማውጫ

ገጽ


መቅድም ........ ፰

መግቢያ ........ ፲፪


## ምዕራፍ አንድ


ነገረ ማርያም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ........ 1


## ክፍል አንድ

### ነገረ ማርያም በኦሪት ዘፍጥረት


- ዕለተ እሑድ ........ 2
- ታቦት ዘዶር ........ 3
- ዕለተ ሰኑይ ........ 5
- ዳግሚት ሰማይ ........ 5
- ደመና ........ 8
- ዕለተ ሠሉስ ........ 9
- ዕፀ ሕይወት ........ 11
- ዕፀ ገነት ........ 15
- ዕለተ ረቡዕ ........ 18
- ዕለተ ኀሙስ ........ 19
- ዕለተ ዐርብ ........ 20
- ዕለተ ቀዳሚት ........ 22
- ረዳኢተ አዳም ........ 22
- የአዳም ኅቱም ጉ ........ 25
- ዳግሚት ሔዋን ........ 26
- ብርሀት ዐይን ........ 33
- የክብር መጐናጸፊያ እና የበለስ ቅጠል ........ 35
- የሴቶች ኹሉ መመኪያ ........ 37
- የአዳምና የሔዋን ተስፋ ........ 39
- የሕያዋን ኹሉ እናት ........ 47
- የአቤል ደግነት ........ 48
- የሴት ቸርነት ........ 50
- የሔኖክ መልካም ሥራ ........ 51
- የኖኅ መርከብ ........ 53
- የኖኅ ርግብ ........ 55
- የኖኅ ቀስተ ደመና ........ 57
- የሴም ቡራኬው ዕድል ፈንታው፤ የማቱሳላ የዕድሜው ርዝማኔ፤ የላሜሕ ዕረፍት ........ 58
- የመልከ ጼዴቅ መሠዊያ ........ 61
- የአብርሃም ርግብ ........ 64
- የአብርሃም ዛፍና የአብርሃም ድንኳን ........ 66
- ዕፀ ሳቤቅ ........ 69
- የአብርሃም እርሻ ........ 72
- የርብቃ መታጨት ........ 73
- ሰዋስወ ያዕቆብ ........ 77
- የበረሓ እንኮይ ........ 81
- የያዕቆብ በትር ........ 83
- የያዕቆብ ትግል ........ 85
- የያዕቆብ ጥንካሬና በረከት ........ 89


## ክፍል ኹለት

### ነገረ ማርያም በኦሪት ዘፀአት


- ዕፀ ጳጦስ ........ 92
- ደመና ግብጽ፤ ደመና ሙሴ ........ 96
- ሥርጉት ደመና፤ የሙሴ በትር ........ 99
- መሶበ ወርቅ ........ 102
- የኮሬብ ቦታ ........ 104
- የሙሴ ክንድ ........ 106
- ደብረ ሲና ........ 109
- የቃል ኪዳን ታቦት ........ 114
- ማዕድ ........ 116
- መቅረዝ ........ 117




www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

ይኸ ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተሰኘው የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር የሚገልጸውን የሃይማኖት መጽሐፍና ሌሎች ተከታታይ በርካቶች መጻሕፍትን ለመጻፍ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር አደርግ ነበር። ይኸውም በቤተክርስትያናችን ከፍተኛ የኾነውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ስማር በነበረ ጊዜና በመምህርነት ተመርቄ በማስተምርበት በምመረምርበት ጊዜ፤ ስለኹ አግዛ እንዲኾነኝ የቅዱሳት መጻሕፍት ከፍተኛ ሰውቀት የነበራቸውን ጥንታውያን የኢትዮጵያ ሊቃውንት ያስተማሩትን የነገረ ማርያም አስተምህሮና፤ ወደ እኛ ቋንቋ በተለያየ ጊዜ የተተረጐሙ የነገረ ማርያም ትምህርቶችን በጥልቀት እመረምራቸው ነበር።

የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀት የነበራቸው ጥንታውያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ሊቃውንት ለቤተክርስቲያኒቱ ጽፈው ካበረከቱት እጅግ ከሚያስደንቁ የነገረ ማርያም መጻሕፍት መኻከል አንቀጸ ብርሃን፤ አርጋኖን፤ መጽሐፈ ሰዓታት፤ ሕይወተ ማርያም፤ እንዚራ ስብሐት፤ ሞገተ ብርሃን፤ መዐዛ ቅዳሴ፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ሰቆቃወ ድንግል፤ መዝሙረ ድንግል፤ ሰላምታ፤ ከዐሥር በላይ የቅድስት ድንግል ማርያም የመላዎቹ ሕዋሳቷን ክብር የሚገልጹ መልኮች፤የተለያዩ ትርጓሜዎች እና ሌሎች እጅግ በርካቶች መጻሕፍት ሲኖሩን፤ በትርጉም የመጡልን የቅዱስ ኤፍሬም፤ የቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ፤ የቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ የአባ ሕርያቆስ፤ የእስክንድርያው ቴዎፍሎስ፤ የእስክንድርያው ጢሞቴዎስ እና የሌሎች ሊቃውንት የነገረ ማርያም ትምህርቶችን ለማየትና ለመመርመር አስችሎኝ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

በተጨማሪም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብቼ የዐምስት ዓመት መደበኛ የዲግሪ መርሐ ግብርን እከታተል በነበረ ጊዜ በቤተ መጻሕፍቱ የሚገኙና በሌሎች ታላላቅ ቤተ መጻሕፍት በተጨማሪም ከሌሎች ብዙ ምንጮች ወደኛ ቋንቋ ያልተመለሱ እጅግ ሰፊና ጥልቅ የኾኑ የቤተክርስትያን ቅዱሳን አበው ያስተማሯቸውን የነገረ ማርያም ትምህርቶችን ለመረዳት ሰፊ ያለ ጊዜን አግኝቻለኍ።

ከእነዚኽ መኻከል ከሐዋርያት ቀጥለው የቀናውን ትምህርት ያስተማሩ ተላውያን ሐዋርያት (Apostolic Fathers) በመባል ከሚታወቁት ከቅዱሳን አበው መኻከል «ምጥው ለአንበሳ» በመባል የሚታወቀው በአንጾኪያ ቤተ ክርስትያን ከቅዱስ ጴጥሮስ በመቀጠል በሦስተኛነት የተሾመው አግናጥዮስና፤ የወንጌላዊ ዮሐንስ ተማሪ የፓሊካርፕ ባልንጀራ የነበረው የኄራጶሊሱ ጳጳስ ፓፒየስ (፷-፻፶ ዓ.ም) ያስተማሩትን ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርትን፤ ዳግመኛም ከእነዚኽ ቅዱሳን አበው ቀጥለው በክርስቶስ ደም የተመሠረተችውን ቤተ ክርስትያን ከተለያዩ የክሕደትና የምንፍቅና ትምህርቶች የጠበቋት ዐቀብተ እምነት (Apologist) ከሚባሉት አበው ሊቃውንት መኻከል የአቴንሱ አርስቲደስ፤ ሰማዕቱ ጀስቲን (ዮስቲኖስ) (+፻፷፭ ዓ.ም)፤ የሰርዴሱ ጳጳስ ሚሊቶ፤ የአቴንሱ አታናጎራስ፤ የፓሊካርፕ ተማሪ የነበረው ሄሬኔዎስ (፪፻፫ ዓ.ም)፤ እስክንድርያዊዉ ቀሌምንጦስ (፻፶-፪፻፲፭ ዓ.ም)፤ የካርቴጁ ጠርጠሉስ (ተርቱልያን) (፻፷-፪፻፳ዓ.ም)፤ የሄሬኔዎስ ተማሪ የሂፓሊተስ እጅግ አስደናቂ የነገረ ማርያም ጥልቆች ትምህርቶችን፤በተጨማሪም የወርቃማው ዘመን ሊቃውንት (The Golden Age Fathers) በመባል ከሚታወቁት ውስጥ የእስክንድርያው ሊቅ ቅዱስ አትናቴዎስ (፪፻፺፮-፫፻፸፫ ዓ.ም)፤ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያ (፫፻፳፱-፫፻፸፱ ዓ.ም)፤ ቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘእንዚናዙ (፫፻፳-፫፻፺ ዓ.ም)፤ ቅዱስ ጎርጎሬዎስ ዘኑሲስ (፫፻፴፭-፫፻፺፭ ዓ.ም)

፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (፫፻፵፬-፬፻፯ ዓ.ም)፤ የእስክንድርያው ቅዱስ ቄርሎስ (፬፻፲፪-፬፻፵፬ ዓ.ም) ፣ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ (፫፻፮-፫፻፸፫ ዓ.ም)፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ (፬፻፶፩-፭፻፳፩ ዓ.ም)፣ ሳዊሮስ ዘአንጾኪያ (፬፻፷፭-፭፻፴፰ ዓ.ም) እና ሌሎች በርካቶች የቤተክርስትያን ሊቃውንት ያስተማሩት ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርቶች ይገኙበታል።

እኔም በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ይሰጥ የነበረውን የነገረ መለኮት ትምህርት ሳጠናቅቅ እኒኽ ኹሉ ሊቃውንት ካስተማሩት ከውቅያኖስ ይልቅ ከጠለቀው የነገረ ማርያም ትምህርት ውስጥ ከዐራት መቶ በላይ ታላላቅ የሃይማኖት መጻሕፍትን የጻፈውና የቤተ ክርስትያን ታሪክ ተመራማሪው ጸሓፊው ሶዘመን ጽሑፎቹ በመሥመር ቢቆጠሩ ሦስት ሚሊዮን እንደሚመሉ ባደረገው ጥልቅ ጥናት የመሰከረለት፤ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ጣዕመ ውዳሴዋ በእጅጉ የበዛለት ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም የጻፈውንና ያስተማረውን የነገረ ማርያም አስተምህሮውን ‹‹Mariological themes in the writings of St. Fphrem the Syrian›› በሚል ርእስ የመመረቂያ ጽሑፌን ጽፌያለኊ፤ ልዑል እግዚአብሔር ቢፈቅድ የመመረቂያ ጽሑፌን ጨምሮ ከላይ የጠቀስኳቸው በርካቶች ሊቃውንት ያስተማሩትን ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርቶችን በሚቀጥለው መጽሐፎቼ አዘጋጅቼ የማቀርበው ይኾናል።

አኹን ባዘጋጀኹት ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በሚለው በክፍል አንድ መጽሐፌና፤ በመቀጠል በማቀርበው በክፍል ኹለት የነገረ ማርያም መጽሐፍ ላይ ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር በብሉይ ኪዳን በትንቢት ከተነገሩት በምሳሌ ከተመሰሉት ከኦሪት ዘፍጥረት አንስቶ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ያሉትን፤ በኹለት ክፍሎች ከቤተክርስትያን የነገረ መለኮት ምሁራን አንጻር የተነተንኩት ሲኾን፤ በቤተክርስቲያናችን ቋንቋ





በግእዝ እና በሌሎች ቋንቋዎች የተጠቀሱት ጥቅሶች በዐማርኛ ሲተረጐሙ አንባቢው ምንጮቹን በቀላሉ ለማግኘት እንዲችል በግርጌ ማስታወሻ (Foot Note) ሥር አስቀምጬዋለኊ።

ይኸም መጽሐፍ በአራት ታላላቅ ምዕራፍ የተከፈለ ሲኾን የመጀመሪያው ምዕራፍ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያሉትን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌዎችን ሲያብራራ፤ ምዕራፍ ኹለት ከመጽሐፈ ኢያሱ እስከ መጽሐፈ መሳፍንት ያሉትን ምሳሌዎች ያብራራል፤ ሦስተኛው ምዕራፍ በመጽሐፈ ሳሙኤል ያሉትን በርካቶች የነገረ ማርያም ምሳሌዎችን በስፋት ሲይዝ አራተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ በመጽሐፈ ነገሥት ያሉትን ምሳሌዎች ይተነትናል፤በተጨማሪም ይኽ የነገረ ማርያም መጽሐፍ ካለው የሃይማኖት ምስጢር ባሻገር የጽሑፉ የፊደላቱ መልኮች በሥርዓቱ ተስተካክለዋል።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ



www.ethiopianorthodox.org

# መግቢያ

ይኽ የነገረ ማርያም (Mariology) ትምህርት ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ከፅንሰቷ ገሮምሮ እስከ ዕርገቷ ያለውን የሕይወቷን ታሪክ ብቻ የሚያጠና ሳይኾን፤ ስለ አምላክ እናትነቷ፣ ስለ ዘላለማዊ ድንግልናዋ፤ በነገረ ሥጋዌ ስላላት ድርሻ፣ ስለ ንጽሕናዋ ቅድስናዋ፤ ስለተሰጣት ክብር ጨምሮ የሚያጠና የሚያካትት የሃይማኖት ትምህርት ክፍል ነው፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ጥንታውያን ሊቃውንት ነገረ ሥጋዌ (ክርስቶስ) (Christology) ከነገረ ማርያም ጋር ያለውን ታላቅ የምስጢር ግንኙነት በመረዳታቸው፤ ምስጢረ ሥጋዌን ከመማራቸው፣ ከማስተማራቸው አስቀድሞ ነገረ ማርያምን በጥልቀት ይማሩና ያስተምሩ ነበር፤ ይኸውም በተለያዩ የአዕማደ ምስጢር መጽሐፎቻቸው የምናገኘው ሲኾን በትምህርታቸውም ነገረ ማርያም ዋሃይማኖት ክፍል መኾኑን አብራርተው ገልጠዋል፡፡ ምክንያቱም ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ እናት የተወለደው ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አካላዊ ቃል ፭ሺሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወለደ፤ እሱ በእውነት የባሕርይ አምላክ ነው፤ እሷ በእውነት የአምላክ እናት ናት ብሎ ማመን መመስከር ሃይማኖት ነውና፡፡

ጥንታዊትና፤ ሐዋርያዊት የኾነችው ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም በሐዋርያት አመክንዮ በቍጥር ፫፻-፳፭ ላይ ‹‹የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት እግዚአብሔር አንድ ነው፤ ዓለም ሳይፈጠር የተወለደ፤ ከርሱ ጋራ የተካከለ የሚኾን አንድ ልጅ፤ ሰራዊትንና ሢመታትን





ሥልጣናትንም ኹሉ የፈጠረ፤ በኋለኛው ዘመን ሰው ይኾን ዘንድ የወደደ፤ ያለ ዘርዐ ብእሲ ቅድስት ከምትኾን ከእመቤታችን ከድንግል ማርያም ሥጋን ነሣ›› በማለት የዓለማት ኹሉ ፈጣሪን በሥጋ የወለደችው መኾኗን ትመሰክራለች፡፡

በዚኽም ምክንያት ክብሯ ከመላእክትና ከደቂቀ አዳም ከፍ ከፍ ያለ በመኾኑና፤ የባሕርይ አምላክ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና ጸንሳ በኅቱም ድንግልና የወለደች በመኾኗ እመ አምላክ (Theotokos)፣ ወላዲተ አምላክ፣ እመ እግዚአብሔር ጸባኦት፣ እመ ብርሃን፣ ማኅደረ መለኮት በማለት ሥያሜዋን ታስተምራለች፡፡ በሥጋዋና በኅሊናዋ ድንግል በመኾኗ ድንግል በክልኤ የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያም ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ ጽንዕት በመኾኗ ምክንያት አምላክን ስትወልደው ማኅተመ ድንግልናዋ አለመለወጡ' አምላክም ሰው ሲኾን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ፤ ዳግመኛም ድንግል ወእም ስትባል መኖሯ አምላክ ወሰብእ ሲባል የመኖሩን ይኽነን ታላቅ የሥጋዌ ምስጢር ያወቅንባት የተረዳንባት መኾኗን አብክሮ ታስረዳለች፡፡

በተጨማሪም እናትነትን ከድንግልና፤ ድንግልናን ከእናትነት ጋር አስተባብራ የተገኘችና፤ በድንግልናም እያለች ከጡቶቿ ወተት ተገኝቶ በዝናም አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግብ መጋቤ ፍጥረታት አምላክን የመገበች፤ እሳታውያን የሚኾኑ ኪሩቤል ሱራፌል በፍርሀት በረዐድ ኾነው ዙፋኑን የሚሸከሙት እሳተ መለኮት ጌታን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፤ በክንዷ የታቀፈች፤ በገርባዋ ያዘለች እናትነትን ከድንግልና፤ አገልጋይነትን ከእናትነት፤ ወተትን ከድንግልና ጋር አጣምራ የያዘች ምልዕተ ክብር ምልዕተ ጸጋ መኾኗን ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ



www.ethiopianorthodox.org

ስትመሰክርላት ትኖራለች።

ስለዚህም ይህንን ጥልቅ የሃይማኖት ትምህርት ለኹሉ ማሳወቅ ተገቢ በመኾኑና፤ ምእመናንም በተለያዩ ዘመን በመጡ በክሕደት ትምህርቶች ተታልለው፤ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱሳን አበው ትምህርት ከተመሠረተውና ከጸናው የነገረ ማርያም አስተምህሮ ተለይተው ወደ ስሕተት መንገድ እንዳይገቡ፤ ስተው የኼዱትም እውነታውን ዐውቀው ወደ ትክክለኛው ትምህርት ለመመለስ መሪ እንዲኾናቸውና፤ በተጨማሪም ፈ"ፈ እግዚአብሔር በፈቃድ ወደ ፊት በተከታታይ ብዙ የነገረ ማርያም መጻሕፍትን የምጽፍ በመኾኔ፤ በመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች የነገረ ማርያም ትምህርትን ለሚያስተምሩ መምህራን መነሻ መምሪያ መጽሐፍ (text) ኾኖ እንዲያገለግላቸው ከውቅያኖስ ይልቅ እጅግን ከሚሰፋውና ከሚጠልቀው ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ይኽንን መግቢያውን ክፍል ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ አገርምራለሁ።

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ





# ምዕራፍ አንድ
# ነገረ ማርያም ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም

## ክፍል አንድ
## ነገረ ማርያም በኦሪት ዘፍጥረት

ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ካም፣ ትውልደ ያፌት ብዕዕት ነሽ እያሉ የሚያመሰግኗት፤ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን አምላክ ፀወር ከኗቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፤ በክንዷ የታቀፈች፤ በገርባዋ ያዘለች፤ የድንግልና ጡቶቿን ያጠባች፤ ምልዕተ ጸጋ ምልዕተ ክብር ስለኾነችው ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕና፤ ቅድስና፤ ዘለዓለማዊ ድንግልናዋና ስለ አምላክ እናትነቷ ከኦሪት ዘፍጥረት አንስቶ እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ድረስ በተለያዩ ሕብረ ትንቢቶችና፤ ሕብረ አምሳሎች አስቀድመው ተገልጸው ነበር።

በእነዚኽ ኹሉ ዘመናትም የተገለጹትን እነዚኽን አምሳል ለመግለጽ መሞከር በዓለም ያሉ ውቅያኖሶችን ኹሉ በዕንቍላል ቅርፊት ቀድቶ እጨርሳለኍ ማለት ነውና፤ በመቅድመ ተአምር ላይ «ሚ ክርታስ ዘይጸውር ለዕበየ እግዝእትነ ማርያም ሶበ ተጽሕፈ ኵሉ አይ እዝን ዘይክል ሰሚዖቶ፤ ወአይ ልብ ዘይክል አግምሮቶ፤ ወአይ ኀሊና ዘይክል ኀልዮቶ ወአብጽሖቶ፤ ወባሕቱ ንስቲተ ንነግረክሙ መጠነ ተክህለ፤ እግዝእትነ ማርያም ተነግረት እምአዳም እስከ አብርሃም ወእምአብርሃም እስከ ሙሴ፤ ወእሙሴ እስከ ዳዊት



www.ethiopianorthodox.org

*ወልደ እሴይ በብዙኅ አምሳል አስተርአየትኒ»* (የእመቤታችን ማርያም ክብሯ፣ ምስጋናዋ ኹሉ ተጽፎ ቢኾን ምን ብራና በቻለው ነበር። ሊሰማው የሚቻለው ምን ገሮ ነው፤ ሊወስነውስ የሚችለው ምን ልብ ነው፤ ዐስቦ ሊደርሰውስ የሚችለው እንደምን ያለ ኅሊና ነው። ነገር ግን የተቻለንን ያኽል ከምስጋናዋ ጥቂት እንነግራችኋለን፤ እመቤታችን ማርያም ከአዳም ገምሮ እስከ አብርሃምና እስከ ሙሴ ድረስ ትነገር ነበር፤ ከሙሴ ገምሮ እስከ እሴይ ልጅ እስከ ዳዊትም ድረስ በብዙ ምሳሌ እየታየች ትነገር ነበር)[1] ብሎ እንደሚያስተምረን ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በመንፈስ እግዚአብሔር ገላጭነት «በመገርመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ብሎ ከገርመረው ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ መጨረሻው መጽሐፉ ኦሪት ዘዳግም ድረስ እጅግ የሚያስደንቁ፤ በርካቶች የነገረ ማርያም ትምህርቶች በስፋትና በጥልቀት ተገልጸው እናገኛለን።

እነዚኽ ምስጢራዊ ትምህርቶችንም ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከዚኽ በታች የዘረዘርኳቸው ሲኾን፤ አንባቢውም ጥልቁን የነገረ ማርያም የምስጢር በርን ለመክፈት ቁልፍ እንደሚኾነውም በማመን ከመገርመሪያዋ ምሳሌ ከዕለተ እሑድ አንሥቶ እስከ መጨረሻው ያሉትን የእመቤታችንን ምሳሌዎች ከዚኽ በታች በስፋት ገልጫቸዋለኊ።

## <u>ዕለተ እሑድ</u>

ፈጣሪ ዓለማት አምላካችንን በድንግልና የወለደችልን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዐሥራው ፍጥረታት የኾኑ አራቱ ባሕርያት በተገኙበት በዕለተ እሑድ ትመሰላለች ( ዘፍ ፩፥፩፤ ኩፋ ፪፥፳)። ሊቀ ነቢያት ሙሴ በዚኽች ዕለት ስለተገኙ ፍጥረታት በዘፍ ፩፥፩ ላይ *«በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር ሰማየ ወምድረ»* (እግዚአብሔር በመገርመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ) በማለት ሲገልጽ (በኩፋ ፪፥፳) ላይ ስንት ፍጥረታት እንደተገኙ ይገልጻል። እነዚኽም ዐሥራው ፍጥረታት (የፍጥረታት ሥሮች መገኛዎች) የኾኑ አራቱን ባሕርያት (እሳት፣ ውሃ፣ ነፋስ፣ መሬትን) ፤ ጨለማን (ዘፍ ፩፥፪) ፤ ሰባቱ ሰማያት ማለት (ጽርሐ አርያም (ዘዳ ፲፥፲፬፤፩ነገ ፳፥፳፯)፤መንበረ

1. መቅድመ ተአምር ቍ ፱-፲፬





መንግሥት (ኢሳ ፯፥፩፤ ሕዝ. ፩፥፳፯፤ ራእ ፬፥፪ )፤ ሰማይ ውዱድ (ሕዝ ፩፥፳፪-፳፯)፤ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት (፩ቆሮ ፪፥፱፤ ገላ ፬፥፳፯፤ ዕብ ፲፪፥፳፪፤ ራእ ፳፩፥፪-፲፬)፤ ኢዮር፤ ራማ፤ ኤረር (፪ቆሮ ፲፪፥፩-፫)፤ መላእክትና ብርሃን (ዘፍ ፩፥፫) ናቸው (ኩፋ ፪፥፳ )።

በዚኽ ዕለት የተገኙ እነዚኽ አራቱ ባሕርያት የፍጥረት ኹሉ መገኛዎች ናቸው፤ ከመላእክትና ከነፍስ በስተቀር ከነዚኽ ከአራቱ ባሕርያት ያልተፈጠረ አንዳችም ፍጥረት የለም። ሊቁ ኤጲፋኒዮስ በአክሲማሮስ ላይ *«ወአልቦ ምንትኒ ዘኢተፈጥረ እምእሉ አርባዕቱ ጠባይዓት ዘእንበለ መላእክት»* (ከመላእክት በቀር ከነዚኽ ከአራቱ ባሕርያት ያልተፈጠረ ምንም ምን የለም)[2] በማለት ዐሥራው ፍጥረት መኾናቸውን ተናግሯል። አዝርዕት፣ አትክልት፣ ዕፀዋት እንኳ የውሃ ባሕርይ እንዳላቸው ለማጠየቅ ቁልቋል፣ ቅንጭብት የወንቸው እንደ ኾነ ደም፣ ውሃ፣ ወተት የመሰለ ይፈሳቸዋል። የእሳት ባሕርይ እንዳላቸው ለማጠየቅ አስታንና ዶግን ቢሰብቁዋቸው እሳት ይወጣቸዋል። የነፋስ ባሕርይ እንዳላቸው ለማጠየቅ ይናወጻሉ። የመሬት ባሕርይ እንዳላቸው ለማጠየቅ በመሬትነታቸው ያድጋሉ፣ ይገዘፋሉ፣ በምሳር (በመጥረቢያ) ተቈርጠው በወደቁ ጊዜ ይፈርሳሉ ይበሰብሳሉ፣ አፈር ትቢያ ይኾናሉ።

በመኾኑም እነዚኽ የፍጥረት ኹሉ መገኛዎች የኾኑ አራቱ ባሕርያት በፈቃደ አምላክ በዚኽች በዕለተ እሑድ እንደተገኙ ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም ለዘኮነ ምክንያተ ፍጥረት በህላዌሁ የተባለ ይኽነን ዓለም እምኀበ አልቦ ኀበቦ (ካለመኖር ወደ መኖር) አምጥቶ የፈጠረ፣ ያለሱ ቃልነት፣ ያለሱ ህልውና ምንም ምን የተፈጠረ የሌለ (የፍጥረታት አስገኝ)፣ አምጻኤ ዓለማት፤ ፈጣሬ ዓለማት ጌታን በግብረ መንፈስ ቅዱስ በነቱም ድንግልና ሆንሳ በነቱም ድንግልና ወልዳ አስገኝታለችና በዕለተ እሑድ ተመስላባታለች (ዮሐ ፩፥፫፤ ፩ቆሮ ፳፥፯፤ ኤፌ ፪፥፲፤ ቆላ ፩፥፲፭-፲፯)።

## <u>ታቦት ዘዶር</u>

የአምላክ ታቦት (ማደሪያ) የኾነች ቅድስት ድንግል ማርያም በኢየሩሳሌም ሰማያዊት በምትገኘው ታቦት ትመሰላለች። እግዚአብሔር አምላክ

2. ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፤ መጽሐፈ አክሲማሮስ



www.ethiopianorthodox.org

በዚኽች በዕለተ እሑድ ከፈጠራቸው ከሰባቱ ሰማያት አንዷ በመንበረ መንግሥት አንፃር ያለችው ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ትገኛለች (ገላ ፬፥፳፮፤ ዕብ ፲፪፥፳፪)፤ ይኽቺውም ሰማይ እንደ ቤተ መቅደስ አራት ማእዘን ያላት ስትኾን፤ ዐሥራ ኹለት ደጃፎች አሏት፤ በዚያም የብርሃን አዕማድ ደግፎ የብርሃን ክዳን ከፍክፎ ፤ዙሪያዋን በከዋክብት አምሳል የብርሃን መርገፍ አዙሮባታል፡፡

ዮሐንስ ወንጌላዊ ስለ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ነገር በራእዩ ላይ ‹‹የእግዚአብሔር ክብር ያለባትን ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አሳየኝ፤ ብርሃንዋም እጅግ እንደከበረ ድንጋይ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ ኾኖ እንደ ብርሌ የጠራ ነበር፤ ታላቅና ረዥም ቅጥር ነበራት፤ ዐሥራ ኹለትም ደጆች ነበሯት›› (ራእ ፳፩፥፲፩-፲፪) በማለት ተናግሮላታል፡፡

በዚኽች በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ጌታ ወርዷ ቁመቷ የተስተካከለ የብርሃን ጽላት ቀርጾ በውስጧ አኑሯል (ራእ ፲፩፥፲፱)፡፡ ይኽቺውም ታቦት ዘዶር ተብላ ትጠራለች፤ ሊቁ ኤጲፋኒዮስ የሥነ ፍጥረትን ነገር በሚናገረው መጽሐፉ *‹‹ወውስቴታ ታቦት ዘዶር ዘየበርህ በጸዳለ ሥሉስ ቅዱስ››* (በሥላሴ ጸዳል የሚያበራ ታቦት ዘዶር በውስጧ (በኢየሩሳሌም ሰማያዊት) አለ)[3] በማለት የተናገረላት ይኽቺ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ያለችው ታቦት ዘዶር የአማናዊት ታቦት የሥላሴ ማደሪያ የኾነቺው በምድረ ኢየሩሳሌም የተገኘችው የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፡፡

ይኸውም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልኮ ቅድስት ድንግል ማርያምን የአምላክ ታቦት (ማደሪያ) መኾኗን ‹‹መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፤ የልዑል ኀይል ይጸልልሻል፤ ስለዚኽ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል›› (ሉቃ ፩፥፴፭)፤ በማለት አጕልቶ መስክሮላታል፡፡ ይኽነን ምስጢር በጥልቀት የተረዳ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ *‹‹ወውስቴታ ታቦት ዘዶር እንተ ይእቲ እግዝእትነ ማርያም››* (ከነርሱም ጋራ ታቦት ዘዶር ወዳለችበት ያግባችኊ፤ ይኽቺውም እመቤታችን ማርያም ናት)[4] በማለት ታቦት ዘዶር የእውነተኛዪቱ የአምላክ ታቦት የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን አጕልቶ ገልጾታል፡፡

3. ዝኒ ከማሁ
4. አባ ሕርያቆስ ፤ቅዳሴ ማርያም ቍ ፻፶፱





## ዕለተ ሰኑይ (የሰኞ ዕለት)

የብርሃን የክርስቶስ እናቱ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የብርሃን ማኅደር የኾነው ጠፈር በተገኘባት በሰኞ ዕለትና በሰማይ መመሰሏን በርካቶች ሊቃውንት ተናግረዋል (ዘፍ ፩፥፮-፰)፡፡

ይኸውም በዚኽ ዕለት እግዚአብሔር አምላክ ከምድር ገፀምሮ እስከ ብሩህ ሰማይ መልቶ የነበረውን ውሃ ከሦስት እጅ በመክፈል፤ አንዱን እጅ ከጠፈር በላይ አኑሮታል ስሙ ሀኖስ ይባላል፤ አንዱን እጅ በጽንፈ ምድር ወስኖታል ስሙ ውቅያኖስ ይባላል፤ አንዱን እጅ በመኻከል አጽንቶ የብርሃን ማኅደር አድርጎ ፈጥሮታል ይኽ የምናየው ሰማይ ነው ጠፈር ይባላል (ኩፋ ፪፥፱) ፡፡ ይኸውም ሰኞ ዕለት የብርሃን እናቱ የድንግል ማርያም ምሳሌ ሲኾን ፤ ብርሃን የዓለም ብርሃን የክርስቶስ ምሳሌ፤ ሰማይ አማናዊ ብርሃን ጌታ ከእመቤታችን የነሣው ሥጋ ምሳሌ መኾኑን መተርጕማን አስተምረዋል (ማቴ ፲፯፥፪፤ ዮሐ ፩፥፫-፱፤ ፰፥፲፪፤ ፲፪፥፵፮፤ ኤፌ ፭፥፰-፲፬፤ ፲፫፥፲፬፤ ፩ጢሞ ፮፥፲፮፤ ፩ዮሐ ፩፥፭፤ ያዕ ፩፥፲፯)፡፡

## ዳግሚት ሰማይ (ኹለተኛዪቱ ሰማይ) Second Heaven

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ዳግሚት ሰማይ የመኾኗን ምስጢር ብዙ የነገረ መለኮት ምሁራን አስተምረዋል፡፡ ከነዚኽ ከታላላቆቹ ሊቃውንት መኻከልም ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግና ኢትዮጵያዊው አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይጠቀሳሉ፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እመቤታችንን ባመሰገነበት በረቡዕ ምስጋናው *‹‹ሰማይ ዳግሚት ዲበ ምድር››* (ከምድር በላይ ያለች ኹለተኛይቱ ሰማይ)፤ በማለት ሰማይ የፀሓይ መገኛ እንደኾነች ኹሉ እመቤታችን ማርያምም የፀሓየ ጽድቅ የክርስቶስ እናት የመኾኗን ነገር በማነጻጸር አስተምሯል፡፡

ዳግመኛም በቅዳሜ ዕለት ምስጋናው ይኽነን በማጕላት *‹‹ኮንኪ ዳግሚተ ሰማይ ዲበ ምድር ኦ ወላዲተ አምላክ ዘአንበለ ርኩስ ሠረቀ ለነ እምኔኪ ፀሓየ ጽድቅ››* (አምላክን ያለ መለወጥ የወለድሽው ሆይ የምድር ኹለተኛ ሰማይን ኾንሽ፤ እውነተኛ ፀሓይ ካንቺ ወጥቶልናልና) በማለት ይኽ ሶርያዊ ሊቅ ኤፍሬም ምስጢሩን ሲገልጸው፤ በጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀቱ



www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *‹‹ኦ ሰማይ ዳግሚት ዘወለደቶ ለፀሐየ ጽድቅ ዘውእቱ ብርሃነ ቅዱሳን ዘሰደደ ለጽልመት* (ጨለማን ያሳደደውን (ያስወገደውን) የቅዱሳን ብርሃን የሚኾን አማናዊ ፀሐይን የወለደችው ኹለተኛይቱ ሰማይ ሆይ)[5] በማለት ጨለማን ከሚያስለቅቀው ፀሐይ ይልቅ፤ በጨለማና በሞት ጥላ ሥር ለነበሩ ኹሉ ብርሃን የኾናቸው ፀሐይ ዘኢየዐርብ (የማይጠልቅ ፀሐይ)፣ የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ፈጣሪያችንን የወለደችልን የፀሐየ ጽድቅ የጌታ መገኛ የኾነች ኹለተኛዪቱ ሰማይ ድንግል ማርያም መኾኗን አስተምሯል።

በጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀቱ የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በትምህርቱ ‹‹ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድር የእግሬ መረገጫ ነው›› (ኢሳ ፷፮፥፩) ብሎ የተናገረው ጌታ ዘመኑ ሲፈጸም ኹለተኛይቱ ሰማይ በተባለች በድንግል ማርያም ማሕፀን ያድር ዘንድ ፈቃዱ መኾኑን ዳግሚት ሰማይ *(second heaven)* በሚለው መጽሐፉ ሲገልጽ‹‹ And because the great heaven and a small womb are worthy of him...›› (ታላቅ ሰማይና ታናሽ ማሕፀን ለማደሪያው ይገቡታልና፤ በዚኽም ሊወሰንና ሊመጠን የማይችል በኹሉም ያለ መኾኑን አስረዳ፤ ወልድ የሌለበት የአብ ዕቅፍ (ዕሪና) የለም፤ ግን በማሕፀን ተወስኗልና፤ በሰማይ በኹሉ ቦታ አለና፤ በሰማይ አልጎደለም በምድርም አልጨመረም፤ የሰማይ ስፋት ለእርሱ ሰፊ አይደለም፤ ከእነርሱ ስፋት በላይ ነውና፤ የታናሽ አገልጋይ የድንግል ማሕፀን ለእርሱ ትንሽ አይደለም፤ ራሱን ሊወስን ደግሞም ወሰን የሌለው ሊያደርግ ይቻለዋልና፤ ከሰማያት ወርዶ በማሕፀኗ ዐደረ...)[6] በማለት ዙፋኑ ሰማይንና የአምላክ ማደሪያ የኾነውን የእመቤታችንን ማሕፀን በማነጻጸር አስተምሯል።

ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ በዚኽ ሃይማኖታዊ ትምህርቱ ድንግል ማርያምንና ሰማይን ቢያነጻጽርም እንኳ፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ክብር ከሰማይ ይልቅ እጅግ የራቀና የመጠቀ መኾኑን ሳያስተምር አላለፈም፤ ምክንያቱም ድንግል ማርያም በሰማይ ብትመሰልም እንኳን ሰማይን የፈጠረ፤ በሰማይ ዐድሮ በሰማያውያን መላእክት ሲመሰገን የሚኖር ጌታን በድንግልና

5. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፭+፲፩
6. Jacob of Serug,On the visitation p 68





ፀንሳ በድንግልና ወልዳዋለች፤ የድንግልና ጡቶቿን አጥብታዋለች እሱ ልጇ፣ እሷ እናቱ በመኾኗ ከሰማይ ይልቅ እጅግ ትበልጣለች።

ይኽ የሰማይና የእመቤታችን የመበላለጣቸውን ምስጢር ይኸው ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ በመጽሐፉ ላይ ‹‹Heaven and Mary were for him equal when he dwelt in her, yet not equal,...››(ሰማይም እመቤታችን ማርያምም ለአምላክ ማደሪያነት እኩል ኾኑ፤ በድንግል ማሕፀን ባደረ ጊዜ ግን እኩል አይደሉም፤ ለሚያስተውል አምላክ ማደሪያው ትኾን ዘንድ መርጧታልና፤ እመቤታችን ማርያም ታላቅ ኾነች። ሰማይ ዙፋኑ ነው፤ እመቤታችን ማርያም ግን እናቱ ናት፤ እንሆ እመቤታችን ማርያም በለጠች፤ ዙፋን ከእናት ጋር አይነጻጸርምና፤ ሰማይንና እመቤታችን ማርያምን መረጠ፤ አንዱን ዙፋኑ አንዷን እናቱ እንዲኾኑ ዐደረገ፤ እመቤታችን ማርያምን ሰማይ አልልም፤ ክብሯን ማሳነስ ነውና፤ የንጉሥ እናትን በዙፋን አምሳል ላነጻጽራት ከቶ አይገባምና፤ አንተ ጥበበኛ እስቲ ፍረድ? የትኛው ይበልጣል? ሰማይ እናቱንና አንድያ ልጇን ይዛል? ከኹለቱ የትኛው እጅግ የከበረ ነው? ማናቸው ለወልድ ይቀርባሉ? ማናቸው ከእርሱ ጋር ተዋሕደዋል፤ ሰማይ ለተወለደው ሕፃን ለክርስቶስ ወተት አልሰጠውም፤ በእመቤታችን ማርያም ዕቅፍ ውስጥ ኾኖ ግን ጡቶቿዋን ጠባ፤ ሰማይ አልፀነሰችውም፣ አልወለደችውም፣ አልመገበችውም ማርያም ግን ወለደችው፣ ዐቀፈችው፣ አሳደገችው ለእርሷ ክብር ይገባል)[7] በማለት እናትና ልጅ ያላቸውን ግንኙነት በቃላት ሊገለጽ የማይችል እጅግ ጥልቅ በመኾኑ፤ ኹለተኛዪቱ ሰማይ ተብላ በሰማይ ብትመሰል እንኳ ክብሯን ቅድስናዋን እናትነቷን በደንብ ሊገልጽ የማይቿል ውሱን መኾኑን ገልጿል።

ታላቁ የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድም በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ምስጢሩን እንደ ወርቅ እንክብሎ እንደ ሸማ ጠቅሎ *‹‹አንቲ ውእቱ ሀገረ አርያም ዘበሰማያት ዘኮንኪ አርያመ በዲበ ምድር››* (በሰማይ ስላለ አርያም ፈንታ በምድር ላይ ያለ አርያምን የኾንሽ አንቺ ነሽ)[8] በማለት አመስግኗታል።

7. ibid p 69
8. ቅዱስ ያሬድ፣ አንቀጸ ብርሃን፤ ቍ ፩



www.ethiopianorthodox.org

## ደመና

የሕይወት ውሃ ጌታን በማሕፀኗ የተሸከመች በክንዷ የታቀፈች ቅድስት ድንግል ማርያም የዝናምን ውሃ በያዘች ደመና ትመሰላለች። ይኸውም በሰኞ ዕለት የተፈጠረውን የጠፈርን ነገር ስንናገር በዚኽ ዕለት በሰማይ የሚታይ ዝናምን የሚሸከም የደመና ተፈጥሮን ማወቅ ይገባናል፤ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ስለ ደመና ተፈጥሮ በመዝሙር *«ያዐርግ ደመናተ እምአጽናፈ ምድር»* (ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል) መዝ ፻፴፬፥፯ በማለት እንደተናገረ፤ እግዚአብሔር አምላክ በሰኞ ዕለት እስከ ብሩህ ሰማይ መልቶ የነበረውን ውሃ ከሦስት በከፈለው ጊዜ፤ መሬት ነፋስ አልነፈሰባትም፤ ፀሓይ አልወጣባትም ጭቃ ኹና ነበር፤ ያን ጊዜ ዐሥራ ኹለቱ ነፋሳትን አውጥቶ መሬትን አስመትቷታል (ሔኖ ፫፥፷፩፤፷፫፥፩-፲፰)። የምሥራቁ ነፋስ ወደ ምዕራቡ፤ የምዕራቡ ወደ ምሥራቁ፤ የሰሜኑ ወደ ደቡቡ፤ የደቡቡ ነፋስ ወደ ሰሜኑ በመላለሱባት ተራራው ኮረብታማ ደንጊያው በብረት የማይወቀር እስኪኾን ድረስ ጸና ረጋ፤ ያን ጊዜ ከደረቅ መሬት ደረቅ ጢስ ከርጡብ ባሕር ርጡብ ጢስ ተጠቅልሎ ወጥቶ አንድ ደመና ኾኗል (ሔኖ ፲፯፥፴፱) ።

ይኽ ደመና ታላቅ አገልግሎት አለው፤የዝናም ውሃን ከውቅያኖስ ቋጥሮ በሰማይ ይታያል። ዝናም ተሸክሞ የሚታይ ደመና እንዳለ ኹሉ የዝናም ውሃን ያልቋጠረ ደመናም በሰማይ ይታያል። ለምሳሌ በግንቦት የሚታይ ደመና በሰማይ ከዞረ በኋላ ሳያዘንብ ይበተናል፤ በሐምሌ በነሐሴ የሚታይ ደመና ግን ከዞረ ዝናም ሳያዘንብ አይበተንም፤ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በመዝ ፻፵፯፥፰ ላይ *«ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና ወያስተዴሉ ክረምተ ለምድር ዘያበቍል ሣዕረ ውስተ አድባር»* (ሰማዩን በደመና ይሸፍናል፤ ለምድርም ዝናብን ያዘጋጃል፤ ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል) በማለት የዝናቡን ውሃ ስለያዘ የደመና ምስጢር ተናግሯል።

በአንጻሩ ሐዋርያው ይሁዳ በመልእክቱ በቍጥር ፲፪ ላይ (በነፋስ የተወሰዱ ውሃ የሌለባቸው ደመናዎች) በማለት የዝናምን ውሃ ያልቋጠረ የደመናን ነገር ገልጧል። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በነዚኽ ኹለት የደመና አይነቶች እንደምትመሰል ከሊቃውንቱ መኻከል ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ያሬድ፣ አባ ጊዮርጊስ አብራርተው አስተምረዋል።





ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ዝናምን በያዘች ደመና ሲመስላት በረቡዕ ውዳሴ ማርያም ላይ *«አንቲ ዘበአማን ደመና እንተ አስተርአይኪ ለነ ማየ ዝናም»* (የዝናምን ውሃ ቋጥረሽ የታየሽ እውነተኛ ደመና አንቺ ነሽ) በማለት ንጹሕ ዝናም እንተ በአማን የተባለ የነፍሳትን ጥም ያበረደ የሕይወት ዝናም፣ የሕይወት ጠል፣ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ፣ በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን እውነተኛዪቱ ደመና ድንግል ማርያም የመኾኗን ምስጢር አጕልቶ ተናግሯል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ስለ አማናዊት ደመና ስለ ድንግል ማርያም ክብር በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *«ንዑ እንከ ከመ ናልዕላ ለዛቲ ደመና ብርሃን እንተ ጾረቶ ለማየ ዝናም ንጹሕ»* (ንጹሑን የዝናም ውሃ የተሸከመችውን የብርሃን ደመና ኑ ከፍ ከፍ እናድርጋት)[9] በማለት የሕይወት ውሃ የንጹሐ ባሕርይ የስቱ ጽሙአን የክርስቶስ እናት መኾኗን አስተምሯል።

በአንፃሩ ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በምስጢር በመራቀቅ በድጓው ላይ ቅድስት ድንግል ማርያምን *«ዕራቁ ደመና»* (የተራቆተች ደመና)[10] በማለት የዝናምን ውሃ ባልተሸከመች ደመና መስሏታል። ይኸውም ይኸቺ የተራቆተች ደመና ከላይ እንዳየነው ምንም ዐይነት የውሃ ነጠብጣብን ያልቋጠረች የዝናምን ውሃ ያልያዘች፣ ያልተቀበለች እንደኾነች ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም በውሃ ነጠብጣብ በዝናም የተመሰለ ዘርዐ ወራዙትን ያልተቀበለች፤ ያለ ዘርዐ ብእሲ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ብቻ አምላክን ፀንሳ የተገኘች በመኾኑ ዕራቁ ደመና በማለት አመስግኗታል (ሉቃ ፩፥፴፬-፴፯፤ ማቴ ፩፥፳)።

## ዕለተ ሠሉስ (የማግሰኞ ዕለት)

የሕይወት የወይን ሐረግ ጌታን ያፈራችልን ቅድስት እመቤታችን በዕለተ ሠሉስ በስፋት ትመሰላለች። ይኸም በዚኽች ዕለት ልዑል እግዚአብሔር «ምድር ዘርን የሚሰጥ ሣርንና ቡቃያን በምድርም ላይ እንደ ወገኑ ዘሩ ያለበትን ፍሬን የሚያፈራ ዛፍን ታብቅል›› (ዘፍ ፩፥፲፩)፤ ብሎ ባዘዘ ጊዜ ምድር ገበሬ ሳይጥርባት ሳይደክምባት፣ ዘር ሳይወድቅባት በቃሉ ብቻ አገርዕትን፣

9. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘሠሉስ ፯፥፪



www.ethiopianorthodox.org

አትክልትን፣ ዕፀዋትንና ዕፀወ ገነት (የገነት እንጨቶችን) አስገኝታለች። (ኩፋ ፪፥፲፪)። እነዚኽ ኹሉ የተገኙባት የማግሰኞ ዕለት በድንግል ማርያም ስትመሰል፤ ዘር ሳይወድቅባት ፍሬን ያስገኘችው ምድር የድንግል ማርያም የማሕፀኗ፤ ፍሬ የሕይወት ፍሬ የጌታ ምሳሌ ነው (ሉቃ ፩፥፴፪-፴፫)። ምክንያቱም እግዚአብሔር ታብቅል ብሎ ባዘዘ ጊዜ ምድር ገበሬ ሳያርሳት ሳይቆፍራት ዘር ሳይዘራባት አዝርዕት፣ አትክልትን፣ ዕፀዋትን እንዳስገኘች ኹሉ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ «ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ» ብሎ ባበሠራት ጊዜ ዘርዐ ብእሲ (የወንድ ዘር) ሳይወድቅባት ዕፀ ሕይወት፣ ፍሬ ሕይወት ክርስቶስን አስገኝታለች (ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰) ።

ይኽነን ልዩ ምስጢር የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በመረዳት በማግሰኞ ውዳሴ ማርያም *«አንቲ ውእቱ ገራህት ዘኢተዘርዐ ውስቴታ ዘርዕ»* (ዘር ያልወደቀባት፣ ገበሬ ያልጣረባት ለታብቍል (ታብቅል) ባለው ትእዛዝ ከልምላሜ፣ ከጽጌ (ከአበባ)፣ ከፍሬ የተገኘሽ *ገራህተ ሠሉስ* (የማግሰኞ እርሻ) አንቺ ነሽ) *«ወፅአ እምኔኪ ፍሬ ሕይወት»* (የሕይወት ፍሬ ጌታ ከአንቺ ተወለደ) በማለት በዚኽች በማግሰኞ ዕለት የተገኘች ገበሬ ያላረሳት፣ ዘር ያልወደቀባት ድንግል ምድር (እርሻ) ከዘርዐ ብእሲ የተለየች የፍሬ ሕይወት የጌታ መገኛ የኾነች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ተንትኖታል።

ዳግመኛም ይኸው ታላቅ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ቅድስት ድንግልን ባመሰገነበት በዚኽ በማግሰኞ ውዳሴ ማርያም መጽሐፉ *«ኮንኪ ዐጽቀ ንጹሐ»* (ፀሓይ ያላጠወለጋት፣ ነፋስ ያልወዘወዛት ለታብቍል (ታብቅል) ባለው ቃል ከልምላሜ፣ ከጽጌ፣ ከፍሬ የደረሰች ዐጽቀ ሠሉስ (የማግሰኞ ዕለት ቅርንጫፍ) ኾንሽ) በማለት ንጽሕናዋን ቅድስናዋን በዕለቱ በተገኙ ዐጽቆች መስሎ አስተምሯል።ምክንያቱም በዚኽ ዕለት የተገኙት ቅጠሎች፣ ቅርንጫፎች ፀሓይ እንዳላጠወለጋቸው፣ ነፋስ እንዳልወዘወዛቸው ኹሉ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምንም ምክንያተ ኀጢአት አለወጣትም በሥጋዋም፣ በነፍሷም፣ በኅሊናዋም ድንግል ናትና፤ ይኽ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም በዐጽቀ ሠሉስ መስሎ ይኽነን ማስተማሩ ምን ያኽል የጠለቀ የነገረ ማርያም





ዕውቀት እንደነበረው ያሳየናል።

በሃገራችን ከነበሩ ጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀት ከነበራቸው ሊቃውንት መኻከል አንዱ የኾነው፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ልዩ ምሳሌ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*«ኦ እግእዝእትየ ማርያም ዕፅ ቡርክት እምነ ዕፀዋት ዘትዔድሚ*
*በኵሉ አውራኀ ዘትትቀሀሚ*
*ዘዘልፈ ታንመለምሊ ወዘልፈ ትለመልሚ*
*እምዓውሎ ኀጢአት ዘኢትትሀወኪ፤ ወበጕድበ አበሳ ዘኢትትገዘሚ»*
(በበደል ምሣር የማትቆረጪ፤ ከኀጢአት ዐውሎ ነፋስ የተነሣ የማትነዋወጪ፤ ዘወትር ፍጹም የምትለመልሚ፤ በዘመኑ ኹሉ የምታፈሪ፤ በወሮች ኹሉ የምትለቀሚ፤ ከዕፀዋት ኹሉ ይልቅ የምታምሪ እመቤቴ ማርያም ሆይ፤ የተባረክሽ ዕፅ ነሽ)[11] በማለት መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስ የሌለባት በንጽሕና በቅድስና በድንግልና ጸንታ የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን ያስገኘችልን ቡርክት ዕፅ መኾኗን ገልጾታል።

## ዕፀ ሕይወት(የሕይወት ዛፍ) Tree of Life

*ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን ምግበ ርኁባን፣ ስቴ ጽሙኣን* የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን የወለደች ቅድስተ ቅዱሳን እመቤታችን፤ በሕይወት ዛፍ የምትመሰል መኾኗን ቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ያስረዱናል። ይኸውም የዓለማት ፈጣሪ ልዑል እግዚአብሔር በምሥራቅ በዔዴን ገነትን ካዘጋጀ በኋላ የሕይወት ዛፍን በገነት መኻከል አበቀለ (ዘፍ ፪፥፱)።

ይኽቺም ዕፀ ሕይወት ፍሬዋ እንደ ሮማን ፍሬ ተነባብሮ ከታች እስከ ላይ የመላ ሲኾን፤ መዐዛዋ ከአፍንጫ ጣዕሟ ከአፍ ሳይለይ እስከ ሰባት ቀን መቆየት የሚችል ነው። ስለዚኽች በገነት መኻከል ስላለችው ስለ ዕፅ ሕይወት ተፈጥሮ፤ ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የሥነ ፍጥረትን ምስጢር በሚተነትነው መጽሐፉ *«ወተከላ እግዚአብሔር ለዕፀ ሕይወት በማዕከለ ገነት ወከተማሃ ዘይበጽሕ እምድር እስከ ሰማይ ወፍሬሃኒ ምሉዕ ከመ ፍሬ ሮማን እምእግሪ እስከ ርእሱ»* (በዚያች በገነት መኻከል ዕፀ ሕይወትን ተከለ፤ ይኽቺም ዕፀ

11. አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት ገጽ 14



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወት ራሷ ከሰማይ ይደርሳል፤ ፍሬዋም እንደ ሮማን ፍሬ ተነባብሮ ከእግሯ እስከ ራሷ ምሉ ነው)[12] ሲል ተናግሯል።

ነቢዩ ሕዝቅኤል በምዕራፍ ፵፯ ቊጥር ፲፪ ላይ «በወንዝም አጠገብ በዳሩ ላይ በዚኽና በዚያ ፍሬው የሚበላ ዛፍ ኹሉ ይበቅላል፤ ቅጠሉም አይረግፍም፤ ፍሬውም አይጎድልም፤ ውሃውም ከመቅደስ ይወጣልና፤ በየወሩ ኹሉ የፍሬ በኲር ያገኛል፤ ፍሬውም ለመብል ቅጠሉም ለመድኀኒት ይኾናል» በማለት በትንቢቱ ተናግሯል። ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ በምዕራፍ ፳፪ ቊጥር ፪ ላይ «በወንዙም ወዲያና ወዲኽ በየወሩ እያፈራ ዐሥራ ኹለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበር፤ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ» በማለት የሕይወት ዛፍን ምንነት አመልክቷል።

ልዑል እግዚአብሔር ለአባታችን አዳም ዕፀ በለስን እንዳይበላ ሲከለክለው፤ የሕይወት ዛፍን ግን ብላም አትብላም አላለውም ነበር፤ አዳም የጌታን ትእዛዝ አክብሮ አትብላ ያለውን ዕፀ በለስን ጠብቆ ቢኖር፤ብላም አትብላም ያላለውን የሕይወት ዛፍን በልቶ ታድሶ ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በገባ ነበር፤ ኾኖም ግን አዳም ምክረ ከይሲን ሰምቶ ከተከለከለው ከዕፀ በለስ በልቶ የፈጣሪውን ትእዛዝ በማፍረሱ እግዚአብሔር አምላክ አዳምን አስወጥቶ፤ ዕፀ ሕይወትን በኪሩቤል የእሳት ሰይፍ እንዳስጠበቀ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕ ፫ ቊጥር ፳፪ – ፳፬ ላይ «... አኹንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፤ ለዘላለምም ሕያው ኾኖ እንዳይኖር፤ ስለዚኽ እግዚአብሔር አምላክ ከዔዴን ገነት አስወጣው፤ የተገኘባትን መሬት ያርስ ዘንድ አዳምንም አስወጣው፤ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውንም መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በዔዴን ገነት በምሥራቅ አስቀመጠ» በማለት ይናገራል።

ይኽን እንጂ በነገረ ድኅነት አስተምህሮ፤ በገነት ያጣነውን የሕይወት ዛፍ በዚኽ ዓለም አግኝተነዋል፤ ይኸውም የሕይወት ዛፍ የተባለ ለአዳም የቀደመ ሀብቱ ልጅነትን የቀደመ ቦታው ገነትን የሰጠው ወሃቤ ሕይወት ጌታ ነው (ዮሐ ፩+፬፤ ፫+፲፭-፲፯፤ ፬+፲፬፤ ፭+፳፩፤ ፮+፳፯-፶፱፤ ፲፩+፳፭)።

ይኽን የዕፀ ሕይወትን ነገር ታላላቅ የቤተ ክርስትያን መምህራን በብዙ

12. ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፤ መጽሐፈ አክሲማሮስ





ምስጢር አራቀው ተርጕመውታል። ይኸውም ዮሐንስ ወንጌላዊ በራእዩ ላይ በስፋት የሕይወት ዛፍን በልጅነት፣ በመንግሥተ ሰማያት እየመሰለ ሲናገር(ራእ ፪+፯፤ ፳፪+፪-፫፤ ፲፬፤፲፱)፤ ከሊቃውንት ውስጥ አፍርሃት፣ ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግና፣ ቅዱስ ያሬድ ዕፀ ሕይወትን ለዓለም ሕይወት ሊኾን በቀራንዮ በተሠዋ በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ሥጋውና በክቡር ደሙ መስለው አስተምረዋል።

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም አዳምና ሔዋንን መላውን የሰው ልጆችን ለማዳን፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ፭ሺ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ (ሰው ኾኖ)፤ በሕይወት ዛፍ ፈንታ ለኹላችን ሕይወት መድኀኒት ሊኾነን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እንደሰጠን ቅድስት ድንግልን ባመሰገነበት በነሙስ የውዳሴ ማርያም መጽሐፉ *«በእንተ ሔዋን ተዐጽወ ኆኅተ ገነት ወበእንተ ማርያም ድንግል ተርኅወ ለነ ዳግመ ከፈለነ ንብላዕ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ ክቡር በእንተ ፍቅረ ዚኣነ መጽአ ወአድኀነነ»* (ስለሔዋን የገነት ደጅ ተዘጋ፤ ዳግመኛም ስለ ድንግል ማርያም ተከፈተልን፤ ከዕፀ ሕይወት እንበላ ዘንድ አደለን፤ ይኸውም እኛን ስለመውደድ መጥቶ ያዳነን የክርስቶስ ክቡር ሥጋው ክቡር ደሙ ነው) በማለት በዘመነ ሥጋዌ የተሰጠንን የድኅነት ምስጢር አድንቋል።

ዳግመኛም ይኸው ታላቅ አባት ቅዱስ ኤፍሬም በመጽሐፉ በገነት ያጣነውን የሕይወት ዛፍ በእመቤታችን በማሕፀኗ ፍሬ በክርስቶስ ማግኘታችንን ሲተረጉም «The tree of life, which lay hidden in paradise, has sprung forth in Mary...» (በገነት የተደበቀ የሕይወት ዛፍ በእመቤታችን ማርያም ተገለጠ፤ አበበ በጥላው ሥርም ፍጥረት ኹሉ ተጠለለ፤ በቅርብም በሩቅም ላሉ ፍሬውን ያዘንባልና... በቀደመው በገነት መኻል የበቀለ ዛፍ ለአዳም ሕይወትን ሊሰጥ አልቻለም፤ ለአዳም እራሱን በመስጠት በድንግልማርያም ዕቅፍ ተገለጠ፤ አዳምም ከእርሱ ሕይወትን ተቀበለ... የአበባው ቦታ ብልኁ ጠባቂ ኹለት ዛፍን ተከለ፤ በአንዱ ሞትን አንጠልጥሎ በሌላው ሕይወትን ደብቆ፤ በዚኽም ለአዳም ፈተና ሰጠው፤ ከዚኽ ፈተና ክብርን ይቀዳጅ ዘንድ፤ ጌታም ለአዳም ሕግን ሰጠው፤ በውስጡም ሞት ካለበት ከዕውቀት ፍሬ እንዳይበላ ከለከለው፤ እባብና



www.ethiopianorthodox.org

ሔዋን ተስማምተው በፈጠሩት ውሸት ተዋጊው (አዳም) ከትግሉ ተሸንፎ ከክብሩ ተዋረደ፤ በሔዋን ምትክ ድንግል ተተካች፤ ከእርሷም አምላክ ተገኘ፤ ፍሬውንም አቆየልን፤ በገነት ያልቀመሱትን ከድንግል ማርያም አገኙት፤ ከፍቅሩ የተነሣ ራሱ የሰጠው፤ ለበሉትም ጥንካሬን የሚሰጥ)[13]በማለት አዳምንና ሔዋን በገነት ያጡትን በኪሩቤል የእሳት ሰይፍ ሲጠበቅ በኖረ በሕይወት ዛፍ ፈንታ፤ በአረጋዊው ዮሴፍ ስትጠበቅ የኖረች፤ እውነተኛ መብል የሕይወት ዛፍ ክርስቶስን ያስገኘችልን የአምላክ ገነት ቅድስት ድንግል መተካቷን አስተምሯል።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በመጽሐፉ የሕይወት ዛፍ የተባለ ክርስቶስን ያስገኘችልንን ድንግል ማርያም እንደኾነች ሲያስተምር «because of her, the cherub had removed his lance that he might no longer guard... (በእርሷ ምክንያት ኪሩብ ሰይፉን አነሣ፤ ከእንግዲኽ የሕይወት ዛፍ ሊበሉ የሚወዱትን ኹሉ እንዳይከለክል በሕይወት የተመላ ጣፋጭ ፍሬን ሰጠችን፤ ከእርሱም እንበላ ዘንድ ለዘለዓለም ከእግዚአብሔር ጋር እንኖር ዘንድ)[14] በማለት «ሥጋዬም የእውነተኛ መብል ነው ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለኹ» (ዮሐ ፮፥፶፫-፶፮) ብሎ በሥጋው በደሙ ምክንያት እንደሚዋሐደን ያስተማረ አካላዊ ቃል ክርስቶስን በሥጋ ወልዳ በገነት ያጣነውን የሕይወት ዛፍ ጌታን በዚኽ ዓለም ለማግኘት ምክንያት የኾነችን ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን ገልጧል።

ታላቁ የዜማ አባት የቤተክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ስለ ሕይወት ዛፍ ምስጢር በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ላይ *«አንቲ ውእቱ ዕፅ ቡሩክ ዕፀ ሕይወት ወዕፀ መድኀኒት ህየንተ ዕፀ ሕይወት ዘውስተ ገነት ዘኮንኪ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር ፍሬኪኒ ፍሬ ሕይወት ውእቱ ወዘበልዐ እምኔሁ ሕይወተ ዘለዓለም የሐዩ»* (አንቺ የተባረክሽ ዕፅ ነሽ፤ የሕይወትና የደኅንነት ዕፅ ነሽ፤ በገነት ውስጥ ባለው ዕፀ ሕይወት ፈንታ በዚኽ ዓለም የሕይወት ዕፅ ኾንሽ፤ ፍሬሽም የሕይወት ፍሬ ነው፤ ከእርሱ ለበሉ የዘለዓለም ሕይወትን የሚያድል)[15]

13. Bride of light pp 34,96,98
14. Jacob of serugh, on the virgin, ET by M.Hansbury p 39
15. ቅዱስ ያሬድ፤አንቀጸ ብርሃን





በማለት የዘላለም ሕይወት የሚያድለንን እውነተኛውን መብል ቅዱስ ሥጋውን ቈርሶ፤ እውነተኛውን መጠጥ ክቡር ደሙን አፍስሶ የሰጠንን ፍሬ ሕይወት ጌታን የወለደችልን ቅድስት ድንግል ማርያምን መኾኗን መስክሯል።

<u>ዕፀ ገነት(የገነት ዛፍ)</u>

የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን በድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያም በገነት ውስጥ ባሉት ዕፀዋት ኹሉ እንደምትመሰል በርካቶች ሊቃውንት በየድርሳናቸው ገልጸዋል። እነዚኽም በገነት ያሉ አዝርዕት፥ አትክልት፥ ዕፀዋት በዚኽ ዓለም ካሉት የተለዩ ናቸው፤ ቅጠላቸው ሰፋፊ ነው ዐሥራ ኹለት ክንድ ይኾናል፤ መዐዛቸው የመንፈቅ መንገድ ኼዶ ይሸታል፤ ፍሬያቸው የጋን መክደኛ ያኽላል፤ ጣዕማቸው ነፍስን ከሥጋ ይለያል፤ አላምጠው እስኪውጧቸው ድረስ ፍሬ ይተካሉ፤ ጥራታቸው እንደ መስታዮት ፊትን ያሳያል (ሕዝ ፵፯፥፲፪-፲፫፤ ራእይ ፳፪፥፪-፫)።

ሊቁ ኤጲፋንዮስ የሥነ ፍጥረትን ነገር በሚያሳውቀው መጽሐፉ የዕፀወ ገነትን ነገር ሲያስረዳ *«ወቈጽለ ዕፀዊሃ ለገነተ ንሉሳን በበ፲ቱ ወ፪ቱ እመት ወጽጌሳን እሙንቱ ከመ ከዋክብት ወአስካለ ፍሬሆሙ ለዕፀወ ገነት ከመ ልጥረ ብሩር ክቡብ ወኢይትፈለጥ ጣዕሙ እምአፍ ወመዐዛሁ እም አንፍ እስከ ፯ቱ ዕለታት»* (በዚኽችም በገነት በውስጧ ያሉት አዝርዕት፥ አትክልት፥ ዕፀዋት ታናናሾ ቅጠላቸው ዐሥራ ኹለት ዐሥራ ኹለት ክንድ ይኾናል፤ ይኸውም እንደ ከዋክብት ያበራሉ፤ ፍሬያቸው እንደተመዘነ ብር ክብ ነው፤ ጣዕማቸው ከአፍ መዐዛቸው ከአፍንጫ ሳይለይ ሰባት ቀናት ይቆያል)[16] በማለት ገልጧል።

ሊቁ ቅዱስ አትናቴዎስም የገነት ተድላ ደስታዋን የዕፀዋቱን አስደሳችነት በቅዳሴው ላይ *«ኦ ሰራፊ ዐቃቢሃ ለገነት ዘበሰይፈ እሳት ኅድጋ ንባእ ንርአያ ለማኅደረ ሕይወት ወአኮ ዘንነብር ውስቴታ ኦ ሰራፊ ኅድጋ ንባእ ንርአያ ለማኅደረ ሕይወት ወአኮ ዘንትነባእ ህየ ኦ ሰራፊ ኅድገነ ንባእ ውስተ ገነት ወናጼኑ አፈዋቲሃ ወይሠወጥ ውስተ ልብነ መዐዛ ዚአሃ ኦ ሰራፊ ኅድጋ ንባእ ውስተ ዘቀዳሚ ርስተ አቡነ ከመ ንትፈሣሕ በዕፀዊሃ ወአኮ ዘንቀጥፍ እምፍሬሃ በአዕዳው ከመ ዘትካት»* (በእሳት ሰይፍ ገነትን የምትጠብቅ ሱራፊ

16. ቅዱስ ኤጲፋንዮስ፤ መጽሐፈ አክሲማርስ



www.ethiopianorthodox.org

ሆይ የሕይወት ማደሪያን ገብተን እናያት ዘንድ ተወን፤ በውስጧም የምንኖር አይደለም፤ ሱራፌ ሆይ የሕይወት ማደሪያን (ገነትን) ገብተን እናያት ዘንድ ተወን፤ በዚያ የምንሸሽግ አይደለም፤ ሱራፌ ሆይ ወደ ገነት ገብተን ሽቱዋን እናሸት ዘንድ ተወን፤ መዐዛውም በልቡናችን ይጨመር ዘንድ፤ ሱራፌ ሆይ ወደ ቀደመ አባታችን ርስት እንገባ ዘንድ ተወን፤ በዕንጨቶቿ ደስ ይለን ዘንድ፤ እንደቀድሞ ከፍሬዋ በእጃችን የምንቈርጥ አይደለም)[17] በማለት በሱራፌ የእሳት ሰይፍ ትጠበቅ የነበረችውን የገነትንና የዕፀዋቷን ነገር አድንቋል፡፡

ለነዚኽ ኹሉ ሊቃውንት መሠረት የኾናቸው ይኽ ታላቅ ምስጢር የተገለጠለት የአዳም ሰባተኛ ትውልድ የኾነው ሔኖክ ያየው እውነት ነው፡፡ ይኽ ሔኖክ ከሰው ተለይቶ ስድስት ዓመት በእግረ ገነት ወድቆ በሰባተኛው ተሰውሯል (ዘፍ ፭፥፳፬፤ ሔኖ ፬፥፩)፡፡ ይኽ አባት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስለኾኑት ስለገነት ዛፎች ያየውን የተገለጠለትን ሲገልጥ ‹‹ወርኢኩ ፯ተ አድባረ ክቡራነ ወኵሉ ፩ዱ እምነ ፩ዱ ወየዐውድዎ ዕፀወ መዐዛ ወሀሎ ውስቴቶሙ ዕፅ አልቦ ግሙራ አመ ጼነውኒ ወኢ፩ዱ እምውስቴቶሙ ወባዕዳንሂ ዘከማሁ ኢኮነ ዘይምዕዝ እምኵሉ መዐዛ ወቈጽሉ ወጽጌሁ ወዕፁ ኢይጸመሂ ለዓለም ወፍሬሁኒ ሠናይ ወፍሬሁሰ ከመ አስካለ በቀልት ወውእተ ጊዜ እቤ ነዋ ዝንቱ ሠናይ ዕፅ ወሠናይ ለርእይ ወአዳም ቈጽሉ ወፍሬሁኒ ሞገስ ጥቀ ለርእየ ገጽ›› (የከበሩ ሰባት ተራራዎችን አየኍ፡፡ ኹሉም አንዱ ከአንዱ ልዩ ልዩ የኾኑ እንጨቶች ከበዋቸዋል፤ ከውስጣቸውም መቼም ቢኾን እንደ እርሱ አድርጎ የሸተተኝ ሌላ ዕፅ የሌለ ከሽቱ ኹሉ የበለጠ የሽቱ ዕንጨት አለ፤ ዛፉም ቅጠሉም አበባውም ለዘላለም አይጠወልግም፤ ፍሬውም ያማረ ነው፤ ያውም እንደ ዘንባባ ፍሬ ያለ ነው፤ ያን ጊዜ ይኽ ዕንጨት መልካም ነው፤ ቅጠሉም አበባውም ለዘላለም አይጠወልግም፤ ፍሬውም ያማረ ነው፤ ያውም እንደ ዘንባባ ፍሬ ያለ ነው፤ ያን ጊዜ ይኽ ዕንጨት መልካም ነው፤ ቅጠሉም ያማረ ነው፤ ፍሬውም ፊት ለፊት ለማየት እጅግ ያማረ ነው አልኍ) ሔኖ ፺፥፩-፲፩ በማለት በገነት ስላያቸው አገርዕት፣ አትክልት፥ ዕፀዋት ምስጢር ተናግሯል፡፡

ይኽቺውም የገነት ዛፍ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ የማይጠወልገው ቅጠሏ ለዘላለም የማይለወጠው

17. ቅዳሴ አትናቴዎስ፤ ቍ ፴፰-፵፩





የድንግልናዋ፤ የዛፏ ፍሬ የልጇ የፍሬ ሕይወት የክርስቶስ ምሳሌ ነው፤ ያ ፍሬ ሲቈርጡት እየተካ እንደማያልቅ ኹሉ ለቤዛ ብዙኃን የተሰጠ የጌታ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ዕለት ዕለት እየተሠዋ ሲሰጥ የመኖሩ ምሳሌ ነውና፤ ይኽነን ልዩ ምስጢር የተረዱ ሊቃውንት ይቺ ነቢዩ ሔኖክ ያያት በሱራፌ መልአክ የምትጠበቅ የገነት ዛፍ የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን መስክረዋል፡፡ ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ እግዝእትየ ማርያም ደብረ ትንቢት ዘየዐውድዋ ዕፀወ መዐዛ*
*በውስተ መጽሐፉ ለሔኖክ አንተ ተጽሕፈ ዕዘዛ››*

(እመቤቴ ማርያም ሆይ በሔኖክ መጽሐፍ ውስጥ ትእዛዟ የተጻፈ፤ የመዐዛ ዕፀዋት የሚከቧት የትንቢት ተራራ ነሽ)[18] በማለት በእውነት ምሳሌዋ መኾኑን ሲያስተምር፤ የማሕሌተ ጽጌ ደራሲያን ሊቃውንት አባ ገብረ ማርያም ዘደብረ ሐንታና አባ ጽጌ ድንግል በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው

*‹‹በኵናተ እሳት ዘይነድድ ዘየዐቅበኪ ሱራፊ*
*ወአጼነወ መዐዛኪ ሔኖክ ጸሐፊ*
*ጽጌ ዕፀ ገነት ማርያም ዘኢትትነገፊ ››*

(ሱራፌ መልአክ የእሳት ጦርን ይዞ የሚጠብቅሽ፤ መዐዛሽንም ጸሐፊ ሔኖክ ያሸተተልሽ የማትረግፊ የማትጠፊ የገነት ዛፍ ማርያም)[19] በማለት ሔኖክ ያያቸው የገነት ዛፎች በእውነት የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾናቸውን ተናግረዋል፡፡ ዳግመኛም እነዚኽ ሊቃውንት የቅድስት ድንግልን የመዐዛ ንጽሕናዋን፣ የመዐዛ ቅድስናዋን፣ የመዐዛ ምግባሯን ድንቅነት በገነት ውስጥ ባሉት ልዩ ሽታን በሚሸቱ በገነት ዛፎች ሲመስሉ

*‹‹እንዘ ይፀውረኪ በሐቂፍ ወይስዕመኪ በአፍ*
*አመ አፍለሰኪ ወልድ ውስተ የማነ ለዐሪፍ*
*ጽጌ ዕፀ ገነት ማርያም ዘትጼንዊ ለአንፍ*
*እንዘ ይትጓድዑ አክናፈ በክንፍ*
*ለቀበላኪ ወረዱ አእላፍ››*

18. አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት ገጽ 69
19. አባ ጽጌ ድንግል፤ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፴፱



www.ethiopianorthodox.org

(ለአፍንጫ መዐዛን የምትሰጪ የገነት ዛፍ ማርያም ሆይ፤ ልጅሽ በክንዱ ዐቅፎ በአፉ እየሳመ በቀኙ ሊያሳርፍሽ ባሳረገሽ ጊዜ፤ አንቺን ለመቀበል ክንፍ ለክንፍ እየተጋጩ እልፍ አእላፋት መላእክት ወረዱ)[20] በማለት የመዐዛዋን ታላቅነት መስክረውላታል።

ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ቅድስት ድንግል ማርያም አማናዊት ዕፀ ገነት መኾኗን በአርጋኖን መጽሐፉ *«ዕፀ ገነት ዘበጸጌሃ ንትሜዐዝ ወእምፍሬሃ ንሴሰይ ወታሕተ አዕጹቂሃ ናጸልል... ኦ ድንግል ዖመ ገነት ዘተከላ የማነ እግዚአብሔር ወአጸገየ ኀይለ መንፈስ ወአፍረየ ጸጋሎተ አብ»* (በአበባዋ የምንሻተትባት፤ ከፍሬዋም የምንመገባት፤ በሥሯም (በቅርንጫፎቿም) የምንጠለልባት የገነት ዕንጨት ናት... ድንግል ሆይ የእግዚአብሔር ቀኝ የተከላት፣የመንፈስ ቅዱስ ኀይል እንድታብብ ያደረጋት፣ የአብ ጥላ እንድታፈራ ያደረጋት የገነት ዛፍ ነሽ)[21] በማለት በሥልጣነ እግዚአብሔር ተጠብቃ በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በንጽሕና፣ በቅድስና ጸንታ በግብረ መንፈስ ቅዱስ አምላክን አፍርታ የተገኘች አማናዊት ዕፀ ገነት የመኾኗን ምስጢር አጕልቶ አሳይቷል (ሉቃ ፩፥፴፰-፵፪)።

## ዕለተ ረቡዕ

የፀሓየ ጽድቅ የጌታችን እናት ድንግል ማርያም ዕለተ ረቡዕ ምሳሌዋ ኾኖ ይነገርላታል። ይኸውም የፍጥረታት አስገኝ ልዑል እግዚአብሔር በዚኽ ቀን *«ለይቁሙ ብርሃናት በገጸ ሰማይ»* ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይኹኑ» ብሎ ባዘዘ ጊዜ የዓመታት፣ የወራት፣ የዕለታት መለያ የኾኑት ፀሓይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት በምሥራቅ ተገኝተዋል (ዘፍ ፩፥፲፬-፲፱)።

በዚኽች በአራተኛው ዕለት፣ በአራተኛው ኬክሮስ የበረደውን የሚያሞቅ፣ የተሰወረውን የሚገልጥ፣ የጨለመውን የሚያስለቅቅ ፀሓይ እንደተገኘ ኹሉ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ ካህናት፤ በአራተኛው ትውልድ ከቤተ ይሁዳ ከተገኘች ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያምም በብርሃኑ ኅልፈት ውላጤ የሌለበት፣ ጠፈር ደፈር የማይከለክለው፣ መዓልትና ሌሊት የማይፈራረቀው፣ የማይጠልቅ የጽድቅ ፀሓይ ክርስቶስ ተወልዶ

20. ገዘ. ከማሁ፤ ቍ ፹፫
21: አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፩፥፭፤ ዘዐርብ ፰፥፮





ዘላለማዊ ፍዳን አርቆልናልና በዚኽች ዕለት ተመስላለች (ሚል ፫፥፪፤ ራእ ፳፩፥፳፪-፳፫)።

ታላቁ አባት ቅዱስ ኤፍሬምም እመቤታችንን ባመሰገነበት በረቡዕ የውዳሴ ማርያም መጽሐፉ *«ኖንተ ምሥራቅ ማርያም ድንግል»* (ድንግል ማርያም የምሥራቅ ደጅ ናት) በማለት የፀሓየ ጽድቅ የክርስቶስ እናት የኾነችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን ሲያመሰግን፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*«ኖንተ ጸባሕ አንቲ ለፀሓየ ጽድቅ ምሥራቁ*
*ኵሉ ፍጥረት ዘላህበ ዚኣሁ ይመውቁ*
*ወበቅድሜሁ ብርሃናት ለፈጽሞ ትእዛዝ ይሠርቁ*
*መክፈልተ ዓመት ጥንቁቀ ለኀበ ርትዕ እንዘ ይነፍቁ»*

(የዓመትን ድርሻ ጠንቅቀው ወደ ቀናው መንገድ እየከፈሉ፤ ትእዛዙን ለመፈጸም ብርሃናት በፊቱ የሚወጡና ፍጥረት ኹሉ የርሱን ወላፈን የሚሞቁ፤ የእውነተኛ ፀሓይ መውጫው ምሥራቃዊት ደጃፍ አንቺ ነሽ)[22] በማለት ለሰው ልጆች ኹሉ ሙቀተ ጸጋን የሰጠ የፀሓየ ጽድቅ የክርስቶስ እናትነቷን መስክሮላታል። ምክንያቱም ይኸቺ የፀሓይ ደጃፍ በአራተኛው ወር ከአራተኛው መስኮት ወጥታ ለዐሥራ ኹለቱ ደጃፎች እንድታበራ፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በአራተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ ካህናት፤ ከአራተኛው ትውልድ ከነገደ ይሁዳ ተገኝታ፤ የእውነት ፀሓይ ክርስቶስን አስገኝታ፤ እሱም ለዐሥራ ኹለቱ ነገድ ብርሃን ወንጌልን ሲያስተምር ተሰምቷልና የዚኽ ታላቅ ሊቅ ምሳሌ እጅግ አድርጎ የሚያስደንቅ ነው (ሔኖክ ፳፩፥፲፬-፲፫)።

## ዕለተ ኀሙስ

ወሀቤ ሕይወት ጌታን ያስገኘች የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ዕለተ ኀሙስ ምሳሌዋ ነው። በዚኽች ዕለት ልዑል እግዚአብሔር «ውሃ ሕያው ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ» (ዘፍ ፩፥፳)፤ ብሎ ባዘዘ ጊዜ በልብ የሚሳቡ፣ በእግር የሚሽከረከሩ፣ በክንፍ የሚበሩ፣ በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን ኾነው የሚኖሩ ደመ ነፍስ ከሌለባት ከባሕር ተገኝተዋል።

22. አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 30



www.ethiopianorthodox.org

ከነዚኽም በርረው በርረው የኼዱ አሉ፤ ከዚያው የቀሩ አሉ፤ አንድ ጊዜ ወደ ባሕር አንድ ጊዜ ወደ የብስ የሚመላለሱ አሉ።

ይኸውም ምሳሌነት አለው፤ ደመ ነፍስ ከሌላት ባሕር በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን ኹነው የሚኖሩ እንደተገኙ ኹሉ፤ ዘርዐ ብእሲ ሩካቤ ብእሲ ከሌለባት ከእመቤታችንም ለምእመናን ምክንያተ ሕይወት የሚኾን ያውም ከጐን በፈሰሰ ውሃ ተጠምቀው ምእመናን ሕያዋን የኾኑለት ኢየሱስ ክርስቶስ ከርሷ ተገኝቷልና በዚኽ ዕለት ተመስላበታለች (ሕዝ ፴፮፥፳፭፤ ዮሐ ፫፥፭፤ ፲፱፥፴፫፤ ቲቶ ፫፥፭)።

## ዕለተ ዐርብ

ዳግማይ አዳም የተባለ ክርስቶስን በኅቱም ድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዕለተ ዐርብ ተመስላበታለች። ልዑል እግዚአብሔር በስድስተኛዪቱ ዕለት ‹‹ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር›› (ዘፍ ፩፥፳፮)፤ በማለት አባታችንን አዳምን በአርአያው በአምሳሉ ከምድር አፈር አበጅቶታል (ዘፍ ፪፥፯)። ይኽቺ አዳም የተገኘባት ዕለተ ዐርብና አዳምን ያስገኘችው ምድር ለቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌዎቿ እንደኾኑ ታላላቅ የቤተክርስትያን ሊቃውንት አስተምረዋል። ይኸውም በዚኽች ዕለት ቀዳማዊ አዳም ያለ ዘር ያለ ግንኙነት ከኅቱም ድንግል ምድር እንደተገኘባት ኹሉ፤ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ዳግማይ አዳም የተባለ ጌታ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ተወልዷልና በዕለቲቱ ተመስላበታለች።

ዳግመኛም ይቺ ድንግል የኾነችው መሬት የኹላችን አባት አዳምን እንዳስገኘች ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም የኹላችን ፈጣሪ ጌታን በድንግልና ወልዳለች፤ ከዚኽም በተጨማሪም ከዚያች ያልታረሰች ድንግል መሬት ከቀዳማዊ አዳም በስተቀር ማንም እንዳልተገኘ ከቅድስት ድንግል ማርያምም ከዳግማይ አዳም ከክርስቶስ በቀር ከቶ ማንም አልተገኘም፤ ጌታን ከመውለድዋ በፊት ድንግል፤ በወለደችው ጊዜ ድንግል፤ ከወለደችው በኋላ ድንግል ናት።





ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም እጅግ በሚረቅና በሚደንቅ ትምህርቱ ላይ ይኽነን ሲገልጽ ‹‹Adam brought forth travel up on the women who sprang from him ... (አዳም ከእርሱ የተገኘችው ሴት ላይ መከራን አመጣ፤ ከእመቤታችን ማርያም የተወለደው አዳኝ ግን መከራውን አስወገደ፤ መወለድን የማያውቅ አዳም፤ ሔዋን እናትን ወለደ (አስገኘ)፤ ያለ ወንድ እርዳታ የወለደች የሔዋን ልጅ ድንግልማርያም ምንኛ ትታመን፤ የጥንቷ ድንግል መሬት የምድር ጌታ የኾነውን አዳምን ወለደች፤ ግን ዛሬ ሌላ ድንግል ሌላ አዳምን ወለደች፤ እርሱም የሰማይ ጌታ ነው)[23] በማለት አዳም ያለዘር የተገኘባት ድንግል መሬትንና ጌታን በድንግልና የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምን እያነጻጸረ አስተምሯል።

ይኸው ሊቅ በዚኽ ንጽጽራዊ ትምህርቱ የአዳም ከታተመች ምድር መገኘት የጌታ ከድንግል ማርያም የመወለድ ምስክር መኾኑን ሲገልጽ ‹‹when the first Adam was created there was he need for martial union... (የመዠመሪያው አዳም ሲፈጠር ጋብቻ አላስፈለገውም፤ አፈርን ወስዶ እግዚአብሔር ራሱ አበጀው እንጂ፤ በዚኽም ኀይሉንና ጥበቡን ገለጠ፤ ይኽም ቃል ከድንግል ማርያም በድንግልና ለመወለዱ ምስክር ነው፤ ሳገቡ ጥንዶች ይኽነን የመምጣቱን ምስጢር አልገለጠም)[24] በማለት ድንግሊቱ መሬትንና የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያምን በማነጻጸር አስተምሯል። ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በሃይማኖተ አበው በምዕ ፷፮፥፳፰ ላይ ስለዚኽ ምስጢር ሲገልጽ ‹‹ *ወቀዳሚን ለሐኮ ለአዳም እምነ ምድር ድንግል ወኀዕበ እምነ አዳም እንበለ ብእሲት ፈጠረ ብእሲተ ወበከመ አዳም እንበለ ብእሲት አውፅአ ብእሲተ ከማሁ ዮም ወለደት ድንግል ሰብአ እንበለ ብእሲ*››( ቀድሞም አዳምም ካልታረሰች ድንግል ምድር ፈጠረው፤ዳግመኛ ሔዋንን ከአዳም ያለ እናት ፈጠረ፤ አዳም ያለ እናት ሔዋንን እንዳስገኘ እንዲኹ ዛሬ ድንግል ማርያም ክርስቶስን ያለ አባት ወለደች) በማለት ድንግሊቱ ምድር የእመቤታችን የድንግልናዋ ምስክር ምሳሌ እንደኾነች ተንትኖታል።

23. Ephrem, Hymns on the Nativity, ET by Mc Vey, p 16
24. Bride of light pp 68-71



www.ethiopianorthodox.org

## ዕለተ ቀዳሚት

ዕረፍተ ነፍስን የሰጠን ጌታን የወለደች ድንግል ማርያም በዚኽች ዕለት ተመስላበታለች። ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር ስድስቱን ቀን ፍጥረታትን ሲፈጥር ሰንብቶ በሰባተኛዪቱ ዕለት ፍጥረት መፍጠሩን አቁሟል (ዘፍ ፪፥፩)። ይኽቺም ዕረፍት የተደረገባት ዕለተ ቀዳሚት የእመቤታችን የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፤ ምክንያቱም በዚኽቺ ቀን ዕረፍት እንደተደረገባት ኹሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም መንፈሳዊ ዕረፍት ጌታ ተገኝቷልና ነው።

ይኸውም የሰው ልጅ ከባድ የኀጢአትና የፍዳ ሸክም ተሸክሞ ለ፶፻፭፻ ዘመን ሲሰቃይ፤ ይኽነን የፍዳ ሸክማችንን ከኛ ለማራቅ ክርስቶስ ፈጣሪያችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሲያስተምር «እናንተ ደካሞች ሸክማችኁ የከበደ ኹሉ ፤ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለኁ፤ ቀንበሬን በላያችኁ ተሸከሙ፤ ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት እንደኾንኹ፤ ለነፍሳችኹም ዕረፍትን ታገኛላችኁ፤ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና» በማለት እውነተኛውን ዕረፍት ሰጠን (ማቴ ፲፩፥፳፰-፴)። በመኾኑም ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍተ ሕዝብ ወአሕዛብ ጌታን በመውለዷ በዚኽ ዕለት ተመስላለች (ኤር ፮፥፲፮፤ መዝ ፳፱፥፫)።

## ረዳኢተ አዳም

እግዚአብሔር አምላክ ከእሑድ እስከ ኀሙስ ሠርክ ፍጥረታትን ከመሰላቸው ጋር ሲፈጥር ሰንብቶ፤ ዐርብ በነግህ ግን አዳምን በአርአያውና በአምሳሉ ብቻውን ከፈጠረ በኋላ በዕለተ ቀዳሚት መፍጠሩን አቆመ። ከዚያም በነጋታው እሑድ እንስሳትንና አራዊትን ለአዳም አምጥቶለት ስም አወጣላቸው፤ ሰኞና ማግሰኞ አዕዋፍን አመጣለት፤ ረቡዕ በየብስ የተፈጠሩ ፍጥረታትን፤ ኀሙስ በባሕር የተፈጠሩ ፍጥረታትን ስም አወጣላቸው፤ አዳምም እነኚኽ ኹሉ ወንድና ሴት ኾነው መፈጠራቸውን አይቶ ብቸኝነቱን ተረድቶ ረዳት በመሻት ከኔ በቀር ብቻውን የተፈጠረ የለም ብሎ ሐዘን ተሰማው (ዘፍ ፪፥፲፱-፳)። ያን ጊዜ ሥላሴ «ሰው ብቻውን ይኾን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት» (ዘፍ ፪፥፲፰-፲፱)፤ በማለት በኑሮው የምትረዳውን የትዳር አጋሩ ሔዋንን ከጐኑ ፈጥረውለታል።





ኾኖም ግን ሔዋን ለባልዋ ለአዳም ረዳት ከመኾን ይልቅ የእግዚአብሔርን ሕግ ወደኋላ በመተው፤ የዲያብሎስን ክፉና መርዛማ የሐሰት ቃልን በመቀበል፤ ለክፉ ምክሩ በመታመን ዕፀ በለስን በልታ ለባልዋ ለአዳም አብልታ፤ ለራሷና ለባሏ መሞት ምክንያት ኾናለች (ዘፍ ፫፥፮)። ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በአንጻሩ ከእግዚአብሔር ታዞ የመጣ ሕይወትን የሚያውጅ እውነተኛ ቃል የኾነውን የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት በእምነት ተቀብላ፤ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ መላውን ዓለም በደሙ ያዳነ ክርስቶስን በመውለዷ፤ ምክንያተ ድኂን (የድኅነት ምክንያት) በመኾን ረዳት ኾናለችና፤ ይኽነን ልዩና ድንቅ ምስጢር የተረዱ ታላላቅ የቤተክርስቲያናችን ሊቃውንት ይኽነን «ረዳት እንፍጠርለት» ያለውን ቃል በነገረ ማርያም ላይ ሲያመሰጥሩ «ረዳኢተ ትሰመይ ቅድስት ድንግል ለአዳም ወለደቂቁ፤ ሔዋንሰ ኢረዳአቶ፤ አላ ዳዕሙ አስሐተቶ፤ ወበ፯ቱ ዓመት እምገነተ ተድላ አውፅአቶ ማርያምሰ ረዳኢተ ኮነቶ ፤በደመ ወልዳ ዘተሣየጠቶ፤ ወውስተ ገነት አብአቶ» (ቅድስት ድንግል ለአዳም ከልጆቹ ጋራ ረዳትን ትባላለች፤ ሔዋን ግን አረዳችውም ፤ይልቁን አሳተችው እንጂ፤ በሰባተኛውም ዓመት ተድላ ደስታ ካለበት ገነት አስወጣችው፤ በልጇ ደም የተወዳጀችው ማርያም ግን ረዳትን ኾነችው ወደ ገነትም አስገባችው) በማለት ረዳት የተባለች ዳግሚት ሔዋን የተባለችው ድንግል ማርያም መኾኗን ጠንቅቀው አስተምረዋል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ረዳትን እንፍጠርለት በማለት ጌታ መናገሩ ስለ ድንግል ማርያም መኾኑን በኖኀተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ «ወካዕበ ይቤ ንግበር ሎቱ ቢጸ ዘይረድኦ፤ ረድኤትኑ ሔዋን ዘአምጽአት ሞተ ላዕለ አዳም፤ አኮ ዘኮነት ረድኤተ አላ ኮነቶ ቃታሊተ ወመሀረቶ ዕልወተ እስመ በምክረ ዚአሃ በበለዐ ሐሰ ስሕተ፤ ረድኤተ እንከ ተሰምየት ሔዋን በእንተ ማርያም ድንግል ቅድስት እስመ ይእቲ ኮነት ረድኤተ ወሊዳ ኢየሱስሀ ለቤዛ ብዙኃን ዘሞተ ዘአዕረገ ርእሶ ለአቡሁ ዕጣነ ንጹሐ ነባቤ መሥዋዕተ ለነፍሳተ ጻድቃን ዘአርኀወ ገነተ እምእደ ሱራፌ ለሰሲሎ ዘእሳት ኮናተ፤ ወበእንተዝ ለማርያም ድንግል ንጽሕት ሰመያ ረድኤተ እስመ ለትዝምደ ሰብእ ኮነት ሕይወተ» (ዳግመኛ የሚረዳው ጓደኛን እንፍጠርለት አለ፤ በውኑ በአዳም ላይ ሞትን ያመጣች ሔዋን ረዳት ናትን? ረዳትን የኾነችው አይደለም፤ ገዳዩን ኾነቺው እንጂ፤ በርሷ ምክር ዕፀን በመብላት ስቷልና፤ ሔዋን ቅድስት ድንግል ስለኾነች ስለ ማርያም ረዳትን



www.ethiopianorthodox.org

በመባል ተጠራች፤ ርሷ ከሱራፌ እጅ የእሳት ሰይፍን አስወግዶ ለጻድቃን ነፍሳት ገነትን የከፈተ፤ ራሱን ንጹሕ ዕጣንና ነባቢ መሥዋዕትን አድርጎ ለአባቱ ያሳረገውንና ለብዙዎች ቤዛ የሞተውን ኢየሱስን ወልዳ ረድኤትን ኾናለችና፤ ስለዚኽም ድንግል ንጽሕት ማርያምን ረድኤትን ብሎ ጠራ፤ ለሰው ባሕርይ (ወገን) ሕይወትን ኾናለችና)[25] በማለት ረዳትነቷን አጕልቶ ተርጕሞታል፡፡

ታላቁ ሊቅ ሄሬኔዎስም ሔዋን ባለመታዘዝ ያመጣችውን ውድቀት በድንግል ማርያም መታዘዝና ረዳትነት እንደቀረ በመጽሐፉ ላይ ‹‹For just the former was led astray by the word of an angel…›› የቀደመችው (ሔዋን) በወደቀው መልአክ ቃል ወደቀች፤ በዚኽም ከእግዚአብሔር ጋር እንዳትኖር ተሰደደች፤ ቃሉን ተላልፋለችና፤ ኹለተኛዋም (ድንግል ማርያም) በመልአክ ቃል የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብላለችና፤ የምሥራቹን ቃል በመቀበል ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ኾነች፤ የቀደመችው እግዚአብሔርን ካልተቀበለች ኹለተኛዋ ድንግል ተቀበለችው፤ ይኸውም ድንግሊቱ ሔዋንን ልትረዳ ነው፤ የሰው ዘር ኹሉ በሞት ማሰሪያ ቢያዝም በድንግል እንዲኹ ዳነ፤ የድንግል (የሔዋን) አለመታዘዝ በሌላ ወገን ያለች የድንግል መታዘዝ ለወጠው፤ የመዠመሪያ ኀጢአትን በማጥፋት ዕርቅ ኾነ፤ የእባብ መምጣት በርግብ የዋህነት ተሸነፈ፤ እሥራታችንም ተፈታ)[26] በማለት የሔዋንን አለመታዘዝን በድንግል ማርያም መታዘዝ መለወጡን በማብራራት አስተምሯል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ የቅድስት ድንግል ማርያምን ረዳትነት ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ሲያጕላ ‹‹The young maid gave healing medicine to her aged mother… (ወጣቷ አገልጋይ ላረጀች እናቷ ኧንደ ሐኪም ኾነች አዳነቻትም፤ እባብና ሔዋን ለአዳም መቃብርን ቆፈሩ፤ በሲኦልም እንዲጣል ዐደረጉ፤ ገብርኤልም ወደርሷ መጣ ተናገራትም፤ ከዚኽም ነገር ምስጢር ተገኘ፤ ይኸውም የሞቱትን ኹሉ የሚያነሣ ኾነ)[27] በማለት ከሞተ ነፍስ ያዳነን መድኀኒታችን ክርስቶስን ያስገኘች የአዳም ረዳት የመኾኗን ምስጢር አምልቶ አጕልቶ አብዝቶ አስፍቶ አስተምሯል፡፡

25. አባ ጊዮርጊስ፤ ምንተ ብርሃን፤ ገጽ 10
26. Irenaeus,Adversus Haeresus v, In Ante Nicean Fathers Vol. 1,547
27. Bride of Light, pp 95,98





<u>የአዳም ኅቱም (የታተመ) ጐን</u>

ልዑል እግዚአብሔር ስሙን እንዲቀድሰው ክብሩን እንዲወርሰው በአርአያውና በአምሳሉ ለፈጠረው ለአዳም አባታችን ረዳት እንድትኾነው፤ እናታችን ሔዋንን ከመኻል ጐኑ አንድ ዐጥንት በመንሣት፤ በእንቅልፍ ላይ ሕመም ሳይሰማው አካል ሳይጐድለው ድንቅ በኾነ አምላካዊ ሥራ ሔዋንን ፈጥሮለታል፡፡ ዐጥንት በወጣበት በአዳም ጐድንም ሥጋ መልቶበታል ‹‹ወነሥአ እግዚአብሔር አሐደ እምዐፅመ ገቦሁ ወመልአ ሥጋ መካና›› (እግዚአብሔርም ከጐኑ ዐጥንት አንድ ዐጥንትን ነሣ ቦታውንም ሥጋ መላ) እንዳለ (ዘፍ ፩፥፳፩፤ ኩፋ ፬፥፰)፡፡ አዳምም ኩተኛበት ቢነቃ ረዳት ልትኾነው እግዚአብሔር ከአካሉ ያስገኛትን ሔዋንን እርሱን መስላና አኽላ ከአጠገቡ ቢያገኛት፤ ‹‹ይኽቺ ዐጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል…›› (ዘፍ ፪፥፳፫)፤ በማለት ከአካሉ የተገኘች እንጂ ባዕድ አለመኾኗን መስክሯል፡፡

ይኽነን የሔዋን ከኅቱም የአዳም ጐን ያለ ዘር ያለ ሩካቤ መገኘትንና፤ ከአካሉ ዐጥንት ቢነሣለት እንኳ አካሉ ያለመጕደሉን፤ በተጨማሪም ምንም ሕመም ሳይሰማው ሔዋን ከሱ የመገኘቷን ድንቅ ምስጢር ከነገረ ሥጋዌ ልዩ ምስጢር ጋር በርካቶች የነገረ መለኮት ምሁራን በማነጻጸር ብዙ መጻሕፍትን ጽፈዋል፡፡ ከነዚኽም ሊቃውንት መኻከል ቅዱስ ቄርሎስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይገኙበታል፡፡ ይኸውም አዳም በዕለተ አርብ በካልዕ ሱባዔ ማእከለ ነቂህ ወነዊም ኹኖ ሔዋንን ከጐኑ እንዳስገኘ፤ ከድንግል ማርያምም በዕለተ ዐርብ ምውት በሥጋ ሕያው በመለኮት ኾኖ፤ ከጐኑ ዳግሚት ሔዋን ጥምቀትን ያስገኘ ኢየሱስ ክርስቶስ ተገኝቷል (ዮሐ ፲፱፥፴፫)፡፡

ዳግመኛም ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ አዳም ከጐኑ አንድ ዐጥንት ስለተነሣ አካሉ ጕድለት እንዳላገኘው ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን በሥጋ በወለደችው ጊዜ ማኅተመ ድንግልናዋ ያለመለወጡን ነገር በቅዳሴው ‹‹ወበከመ ኢሐጸ ለአዳም እምሕንፃ ሥጋሁ ዘቀዲሙ በእንተ ዘተነቅለ ዐፅመ ገቦሁ ከማሁ ኢሐጸ ማኅተመ ድንግልናሃ ለማርያም አመ ወለደቶ ለአበ አዳም በሥጋዌሁ›› (አዳምም የጐኑ ዐጥንት ስለተነቀለ ከቀደመው የሥጋው ፍጥረት እንዳልጐደለበት፤ እንደዚኹ የአዳምን አባት በሥጋ በወለደችው ጊዜ የማርያም



www.ethiopianorthodox.org

ማኅተመ ድንግልናዋ አልጎደለም)[28] በማለት ቅድመ ፀኒስ ቅድመ ወሊድ፣ ጊዜ ፀኒስ ጊዜ ወሊድ፣ ድኅረ ፀኒስ ድኅረ ወሊድ ማኅተመ ድንግልናዋ ያልተለወጠ ዘላለማዊት ድንግል መኾኗን ከአዳም ጐን ምሳሌ ይዞ አስተምሯል።

ይኸው ሊቅ በተጨማሪም አዳም ሔዋን ከጎኑ ስትገኝ ምንም ሕመም እንዳልተሰማው ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም ጌታን በኅቱም ድንግልና ስትወልደው ምንም ዐይነት ሕማመ ወሊድ ያልተሰማት መኾኑን «ወበከመ ኢያሕመሞ ለአዳም ሶበ ተንቅለ ዕፅመ ገቦሁ ከማሁ ኢረከባ ሕማመ ወሊድ ለእመ አምላክ ገሊላዊት» (አዳምን የጎኑ ዐጥንት በተነቀለ ጊዜ እንዳላሳመመው፤ እንደዚኹ የገሊላ ወገን የምትኾን የአምላክን እናት ሕማመ ወሊድ አላገኛትም) ሲል አመስጥሮታል።

የቁስጥንጥንያ ፓትርያርክ ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም በተመሳሳይ መልኩ የአዳምን ጐንና የቅድስት ድንግል ማርያምን ማኅተመ ድንግልና እያነጻጸረ ሲያስተምር «ወበከመ አውፅአ ዕፅመ ገቦ እምገቦሁ ለአዳም ወኢሐጸ ለአዳም ከማሁ ዓዲ ነሥአ እምድንግል ሥጋ ዘቦቱ ነፍስ ነባቢት ወለባዊት ወኢተወለጠ ድንግልናሃ ከነ አዳም ፍጹመ እምድኅረ ፀአተ ዐፅመ ገቦ እምኔሁ፤ ወድንግልሂ ዓዲ ነበረት እንበለ ሙስና እምድኅረ ፀአተ ሕፃን እምኔሃ» (ከአዳም ጐን የጎድን ዐጥንት እንደተነሣ አዳምንም አካል እንዳልጎደለው፤ እንዲኹ ከድንግል የምትናገር የምታውቅ ነፍስ ያለችውን ሥጋን ነሣ፤ ማኅተመ ድንግልናዋ አልተለወጠም፤ አዳም የጎድን ዐጥንት ከእርሱ ከተነሣ በኋላ አካል ሳይጎድለው ፍጹም ኾኖ ኖረ፤ ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ ከእርሷ ከተወለደ በኋላ እንዲኹ ያለመለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች)[29] በማለት የረቀቀውን የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስጢር አጉልቶ አስተምሯል።

## ዳግሚት ሔዋን (ኹለተኛዪቱ ሔዋን) Second Eve

ቅድስት ድንግል ማርያም ሐሰተኛ የኾነ የእባብ ክፉ ምክርን በመስማቷ በመቀበሏ ለሰው ልጆች ኹሉ የውድቀትና የሞት ምክንያት ከኾነችው ከሔዋን ተለይታ፤ ለእግዚአብሔር ታዛዥ በመኾን ፲፪ት ዓመት በቤተ መቅደስ ኖራ፤

28. ቅዳሴ ቄርሎስ፤ ቍ ፲፯፡፲፱
29. ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ፤ ሃይማኖተ አበው፤ ምዕ ፷፮፥፴





እውነተኛ መልእክት የያዘውን የቅዱስ ገብርኤል ብሥራትን በእምነት ተቀብላ፤ የሰው ልጆችን ወደ ቀደመ ክብራቸው ወደ ቀደመ ቦታቸው የመለሰ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን የተስፋ ምንጭ ናትና፤ የቤተክርስቲያን ታላላቅ የነገረ መለኮት ምሁራን ሔዋንና ቅድስት ድንግል ማርያምን በማነጻጸር ድንግል ማርያምን *ዳግሚት ሔዋን* (Second Eve) ወይም *ዐዲሲቱ ሔዋን*(New Eve) የሚል ሥያሜን ሰጥተዋታል።

ለነዚኽም ኹሉ ሊቃውንት መሠረት የኾናቸው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የመገናኛሪያው አዳምንና ዳግማይ አዳም የተባለ ክርስቶስን እያነጻጸረ ያስተማረው ትምህርት ሲኾን፤ ይኸ ሐዋርያ በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ወደ ዓለም ስለመጣው ሞትና፤ ኹለተኛ አዳም በተባለ በአምላካችን በክርስቶስ ስለተሰጠን ትንሣኤ ሲያነጻጽር፤ «ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ኾኗልና፤ ኹሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲኹ ኹሉ በክርስቶስ በኩርነት ሕያዋን ይኾናሉ» ብሏል (፩ቆሮ ፲፭፥፳፩-፳፪)።

ዳግመኛም ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈላቸው በኹለተኛ መልእክቱ ላይ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እንዳያቋርጡ፤ እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት ዛሬም መናፍቃንን በሐሰት ትምህርታቸው እንዳያታልሏቸው በማነጻጸር ሲመክር «ነገር ግን እባብ በተንኰሉ ሔዋንን እንዳሳታት፤ አሳባችኁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚኾን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለኁ» በማለት አስተምሯል(፪ቆሮ ፲፩፥፫)። በዚኽ በቅዱስ ጳውሎስ ንጽጽራዊ ትምህርት (comparative teaching) የተማረኩት፤ ሐዋርያትን በእግር የተከተሉ በግብር የመሰሉ በኹለተኛውና በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መምህራን፤ ቅዱሳት መጻሕፍትን በጥልቀት በመመርመር፤ ቅድስት ድንግል ማርያምንና ሔዋንን በማነጻጸር *ዳግሚት ሔዋን* (second Eve) ወይም *ዐዲሲቱ ሔዋን* (new Eve) የመባሏን ምስጢር አጉልተው በመጽሐፎቻቸው አሳይተዋል።

ከነዚኽም መኻከል ጀስቲን ሰማዕት (Justin the martyr, +፻፷፭ ዓ.ም) እና ሄሬኔዎስ (Irenaeus of Lyons +፪፻፫ ዓ.ም) የወንጌላዊው ዮሐንስ ተማሪ የፖሊካርፕ ጓደኛ የነበረው የኄራጳሊስ ጳጳስ ፓፒየስ (፷-፻፴) ተጠቃሽ ሲኾኑ፤ ከኋለኞቹ ሊቃውንት እና አፍርሃት (፫፻፵፯)፤ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ (፫፻፮-



www.ethiopianorthodox.org

፫፻፸፫ ዓ.ም)፣ ያዕቆብ ዘስሩግ(፬፻፶፩-፭፻፳፩ ዓ.ም)፣ የኢየሩሳሌሙ ጳጳስ ቄርሎስ (+፫፻፹፮) የሳላሚሱ ጳጳስ ኤጲፋኒዮስ፣ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ (፫፻፵፯-፬፻፯ ዓ.ም) ጎርጎርዮስ ዘኑሲስ (፫፻፴፭-፫፻፺፭)፣ ቅዱስ ቄርሎስ እስክንድርያዊ (+፬፻፵፬) እና ቴዎዶጦስ ዘአንቀራ ይገኙበታል።

ለነዚኽ ኹሉ ሊቃውንት መነሻ ኾኖ ያለፋቸው (በዘፍ ፫፥፩-፯) ያለው ቅዱስ ቃል ሲኾን፤ በታሪኩ እንደተጠቀሰው አዳምና ሔዋን በገነት የጌታን ሕግ ጠብቀው ሰባት ዓመት ከቆዩ በኋላ፤ ዲያብሎስ ሔዋንን አካል ከይሲን ማደሪያ ልሳነ ከይሲን መናገሪያ በማድረግ፤ ዕፀ በለስን ብትበሉ የባሕርይ አምላክ ትኾና ላችኁ፤ ቢላት የእባብ የሐሰት ምክሩን በመቀበል አምላክነትን ሽታ የእግዚአ ብሔርን ሕግ በማፍረስ፤ የተከለከሉት ዕፀ በለስን በልታ ለባሏ ለአዳም አብልታ ለባሏና ባጠቃላይ ለሰው ዘር ኹሉ መውደቅ ምክንያት ኾናለች (ዘፍ ፫፥፩-፯)።

ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የአምላኳን ሕግ ካፈረሰችው ከሔዋን ግብር ተለይታ፣ በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በንጽሕና፣ በቅድስና ጸንታ ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣ፤ የጨለማ መልአክ ያይደለ የብርሃን መልአክ ቅዱስ ገብርኤል የነገራትን የእውነት የብሥራት ቃልን በታላቅ እምነት ተቀብላ፤ ለአምላክ ቃል ታዛዥ በመኾን እንደቃልኽ ይደረግልኝ (ሉቃ ፩፥፴፰) በማለት ታማኝነቷን በማሳየቷ ቅድስት ድንግል ማርያም ኹለተኛይቱ ወይም ዐዲስቱ ሔዋን ተብላ ተጠርታበታለች።

ይኽነን በሔዋንና በድንግል ማርያም መኻከል ያለውን ታላቅ የታማኝነት ልዩነት ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ በጥልቀት ሲገልጽ *‹‹እስመ ቀዳሚኒ ሔዋን ኮነት ድንግል ወአስሐታ ዲያብሎስ ለማርያምሂ ድንግል አብሠራ ገብርኤል ወባሕቱ ለሔዋንሰ አስሐታ ዲያብሎስ ወወለደት ቃየልሀ ዘውእቱ ምክንያተ ሞት ወማርያምሰ ሶበ አብሠራ መልአክ ወለደት ቃለ በሥጋ ዘውእቱ መራሒ ኵሉ ኀበ ሕይወት ዘለዓለም››* (ቀድሞም ሔዋን ድንግልን ነበረችና ዲያብሎስ አሳታት እንጂ፤ ድንግል ማርያምን ግን ገብርኤል አበሠራት፤ ነገር ግን ሔዋንን ዲያብሎስ አሳታት፤ የሞት ምክንያት የሚኾን ቃየልን ወለደች፤ ማርያም ግን መልአክ ባበሠራት ጊዜ ኹሉን ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራ አካላዊ ቃልን በሥጋ ወለደች)[30] በማለት ሔዋንና ድንግል

30. ገጸ ከማሁ፤ ምዕ ፳፯፥፬-፯





ማርያም ያላቸውን ልዩነት በማነጻጸር ገልጾታል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ ሔዋን አምላክነትን ሽታ እንብላ ያለችው ፍሬ ለኹሉ ምክንያተ ሞት የኾነ ዕፀ በለስን አስገኘ፤ በዚኹ ምክንያት አዳም ከገነት ቢባረር እንኳን፤ ከቅድስት ድንግል ማርያም የተገኘ አካላዊ ቃል ግን ዕፀ ሕይወት መስቀልን አስገኘ፤ በዕፀ በለስ ምክንያት ከገነት የወጣውን አዳምን በዕፀ ሕይወት በመስቀሉ ወደጥንት ቦታው ገነት እንደመለሰው በትምህርቱ *‹‹ቃላ ለሔዋን ከሠተ ዕፀ ወበውእቱ ዕፅ ወፅአ አዳም እምገነት ተድላ ወቃልሰ ዘተወልደ እምድንግል ከሠተ መስቀለ ወቦቱ ቦአ ፈያታዊ ውስተ ገነተ ተድላ ዘምስለ አቡሁ አዳም ወኵሎሙ አበው ቀደምት››* (የሔዋን ልብላ ልብላ ማለቷ ዕፀ በለስ የሞት ምክንያት እንደኾነ አስረዳ፤ በዚያም ዕፅ አዳም ተድላ ደስታ ካለበት ከገነት ወጣ፤ ከድንግል የተወለደ አካላዊ ቃል ግን መስቀል የድኅነት ምክንያት እንደኾነ ገለጠ፤ በዚያም መስቀል ቀማኛ ወንበዴ የነበረው ሰው ከአባቱ ከአዳምና ከቀደሙ አባቶች ኹሉ ጋር ተድላ ደስታ ወዳለበት ገነት ገባ) በማለት እያነጻጸረ አስተምሯል (ዘፍ ፫፥፳፬፤ ሉቃ ፳፫፥፵፩-፵፫፤ ፩ቆሮ ፩፥፲፰)።

ሔዋንንና ድንግል ማርያምን እያነጻጸሩ ሊቃውንት ያስተማሩትን ጥልቅ ትምህርት ኹሉ በዚኽ ማጠቃለል ባይቻልም ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ድንግል ማርያም ዳግሚት ሔዋን የመባሏን ምስጢር በስፋትና በጥልቀት ያስተማረውን ትምህርት ለማየት እንሞክራለን። ይኽ ሊቅ የሐሰትንና የሞት መልእክትን የያዘውን እባብንና፤ የእውነትና የሕይወት መልእክትን የያዘውን ቅዱስ ገብርኤልን፤ የሐሰት የዲያብሎስን መልእክት በደስታ በመቀበል ለሰው ልጆች ውድቀት መነሻ የኾነችውን ሔዋንንና፤ ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣውን መልእክት በፍጹም እምነት ተቀብላ ሕይወት የሰጠን ጌታን የወለደችው ድንግል ማርያምን ሲያነጻጽር ‹‹The evil time which had killed Adam was changed, another good time came…›› (አዳምን እንዲሞት ያደረገች ያቺ ክፉ ቀን ተለወጠች፤ እርሱም ከሞት የሚድንባት ሌላ ቀን መጣች፤ እባቧ ሳትኾን ገብርኤል ሊናገር ተነሣ፤ ሔዋን ሳትኾን ድንግል ማርያም ቃሉን ልትቀበል ተዘጋጀች፤ በተንኰል ቃል የሚያሳስተው ሳይኾን ሕይወትን የሚያውጅ እውነተኛ ቃል ወጣ፤ በሞት ዛፍ መኻከል የሞት ዕዳዋን በጻፈችው እናት ፈንታ፤ ልጇ የአባቷን ዕዳ ኹሉ ከፈለች፤ ሔዋንና እባቡ በመልአኩና



www.ethiopianorthodox.org

በድንግል ማርያም ተተኩ፤ ያ ከመገርመሪያው የተበላሸውም ጉዳይ እንደገና ተስተካከለ፤የሔዋን ገሮርና ቀልብ አታላዩ በሚናገርበት ጊዜ ምን ያኽል እንዳዘነበለ አስተውል፤ ነገር ግን ያ በገነት ሲመለከታቸው የነበረ መልአክ አኹን በማርያም ጕሮ የድኅነት የተስፋ ቃል ሲያሠርጽ የእባቡን ክፉና መርዛማ ቃል ሲያጠፋ እርሷንም ሲያጽናና ተመልከት፤ ያንን እባብ ያፈረሰችውን ሕንጻ ገብርኤል ገነባው፤ በዔዶን ሔዋን ያፈረሰችውን ድንግል ማርያም መሠረቱን ገነባች፤ ከኹለት መልእክተኞች መልእክት የተቀበሉ ኹለት ደናግል ኹለት ኹለት ኾነው ትውልዶችን ቀጠሉ፤ አንዱ የአንዱ ተቃራኒ ኾነ፤ በእባብ አማካኝነት ሰይጣን ምስጢርን ለሔዋን ላከ፤ በመልአክ አማካኝነት ደግሞ ጌታ የምሥራቹን ወደ እመቤታችን ማርያም ላከ፤ እባብ የሐሰትን ቃል ለሔዋን ስትናገር ገብርኤል ግን የእውነትን ቃል ለድንግል ማርያም ተናገረ፤ እውነትን በሚናገር አንደበቱ መልአኩ ቃሉን አደሰው፤ እውነትን ተናገረ በዚኽም ሐሰትን ኹሉ አስወገደው፤ ተንኰልን ከራሱ ባወጣ በሰይጣን በዔዶን ገነት ድንግሊቷ ተታለለች፤ ታላቁ ስሕተት በገሮዋ ዐልፎ እንዲሰማት ዐደረገች፤ በመገርመሪያዋ ድንግል ፈንታ ሌላ ድንግል ተመረጠች፤ በዚኽችም ድንግል ገሮ ከአርያም የመጣ የእውነት ቃል ገባ፤ ሞት በገባበት በዚያው በር ደግሞ ሕይወት ገባ፤ ክፉው ያጠበቀውን ጽኑዕ የሞት ማሰሪያ ፈታ፤ ኀጢአትና ሞት ከመገርመሪያው እጅግ እንደሰለጠኑ ኹሉ፤ እንዲኹ ጸጋ ከመጠን ይልቅ በዝቶ በአዳም ታየ፤ እባብ ከሔዋን ጋር ስትነጋገር ሔዋን አልተንበረከከችም አልሰገደችም፤ ሞት በመላበት ጕዳና ሰላምና ትሕትና አይገኙምና፤ እባብ የስሕተትን ዜማ ለሔዋን ዘመረ ሐሰትን ረጨባት፤ በተፈጥሮዋ ገና ድንግል በኾነች ሔዋን ላይ ክፉ ምክርና ስሕተት ፈሰሰ፤ ለመግደል የኾነ ጠላትነትና ክፉ ምክር ደምን የተጠማ መርዙን በንግግሩ ውስጥ በአዳም ቤት ውስት አስገባ፤ በወልድ የተላከው መልአክ እንዚኽን የክፋት ሰይፎች ለመቋቋም ኼደ፤ ለድንግል ማርያም ከእግዚአብሔር የኾነውን የመዳን ብሥራትን ነገረ፤ ሰገደላት፤ ሕይወትን በውስጧ አሠረጸ፤ ሰላምን ዐወጀላት፤ በፍቅር ቀረባት የቀደመውን የሞት ዳባ በጣጠሰ፤ እባብ የገነባው የማታለል ግንብ ዳግመኛ ላይገነባ በእግዚአብሔር ልጅ በወልድ ተናደ፤ በእባብ የታጠረው የሞት ቅጥር በወልድ መውረድ ተሰባበረ፤ በሰማያትና በምድር በሚኖሩ ኀይላት መኻከል





ሰላም ይወርድ ዘንድ)[31] በማለት ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ የቀደመችቱ ሐሰ… ሐሰተኛ የኾነውን የእባቡን መርዝ የመላበት ንግግሩን ተቀብላ ባሏን በአጠ… የሰው ልጆችን በዲያብሎስ የክሕደት መርዝ እንዲወጉ ስታደርግ፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤል የእውነት ብሥራትን በእምነት በመቀበሏ፤ ዲያብሎስ የተከለውን የኀጢአት መርዝን ነቃቅሎ ያጠፋ ወሀቤ ሕይወት ጌታን ያስገኘችልን መኾኗን አስረድቷል።

በዚኽ ትምህርቱም ሔዋን ለታማኝነት የማትበቃ ተወቃሽ ስትኾን፤ ድንግል ማርያም ግን አስተዋይ የአባቷን ዕዳ የከፈለች ፍጹም እምነትን የተመላች መኾኗን ሳያስተምር አላለፈም፤ ይኽነንም በጥልቀት ስናየው ሔዋን የሐሰት መልእክትን ከሐሰተኛው በሰማች ጊዜ ከመጠየቅ ይልቅ ዝምታን በመምረጥ የሚያባብል የተንኰልና የክፋት ቃሉን በደስታ ተቀብላ፤ አምላክ መኾንን ፈልጋ በስሕተት ስትወድቅ፤ በአንጻሩ ግን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት እንደምትኾን ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሥራት፤ ይኽነን ል… ከኀሊናት ኹሉ በላይ የኾነውን ምስጢር ለመረዳት አጥብቃ የጠየቀች አስተዋ… ናት፤ ይኸውም በድንግል ማርያም መናገር ሕይወት፣ ብርሃን ሲኾን በሔዋ… ዝምታ ግን ኀጢአት፣ ውርደት፣ ሞት መምጣቱንና ዳግመኛ የሔዋን ገሮ… የሞትና የውድቀት መልእክትን ሲሰማ የድንግል ማርያም ገሮ ግን ታላቅ የኾነ… የሕይወትና የድኅነት መልእክትን መስማቱን ይኽ ቅዱስ ያዕቆብ ሲመሰክር፦ ‹‹on this account, the watcher had saluted Mary as a pledge of great peace for the whole world...›› (በዚኽም መልአኩ ድንግል ማርያምን አከበራት፤ ለዓለም ኹሉ ሰላም ታላቅ ቃል ኪዳን ነውና። ‹‹ማርያም ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ በድንግልና ትፀንሻለሽ በድንግልናም ወንድ ል… ትወልጃለሽ›› አላት። ድንግል ማርያም መለሰች እንዴት ይኽ ሊኾን ይችላል? እኔ ድንግል ነኝ እንዴት እፀንሳለኍ? በዚኽ ቅጽበት መጠየቋ እጅግ ግድ ነበር… የወልድ በእርሷ ማሕፀን የማደር ምስጢርን መልአኩ ይገልጥላት ዘንድ… እመቤታችን ማርያም ጠየቀች ከመልአኩ መልስ እንማር ዘንድ፤ ስለመ… እንድትረዳ ዐደረጋት፤ ትርፉ የእርሷንና እርሷን ለሚሰሙ ኹሉ ነውና) ሲ… እመቤታችን ከመልአኩ ጋር ያደረገችው ምልልስ እንደ ዘካርያስ በመጠራጠ…

31. Jacob of Serugh. On the Virgin pp 29-34



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ኒቆዲሞስ በመከራከር ሳይኾን፤ ብልኀ ደቀ መዝሙር ምስጢር ለመረዳት ሲል ከመምህሩ ጋር ክርክር እንደሚያነሣ ኹሉ ድንግል ማርያም በማስተዋል እየጠየቀች መልአኩ እየመለሰ ብዙ ምስጢር በመገለጹ፤ በጥያቄዋ ለስውሩ ምስጢር መታወቅ ምክንያት የኾነች መኾኗን አስተምሯል።

ሔዋን ግን የሐሰትና የሞት መልእክትን ስትሰማ ለምን? እንዴት? ብላ ሳትጠይቅ ሐሰትን በማመኗ ፈጽማ ተወቃሽ መኾኗን ሲቁ ሲያነጻጽር «Eve had not questioned the serpent when he led her astray… ሔዋን እባብ ወደሞት ሲመራት ለምን? አላለችም ነበር፤ ነገር ግን በፈቃዷ ዝምታን መረጠች፤ የሚያባብል የተንኰል ቃልንም ሳትጠራጠር አመነች፤ ኹለተኛዋ ሴት ግን የእውነት ቃል ከሚታመነው ሰማች፤ ቢኾንም ነገሩ የተረዳ እንዲኾንላት አጥብቃ ጠየቀች፤ የቀደመችው ሴት ሔዋን የዛፍን ፍሬ በመብላት አምላክ እንደምትኾን ሰማች፤ እንዴት ይኽ ሊኾን ይችላል? ብላ ግን አልጠየቀችም፤ ድንግል ማርያም ግን መልአኩ የእግዚአብሔር ልጅን እንደምትፀንስ በነገራት ጊዜ ግን የበለጠ እስክትረዳው ድረስ አልተቀበለችውም። አምላክ እንደምትኾን የአዳም ሚስት የኾነችው ድንግሊቷ ሔዋን ሳትጠራጠር የሐሰተኛውን ቃል ተቀበለች፤ የእግዚአብሔርን ልጅ ትፀንሳለች የተባለላት ግን መረመረች፣ ጠየቀች፣ ተማረች ግን ዝም አለች፤ ኹለተኛዋ ከመጀመሪያዋ ሴት እጅግ ውብ እንደነበረች አስተውሉ፤ ስለውበቷ ምክንያትም ጌታ መጥጣት እናቱ እንድትኾን ወደረጋት፤ ለእርሷ ዝም ማለት ቀላል ነበር ጥያቄ ማቅረብም እንዲኹ፤ ግን በማስተዋሏ ከመልአኩ የሰማችውን እውነት ዐወቀች ተረዳች፤ ሔዋን በምርጫዋ ተወቃሽ እንደኾነች፤ እንዲኹ ድንግል ማርያም በምርጫዋ የከበረች ኾነች፤ እንደመጀመሪያዋ ጥበብ ማነስ ኹሉ የኹለተኛዋ ጥበብ ተገለጠ፤ የመጀመሪያዋ ሴት ክፉን በፈቃዷ ስታመጣ እንዳላፈረችበት የኹለተኛዋ ስለ ወልድ በማሕፀኗ በግብረ መንፈስ ቅዱስ መፀነስ አላፈረችበትም፤ የቀደመችው ጥበብ እንደጐደላት ኹሉ ኹለተኛዋ ለሚያስተውል እጅግ ጥበብ የመላባት ኾነች፤ በቀደመችው የነበረባትን ዕዳ ኹሉ ይኽቺ ከፍላለችና፤ በቀደመችው ውድቀት ፤በኹለተኛዋ ትንሣኤ ለዘራችን ኹሉ ደረሰ፤ ነጢአት በሔዋን ቢመጣም ጽድቅ ግን ከድንግል ማርያም ተገኘ፤ በሔዋን ዝምታ ኀጢአትና ውርደት፤ በእመቤታችን ማርያም መናገር





ሕይወትና ብርሃን ከድል መንሣት ጋር ኾነ፤ እንዲኽ ብላ ለመልአኩ መለሰች «እንዴት የምትለው ይኾናል?» የወልድን ከሰማያት መውረድ በእርሷም የማደሩን አሠራር ገለጠላት፤ የተባረክሽ ሆይ መንፈስ ቅዱስ ወደ አንቺ በክብር ይመጣል፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል» እኹን የምላስ ንግግር ኹሉ የማያስፈልግ ትርፍ ነገር ነው ስለሚያስደንቅ እምነቷ ካልኾነ በቀር ማንም አይናገርም) በማለት የመጀመሪያዪቱ ሔዋንና ዳግሚት ሔዋን የተባለች ቅድስት ድንግል ማርያምን በማነጻጸር ያስተማረው ትምህርት እጅግ አድርጎ የሚረቅ የሚያስደንቅ መኾኑን ከልብ እናስተውለዋለን።

## ብርህት ዐይን (The Luminous Eye)

የቤተክርስትያን መምህራን መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት በመመርመራቸው ሔዋን ለሰዎች ኹሉ የመውደቅ የተስፋ መቁረጥ ምክንያት ስትኾን፤ ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የተስፋ ምንጭ የመኾኗን ምስጢር በድርሳናቸው በስፋት ገልጸውታል።

ከነዚኽ ሊቃውንት መኻከል አንዱ የኾነው ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ስለ ቤተክርስትያን ክብር በደረሰው ታላቅ መንፈሳዊ ድርሳን ላይ ክርስቶስን በብርሃን ሲመስል ሔዋንንና ቅድስት ድንግል ማርያምን በዓለም ላይ ባሉ ኹለት ዐይኖች መስሎ እጅግ በሚያስደንቅ አገላለጽ አነጻጽሮ አስተምሯል። ይኸውም ሔዋን በዓለም ላይ ባመጣችው ጉዳት ምክንያት በጨለመ፣ በታወረ፣ በዓለም የግራ ዐይን መስሎ ሲገልጻት ቅድስት ድንግል ማርያምን ግን ብርህት፣ የጠራች፣ ጤናማ በኾነች በቀን ዐይን መስሏታል።

ጌታችን በተራራ ስብከቱ ላይ የሥራ ኹሉ ማከናወኛ ስለኾነችው ስለ ዐይን ጥቅም ሲያስተምር «የሰውነት መብራት ዐይን ናት፤ ዐይንኽ እንዲኽ ጤናማ ብትኾን ሰውነትኽ ኹሉ ብሩህ ይኾናል፤ ዐይንኽ ግን ታማሚ ብትኾን ሰውነትኽ ኹሉ የጨለመ ይኾናል፤ እንግዲኽ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከኾነ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ?» (ማቴ ፮፥፳፪- ፳፫) በማለት ጤናማ ዐይን የሚሰጠውን ጥቅምና የታመመ የጨለመ ዐይን የሚያደርሰውን ጉዳት አስተምሯል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ከጌታ ትምህርት በመነሣት እጅግ ልዩ በኾነ



www.ethiopianorthodox.org

ሃይማኖታዊ አገላለጽ ድንግል ማርያምንና ሔዋንን በኹለት ዐይን መስሎ አነጻጽሯቸዋል። ይኸውም ሔዋንን በታማሚና በታወረ ግራ ዐይን የመሰለበት ምክንያት፤ ዐይን ጨለማ ቢኾን ሰውነት እንደሚጨልም እግርንም በየመንገዱ እንቅፋት እንደሚያጋጥመው እሾኽ እንደሚወጋው ኹሉ፤ በሔዋን ስሕተትም ምክንያት የሰው ዘር ከእውነተኛው ብርሃን ከእግዚአብሔር ተለይቶ ኀጢአት በመሥራት ጣዖት በማምለክ እየተሰነካከለ ለ፭ሺ፭፻ ዘመን ያኽል በታላቅ ጨለማ ውስጥ እንዲኖር ኾኗል።

በአንጻሩ ግን ሊቁ ቅድስት ድንግል ማርያምን ጤናማ ብርሀት በኾነች ዐይን የመሰለበት ምክንያት ዐይን ጤናማና ብሩህ ቢኾን ኹለመናችን ብሩህ እንደሚኾንልን ጨለማ እንደሚርቅልን ኹሉ፤ በሔዋን ስሕተት ምክንያት ጣዖት በማምለክ፣ ኀጢአት በመሥራት፣ በኀጢአትና በሞት ጥላ በመኖር ለጨለመበት ዓለም፤ ፍዳውን አስወግዶ የጣለ ብርሃን ክርስቶስ ብርሀት ዐይን ከተባለች ከቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ፤ ይኽ የጨለመበት ዓለም እንደገና የእግዚአብሔርን መንገድ የሚያይበትን የሃይማኖት ዐይን ገንዘብ ያደረገ ስለኾነ ሊቁ በብርሀት ዐይን መስሏታል።

ይኽነንም በመጽሐፉ ሲገልጸው ‹‹It is through the eye that the body, with its members… ሰውነት ኹሉ በአንዲት ዐይን ብርሃን ይኾናል፤ በማየትም ይመላለሳል፤ መልካም ክብር ያለውን የስሜት ሕዋስ ይሰጣል፤ ለኹሉም ሕዋሳት ታላቅ ክብር ይኾናቸዋል፤ ድንግል ማርያም የብርሃንን ምንጭ የተቀበለች መሬት ናት፤ በእርሷ በኩል ዓለምና በዓለም ያለው ኹሉ በብርሃን ተመላ፤ በሔዋን ምክንያት ጨልሞ ነበር፤ የክፉ ኹሉ ምንጭ ኾናለችና፤ እመቤታችን ማርያምና ሔዋን በምሳሌያቸው አንድ ዐይኑን እንዳጣ በአንድ ዐይኑ ሰውነቱ ኹሉ ብርሃን የኾነለትን ሰው ይመስላሉ፤ የሚታየው ዓለም ኹለት ዐይኖች አሉት፤ ሔዋን የታወረው የግራ ዐይኑ ናት፤ የሚያየው የቀኙ ዐይኑ ግን ድንግል ማርያም ናት፤ በጨለመው ዐይን በኩል ዓለሙ ኹሉ በጨለማ ተውጧል፤ ሰዎችም በጨለማ ዳበሳ ገቡ፤ ግን የሚያደናቅፋቸው ድንጋይ ጣዖት ሐሰትን የሚናገር በድን ነው፤ ነገር ግን በቀኝ ዐይኑ ዓለም በብርሃን ሲመላ ከሰማይ የወረደው ብርሃን በመኻከል ሲገኝ፤ ሰው ዳግመኛ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቀ፤ የሚያሰናክለው ዐለት ኹሉ የሕይወቱ አጥፌ





እንደኾነ ተረድቷልና››[32] በማለት በንጽጽር ገንጾታል። ይኽነን የቅዱስ ኤፍሬም ታላቅ የነገረ ማርያም ትምህርቱን ‹‹Mariological Themes in the writings of St. Ephrem the Syrian ብዬ በጻፍኩት የመመረቂያ ጽሑፌ ላይ በስፋት በጥልቀት ተንትኼ አብራርቼዋለኍ።[33]

## የክብር መጐናጸፊያ እና የበለስ ቅጠል (Rob of Glory)

አባታችን አዳምና እናታችን ሔዋን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ የዲያብሎስን የሐሰት ንግግሩን በማመን ዕፀ በለስን በበሉ ጊዜ ያገኙት የልጅነት ጸጋ የለበሱት የብርሃን ልብስ ተለይቷቸው ዕርቃናቸው እንደቀሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ይኸውም አዳም በ፴ቀኑ ሔዋን በ፹ቀኗ ያገኙትን ልጅነት በማጣት ከእግዚአብሔር ጸጋ በመራቄት በዚያች የበለስ ቅጠል ዕርቃናቸውን ለመሰወር ሞክረዋል። በዘፍ ፫፥፯ ላይ ‹‹የኹለቱም ዐይኖች ተከፈቱ፤ እነርሱም ዕርቃናቸውን እንደኾኑ ዐወቁ የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም ዐደረጉ›› በማለት ያጡትን የልጅነት ሀብት ይገልጽልናል።

ኾኖም ግን ያቺ የበለስ ቅጠል ለአዳምና ለሔዋን ዕርቃናቸውን ብትሰውርላቸውም እንኳ የተገፉትን የልጅነት ጸጋ ልትመልስላቸው ወይም ልታጐናጽፋቸው አልቻለችም። አዳምና ሔዋን በአጠቃላይ የሰው ልጆች ያጣነውን የልጅነትን ጸጋ ያገኘነው ተጠምቀን በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስትያን የተሰኘንበት፤ ራቁታችንን ገብተን የልጅነትን ጸጋ ተጐናጽፈን የወጣንበት ማየ ገቦ (ከጌታችን ቀኝ ጐን የፈሰሰ ንጹሕ ውሃ) የልጅነትን ጥምቀት ያገኘነው ጌታችን ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ከተወለደ ወዲኽ ነውና (ዮሐ ፲፱፥፴፬)፤ ይኽነን ምስጢር በማወቅ በርካቶች የነገረ መለኮት ምሑራን ቅድስት ድንግል ማርያምን ለአዳም የክብር ካባ የፈተለችለት፣ አዳም ከዕርቃኑ የተሰወረባት የበለስ ቅጠል እያሉ አመስግነዋታል።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ አዳም ቀድሞ ስላጣው በኋላ ግን ስላገኘው የልጅነት ጸጋ በመጽሐፉ ላይ ‹‹The child (Mary) gave her hand to help

32. St Ephrem, Hymns On the Church no 37
33. Rodas Tadese, Mariological Themes in the writings of St. Ephrem the Syrian,Un published essay, H.T.T.C pp 43,46



www.ethiopianorthodox.org

her aged mother... (ልጇ ማርያም ያረጀች እናቷን አገዘች (ረዳቻት)፤ እባብ ጥላት የወደቀችዪቱን አነሣቻት፤ የክብርን ካባ የፈተለች ልጇ ድንግል ማርያም ናት፤ ላባቷ ለአዳም የሰጠች፤ እርሱም ከሞት ዛፍ በኋላ የተራቈተውን ሰውነት ሸፈነበት)[34] በማለት ልጅነትን የሰጠንን ጌታ የወለደችልን መኾኗን መስክሮላታል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም የልደትን ነገር በተናገረበት ድርሳኑ ሔዋን የእግዚአብሔርን ሕግ በመጣሷ የልጅነት ጸጋዋ ተገፎ በኀፍረት በኀስቍልና ስትገኝ ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በንጽሕና በቅድስና ጸንታ ስለመኖሯ ‹‹Eve in her virginity put on leave of shame...›› (ሔዋን በድንግልናዋ እያለች የሐፍረትን ቅጠል ለበሰች፤ ነገር ግን ጌታ ያንተ እናት ማርያም በድንግልናዋ የክብርን ልብስ ለበሰች፤ ይኸውም የሰውን ዘር አጠቃለለ)[35] ሲል ገልጧል፤ ዳግመኛ ይኸው ሊቅ ጥንት አዳምና ሔዋን በአጠቃላይ የሰው ዘር ያጣውን የልጅነትን ጸጋ፤ ክብር ይግባውና ዐማኑኤል አምላካችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ ወዲኽ እንደመለሰልን በመጽሐፉ ‹‹Mary has woven a robe of glory to give to her ancestor...›› (በዛፎች መኻከል ራቁቱን ለነበረው ወገኗ ድንግል ማርያም የክብር ልብስን አዘጋጀችለት፤ ለበሰው ውበትን ተቀዳጀ፤ ሚስቱ ከክብር እንዲያንስ ዐደረገችው፤ ሴት ልጁ (ማርያም) ግን ረዳችው እርሱም ብርቱ ኾነ... ጌታ ሆይ ባንተ እነዚኽ በዔዶን ገነት የሚያገዘኑ ኹለት ሰዎች መጽናናትንና መነቃቃትን ያግኙ፤ ክብራቸውን የተነጠቁ ቅጠልን ለበሱ፤ ስለእነርሱ ስትል በመጠቅለያ ጨርቅ ተጠቀለልክ እነርሱ ወደ ገነት ይገቡ ዘንድ)[36] በማለት ልጅነታቸውን ተገፈው በመንጸፈ ደይን ወድቀው፣ በእግረ አጋንንት ተረግጠው ለነበሩ ለሰው ልጆች የቀደመ ቦታቸው ገነትን፣ የቀደመ ክብራቸው ልጅነትን የሰጠ ክርስቶስን ወልዳ ያስገኘችልንና፤ አዳም በማጣቱ በሔዋን ያጣውን የክብር ልብስ ዳግመኛ ያዘጋጀችለት ድንግል ማርያም መኾኗን መስክሯል።

በተጨማሪም ይኽነን የቅዱስ ኤፍሬም ጥልቅ ትምህርቱን በመመረቂያ

34. Jacob of serugh, on the mother of God. P. 11
35. St Ephream Hymns on the Nativities by Mc Vey p 154
36. Bride of Light p 34





ጽሑፌ ‹‹The Robe of glory›› በሚለው ክፍል በስፋት ተንትኜዋለኊ[37] ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም የኹላችንን ዕርቃን የከደነ ልጅነትን ያጐናጸፈንን ክርስቶስን ያገኘንባት መኾኗን በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *‹‹ዕፀ በለሳን እንከ እሰምየኪ፤ ወህየንተ ቈጽለ በለስ ዘሰፈየ አዳም ወገብረ ሎቱ መዋርዕተ ወከደነ ዕርቃኖ፤ ወከማሁ አነሂ ተከደንኩ በመርዓ ጥምቀት ዘውሕዘ እምገቦ ወልድኪ››* (እንግዲኽ የበለሳን ዕንጨት ብዬ እጠራሻለኊ፤ አዳም ሰፍቶ መከለያ አድርጐ ዕርቃኑን በሰወረበት የበለስ ቅጠል ፋንታ እንዲኹ እኔም ከልጅሽ ጐን ከፈሰሰው ጥምቀት ውሃ (ልጅነትን) ተከደንኊ)[38] በማለት አጕልቶ አስተምሯል።

## የሴቶች ኹሉ መመኪያ

ልዑል እግዚአብሔር ሔዋንን በአርአያ፣ በአምሳል፣ በክብር ከአዳም እኩል አድርጐ ቢፈጥርም በሔዋን ስሕተት ምክንያት ሴቶች ኹሉ የሚመኩበት ነገር አጥተው፣ የሴትነት ክብር ተነፍጓቸው ምድረ ርስት ከመውረስ ተከልክለው ወንዶች እየተመኩባቸው ይኖሩ ነበር። ኾኖም ግን በሔዋን ምክንያት ያጡትን ክብር ዳግመኛ በቅድስት ድንግል ማርያም ተመልሶላቸው ከወንዶች ጋር መተካከላቸው በጕልሕ ታውቋልና እመቤታችን የሴቶች ኹሉ መመኪያ ትባላለች።

ይኸውም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ወንዶች ሴቶችን ‹‹ሔዋን ከእኛ ወገን ከኾነ ከአዳም ብቻ ተገኘች እንጂ፤ አዳም ከሔዋን አልተገኘም›› እያሉ በሴቶች ላይ እየተመኩባቸው ይኖሩ ነበር፤ በዚኽም ሲያዝኑ ፭ሺ.ሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም አካላዊ ቃል ክርስቶስ ያለ አባት ከቅድስት ድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ከተወለደ በኋላ ግን፤ሴቶች ኹሉ ሐዘናቸው በደስታ ተለውጦ *‹‹ሔዋን ከእናንተ ወገን ከኾነ ከአዳም ብትገኝም ከኛ ወገን ከኾነች ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰማያዊው ንጉሥ ክርስቶስ እንበለ ዘርዕ ተወልደ የለምን››* እያሉ የሚመኩባት ኾነዋልና እመቤታችን የሴቶች እናቶቻችን እኅቶቻችን ኹሉ መመኪያቸው ናት (፩ቆሮ ፲፩+፲፪፤ ገላ ፬+፬)።

37. Rodas Tadese, Mariological Themes in the writings of St. Ephrem the Syrian,Un published essay, H.T.T.C p 46
38. አባ ጊዮርጊስ፤አርጋኖን ዘሰኑይ ፮+፰



www.ethiopianorthodox.org

ሊቁ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ሴቶች በድንግል ማርያም ምክንያት ያላገኙት መተካከል በመጽሐፉ ላይ «*ከመ ኢይትመካሕ በእንተ ዘአውጽአ ብእሲተ ዘእንበለ ብእሲት፤ ወለደት ድንግል ብእሴ ዘእንበለ ብእሲ ከመ በሱታፌ መንክር ይትዐወቅ ዝንቱ አሐዱ ክብር እንተ ፍጥረት*» (አዳም ያለ እናት ሔዋንን ስለአስገኘ እንዳይመካ ድንግል ያለ አባት ክርስቶስን ወለደች፤ ድንቅ በሚኾን አንድነት ይኽ አንድ የፍጥረት እኩልነት ይታወቅ ዘንድ)[39] በማለት አስረድቷል።

በብሉይ ኪዳን ቀድሞ ወንዶች ሴቶችን ከእናንተ ወገን በኾነች በሔዋን ስሕተት ምክንያት ክርስታችን ከገነት ወጥተናል እያሉ፤ ምክንያት በመፍጠር ሴቶችን ምድረ ርስትን አያካፍሏቸውም ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈላቸው መልእክቱ ላይ «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትኾኑ ዘንድ የተጠመቃችኁ ኹሉ ክርስቶስን ለብሳችኊልና፤ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፤ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፤ ወንድም ሴትም የለም፤ ኹላችኁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችኹና፤ እናንተም የክርስቶስ ከኾናችኹስ፤ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችኁ» (ገላ፫፥፳፰) በማለት እውነተኛውን ትምህርት በማስተማር እኩልነታቸውን አጕልቶ አስተምሯል። ሴቶችም ይኽነን ትምህርት በመረዳታቸው የሰውን ዘር ኹሉ ወደቀደመ ቦታችን ወደቀደመ ርስታችን ወደቀደመ ክብራችን የመለሰ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ ወዲኽ ወንዶችን «*በኛ ምክንያት ከገነት ከመንግሥተ ሰማያት ብትወጡ፤ ከኛስ ወገን ከኾነች ከቅድስት ድንግል ፤ጌታ ተወልዶ ርስታችኁ ገነት መንግሥተ ሰማያትን አግኝታችኁ የለምን*» እያሉ የሚመኩባት ኾነዋልና ቅድስት ድንግል ማርያም የሴቶችን ዕዳ የከፈለችላቸው መመኪያቸው ናት።

ይኽነንም ልዩ ምስጢር ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ «*ወሀሎ ላዕለ ትዝምደ አንስት ዕዳ ለትዝምደ ዕደው እስመ እምአዳም ወፅአት ብእሲት እንበለ ብእሲት ወበእንተ ዝንቱ ወለደት ድንግል ብእሴ እንበለ ዘርዐ ብእሲ ከመ ትፍድዮ ለብእሲ ዕዳሃ ለሔዋን*» (ለወንዶች የሚከፈለው ዕዳ በሴቶች ላይ ነበረ፤ ያለ እናት ሔዋን ተገኝታ ነበርና፤ ለዚኽም ድንግል ያለ ወንድ ዘር ክርስቶስን

39. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ሃይማኖተ አበው፤ ምዕ ፷፮፥፷፱፤ገጽ ፪፻፳፬





ወለደች፤ የሔዋንን ብድራት ለወንዱ ትከፍለው ዘንድ) በማለት ሲገልጸው፤ ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በሔዋን ስንፍና ምክንያት ሴቶች ያጡትን ክብር ዳግመኛ በድንግል ማርያም ምክንያት ማግኘታቸውን በስፋትና በጥልቀት ሲገልጽ «O daughters of the nations, approach and learn to praise ...» (የሕዝቦች ሴቶች ልጆች ሆይ ካባቶቻችኁ ስሕተት ነጻ ያወጣችኹን ቅረቡቱ፤ እርሱንም ማመስገን ተማሩ፤ ያ ሔዋን የዘጋችውን የማይናገር አፍ አኹን በእመቤታችን ማርያም ተከፈተ፤ ለእኅታችኁ ምስጋናን ለመዘመር፤ አሮጊቷ ሴት (ሔዋን) በምላሶቻችኁ ዙሪያ የዝምታን ገመድ ቋጠረች፤ የድንግል ልጅ እሥራታችኹን ፈታ፤ ጮኻችኁ ታመሰግኑ (ትዘምሩ) ዘንድ፤ ያገባችው (ሔዋን) የዝምታን መጠምጠሚያ በአፋችኁ አኖረች፤ ግን ድንግሊቱ የተዘጋውን የምላሳችኹን በር ከፈተች፤ እስከ አኹን ወገናችኁ በሔዋን ምክንያት አንሶ ነበር፤ ከእንግዲኽ ወዲኽ ግን ሃሌ ሉያን ለመዘመር ተመልሷል፤ ከእናታችኁ ከሔዋን ክፋት የተነሣ ከፍርድ በታች ነበራችኁ፤ ከእኅታችኁ ከድንግል ማርያም ልጅ የተነሣ ግን ነጻ ወጣችኁ፤ ያለ ኀፍረት ምስጋናን ለማዜም ፊታችኹን ግለጡ፤ በልደቱ ለሰው ልጆች ነጻነት የሰጣችኹን ታመሰግኑ ዘንድ)[40] በማለት ድንግል ማርያም ለሰው ልጆች ነጻነት በተለይ ለሴቶች እኩልነት ያደረገችውን ድርሻ በስፋት አስተምሯል።

ይኸውም ሔዋን ሴቶች ኹሉ ለእግዚአብሔር ምስጋና እንዳያቀርቡ የዘጋቺውን አፍ ዳግመኛ ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ክብር ዝማሬ እንዲያቀርቡበት ምክንያት ኾናቸዋለችና የሴቶች ኹሉ መመኪያ ተብላለች።

## የአዳምና የሔዋን ተስፋ

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔር አምላክ የሰጣቸውን ሕግ በዲያብሎስ ክፉ ምክር አፍርሰው ዕፀ በለስን ከበሉ በኋላ፤ ለስሕተታቸው ምክንያት የኾናቸውን በእባብ ያደረ ዲያብሎስን ታላቅ እርግማንን ረግሞታል። ይኽም ዲያብሎስ የተረገመው እርግማን ለአዳምና ለሰው ዘር ታላቅ የተስፋ ቃል ሲኾን በኋለኛው ዘመን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በመስቀሉ ዲያብሎስን ድል እንደሚነሣው የሚያሳውቅ የመገናኛረያው የድኅነት ተስፋ

40. Jacob of Serugh,A Metrical Homily On Holy Ephrem p 47



www.ethiopianorthodox.org

ነበር። ይኸውም በዘፍ ፫፥፲፭ ላይ እንደተጻፈ በእባብ አንጻር ዲያብሎስ የተረገመው እርግማን ይኸ ነበር ‹‹በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኊ፤እርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ›› ብሎታል።

ይኸውም *<u>‹‹ባንተና በሴቲቱ››</u>* ማለት በሔዋን መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኊ ብሎ፤ በዲያብሎስና በሔዋን መኻከል የሚኾነውን ታላቅ ጸብና ክርክር ነግሮታል። አኹን እግዚአብሔር እንዲኽ ማለቱ ሔዋን ከዲያብሎስ ጋር ተጣልታ ድል የምትነሣው ኾና አይደለም፤ ኾኖም ግን ከሔዋን ባሕርይ ከተገኘች ዳግሚት ሔዋን ከምትባል ከቅድስት ድንግል ማርያም ፤የዲያብሎስ ምክሩን የሚያፈርስ፤ኀይሉን የሚያደክም፣ አሽክላውን የሚቈርጥ፣ መርዙን የሚያጠፋ ቤዛ ኵሉ ክርስቶስ የመወለዱን ነገር ሲናገር ነው (፩ዮሐ ፫፥፰- ፱)። *<u>‹‹በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኊ››</u>* በማለት የዲያብሎስ የግብር ልጅ በተባሉት ዲያብሎስ ባደረባቸው በአይሁድ መኻከልና፤ ከሔዋን ባሕርይ ከተገኘ ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም በድንግልና በተወለደው በባሕርይ ልጇ በክርስቶስ መኻከል ጸብና ክርክር እንደሚኾን አስቀድሞ ገልጧል።

በዚኽ በሰጣቸው ተስፋ *መሠረት* አካላዊ ቃል ክርስቶስ ሰው በኾነ ጊዜ ይኽ ሲፈጸም ዲያብሎስ በአይሁድ ልቡና ዐድሮ ጌታን እንዲሰቅሉት ያነሣሳቸው ነበር። ጌታም አይሁድን ‹‹ንግግሬን የማታስተውሉ ስለምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው። እናንተ ከአባታችኊ ከዲያብሎስ ናችኊ፤ የአባታችኹንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችኊ፤ እርሱ ከመጀመሪያ ነፍሰ ገዳይ ነበር፤ እውነትም በእርሱ ስለሌለ በእውነት አልቆመም፤ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፤ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና፤ እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለኾንኊ አታምኑኝም።›› (ዮሐ ፰፥፵፬-፵፭) በማለት ማኅበራነ አይሁድ የግብር አባታቸው የዲያብሎስን ፈቃድ ፈጻሚዎች መኾናቸውን ነግሯቸዋል።

ይኸውም ኀጢአት በመሥራት የተጐዱ ኹለቱ (አዳምና ሔዋን) ሲኾኑ ተስፋውም የአዳምና የሔዋን ሲኾን *‹‹ማእከለ ዘርያመ››* (በዘሮቻቸው) አላለም፤ ነገር ግን ሔዋንን ብቻ ለይቶ *<u>‹‹በዘርዋ››</u>* ብሎ ተስፋውን የሰጠበት ምክንያት አካላዊ ቃል ክርስቶስ ተወልዶ የሚያድናቸው ቅድመ ዓለም ከአብ ያለ





እናት እንደተወለደ ኹሉ፤ ድኅረ ዓለም ያለ አባት ከዳግሚት ሔዋን ከድንግል ማርያም ብቻ በድንግልና ተወልዶ ነውና ለሔዋን ብቻ ሰጥቶ ተስፋውን ገልጾለታል።

ይኸውም አካላዊ ቃል በሰጠው ተስፋ *መሠረት* ከሔዋን ዘር ይወለድ ዘንድ ስላለው ቅዱስ ጳውሎስ ሲናገር ‹‹እንግዲኽ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ›› (ገላ ፫፥፲፱) በማለት የሰጠውን ተስፋ አጕልቶ ከተናገረ በኋላ፤ በሰጠው ተስፋ *መሠረት* ከቅድስት ድንግል የመወለዱን ነገር ሲገልጽ ‹‹ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ፤ ከሴትም ተወለደ›› (ገላ ፬፥፬) ሲል ጌታ የተሰጠውን ተስፋ እንደፈጸመው አስተምሯል።

*‹‹እርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ›*› በማለት እንደተናገረው አካላዊ ቃል ወልደ እግዚአብሔር ሰው በኾነ ጊዜ ዲያብሎስ በገዳመ ቆሮንቶስ በአካል በመምጣት በመፈተን፤ ከዚያም በልበ አይሁድ በማደር ሰኰና ትምህርቱን፣ ሰኰና ተአምራቱን በመቃወም በመስቀል ሲያሰቅለው፤ ጌታም በመስቀል ተሰቅሎ በመስቀሉ የእባቡ የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ድል ነሥቶት ዓለምን አድኖ ለአዳምና ለሔዋን የሰጠውን የተስፋ ቃሉን ፈጽሞታል። በማእከለ ምድር በቀራንዮ በመስቀል ተሰቅሎ የእባብ የዲያብሎስን ራስ ቀጥቅጦ ሥልጣኑን እንደሚያጠፋ ፤ልበ አምላክ ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በመዝሙሩ ላይ ‹‹እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፤ በምድርም መኻከል መድኀኒትን ዐደረገ፤ አንተ ባሕርን በኀይልኽ አጸናኻት፤ አንተ የእባቦችን ራስ በውሃ ውስጥ ሰበርኽ፤ አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥኽ›› (መዝ ፸፫፥፲፪-፲፬) በማለት ለአባታችን አዳም በሰጠው ተስፋ መሠረት፤ በመስቀል ዲያብሎስን ሰራዊተ አጋንንትን ድል የማድረጉን ነገር ተናግሯል።

በኦርቶዶክስ የነገረ መለኮት ትምህርት ታላቅ አባት የተባለው ሄሬኔዎስ ለመናፍቃን ምላሽ በሰጠበት መጽሐፉ እግዚአብሔር በዘፍ ፫፥፲፭-፲፯ ላይ ለዲያብሎስ መርገም የኾነ ለአዳምና ለሔዋን ግን በረከትና ተስፋ አድርጎ የሰጣቸው ዐዲስ ተስፋ በክርስቶስ ስለመፈጸሙ ሲያስተምር ‹‹Christ completely renewed all things...›› (ክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ኹሉንም ነገር



www.ethiopianorthodox.org

ሰጠ፤ እናም ከጥንት ገሮምሮ በአዳም ምክንያት እስረኛ ያደረገን እሱን አደቀቀ፤ ራሱን ረጋገጠ፤ በኦሪት ዘፍጥረት ላይ ጌታ ለእባቡ እንዲኽ እንዳለ ‹‹በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነት አደርጋለኊ፤ እርሱ ራስኽን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለኽ››(ዘፍ ፫፥፲፭) ፤ከዚያ ጊዜ ገሮምሮ በአዳም አምሳል ከድንግል የሚወለድ እሱ፤ የእባብን ራስ የሚቀጠቅጥ መኾኑ በግልጽ ታየ(ታወጀ)፤ ይኽ ዘር ሐዋርያው በገላትያ መልእክቱ ላይ ‹‹እንግዲኽ ሕግ ምንድር ነው? ተስፋው የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ››(ገላ ፫፥፲፱ ) ፤በማለት የተናገረለት ነው፤ ይኽንን በግልጽ በተመሳሳይ መልእክቱ ላይ ‹‹ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ላከ ከሴትም ተወለደ›› (ገላ ፬፥፬) በማለት ተናግሯል፤ ጠላት በትክክል አይሸነፍም፤ እሱን ለመማረክ ሰው ኾኖ ከሴት ካልተወለደ በቀር፤ ሰውን ከጥንት ገሮምሮ ለመቃወም በሴት በኩል ኀይል አግኝቶ ነበር በዚኽ ምክንያት ጌታ ራሱን የሰው ልጅ በማለት ተናገረ)[41] ሲል ተንትኖ ገልጾታል፡፡

. ሊቁ አባ ጊዮርጊስም እንደ ሄሬኔዎስ የተፈጸመውን የድኅነት ምስጢር እያነጻጸረ በመጽሐፈ ምስጢር ላይ ሲያብራራ *‹‹ቀደመ እግዚአብሔር ረጊሞታ ለአርዌ ምድር ወኢተሰአላ በእንተ አበሳሃ ዘከመ ተስእሎሙ ለአዳም ወለሔዋን እስመ አእመረ ከመ መሠረተ ኀጢአት እምአርዌ ምድር ወፅአ፡፡ ዓዲመ ተቀሐዎ እግዚአብሔር ለሰይጣን በከመ አምጽአ ሞተ ሰይጣን በምክረ እምነ ሔዋን ወከማሁ አምጽአት ሕይወተ እግዝእትነ ማርያም በከመ ተሰደድነ በእንተ ብእሲት ኮነ ልጹቃነ መንገለ እግዚአብሔር በብእሲት በከመ አሰፈዎሙ ዲያብሎስ ከዊነ አምላክ ለአዳም ወለሔዋን ከማሁ አሰፈዋ ገብርኤል ለማርያም ወሊደ አምላክ በሥጋሃ በከመ ሔሰነ እግዚአብሔር በበሊዐ ዕፀ ዕልወት ከማሁ ተሣሃለነ እግዚአብሔር በዕፀ መስቀሉ በከመ ተከሥተ ዕርቃነ አዳም ማእከለ ዕፀዊሃ ለገነት ከማሁ ተከሥተ ዕርቃነ ትስብእቱ ለመድኀኒነ ማእከለ ጉባዔሆሙ ለማኅበረ እስራኤል››* (እግዚአብሔር እባብን በመርገም ገሮመረ፤ አዳምንና ሔዋንን እንደጠየቃቸው ስለ በደሏ አልጠየቃትም፤ የኀጢአት መሠረት ከእባብ እንደወጣ ዐውቋልና፤ዳግመኛም እግዚአብሔር ሰይጣንን ተቃወመ፤ እናታችን ሔዋንን በመምከር ሰይጣን ሞትን እንዳመጣ፤ እንዲኹ

41. Ireneaus,Against Haeresus V





በእመቤታችን በማርያም ሕይወትን አመጣ፤ በሴት ምክንያት እንደተሰደድን በሴት ምክንያት ወደ እግዚአብሔር ቀረብን፤ ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን አምላክ መኾንን እንዳስመኛቸው፤ እንዲኹ ገብርኤል ለድንግል ማርያም በሥጋዋ አምላክን እንደምትወልድ አበሠራት፤ የክሕደትን ዛፍ በመብላት እግዚአብሔር እንደነቀፈን በዕፀ መስቀሉ ይቅር አለን፤ በገነት ዛፎች መኻከል የአዳም ራቁትነት እንደተገለጠ እንዲኹ የመድኀኒታችን የሰውነት ራቁትነት በእስራኤል ሕዝብ ጉባዔ መኻከል ተገለጠ)[42] በማለት በዘመነ *ሥጋዌ* የተደረገውን የተስፋው ቃል የድኅነት ምስጢርንና የተፈጸመውን ካሳ አብራርቷል፡፡

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ሔዋን እና እባብ በፈጠሩት ስምምነት የሰው ኹሉ ዘር ቢወድቅም፤ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የጠላታችን የዲያብሎስን ምክሩን አፍርሶ ድል ነሥቶ ያጣነውን ገነትን ዳግመኛ እንደመለሰልን ሲተነትን ‹‹In Eden Eve wrote out...›› (በዔዴን ሔዋን ጠንካራ የዕዳ ሰነድ በጽሑፍ ገለጸች (ቆላ ፪፥፲፬)፤ ውጤቱም በእሷ ልጆች ላይ ሰቈቃውና ሁከት ኾነ፤ ከትውልድ ወደ ትውልድም ሞትን አመጣ፤ እባቡ ሸረኛው ጸሐፊ በተንኰሉ ጽፎ ፈርሞ አተመው፤ ጥንት የነበረ ዘንዶ በምክሩ ዕዳው እንዲሰፋ ዐደረገ፤ የሰው ዘር በማራኪው ጉድን (ባልንጀራነት) ፍቅር እንዲወድቅ ኾነ፤ ዘንዶውን በመስማቱ አዳምም ከገነት ለመውጣቱ ምክንያት ኾነ፤ የሔዋን ኀጢአት የዕዳውን ስምምነት ዐደረገ... ዘለዓለማዊቷ ድንግል ወጣት የእሷን እናት ዕዳ ከፈለችላት ለእሷ ምስጋና ይግባት፤ ትውልዱን ኹሉ ያሳመመ (ያስለቀሰ) ሰነድ ተቀዷልና፤ እባቡ በመርዘኛ እቅዱ በደካማዪቱ በሔዋን ገሮሮ መርዝ ተነፈሰ፤ ይኽ ከመግደል የማይመለስ ውጤት ከትውልድ ወደ ትውልድ ተሻገረ፤ ከድንግል ማርያም የተወለደው ሕፃን ያን እባብ እስኪገድለው ድረስ፤ የአብ ቃል ርደቱን ከፋው በገባበት በዚያ ገሮሮ ዐደረገ፤ የእባቡን መሥመር ተመልክቶ ዱካውን ተከተለ፤ በንጽሕት ድንግል ገሮሮ ፈጣን ርደቱ የእባቡን መርዝ ጠርጎ ጣለ፤ ጥፋትን ያስከተለ የእባቡ ጥቆማ በገሮሮ በኩል ገባ፤ ሞት በገባበት በዚያ በር ሕይወት ሊገባ ይገባዋልና፤ ኀጢአት በተቀመጠበት በዚያ ስፍራ ጸጋ ሊነግሥበት ሊትረፈረፍ ይገባዋል (ሮሜ ፭፥፳)፤

42. አባ ጊዮርጊስ፤መጽሐፈ ምስጢር ፤ገጽ ፵፮



www.ethiopianorthodox.org

አብ ለቃሉ ታማኝ መልእክተኛ ገብርኤልን ላከ፤ ዐላማውም ለወጣቷ ድንግል ለኹሉ ደስታን የሚሰጥ ሰላምታን ለማቅረብና ያ ርጉም በገነት ያስተዋወቀው የከረረ ኹኔታ ፍጻሜውን ሊያመጣ ነው፤ ያ መንፈሳዊ ፍጥረት ወደታች በረረ፤ ወደ እመቤታችን ማርያም ሲደርስ ወደ ታች እጅ ነሥቶ ብሥራቱን አሰማ፤ አፉን ከፍቶ ለእሷ ደስታ ሰላምታውን በገሮዋ ዘራ፤ አብ ልጁን በሚመለከት ለእሷ የላከውን ረኀርሙን ደብዳቤ አውጥቶ ለእሷ ሰጠ፤ የእግዚአብሔር የኾነ ይኽ ስውር ምስጢር በተላከው ጠባቂ ምክንያት በግልጽ ወጣ፤ በዐዲሱ ዐዋጅ በእሳታዊ ፍጡር አፍ በነበልባላዊ ልሳን ስውሩ ምስጢር ተነገረ)[43] በማለት ዲያብሎስ ከሥጋ ከይሲ ሥግው ኾኖ በሔዋን ገሮ ለትውልድ ኹሉ ፍዳን ያስከተለ ሞትን ቢያመጣም ክብር ይግባውና ጌታ በመልአኩ አማካኝነት በቅድስት ድንግል ማርያም ገሮ እውነትን ልኮ ሥጋዋን ተውሕዶ ዲያብሎስን ድል የነሣ መኾኑን አስተምሯል።

የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴ የበዛለት ይኸው ሊቅ የተረገመው እባብና ሔዋን የፈጠሩት ስምምነት ያመጣውን ሞትና፤ የቅዱስ ገብርኤልና የድንግል ማርያም ስምምነት ያመጣውን ሕይወት ሲገልጽ ‹‹The serpent and Eve had dug a grave for Adam...›› (እባብና ሔዋን ለአዳም መቃብርን ቆፈሩ፤ በሲኦልም እንዲጣል ዐደረጉት፤ ገብርኤልም ወደ ድንግል ማርያም መጣ ተናገራትም፤ ከዚኽም ነገር ምስጢር ተገኘ፤ ይኸውም የሞቱትን ኹሉ የሚያነሣ ኾነ (ነው)፤ የአዳም ድንግሊቱ ሚስቱ በተንኰል ያታለላትን ውሸታሙን ተቀበለች፤ አጥፊውን ሰማችው በጅልነት አመነችው፤ እናም በገነት በነበረ መራራ ፍሬ አዳም እርቃኑን እንዲኾን ዐደረገች (ዘፍ ፫፥፮-፯)። ወደ ዳዊት ልጅ ወደ ድንግል ማርያም ስንመጣ የጠባቂውን ሰላምታ ተቀብላ የክብር ካባን አዘጋጅታ አዳም ለዕርቃኑ ልብስ እንዲኾነው አቀረበችለት፤ አኹን ሙሽራው በሰርግ ክፍሉ አሸብርቆ ቆመ፤ ኹለት ደናግል አሉ ምግባራቸው የተለያየ፤ አንዷ ባሏን የጣለች ሌላዋ ለአባቷ ረዳት የኾነች፤ በሔዋን ምክንያት አዳምን ሞት አገኘው፤ በእመቤታችን ማርያም ግን ገነትን ተሰጠው፤ ኹለት መልእክተኞች ወደ ዓለም ተላኩ፤ አንዱ ሰይጣን ሌላው መልአክ፤ እባብ ወደ ሔዋን ገብርኤል ወደ ድንግል ማርያም፤ በኹለቱም የሞትና የሕይወት ምርጫ ያለበት፤

43. Bride of light, pp, 92-97





የአትክልቱ ቦታ ብልኁ ጠባቂ ኹለት ዛፎችን ተከለ፤ በአንዱ ሞትን አንጠልጥሎ በሌላው ሕይወትን ደብቆ፤ በዚኽም ለአዳም ፈተናን ሰጠው፤ ከዚኽ ፈተና ክብርን ይቀዳጅ ዘንድ፤ ጌታም ለአዳም ሕግን ሰጠው፤ በውስጡም ሞት ካለበት ከዕውቀት ፍሬ እንዳይበላ ከለከለው፤ እባብና ሔዋን ተስማምተው በፈጠሩት ውሸት ምክንያት ተዋጊው በትግሉ ተሸንፎ ከክብሩ ተዋረደ፤ በሔዋን ምትክ ድንግል ተተካች፤ ከእርሷም አምላክ ተገኘ፤ ፍሬውንም አቆየልን፤ በገነት ያልቀመሱትን ከድንግል ማርያም አገኙት፤ ከፍቅሩ የተነሣ ራሱ የሰጠው ለበሉትም ጥንካሬን የሚሰጥ፤ ዛፉም ባፍቅሩ ነደደ ከእርሱም ለበሉት፤ ነገር ግን በሰይጣን ተታለው በገነት ያገኛቸውን ውርደት የሚያስቀር፤ ዛፉ ሲሸሻቸው እርሱ በታላቅ ርኅራኄ ተከተላቸው፤ በራሳቸው ቦታ እንዲበሉት የተሰጣቸው፤ ከዕውቀት ዛፍ ኀይልን ተራቡ ተመኙ፤ ነገር ግን ድንግል ካለመሻት ያንን ፍሬ ፀነሰች፤ በዚኽም በመመኘት ምክንያት ወደ አዳም ዞሮ የመጣ ሞት፤ በእርሷ ከኹሉም ትውልድ እንዲወገድ ኾነ፤ ድንግል ማርያም የዕውቀት ዛፍ በውስጧ ሳይኖር፤ እንደ ሔዋን ያለ ሞትን የሚያመጣ አሳሳች እባብ የሌለባት የአምላክ ገነት ናት፤ ከእርሷም ሕይወትን የሚሰጥ በቅጣት ያለውን ከግዞቱ ወደ ገነት የሚመልስ የሕይወት ዛፍ ወጣ፤ ኹለት ደናግል አሉ ምግባራቸው የተለያየ፤ አንዷ ባሏን የጣለች ሌላዋ ለአባቷ ረዳት የኾነች፤ በኪሩቤልና በእሳት ሰይፍ ሲጠበቅ የነበረ ያ ዛፍ ከንጹሕቲቷ ድንግል ተገኘ (ዘፍ ፫፥፳፬)) በማለት በእባብ ተንኰል ምክንያት በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ፣ በርደተ መቃብር ላይ ርደተ ገሃነም ተፈርዶባቸው ለ፭ሺሕ፭፻ ዘመን በመንጸፈ ደይን ወድቀው በእግረ አጋንንት ተረግጠው የነበሩ የሰው ልጆችን ለማዳን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ የእባብ የዲያብሎስን ራስ በመስቀል ቀጥቅጦ፤ ለእኛ ሕይወትንና መድኀኒትን ሊኾነን በገነት ያጣነውን የሕይወት ዛፍ ማለት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በዚኽ ዓለም የሰጠን መኾኑን በጥልቀት አስተምሯል።

በመኾኑም እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያን ታላቅ ተስፋ ለአዳምና ለሔዋን የሰጠ፤ የሰጠውንም ተስፋ የፈጸመ የጌታችን እናቱ ናትና እንወዳታለን፣ እናመሰግናታለን፣ እናከብራታለን፣ እናገናታለን። አዳምና ሔዋን ለነሱ የድኅነት ተስፋ ለዲያብሎስ ግን የሽንፈት ዜና የኾነውን ይኽነን የተስፋ ቃል ከሰሙ በኋላ እንኳ አዳም የቤተ ፈት ልማድ አላገኘውም፤ ቤተ ፈት በዚኽ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ እበላ እጠጣ፤ በዚኽ ጊዜ ተድላ ደስታ አድርግ ነበር ብሎ ያዝናል፤ እሱ ግን ፈጣሪዬ አትብላ ያለኝን ዕፀ በለስን በልቼ በደልኊ ብሎ በኀጢአቱ ፲፩ሱባዔ ፺፰ ዓመት መሪር ለቅሶን አለቀሰ *‹‹ወአልቦቱ ካልዕ ኀሢና ላዕለ ኀጢአቱ ዘእንበለ ብካይ ወላሁ››* እንዲል መቅድመ መንጌል ያን ጊዜ ‹‹በአንተና በሴቲቱ መኻከል በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነትን አደርጋለኊ›› ሲል የተናገረውን የተስፋ ቃል በማጕላት *‹‹ወእምድኅረ ኀሙስ መዋዕል ወመንፈቀ መዓልት እምሕረከ ወእሣሃለከ በብዝኀ ሣህልየ ወምሕረትየ፤ ወእወርድ ውስተ ቤትከ ወአኀድር ውስተ ከርሥከ ወበእንቲኣከ ኦ አዳም እትወለድ ከመ ሕፃን ወበአንቲአከ ኦ አዳም አሐውር ውስተ ምሥያጥ፤ ወበእንቲኣከ እጸውም ፵ መዓልተ ወ፵ ሌሊተ፤ ወበእንቲኣከ እትዌከፍ ወእትዔገሥ ሕማማተ ወበእንቲኣከ እሰቀል ዲበ ዕፀ መስቀል››* (በፍጹም ይቅርታዬ ከዐምስት ቀን ተኩል በኋላ በፍጹም ምሕረቴ ይቅር እልኻለኊ፤ ወደ ቤትኽም ወርጄ በባሕርይኽ ዐድራለኊ፤አዳም ሆይ ስለ አንተ እንደ ሕፃን እወለዳለኊ፤ስለ አንተ ወደ ገበያ እኼዳለኊ፤ስለ አንተም አርባ ቀን አርባ ሌሊት እጾማለኊ፤ስለ አንተ መከራ መስቀል በትእግሥት እቀበላለኊ፤ ስለ አንተም በዕንጨት መስቀል ላይ እሰቀላለኊ)ብሎ ተስፋውን ነግሮታል። (መጽሐፈ ቀሌምንጦስ፣ ፫መቃ ፬+፳፫-፳፬፤ ዕገ ሱቱ ፬+፭፤ ሲራ ፳፬+፮፤ ገላ ፬+፬)።

ይኽነን ተስፋ ይዞ ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው ላይ *‹‹አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመ ይሰደድ እምገነት››* (ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም ተስፋው አንቺ ነሽ)[44] በማለት ያመሰገናት፤ ምክንያቱም አዳም በ፭ቀን ተኩል ያለውን የተስፋ ቃል እንደሱ አቈጣጠር መስሎት ፭ቀናት ጠብቋል፤ ኋላ ግን ዘመኑ ፭ሺሕ፭፻ መኾኑን ተረድቶ ይኽነን ተስፋ በመተከፈ ልቡናው ይዞ ይኖር ነበር።

ዛሬ ነጋዴ ሥንቁን ያዘ እየበላለት ከዚኽ እስከዚያ ያደርሰኛል እያለ በተስፋ እንዲጓዝ፤ አዳምም በዐጸደ ሥጋ በዐጸደ ነፍስም ሳለ ፈጣሪዬ እንዲኽ ብሎኛል ይምረኛል፤ እያለ ተስፋውን አጽንቶ ሲጠባበቅ ኖረ፤ ይኽነን ተስፋውን ስልጆቹ አስቀድሞ ነግሯቸዋልና ልጆቹ አንዱ ሲቀበር አንዱ ሲወለድ፤ የአካላዊ ቃል ከድንግል ማርያም ተወልዶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ዓለምን የማዳኑ ምስጢር እየተገለጸላቸው ፭ሺሕ፭፻ ዘመን እስኪፈጸም ትንቢት እየተናገሩ

44 አባ ሕርያቆስ ፤ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፭





ሱባዔ እየቈጠሩ ኖሩ (ማቴ ፲፫+፲፯፤ ዮሐ ፰+፶፮፤ ፳+፶፯፤ ዕብ ፩+፩-፪ ፤፩ዮሐ፩+፩-፪)። የተናገረውን የማይረሳ የሰጠውን ተስፋ የማይነሣ አምላክ ፭ሺሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ቀን ቢደርስ አምባ ይፍረስ እንዲሉ፤ በልዩ አመጣጡ በጽኑ ቀጠሮው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ ፴፫ ዓመት ከ፫ወር የጌትነቱን ወንጌል አስተምሮ ፤በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ፤ በለበሰው ሥጋ ሞቶ በደሙ ክሶ፤ አዳምን ከነልጅ ልጆቹ ወደ ጥንት ቦታው ወደ ገነት መልሶታልና፤ ተስፋውን የሰጠውና የፈጸመው ጌታን በመውለዷ የአዳም አለኝታ ተስፋው ተብላ ትመሰገናለች።

ሊቃውንቱም ይኽነን ታላቅ የድኅነት ሥራ በማድነቅ *‹‹ተፈጸመ ተስፋ አበው በማርያም ድንግል ወበቀራንዮ ተተክለ መድኀኒት መስቀል››* (በድንግል ማርያም የአባቶች ተስፋ ተፈጸመ በቀራንዮ መድኀኒት መስቀል ተተከለ)[45] እያሉ በያሬዳዊ ዜማ ይኽነን ምስጢር ያሰማሉ።

## የሕያዋን ኹሉ እናት

አባታችን አዳም እግዚአብሔር ‹‹በአንተና በሴቲቱ በዘርኽና በዘርዋም መኻከል ጠላትነት አደርጋለኊ›› ብሎ የተናገረውን ቃል በመያዝ ለሚስቱ ሔዋን የሚል ስምን አውጥቶላታል። ይኸውም በዘፍ ፫+፳-፳፩ ላይ እንደተጻፈ *‹‹ወሰመየ አዳም ስማ ለብእሲቱ ሔዋን እስመ ይእቲ እምሙ ለሕያዋን››* (አዳምም የሚስቱን ስም ሔዋን አለው፤ የሕያዋን ኹሉ እናት ናትና) ይላል፤ ይኽነን ቃል በጥልቀት ስንመረምረው አዳም በሔዋን ምክንያት ሕይወትን ከማግኘት ይልቅ ሞት ነበር የመጣበት፤ ዳሩ ግን ጌታ የሰጣቸው የሕይወት፣ የድኅነት፣ የተስፋ ቃል ኪዳን የሚፈጸምላቸው ወሃቤ ሕይወት ጌታ ከሔዋን ወገን ከኾነች ከዳግሚት ሔዋን ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት ተወልዶ ነውና፤ አዳም በተሰጠው ሀብተ ትንቢት ይኽነን ተረድቶ ሚስቱ ሔዋንን የሕያዋን ኹሉ እናት ብሎ ጠርቷል።

በመቅድመ ተአምር ላይ አዳም ሔዋንን ሕይወት ብሎ ለምን እንደጠራት ሲተረጕም *‹‹ሕይወትየ ይቤላ አዳም ለብእሲቱ አእሚሮ ከመ ትወጽእ እግዝእትነ ማርያም እመሐቋሁ ወእምከርሣ ብእሲቱ››* (አዳምም

45. አባ ስብሐት ለአብ፤ መልክአ ሥላሴ፤ ለኵልያቲከሙ



www.ethiopianorthodox.org

እመቤታችን ማርያም ከሱ አብራክ እንድትከፈል ከሔዋንም ማሕፀን እንድትወለድ ዐውቆ፤ ሔዋንን ሕይወቴ ነሽ ይላት ነበር)[46] በማለት ወሃቤ ሕይወት ክርስቶስን ስለ ወለደች ስለ ዳግሚት ሔዋን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም መናገሩን ይገልጻል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በማግሰኞ ውዳሴ ማርያም መጽሐፉ የሕይወት ኹሉ መገኛ የኾነ ክርስቶስን የወለደች እመ ሕይወት ቅድስት ድንግል ማርያምን ሲያመሰግን *«ተፈሥሒ ኦ ቅድስት እምሙ ለኵሎሙ ሕያዋን»* (የሕያዋን ኹሉ እናታቸው ቅድስት ሆይ ደስ ይበልሽ) በማለት የሕያዋን ኹሉ እናት ሔዋን ሳትኾን ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አስረድቷል።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ይኽነን ልዩ ምስጢር በጥልቀት ሲያብራራ «With out martial union, Adam had generated the mother of life...» (ያለባልና ሚስት ግብር አዳም የሕይወት እናት ሔዋንን አስገኘ፤ በዚኽም አማናዊው የሕይወት ምንጭ የጌታችንን መወለድ ምሳሌ ኾኖ አስረዳን... አዳም ያለ ሩካቤ ድንግል የኾነች ሔዋንን አስገኘ «የሕይወት እናት» ብሎም ጠራት፤ በዚኽም ነቢይ ኾነ፤ በኹለተኛ ልደት ከእርሷ የሚያበራ ሕይወት ይገለጣልና፤ በድንግልናዋም የእግዚአብሔር ልጅን ታስገኛለችና፤ በአዳም ትንቢት የእውነት ሕይወት የኾነው የጌታችንን መምጣት በምሳሌ ተነገረ፤ እናቱም ድንግል ማርያም ኾነች፤ ሔዋንን «የሕይወት እናት» ብሎ ጠራት፤ ትንቢት ተናገረ ሕይወትን አስገኘታለችና፤ እርሱም ኢየሱስ የተባለው ጌታችን ነው)[47] በማለት የተነገረውን ምስጢር በጕልኽ አስተምሯል። (ዮሐ ፩፥፬፤ ፳፥፳፮፤ ፲፩፥፳፭)

## የአቤል ደግነት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለአቤል የየዋሃቱን ዋጋ ያሰጠችው መኾኗ በአባ ሕርያቆስ ተመስክሮላታል። ይኸውም አባታችን አዳም ሔዋንን በግብር ካወቃት በኋላ ቃየልንና ሉድን ወልዳለች፤ ኋላም ቃየልንና ሉድን ካሳደገች በኋላ ወንድሙ አቤልንና አቅሌማን ወለደች (ዘፍ ፬፥፩-፪፤

46. መቅድመ ተአምር ቍ ፲
47. Jacob of Serugh, On the Virgin p 36





ኵፋ ፳፥፴)፤ ስለኹለቱ ወንድማማቾች ታሪክ የሚናገረው የአዳም ገድልና ትርጓሜ ኦሪት ቃየል ከልጅነቱ ዠምሮ ክፉ እንደነበር ያስረዳል።

ይኸውም አዳም መሥዋዕት ለማቅረብ እንኺድ እንኺ ሲለው አይኾንም እያለ ይቀር ነበር፤ *ወኮነ ብዙኀ ጊዜ ሶበ ያዐርግ ቍርባነ አቡሁ ይተርፍ ወኢየዐርግ ምስሌሆሙ* ይለዋል ትርጓሜ ኦሪት። ወንድሙ አቤል ግን ከሕፃንነቱ ዠምሮ ደግ ስለነበር ለአባቱና ለእናቱ ይታዘዝ ደስ ያሰኛቸው ነበር፤ መሥዋዕት ለማቅረብ ያተጋቸው ነበር፤ *ወአቤልሰ ኮነ ሎቱ ልብ ጥዑም ወኮነ ይደነግፅ ለአቡሁ ወለእሙ ወየሀውኮሙ በእንተ ቍርባን ብዙኀ ጊዜ እስመ ውእቱ ኮነ ያፈቅር ቍርባነ* ይለዋል።

ኹለቱ ወንድማማቾች እንዲኽ ኹነው ካደጉ በኋላ አቤል በግ ጠባቂ ሲኾን ቃየል ገበሬ ኾነ። አባታቸው አዳምም ትውልድን ለማራራቅ ሲል የቃየልን መንትያ ሉድን አቤል፤ የአቤልን መንትያ አቅሌማን ቃየል ያግባ አለ፤ ቃየል ግን በአባቱ ሐሳብ አልተስማማምና፤ በዚኽ ምክንያት አዳም መሥዋዕት ሠዉና መሥዋዕቱን የተቀበለለት ሉድን ያግባት አላቸው። አቤልም ንጹሐ ባሕርይ እግዚአብሔር ንጹሕ ነገር ቢያቀርቡለት ይወዳል ብሎ ከበጎቹ በኵራት ጸጕሩ ያላረረውን፣ ቀንዱ ያልከረከረውን፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን፣ ዓመት የኾነውን ጠቦት አቀረበ፤ እግዚአብሔርም የልቡናውን ቅንነት የመሥዋዕቱን መበጀት አይቶ መሥዋዕቱን ተቀብሎታል (ዘፍ ፬፥፬)። ቃየል ግን አባር የመታውን ስንዴ እንክርዳዱን ሳይለቅም አቀረበ፤ ጌታም የመሥዋዕቱን አለመበጀት፤ የልቡናውን ጥመት አይቶ መሥዋዕቱን አልተቀበለለትም፤ በዚኽም ምክንያት ቀንቶ ወንድሙ አቤልን በግፍ ገድሎታል (ዘፍ ፬፥፪-፰፤ ዕብ ፲፩፥፬)።

አቤልሰ አሥረጸ ጽድቀ እምነፍሱ እንዲል የአቤል ወላጆች አዳምና ሔዋን እንዳያስተምሩት ሕግ አፍራሾች ኾነው፤ ወንድሙ ቃየል እንዳያስተምረው በክፉ ምኞት እየተጓዘ፤ ከሌላ እንዳይማር ሌላ አስተማሪ ባልነበረበት ጊዜ፤ ጽጌያት ከአዕፁቃቸው እንዲፈነዱ እሱም እግዚአብሔር ንጹሕ ባሕርይ ነው ማለትና ከኀሊናው አፍልቆ በደግነቱ በጎ መሥዋዕትን ሲያቀርብ በየዋህነቱም ለሞት በቅቷል።

ታላቁ ሊቅ አባ ሕርያቆስም የዚኽ የአቤል የደግነቱን ዋጋ ገነትን



www.ethiopianorthodox.org

የሰጠው ክርስቶስን ወልዳ ያስገኘችልን ቅድስት ድንግል ማርያምን በቅዳሴው ላይ *‹‹የዋሃቱ ለአቤል ዘተቀትለ በዐመፃ›* (በግፍ የተገደለ የአቤል የዋሃቱ አንቺ ነሽ)[48] በማለት የየዋሀነቱም ዋጋ ያሰጠችው መኾኗን በመጥቀስ እመቤታችንን አመስግኗታል። ምክንያቱም አቤል ይኽነን የየዋህነትና የጽድቅ ሥራን ቢሠራም፤ ደግነቱ በእደ እግዚአብሔር ለመጠበቅ አበቃው እንጂ ሲኦል ከመውረድ ግን ሊያድነው አልቻለም፤ የደግነቱን የየዋህነቱን ዋጋው ገነትን ማግኘቱ ክብር ይግባውና ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን ካዳነ ወዲኽ ነው።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ በመጽሐፉ ላይ ይኽነን የድኅነት ምስጢር ሲያብራራ *‹‹ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘበዕብራይስጢ ማሪሃም አይቴ ፈውስ ወአይቴ ሣሕል ተገብረ ዘእንበሌኪ ወአይቴ ረድኤት ወአይቴ መድኃኒት ኮነ ዘእንበለ ትትወልዲ አንቲ፤ አቤል ተቀትለ በግፍዕ እምቃየል ወኢያሥለጠ ደሙ ወኢመነሂ ወደመ ፍሬ ከርሥኪሰ ቤዘዎሙ ለአዳም ወለደቂቁ›* (በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ፤ ያለ አንቺ ከአንቺ በቀር እንደምን ያለ ፈውስ እንደምን ያለ ይቅርታ ተደረገ፤ አንቺ ሳትወለጂ ከመወለድሽ አስቀድሞ እንደምን ያለ መድኀኒት እንደምን ያለ ረድኤት ተደረገ? ኾነ? አቤል በቃየል በግፍ ተገደለ፤ ደሙ ማንንም ማንን አላዳነም፤ የማሕፀንሽ ፍሬ የክርስቶስ ደም ግን አዳምንና ልጆቹን አዳናቸው)[49] በማለት ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ፤ አዳምን ልጆቹን ሙሉውን ዓለምን ያዳነ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ወልዳ ያስገኘችልን መኾኗን መስክሯል።

## የሴት ቸርነት

አዳምና ሔዋን በወንድሙ በግፍ በተገደለው በልጃቸው በአቤል ሞት ምክንያት ብዙ ሱባዔ አልቅሰዋል፤ ከዚኽ በኋላ መልአኩ መጥቶ ‹‹*ናሁ አቤል ወልድከ ተሳለመ ዕፀዊሃ ለገነት*›› ብሎ በእደ እግዚአብሔር ለመያዝ መብቃቱን ከነገረው በኋላ ሔዋንን በግብር አወቃት፤ ሴትን ወለደች፤ ሴት ማለት ምትክ፤ ተክለ አቤል ማለት ነው (ዘፍ ፬፥፳፭፤ኩፋ ፭፥፲፪)። ይኽ ሴት በሙሴ ጊዜ

48. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፩
49. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘነሙስ ፭ ፥ ፩-፪





አባትኽን እናትኽን አክብር የምትል ሕግ እንድትሠራ አስቀድሞ በሕገ ልቡና ተገልጾለት፤ አባቱንና እናቱን በቅንነት አገልግሏል፤ በማገልገሉም ብዙ ጥቅም የተጠቀመ ታላቅ አባት ነው።

ይኽ ኹሉ ለሴት መደረጉ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም በእሱ ባሕርይ ቢኖሩ ከሱ ወገን ቢወለዱ ነውና ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ላይ *‹‹ኂሩቱ ለሴት››* (የሴት ቸርነት አንቺ ነሽ)[50] ማለት የቸርነቱን የቅንነቱን ዋጋ የምታሰጪው አንቺ ነሽ ሲል ቅድስት ድንግል ማርያምን አመስግኗታል፤ ይኸውም የቅንነት ዋጋውን ገነትን የሚሰጠውን ጌታን ወልዳለችና ይኽነን ሲያይ ሊቁ *ኂሩቱ ለሴት* ብሏታል ። ወንጌላዊው ሉቃስም የጌታችንን የትውልድ ሀረጉን ባስተማረበት ምዕራፍ ላይ ጌታችን በሴት ባሕርይ መኖሩን አስተምሮአል (ሉቃ ፫፥፴፰)።

## የሔኖክ መልካም ሥራ

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሔኖክ መልካም ሥራ ትባላለች። ይኸውም ሔኖክ የአዳም ሰባተኛ ትውልድ ሲኾን የያሬድ ልጅ ነው፤ ይኽም ሔኖክ ፫፻፷፭ ዓመት ቤት ንብረት ይዞ በዚኽ ዓለም ከኖረ በኋላ፤ ይኽነን ዓለም ካልተውት አይተው በማለት፤ ቤቱን ንብረቱን ለልጁ ለማቱሳላ አውርሶ፤ ለስድስት ዓመት በእግረ ገነት ወድቆ፤ እግዚአብሔርን በሃይማኖት በምግባር በትሩፋት ደስ ቢያሰኘው፤ ከረዐይት ከግብራቸው ከፍዳቸው ከዐይነ ሞት ሰውሮ በሰባተኛው ዓመት በገነት አኑሮታል ( ዘፍ ፭፥፳፩-፳፬)።

ለዚኽ ለሔኖክ ልዑል እግዚአብሔር የፀሓይ፣ የጨረቃ፣ የከዋክብት ምስጢርን፣ የነፋስን አወጣጥ ፣የገነትን ነገር፣ የብርሃናትን መመላለስ ገልጾለት ያንን በመጽሐፍ ላይ ጽፎ አስፍሮታል (ኩፋ ፬፥፳፫-፴)። ይኸውም ዓለም በተፈጠረ በ ፩ሺሕ፩፻፹፱ ዓመት ነው። ሐዋርያው ይሁዳም ስለ ጌታ ፍርድ በመልእክቱ ላይ ከመጽሐፈ ሔኖክ ጠቅሶ አስተምሯል (ይሁ ቍ ፲፬-፲፭)፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ሔኖክ የእምነት ጥንካሬ በዕብ ፲፩፥፭ ላይ ‹‹ሔኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፤ እግዚአብሔርም ስለወሰደው አልተገኘም፤ ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና››

50. አባ ሕርያቆስ፤ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፩



www.ethiopianorthodox.org

በማለት ሔኖክ አኪያኺያዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ ሞትን እንዳያይ ጌታ እንደሰወረው መስክሯል።

አባታችን አዳም ዕፀ በለስን በልቶ ብልየተ *ሥጋን* ቢያመጣ፤ ሔኖክ ደግሞ ከምግበ *ሥጋ* ተከልክሎ በጾም በጸሎት መታደስን አግኝቷል፤ ሞት መኖሩ በአቤል ሲታወቅ ትንሣኤ መኖሩ ደግሞ በሔኖክ የታወቀ በመኾኑ እነ ቅዱስ ኤጲፋኒዮስ እነ ዮሐንስ አፈወርቅ የትንሣኤ ሙታን ምሳሌ አድርገውት አስተምረዋል።[51] ጌታ ሔኖክን ስለ መልካም *ሥራው* የሰወረው የሴትና የቃየል ልጆች ተባብረው ከሚሠሩት ኀጢአትና፤ በኋላ በኖኅ ዘመን ከላይ በሰባት ዐይነት ከሐኖስ ጉልቻ ጉልቻ የሚያኽል በረዶን አውርዶ ጭንቅላታቸውን እየፈነከተ፤ ከምድርም ከሰባ ቦታ ቀዶ እንደ እሳት የሚያቃጥል ፍል ውሃ አውጥቶ ካጠፋቸው ታላቅ መቅሠፍት ነው።

ይኽ ኹሉ ለሔኖክ መደረጉ ጌታችንና እመቤታችን በባሕርዩ ቢኖሩ ነውና፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም ቅድስት ድንግልን ባመሰገነበት የቅዳሴ መጽሐፉ በቍ ፴፩ ላይ *‹‹ወምግባራቲሁ ለሔኖክ››* (የሔኖክ መልካሞች *ሥራዎቹ* አንቺ ነሽ) በማለት ለሔኖክ መልካም *ሥራ* ዋጋን የሚከፍል ጌታን የመውለዷን ነገር በምስጢር አመልክቷል (ሉቃ ፫፥፴፯)። ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ስለዚኽ ነገ[ር] በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *‹‹ሔኖክ ዘወእቱ ሳብዕ እምነ አዳም አሥመረ ለእግዚአብሔር ወተከብተ እምገጸ ሞት ወኢተረክበ እስመ ነሥኦ እግዚአብሔር ሐይወ በጽድቀ ርእሱ ወኢበቍየሙ ለባዕዳን ጽድቀ ዚኣሁ ወሠርጸ ድንግልናኪ ስ ጥዕመ ሞተ በሥጋ በኂሩተ ዚአሁ ወአሕየዎሙ ለምውታን በመለኮቱ››* (ከአዳም ሰባተኛ የሚኾን ሔኖክ እግዚአብሔርን አገለገለው፤ ከሞት ፊትም ተሰወረ አልተገኘም እግዚአብሔር ሸሽጎታልና፤ በራሱ ትሩፋት ዳነ፤ የርሱ ትሩፋት ለሌሎቹ አልረባቸውም አልጠቀማቸውም፤ የድንግልናሽ ቡቃያ ግን በቸርነቱ ሞትን በሥጋ ቀመሰ፤ ሙታንንም በአምላክነቱ በነሣው ሥጋ አዳናቸው)[52] በማለት የኹላችን መድኀኒት ጌታን ያገኘንባት ብቸኛ መመኪያችን እሷ መኾኗን መስክሮላታል።

ታላቁ አባት ሔኖክ በእምነቱ በመልካም *ሥራው* የሴትና የቃየል ልጆች ከሚሠሩት ኀጢአትና ከመጣባቸው ታላቅ ቅጣት እንደዳነ ኹሉ፤ ዛሬም እኛም

51. ሃይማኖተ አበው ዘኤጲፋኒዮስ ፤ምዕ ፶፱፥፩፤ ፳፰-፳፱
52. አባ ጊዮርጊስ፤አርጋኖን ዘነመስ ፤ምዕ ፳፥፫-፬





የሔኖክ መልካም *ሥራ* በተባለች በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ከዓለም የኀጢአት *ሥራና* ከክፉ መቅሠፍት ከዘላለማዊ ሞት እንሰወራለንና ይኽው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ ሀገረ ብዕል መካነ ተድላ*
*ዐቅሚ ምስሌየ ኪዳነ በመሐላ*
*ወሰውርኒ እምሥልጣነ ሞት ዘይመሥጥ ከመ ተኩላ*
*ሰድኒ ምድረ ሕያዋን ከመ ሔኖክ አበ ማቱሳላ ወአብሕኒ አንፈርዐጽ በማዕከላ››*

(የተድላ የደስታ ቦታ የብልጽግና ሀገር ሆይ፤ ከእኔ ጋር ቃል ኪዳንን በመሐላ ዐቁሚ (አጽኚ)፤ እንደተኩላ ከሚነጥቅ ከሞት ሥልጣን ሰውሪኝ ሸሽጊኝ፤ እንደማቱሳላ አባት ሔኖክም ወደ ሕያዋን ምድር ውሰጂኝ፤ በመኻከሏም እዘል ዘንድ አሠልጥኚኝ (አሰናብቺኝ)[53] በማለት ተማጽኖውን አቅርቧል።

## የኖኅ መርከብ

አምላክን የወለደች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ቅድስት ድንግል ማርያም ኖኅና ቤተሰቡ ከጥፋት ውሃ በዳኑባት ሦስት ክፍል ባላት መርከብ ትመሰላለች (ዘፍ ፮፥፩-፳፪፤ ዘፍ ፯፥፩-፳፬)። ይኽውም በኖኅ ዘመን የሴት ልጆች፤ እንደ መላእክት ፈጣሪያችንን ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉን እያመሰገኑን በደብር ቅዱስ እንኖራለን፤ ብለው ከተሳሉ በኋላ የቃየል ልጆች የሚሠሩትን የዝሙት ኀጢአት አይተው፤ በሐጸ ዝሙት ተነድፈው ከደብር ቅዱስ ወርደው ከቃየል ልጆች ጋር ተጋብተው ብዙ ኀጢአትን ሠሩ። ጌታም በዚኽ አዝኖባቸው ለኖኅ የጥፋትን ውሃ የማመጣ ነኝና፤ አንተና ቤተሰቦችኽ የምትድኑበትን መርከብ ሥራ ብሎት አሠራሩን ነግሮታል። ኖኅም በታዘዘው መሠረት ሦስት ክፍል አድርጎ ሠርቷታል። ከዚያም የጥፋት ውሃ ሳያቋርጥ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ዘንቧል፤ መቶ ዐሥር ቀን ሳይመላም ሳይጎልም ሰንብቷል ፤በድምሩ መቶ አምሳ ቀን ይኾናል፤ ኖኅና በመርከቡ ውስጥ ያሉት ብቻ ሲተርፉ ከመርከቧ ያልገቡት ግን በጥፋት ውሃ ተደምስሰው አልቀዋል።

ይኽቺም ኖኅና ቤተሰቡን ከንፍር ውሃ ያዳነች፣ የታደገች መርከብ

53. እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 7



www.ethiopianorthodox.org

የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ሊቃውንት አስተምረዋል፡፡ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ላይ *‹‹ታቦት እንተ ኖኅ በዘባተ ድኅነ እም አኩይ አይኅ›* (ከክፉ ጥፋት የዳነባት የኖኅ መርከብ አንቺ ነሽ)[54] በማለት አመስግኗታል፡፡ ይኸቺውም መርከብ የድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ያቺ ሦስት ክፍል መኾኗ እመቤታችን የሥላሴ ማደሪያ የመኾኑዋ ምሳሌ (ሉቃ ፩፥፴፭)፤ ዳግመኛም የሥላሴ ማደሪያ የኾነችው ቅድስት ድንግል በሦስት ወገን ማለት በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና ንጽሕት የመኾኗ ምሳሌ ነው (መሐ ፬፥፯፤፬፥፲፪፤ሉቃ ፩፥፳፰)፡፡ በመርከቧ ውስጥ ያሉ እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ናት በማለት በቃል ኪዳኗ ያመኑ የምእመናን ምሳሌ ሲኾኑ (መዝ ፺፬፥፬- ፲፯፤ መሐ ፯፥፬- ፲፤ ኢሳ ፺፱፥፳፫)፤ በውጭ ያለቁት ግን እመ አምላክ ወላዲተ አምላክ ብለው ያላመኑ ቃል ኪዳኗን ያልተቀበሉ የመናፍቃን ምሳሌ ናቸው (መዝ ፻፳፮፥፳፮፤ ራእ ፲፪፥፬- ፮፤፲፫- ፲፯፤፲፫፥፯)፡፡ ይኸውም በመርከቧ ውስጥ ያሉት ከንፍር ውሃ እንደዳኑ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን አማላጅነት የሚማፀኑት ከገሃነመ እሳት ሥቃይ የመዳናቸው ምሳሌ ነው፤ በአንጻሩ ከመርከቧ ውስጥ ያልገቡት የንፍር ውሃ እንዳቃጠላቸው የቅድስት ድንግል ማርያምን የአምላክ እናትነትን አማላጅነትን የማይቀበሉ መናፍቃንም በእሳተ ገሃነም ሲቃጠሉ የመኖራቸው ምሳሌ ነው፡፡

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በድጓው ላይ ስለ ሐመረ ኖኅ ሲተነትን *‹‹አይ ይእቲ ዛቲ መድኀኒት እንተ ኀሠሥዋ ወዖድዋ ነቢያት ወይቤሉ ለኖኅ አመ አይኅ ግበር ታቦተ በዘትድኅን፤ እትአመን ባቲ እስመ አርአያ መስቀል ይእቲ አክሊለ ተቀጺላ ታንሶሱ››* (ነቢያት በእግረ ትንቢት የኗት (የፈለጓት) ይኽች መድኀኒት ምንድን ናት? ኖኅንም እንዲኽ አለው በጥፋት ውሃ ጊዜ በምትድንበት ገንዘብ ማደሪያ መርከብን ሥራ ፤ እኔም አምንባታለኍ የመስቀል ምልክት ናትና፤ የክብር አክሊልን ተቀዳጅታ ትመላለሳለች)[55] በማለት አመስጥሮታል፡፡

ይኽቺ መርከብም ነቢያት በእግረ ትንቢት ዞረው የፈለጓት መድኀኒት እመቤታችን ናት፤ ይኸውም በመድኀኒት ድዉያነ ሥጋ ከጽኑ ደዌ ሥጋቸው እንዲድኑ፤ ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘው አማናዊ

54. አባ ሕርያቆስ፤ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፩
55. ቅዱስ ያሬድ፤መጽሐፈ ድጓ





መድኀኒት ኢየሱስ ክርስቶስም በጥንተ በደል ምክንያት ድዉያነ ነፍስ ቁሱላነ ነፍስ ኾነው ወደ ሲኦል ወርደው የነበሩ የአዳም ልጆች በሙሉ ከቊስለ ነፍስ ከደዌ ነፍስ ድነው ወደ መዠመሪያቱ የአዳም ቦታ ተመልሰው ገብተዋል፡፡ ዳግመኛም ኖኅም በሠራው መርከብ የዳኑ ነፍሳት ምድርን እንደመሏት ኹሉ ሊቃውንት በየድርሳናቸው ሐመረ ኖኅ ብለው ከሠየሟት ከድንግል ማርያም በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የተወለደው አካላዊ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በመስቀሉ ትርክዛ እየቀዘፈ ከባሕረ እሳት ነጻ ያወጣቸው ነፍሳት ገነትን መልተዋታል፡፡ ነፍሳት የዳኑባት መርከብ ምሳሌዋ መስቀል እንደኾነ፤ የአብ አካላዊ ቃል ዓለሙን ኹሉ ያዳነው የእመቤታችን ሥጋ ተዋሕዶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ነውና፤ ይኽ የቅዱስ ያሬድ ንጽጽራዊ ትምህርት እጅግ ያስደንቃል፡፡[56] ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ምስጢሩን በመጠቅለል በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ እግዝእትየ ማርያም ለተረፈ ዐለም ኖኅ ማሕየዊት ዕፁ፤*
*አዕፁቀ ፍጥረት ሐዳስ እንተ እምኔሃ ሠረጹ››*

(የሐዲስ ፍጥረት ቅርንጫፎች ከርሷ የበቀሉ ከሰው የተረፈ የኖኅ አዳኝ ዕፁ (መርከቡ) አንቺ ነሽ)[57] በማለት አስተምሯል፡፡

## <u>የኖኅ ርግብ</u>

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የጥፋት ውሃ የመጉደሉን ነገር ባፏ የዘይት ቅርንጫፍ ይዛ የምሥራቹን ለኖኅ ባሳወቀችው ርግብ ትመሰላለች (ዘፍ ፰፥፲፩) ፡፡ይኸውም ከጥፋት ውሃ በመርከቡ ውስጥ ኾኖ የተረፈው ኖኅ የጥፋት ውሃ መጉደሉና አለመጉደሉን ለማየት የመርከቢቷን መስኮት ከፍቶ ቁራን ላከው፤ ቁራው ግን የኖኅን ፈቃድ ሳይፈጽም በዚያው ቀርቷል፡፡ *‹‹ወተዐገሠ ሰቡዐ መዋዕለ ካዕበ ፈነዋ ለርግብ ውስተ ምድር ከመ ትርአይ››* ይላል ሰባት ቀንም ቆይቶ ምድርን ታይ ዘንድ ዳግመኛ ርግብን ላካት *‹‹ወገብአት ኀቤሁ ርግብ ፍና ሠርክ ወባቲ ውስተ አፉሃ ቈጽለ ዘይት ወአእመረ ኖኅ ከመ ነትገ ማየ አይኅ እምነ ምድር››* (ርግብም በማታ ጊዜ ወደሱ ተመለሰች፤ በአፏም የዘይት ቅጠል

56. ነገረ ማርያም በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ፤መምህር ዐምደ ወርቅ፤ሐመር ሰኔ/ሐምሌ 1991 ገጽ 11



www.ethiopianorthodox.org

ይዛ ነበር። ኖኅም ውሃው ከምድር ላይ እንደጐደለ ዐወቀ) ይላል።

ይቺ ምሥራችን ያመጣች ርግብ ምሳሌነቷ የድንግል ማርያም ነው፤ ምክንያቱም ያቺ ርግብ የጥፋት ውሃ የማብቃቱን ነገር *‹‹ሐጸ ማየ አይኅ ኅትገ ማየ አይኅ ››* (የጥፋት ውሃ ጐደለ፤ የጥፋት ውሃ ተገታ) ስትል የምሥራቹን የዘይት ቅጠል ይዛ እንደታየች ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም *‹‹ሐጸ ማየ ኀጢአት ኅትገ ማየ መርገም››* (የኀጢአት ውሃ ጐደለ፤ የመርገም ውሃ ተገታ) ስትል ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔን አሳልፎ ዓመተ ምሕረትን የተካ፤ ለዓለሙ ኹሉ ታላቅ የምሥራች የኾነ፤ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስን ወልዳልናለችና በኖኅ ርግብ ተመስላለች።

ይኸውም ሊታወቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም በቤተልሔም ሲወለድ አንድ ዓመተ ምሕረት ተብሎ የምሕረት ዘመን የድኅነት ዘመን መቈጠር ተጀምሯል። ለዚኽም ነው ጌታ ሲወለድ መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ ላደሩ እረኞች፤ የጌታ መልአክ ተገልጾ ‹‹እንሆ ለሕዝቡ ኹሉ የሚኾን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኊለኹና አትፍሩ፤ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኀኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የኾነ ተወልዶላችኊልና፤ ይኽም ምልክት ይኾንላችኊል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችኊ›› ብሎ ዓለም ከጥፋት ወጥቶ ድኅነትን የሚያገኝበት ታላቁ ምሥራች፤ የጌታ ከድንግል መወለድ መኾኑን አብሥሯል (ሉቃ ፪፥፲-፲፪)። ኖኅም የጥፋት ውሃ ዐልፎ ምድር እንደቀድሞዋ ሰላም ማግኘቷን ርግቧ ይዛ በተገኘችው የዘይት ቅጠል እንደተረዳ ኹሉ፤ ቅዱሳን መላእክትና እረኞችም ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን በቤተልሔም በወለደችው ጊዜ፤ የኀጢአት ባሕር የኩነኔ ዘመን ዐልፎ የምሕረትና የሰላም ዘመን መድረሱን በመረዳት ‹‹ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይኹን፤ ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ›› በማለት ፈጣሪያቸውን ክርስቶስን አመስግነዋል (ሉቃ ፪፥፲፬)። ለዚኽ ነው አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ *(ጽሑፉ አርጋኖን? -- see note)*





(ከለመለመ የወይን ቅጠል ጋር ወደ መርከብ በገባሽ ጊዜ ለኖኅ የይቅርታ ጊዜው ምልክትን እንደነገርሽው፤ ንጹሕ አበባን በመያዝ ጽድቅን አብሥሪኝ፤ ክንፎችሽ መስቀል የኾኑ የቊስቋም ርግብ ማርያም)[58] በማለት አመስግነዋታል።

## የኖኅ ቀስተ ደመና

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ኖኅ ከእግዚአብሔር ዘንድ የጥፋት ውሃ ዳግመኛ እንዳይመጣ ምልክት አድርጎ በተቀበላት አራት ኅብር ባላት ቀስተ ደመና ትመሰላለች (ዘፍ ፱፥፰-፲፯)። ይኸውም ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቀረበ፤ ያን ጊዜ ዳግመኛ *‹‹ብዝኁ ወተባዝኁ ወምልዕዋ ለምድር››* (ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት) ቢለው፤ እኔ ብበዛ ምን ያደርግልኛል፤ የኔ ልጆች ኀጢአት ከመሥራት አያቋርጡ፤ አንተም በእውነት ፈርደኽ ልታጠፋቸው ነው፤ አለ፤ ጌታም ዳግመኛ በንፍር ውሃ እንዳላጠፋት *‹‹ቀስትየ እሠይም በደመና ወትከውን ተአምረ ለኪዳንየ ማእከሌየ ወማእከሌክሙ ወማእከለ ምድር››* (በናንተና በኔ መኻከል በምድርም መኻከል ለመሐላዬ ምልክት አድርጌ ቀስቴን በደመና አኖራለኊ) *ወይከውን ሶበ አጼምን ደመና ላዕለ ምድር ታስተርኢ ቀስትየ ላዕለ ደመና* (ደመናን በምድር በጋረድኊ ጊዜ እንዲኽ ይኾናል፤ ቀስቴ በደመናው ላይ ይታያል) *‹‹ወትወጽእ ቀስትየ ውስተ ደመና ወእሬእያ ከመ እዘከር ኪዳንየ ዘለዓለም በማእከሌየ ወማእከለ ኵሉ ዘሥጋ ዘቦ መንፈሰ ሕይወት ዘሀሎ መልዕልተ ምድር››* (ቀስተ ኪዳኔ ከደመና ውስጥ ትወጣለች፤ በምድርም ላይ ባለ ሕይወት ባለው በሥጋዊ ፍጥረት ኹሉ መኻከልና በኔ መኻከል ያለ ለዘላለም ጸንቶ የሚኖር ኪዳኔንም ዐስብ ዘንድ እሷን አመለከታለኊ) ዘፍ ፱፥፲፪- ፲፯ በማለት አራት ኅብር ያላት ቀስተ ደመና በዐርበኛ (በቀስተኛ) ልማድ አሳይቶታል።

ጌታ ይኽነን አራት ኅብር ለኖኅ ማሳየቱ፤ እንግዲኽ ወዲኽ ከአራቱ ባሕርያት የተፈጠረ ሰውን በንፍር ውሃ አላጠፋውም ሲለው ነው፤ አንድም ደመና የቅድስት ድንግል ማርያም፤ አራቱ ኅብር የአራቱ ባሕርያት ምሳሌ ሲኾን፤ ጌታ ይኽነን ማሳየቱ ከእመቤታችን አራቱን ባሕርያት ነሥቼ ተወልጄ ሰውን አድነዋለኊ ሲል ነው። ይኽነንም በርካቶች ሊቃውንት በሰፊው

58. አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፳፩



www.ethiopianorthodox.org

ተርጉመውታል፤ ከነዚኽ መኻከል ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም፣ አባ ጊዮርጊስና አባ ጽጌ ድንግል ይገኙበታል። ይኸውም ጌታ ለወዳጁ ለኖኅ በሰጠው ቀስተ ደመና ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውሃ እንዳላጠፋት ኹሉ ለእናቱ ለድንግል ማርያም በሰጣት ቃል ኪዳን ፍጥረቱን አያጠፋምና(ኢሳ ፩፥፱፤ መዝ ፹፰፥፫፤፻፴፩፥፲፫-፲፯)፤ ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ትእምርተ ኪዳን አንቲ ዘተሰመይኪ ቀስተ ደመናት*
*ከመ ኢይምጻእ ውስተ ምድር ዳግመ ዝናመ መዓት››*

(ዳግመኛ የመዓት ዝናም ወደ ምድር እንዳይመጣ ቀስተ ደመናት የተባልሽ የኪዳን ምልክት አንቺ ነሽ)[59] በማለት ከአምላክ የተሰጠችን የድኅነት ምልክት መኾኗን አስተምሯል።

ሊቁ አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያምም በመንፈሳዊ መጽሐፋቸው ላይ

*‹‹ቀስተ ደመና ማርያም ትእምርተ ኪዳኑ ለኖኅ*
*ዘእግዚአብሔር ሄመኪ ለተዝካረ ምሕረት ወፍትሕ*
*ህየንተ ቀሠፋ ለምድር ወእማሰና በአይኅ*
*በእንቲአኪ አሰርገዎ በጽጌ ኵሉ አቅማሕ*
*ከመ በከዋክብት አሰርገዎ ለሰማይ ስፉሕ››*

(ለምሕረትና ለፍርድ መታሰቢያ አድርጎ ያኖረሽ፤ የኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም፤ ምድርን በንፍር ውሃ ስለመታትና ስለአጠፋት ፈንታ፤ ሰፊ ሰማይን ስፍር ቍጥር በሌላቸው ከዋክብት እንደ አስጌጠው ኹሉ፤ በአንቺ ምክንያት ልዩ ልዩ በኾኑ አበባዎች ፍሬዎች ምድርን አስጌጣት)[60] በማለት አማናዊት ቀስተ ደመና የድኅነት ምልክት የኾነችው ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን መስክረውላታል።

## <u>የሴም ቡራኬው ዕድል ፈንታው፤ የማቱሳላ የዕድሜው ርዝማኔ፤ የላሜሕ ዕረፍቱ</u>

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የሴም ምርቃቱ ዕድል ፈንታው

59. አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 46
60. አባ ጽጌ ድንግል፤ማሕሌተጽጌ፤ቍ ፱





ትባላለች (ዘፍ ፱፥፳፯)። ይኸውም አባታችን ኖኅ ከመርከብ ከወጣ በኋላ ገበሬ መኾን ገ'መረ፤ ከተከለውም የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰክሮ በቤት ውስጥ ዕርቃኑን ኾኖ ሳለ ያን ጊዜ ከነዓን አይቶ ላባቱ ለካም ነገረው፤ የከነዓን አባት ካምም የአባቱን የኖኅን ዕርቃን አይቶ በመዘባበት ለኹለቱ ወንድሞቹ ለሴምና ለያፌት አበ ዓለም ኖኅ ዕርቃኑን መኾኑን ነገራቸው፤ ሴምና ያፌት ግን ልብሳቸውን ጋርደው የኋሊት ኼደው አልብሰውታል። ኖኅ ከስካሩ በነቃ ጊዜ በልጆቹ የተደረገውን ነገር ዐውቆ *‹‹ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኩ ለሴም ወይኩን ከነዓን ገብሮ ወለያርኅብ እግዚአብሔር ብሔሮ ለያፌት ወይኅድር ውስተ ቤቱ ለሴም››* (የሴም ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን፤ ከነዓንም አገል ጋዩ ይኹነው፤ እግዚአብሔርም የያፌትን ሀገር ያስፋ፤ በሴም ቤትም (ድንኳን) ይደር) ዘፍ ፱፥፳፮- ፳፯ በማለት ሴምን መርቆታል።

ለጊዜው ኹሉ ተደርጓል ፍጻሜው ግን ኖኅ የጌታ፤ ወይን የሰው ልጆች ፍቅር ምሳሌ፤ ኖኅ በወይን ምክንያት ራቁቱን እንደኾነ ጌታም በሰው ልጆች ፍቅር ተስቦ ዕራቁቱን በዕፀ መስቀል ላይ ተሰቅሏልና (ማቴ ፳፯፥፴፭)። ከነዓን የይሁዳ፤ ካም የጻሐፍት ፈሪሳውያን፤ ከነዓን አይቶ ለአባቱ እንደነገረው ይሁዳም ለጸሐፍት ፈሪሳውያን ነግሮ ጌታን የማስያዙ ምሳሌ (ማር ፲፬፥፶፫)። ካም አይቶ እንደሳቀበት እንደዘበተበት ጸሐፍት ፈሪሳውያንም በሻሽ ሸፍነው ተዘባብተውበታልና (ሉቃ ፳፪፥፷፬)። ሴምና ያፌት የፀሐይና የጨረቃ ምሳሌ፤ ሴምና ያፌት ልብሳቸውን ገፈው እንዳለበሱት ፀሐይና ጨረቃም ብርሃናቸውን ተገፈው የጌታን ዕርቃን ሠውረዋል (ሉቃ ፳፫፥፵፬)፤ በማለት መተርጕማን ብሉይ ያብራራሉ።

እግዚአብሔር በሴም ድንኳን (ቤት) ይደር ማለቱ፤ ለጊዜው የሴም ወገን በኾነ በአብርሃም ድንኳን ሥላሴ የመግባታቸው ትንቢት ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን ከሴም ቤት (ወገን) በኾነች በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ወልደ እግዚአብሔር የማደሩን ነገር ትንቢት ሲናገር ነው( ዕብ ፱፥፲፯ )።ሊቁ አባ. ሕርያቆስም ይኽነን ይዞ በቅዳሴው በቍ ፴፩ ላይ *‹‹ቡራኬሁ ለሴም››* (የሴም በረከቱ (ምርቃቱ) አንቺ ነሽ) በማለት አመስግኗታል። ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽ ኖኅ ልጁ ሴምን የመረቀው ምርቃት በእመቤታችን የመፈጸሙን ምስጢር በመጽሐፉ ላይ *‹‹ኖኅ ምስለ ወልዱ ይዌድሰኪ እስመ በላዕሌኪ ተፈጸመ ቃለ በረከቱ ዘይቤ ለይኅድር እግዚአብሔር ውስተ ቤቱ ለሴም››* (ኖኅ ከልጁ ጋራ



www.ethiopianorthodox.org

ያመሰግንሻል፤ በሴም ድንኳን እግዚአብሔር ይደር ብሎ የተናገረው የበረከቱ ቃል በአንቺ ተፈጽሟልና)[61] በማለት ገልጾታል።

በተጨማሪም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሴም በረከት ብቻ ሳይኾን፤ በተሰጠው ርስትም ትመስላለች። ይኸውም የኖኅ ልጆቹ ሴም፣ ካም፣ ያፌት በርስት እየተጣሉ ቢያውኩ፤ የሦስት ልጆቹን ስም በክርታስ ጽፎ፤ በቅዱስ ሚካኤል ዳኝነት በሱ ሽማግሌነት ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ ቀኝ ቀኙን ለያፌት፤ ግራ ግራውን ለካም፤ መኻል መኻሉን ለሴም አካፍሏቸዋል (ዘፍ ፲፥፩-፴፪፤ ኩፋ ፱፥፩-፱)። ይኸቺውም የሴም ዕጣ ደጋግ ተአምራት የተደረገባት ጌታ የተወለደባት ቤተልሔም፣ የተጠመቀባት ዮርዳኖስ፣ ብርሃነ መለኮቱን የገለጸባት ደብረ ታቦር፣ በመስቀል ተሰቅሎ ዓለምን ያዳነበት ማእከለ ምድር ቀራንዮ፣ የተነሣባት፣ ያረገባት፤ ዳግመኛም እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም የተፀነሰችበት፣ የተወለደችበት፣ የሞተችበት፣ የተነሣችበት እነዚኽ ኹሉ ደጋግ ተአምራት የተደረገ በሴም ዕፃ ነው፤ ይኽ ኹሉ ለሴም መደረጉ ጌታችን እመቤታችን በባሕርዩ ቢኖሩ ነውና ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው በቍ ፴፩ ላይ *‹‹ቡራኬሁ ለሴም ወክፍል ለሙ››* (የሴም ቡራኬው ዕድል ፈንታው አንቺ ነሽ) ሲል ገልጾታል (ሉቃ ፫፥፴፮)። ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ስለዚኽ ምስጢር

*‹‹አንቲ ውእቱ መያጢተ በረከት*
*ለኀበ ሴም ዘይልህቅ እመንገለ ካም ወያፌት››*

(ከያፌትና ከካም ዘንድ በረከትን ታላቅ ወደሚኾን ወደሴም የመለስሽ አንቺ ነሽ)[62] በማለት የሴም በረከቱ መኾኗን ሲያስተምር፤ ዳግመኛም

*‹‹አንቲ ውእቱ ቤተ ሴም ዘበጽሐኪዮ በዑፃዌ እምአኃዊሁ*
*ዘብኪ ተሠልጠ በረከተ ኖኅ አቡሁ››*

(የሴም የአባቱ የኖኅ በረከት የተፈጸመብሽ፤ ከወንድሞቹ በዕጣ የደረሰሽው የሴም ቤት አንቺ ነሽ)[63] በማለት ቅድስት ድንግል ማርያም የሴም በረከቱ ዕድል ፈንታው ጽዋ ተራው መኾኗን አጕልቶ አስተምሯል።

ይኽ ኢትዮጵያዊ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቅ ከአዳም ገሮምሮ ስለ እሷ የተነገረውን ምስጢር በመጠቅለል በኖኅተ ብርሃን መጽሐፉ ‹‹ኦ መድኀኒቱ

61. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ፤ ፲፪፥፱
62. እንዚራ ስብሐት ገጽ 46 , 63. ገዘኒ ክማሁ ገጽ 2





ለአዳም፣ ወሙካፈ መሥዋዕቱ ለአቤል፣ መስተባዝኂተ አዝርእቲሁ ለሴት፣ ሕይወተ ነፍሱ ለሔኖክ፣ ወኑኁ መዋዕሊሁ ለማቱሳላ፣ ዕረፍቱ ለላሜሕ፣ ሀብተ ጸጋሁ ለሴም፣ ወሀብተ ቡራኬሁ ለያፌት፣ ወመስተሥርይተ መርገመ ለካም›› (የአዳም መድኀኒቱ የአቤል መሥዋዕቱ ማስቀበያ ሆይ፤ የሴት አዝመራውን የምታበረክቺለት፣ የሔኖክ የሰውነቱ ሕይወት፣ የማቱሳላ የዕድሜ ርዝማኔው፣ የላሜሕ ዕረፍተ ሥጋው፣ የሴም የጸጋው ሀብት፣ የያፌት የቡራኬው ሀብት፣ የካም የርግማኑ ትድግና አንቺ ነሽ)[64] ብሏታል።

ይኸውም ታላቁ አባት ማቱሳላ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባብራኩ በባሕርዩ ቢኖሩ፤ ፱፻፷፱ ዓመት በዚኽ ዓለም ኑሮ ማንም ሰው ያላገኘውን የዕድሜ ጸጋ ሲቀበልባት፤ እኛም ክርስቲያኖች በልጇ ቸርነት፤ በእሷ ምልጃና ቃል ኪዳን በመንግሥተ ሰማይ ለዘላለም እንኖራለንና፤ ሊቁ በምስጢር የማቱሳላ የዕድሜ ርዝማኔው ብሏታል(ሉቃ ፫፥፴፮-፴፯)። ይኽ ብቻ ሳይኾን የወለደው ልጁ ላሜሕም ፯፻፸፯ ዓመት በዚኽ ዓለም ከኖረ በኋላ፤ የወለደው ልጁን እግዚአብሔር በረገማት ምድር ከተግባራችን ከእጅ ሥራችን ያሳርፈናል ሲል ስሙን ኖኅ ብሎታል፤ ይኽ ለጊዜው ቢደረግም ፍጻሜው ግን የሰው ልጆች ኹሉ የተፈረደባቸውን መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስን አስወግዶ፤ ዘላለማዊ ዕረፍትን የሚሰጥ አካላዊ ቃል ክርስቶስ በምልጃዋ ዕረፍተ ነፍስ ከምናገኝባት ከላሜሕ ዘር ከኖኅ ዘር ከኾነች ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታልና፤ የላሜሕ ዕረፍቱ አንቺ ነሽ፤ በማለት ያስተማረው የነገረ ማርያም ትምህርት፤ እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለ እናቱ የገለጠውን ምሳሌ አብራርቶ ያሳየ ነው።

## የመልከ ጼዴቅ መሠዊያ

ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን ሊቀ ካህናት ዐማኑኤልን የወለደች ድንግል ማርያም መልከ ጼዴቅ በኅብስትና በወይን መሥዋዕት ያቀርብባት በነበረው የመሠዊያ ቦታ ትመሰላለች። ይኽ መልከ ጼዴቅ ዐፅመ አዳምን እንደ ታቦት አድርጎ በኅብስት በወይን መሥዋዕት ያቀርብ የነበረ ደገኛ

64. ኖኅተ ብርሃን፤ ገጽ 95



www.ethiopianorthodox.org

ካህን ነበር (ዘፍ ፲፬+፲፰)። ይኸውም ኖኅ ከጥፋት ውሃ በኋላ ከመርከብ ሲወጣ ከዚኽ ኹሉ ላዳነኝ ለእግዚአብሔር ምስጋና ይገባዋል ሲል፤ ዐፅመ አዳምን እንደ.ታቦት አድርጎ መሥዋዕት ሠዋ። ከዚኽም በኋላ ሴምን ጠርቶ ዐጽመ አዳምን ወስደኽ እግዚአብሔር ካዘዘኽ ቦታ አኑር ብሎታል። ሴምም መልከ ጼዴቅን ከናት ካባቱ አሰናብቶ ዐጽሙን አሸክሞ ይዞት ኼደ፤ መላእክት እየመሩ ቀራንዮ ዐደረሱት መስቀል ከሚተከልበት ቦታ ሲደርስ ምድር ተከፈተችለት፤ ዐፅመ አዳምን አግብቶ አኖረ መልከ ጼዴቅም ዐፅመ አዳምን እንደታቦት አድርጎ መሥዋዕት ጸሎት ያቀርብ ነበር።[65] የሶርያ ሰዎች በነገር ተከራክረው ወደ እሱ ሲኼዱ እውነት ይፈርድላቸው ስለነበር «ንጉሠ ጽድቅ» ሲሉት፤ ቢጣሉ ስለሚያስታርቃቸው «ንጉሠ ሰላም» ብለው ጠርተውታል። ክህነቱም ከሌዊ የሚበልጥ ደገኛ ክህነት ነበርና በስንዴና በወይን ሲያስታኩት ኖሯል።

በኦሪት ዘፍጥረት ምዕ ፲፬ ላይ እንደምናነበው ዐምስቱ ነገሥተ ሰዶም ወገሞራ ለአራቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ፲፪ ዓመት ገብረው በ፲፫ኛው ዓመት አንገብርም በማለታቸው፤ በዐዘቅተ ኤሴቅ በተዋጉት ውጊያ፤ አራቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር ድል አድርገው ሎጥን ከዚያ አግኝተው ማርከውታል። አብርሃምም ይኽነን ሰምቶ ከቤተሰቦቹ ፫፻፲፰ት ሰዎች ይዞ ኼዶ ነገሥተ ኮሎዶጎምርን ድል ነሥቶ የተማረከ ወንድሙ ሎጥን መልሶታል።

ይኽም ምሳሌ ነው አብርሃም የጌታ፤ ሎጥ የሃይማኖት፤ ፫፻፲፰ቱ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት፤ አራቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞር የመናፍቃን፤ ዐምስቱ ነገሥተ ሰዶም የምእመናን ምሳሌ፤ አብርሃም ፫፻፲፰ ሰው ይዞ አሕዛብን ድል ነሥቶ ሎጥን እንደመለሰ ጌታም በ፫፻፲፰ቱ ሊቃውንት ዐድሮ ሃይማኖትን የመመለሱ ምሳሌ እንደኾነ መርተርጕማን ብሉይ ያስተምራሉ።

ከዚኽ በኋላ አብርሃም ደስ ብሎት ለአዳምና ለልጆቹ የድኅነት ተስፋን የሰጠ አምላክን በዐይነ ሥጋ ለማየት ተመኝቶ *«ቢጦዋዕልየኑ ትፌኑ ወልድከ ወሚመ ታርእየኒ ኪያሃ ዕለተ»* (ልጅህን በዘመኔ ትልክዋለኽ? ወይንስ ዕለቷን ታሳየኛለኽ) አለው፤ ጌታም *«እስ ዘአርእየከ ኪያሃ አላ አምሳሊሃ ዕድዎ ለዮርዳኖስ ወትረክቦ ለመልከ ጼዴቅ»* (ያችንስ ዕለት የማሳይኽ አይደለም፤ ምሳሌዋን እንጂ፤ ዮርዳኖስን ተሻገር መልከ ጼዴቅን ታገኘዋለኽ) ብሎ

65. መጽሐፈ ቅዳሴ ንባብና ትርጓሜ፤ የቅዳሴ ታሪክ





ምሳሌውን ጠቆመው። አብርሃምም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ሲኼድ ታላቅ ግርማ የነበረውን መልከ ጼዴቅን አይቶ ደነገጠ፤ መልከ ጼዴቅም አብርሃምን አትፍራ፤ አንተን ወደ ዮርዳኖስ እንድትሻገር ያዘዘኽ እግዚአብሔር እኔን ኅብስተ አኰቴት ጽዋዐ በረከት ይዤ ወደ ዮርዳኖስ እንድመጣ ለአንተ እንድሰጥኽ አዞኝ ነው፤ በማለት ከያዘው ኅብስትና ወይን ለአብርሃም ሰጥቶ ባርኮታል፤ አብርሃምም ከያዘው ኹሉ ዐሥራትን ሰጠው።

ይኽ አብርሃምም በኋላ ዘመን አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሥጋውን ደሙን በኅብስት በወይን የሚሰጥ መኾኑን በማወቁ እጅግን ተደስቷል፤ ጌታም ይኽቺን ታላቅ ሰዓት አብርሃም ለማየት እንደተመኘ ለአይሁድ «አባታችኍ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት ዐደረገ፤ አየም ደስም አለው» በማለት ነግሯቸዋል (ዮሐ ፰+፶፮)።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ለመጣ ለአብርሃም መልከ ጼዴቅ በመሶብ ከያዘው ከስንዴው ኅብስት በጽዋው ከያዘው ከወይኑ እንደሰጠው ኹሉ፤ ዘመኑ ሲፈጸም አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ተወልዶ፤ ከአብራክ መንፈስ ቅዱስ ከማኅፀነ ዮርዳኖስ ለተወለድነው ክርስትያኖች፤ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን በስንዴና በወይን አምሳል የሰጠን መኾኑን በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*«መካነ ሞጻሕቱ አንቲ ለመልከ ጼዴቅ*
*በኅብስተ ሥርናይ ወወይን ዘከሡተ ምሥጢረ ጽድቅ»*

(በወይንና በስንዴ የእውነትን ምስጢር የገለጠ የመልከ ጼዴቅ የመሠዊያ ቦታ አንቺ ነሽ)[66] በማለት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ተወልዶ ቅዱስ ሥጋውን በአምሳለ ኅብስት የሰጠ ምግበ ርኁባን፤ ክቡር ደሙን በአርአያ ወይን የሰጠ ስቴ ጽሙኣን፤ አማናዊ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስን ያገኘንባት መኾኗን መስክሯል (ማቴ ፳፮+፳፮- ፳፱፤ ማር ፲፬+፳፪- ፳፭፤ ሉቃ ፳፪+፲፱- ፳፤ ፩ቆሮ ፲፩+፳፫- ፴፪)።

ስለዚኽ ነው ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስትያናችን በሥርዓተ ቅዳሴዋ ላይ በካህኑ አማካይነት *«አአምን አአምን አአምን ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ከመ ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ*

66 እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 33



www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘነሥአ እምእግዝእተ ኵልነ ቅድስት ድንግል በ፪ ማርያም ወረሰዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበለ ቱስሕት ወኢትድምርት ዘእንበለ ፍልጠት ወኢውላጤ ወኮነ ሰማዕተ በስምዕ ሠናይ በመዋዕለ ጲላጦስ ጰንጤናዊ ወመጠዎ በእንቲአነ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ» (አምናለኹ አምናለኹ አምናለኹ እስከ መጨረሻዩቱም እስትንፋስ እታመናለኹ፤ በኹለት ወገን ድንግል ከምትኾን ከኹላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የነሣው የጌታችንና የአምላካችን የመድኀኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይኽ እንደኾነ፤ ያለመቀላቀልና ያለ ትድምርት ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው፤ በጰንጤናዊ ጲላጦስም ዘመን ባማረ ምስክርነት ምስክር የኾነ፤ ስለእኛና ስለ ኹላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው)[67] በማለት እምነቷን ትገልጻለች።

ሊቁ አባ ሕርያቆስ ዮሴፍ የተወዳጃት በውስጧም ክቡር ዕንቍን ካገኘባት ማጥን በተገኘው ኅብስትና በውስጧ ሰው ካልገባባት አዳራሽ በተገኘው ጽዋ እንደተደነቀ ኹሉ፤ የኅብስተ ሕይወት (የሕይወት እንጀራ)፣ የስቴ ሕይወት (የሕይወት መጠን) የክርስቶስ ከቅድስት ድንግል መገኘት ሲቃውንቱን እጅግ በማስደነቁ፤ በነገረ ማርያም ላይ«ወአጸደ ወይን ዘጽድቅ ዘሐንበበቶ ለአስካለ መለኮት ዘርእየ አምሳሊሁ መልከ ጼዴቅ አመ አውጽሐ በኅብስተ ሥርናይ ወበደመ ወይን» (መልከ ጼዴቅ በስንዴ ኅብስትና በወይን ደም ባስታኰተ ጊዜ፤ ምሳሌውን ያየው የመለኮት ፍሬን ያፈራቺው ፤እውነተኛ የወይን ቦታ ርሷ ናት) በማለት ታላቅ የነገረ ድኅነት ትምህርትን እንዲተነትኑ አድርጓቸዋል።

<u>የአብርሃም ርግብ</u>

ቅድስት ድንግል ማርያም አበ ብዙኃን አብርሃም ባያት ርግብ ትመሰላለች (ዘፍ ፲፭፥፱)። ይኸውም አብርሃም ለዐምስቱ ነገሥተ ሰዶም ረድቶ አራቱ ነገሥተ ኮሎዶጎሞርን ድል ነሥቶ ሲመለስ፤ ጌታ የሚሰጠውን ዋጋ ነገረው። ያን ጊዜ አብርሃም ከዘመዴ ወገን የተወለደ የደማስቆ ሰው የሚኾን የማሴቅ ልጅ ኢያውብር የሚባለው ይወርሰኛል፤ ልጅ ከሌለኝ ገንዘብ ብትሰጠኝ ምን ይኾነኛል? አለው ጌታም «ውእቱሰ ኢይወርሰከ አላ ካልእ ዘወጽአ

67 ቅዳሴ ሐዋርያት፣ ቍ ፻፲፩





እምሐቌከ ውእቱ ይወርሰከ» (ከአብራክኽ የተወለደ ልጅኽ ይወርስኻል እንጂ ኢያውብር አይወርስኽም) ብሎ ነገረው። ከዚኽ በኋላ ምድረ ከነዐንን ላንተና ለዘሮችኽ እሰጣለኍ፤ ቢለው በምን አውቃለኍ? ብሎት ነበርና ሦስት ዓመት የኾነውን ላም፣ ሦስት ዓመት የኾነውን ፍየል፣ ሦስት ዓመት የኾነውን በግ፣ ዋኖስና ርግብ አምጣ ላሙን፣ ፍየሉን፣ በጉን አረዳቸው አወራርዳቸው «ወአንበር ሥጋ በአንጻረ ቢጹ» ሥጋውን በየወገኑ አፋዛዝ ከኹለት ከፍለኽ አኑር፤ ርግብን ዋኖስን ግን ኢትምትሮን ይላል «ገዘግዘኽ ተዋቸው እንጂ አትረዳቸው» ብሎታል። ይኽነን ሲያዘጋጅ «ወኮነ ምሴተ ወመጽአ ግሩም ጽልመት» ይላል፤ በመሸ ጊዜ ታላቅ ጨለማ ኾነ፤ አብርሃምም ተደሞ መጣበት፤ እሳት በምድጃ ኾኖ በመኻከል ሲመላለስ፤ ሥጋው እሳቱን ሳያጠፋው፤ እሳቱ ሥጋውን ሳያቃጥለው፤ አዕዋፍ ሥጋውን እኁበላለን ብለው ሲመጡ፤ በዘንግ ሲከለክላቸው አይቷል።

ይኽ አብርሃም ያየውና የተገለጸለት ይኽ ልዩ ራእይ ብዙ ምሳሌዎችን ይዟል። ይኸውም ሦስት ሦስት ማድረጉ እስራኤል በሦስተኛው ትውልድ በያዕቆብ ዘመን ግብጽ የመውረዳቸውን (ዘፀ ፩፥፩)፤ ከኹለት ከፍሎ ማኖሩ ፪፻፲፭ ዓመት በከነዓን፤ ፪፻፲፭ ዓመት በግብጽ የመኖራቸው፤ በየአንጻሩ አኑረው ማለቱ በግብጽ መከራውን አንድ ላይ የመቀበላቸው፤ ሥጋው እሳቱን አለማጥፋቱ እስራኤል መከራውን በቀኖና አለማራቃቸው፤ እሳቱ ሥጋውን አለማቃጠሉ መከራው እስራኤልን አለማጥፋቱ፤ አዕዋፍ ሥጋውን እንበላለን ብለው ሲመጡ በዘንግ ሲከላከላቸው ማየቱ አሕዛብ እስራኤልን እናጠፋለን ሲሉ እስራኤል ግን በኪዳነ አብርሃም፣ በኪዳነ ይሥሐቅ፣ በኪዳነ ያዕቆብ ተጠብቀው የመኖራቸውንና ሌላ ብዙ ምስጢርን ሲያመለክት፤ በተጨማሪ የሐዲስ ኪዳን ምስጢርንም ያሳያል።

ይኸውም ላሕም የጌታ፤ ጠሊ የሐዋርያት፤ በግዕ የአርድዕት፤ ርግብ የድንግል ማርያም፤ ዋኖስ የዮሐንስ ወንጌላዊ ምሳሌ፤ ዋኖስና ርግብን ከርክረኽ ተዋቸው አትለያቸው ማለቱ ከእግረ መስቀል አይለዩምና (ዮሐ ፲፱፥፳፮- ፳፯)። አንድም ዋኖስ የዮሐንስ መጥምቅ፤ ርግብ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ፤ ዋኖስ በበረሓ መኖርን እንድትወድ ዮሐንስ መጥምቅም በገዳም ኖሯል (ማቴ ፫፥፩- ፫)፤ ርግብ በግምብ መኖርን እንድትወድ ድንግል ማርያምም በቤተ



www.ethiopianorthodox.org

መቅደስ ኑራለችና ይኸነን ሲገልጽለት መኾኑን መተርጉማን አስተምረዋል፡፡ ሊቁ ሳዊሮስ ዘእስሙናይን ይኸ ለአብርሃም የተገለጸውን ልዩ ምስጢር ሲተረጉም ሦስት ላም፣ሦስት ፍየል፣ ሦስት በግ አምጣ ብሎታል፣ይኸነን ቢከፍሉት ዐሥራ ስምንት ይኾናል፤ ርግብ ዋኖስ ሲጨመሩ ኻያ ይሆናል፤ ይኸም አብርሃም ይኸነን ባየ በኹለት ሺሕ ዘመን ጌታ ከቤተ አብርሃም ከተወለደች ከቅድስት ድንግል ማርያም የመወለዱ ሰው የመኾኑ ምሳሌን ያመለከተ ነው በማለት ተርጉሞታል(ዕብ ፱፥፲፮)፡፡

## የአብርሃም ዛፍና የአብርሃም ድንኳን

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም እግዚአብሔር ለአብርሃም በአንድነት በሦስትነት በተገለጠባት ዛፍና፤ በገባበት ድንኳን ትመሰላለች (ዘፍ ፲፰፥፩-፲፭)፡፡ ይኸውም አብርሃም ከደግነቱ ብዛት እንግዳን ከመውደዱ የተነሣ ድንኳኑን በተመሳቀለ ጎዳና ሠርቶ የወጣ የወረደውን ያለፈ ያገደመውን ሲቀበል የሚኖር በሥራው ኹሉ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ጻድቅ ነበር (ሮሜ ፬፥፩-፫)፡፡ ጽድቁም ሊታወቅ ስድስት ሰዓት ላይ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ፤ በመምሬ ዛፍ ሥር እግዚአብሔር በአንድነት በሦስትነት ተገለጸለት «ወሶበ አልዐለ አብርሃም አዕይንቲሁ ነጸረ ሠለስተ ዕደወ እለ ይቀውሙ ወርእየ ወሮጸ ለተቀብሎቶሙ እምኆኅተ ኀይመት ወሰገደ ውስተ ምድር» ይላል ዐይኑን አቅንቶ ሲመለከት፤ ሥላሴ በአምሳለ ዕደው ቆመው አይቶ፤ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፤ ወደ ምድርም ሰገደ፤ ከዚኽ በኋላ «አቤቱ በፊትኽስ ሞገስ አግኝቼ እንደኾነ ባሪያኽን አትለፈኝ ብዬ እለምናለኊ፤ ጥቂት ውሃ ይምጣላችኊ፤ እግራችኹን ታጠቡ፤ ከዚኽችም ዛፍ በታች ዕረፉ...» በማለት ተናግሯል፡፡ «በፊትኽ ሞገስን አግኝቼ» ብሎ አንድነታቸውን፤ «ውሃ ይምጣላችኊ» ብሎ የሦስትነታቸውን ምስጢር ገልጾአል፡፡

ይኸቺ አንድነቱ ሦስትነቱን ሳይጠቀልለው ሦስትነቱ አንድነቱን ሳይከፍለው በአንድነት በሦስትነት የሚመሰገን እግዚአብሔር የተገለጠባት ዛፍ፤ አንድነት ሦስትነት በጕላ በተረዳ ነገር የታወቀባት ከሦስቱ አካል አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድን በድንግልና የወለደች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ እንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ





«አንቲ ውእቱ ዕፀ ድርስ ዘለአብርሃም በርስአኒሁ
ዘብኪ አጽለለ እግዚአብሔር በሥላሴሁ»

(ለአብርሃም በእርጅናው ወቅት፤ እግዚአብሔርን በሦስትነት ያስጠለለብሽ የወይራ ዕንጨት አንቺ ነሽ)[68] በማለት ሲገልጥ፤ ዳግመኛም በዚኹ መጽሐፉ

«አንቲ ውእቱ ሰሀት ዘነበርኪ ጥቃ ኀይመት፤
ዘብኪ አጽለሉ ሠለስቱ አጋዕዝት»

(ባንቺ ሦስቱ ጌቶች (ሥላሴ) የተጠለሉብሽ በድንኳን አጠገብ የቆምሽ ዕንጨት አንቺ ነሽ)[69] በማለት በአንድነቱ ምንታዌ (ኹለትነት)፤ በሦስትነቱ ርባዔ (አራትነት) ለሌለበት አምላክ የሦስትነቱ የአንድነቱ ምስጢር መገለጫ የሥላሴ ማደሪያ መኾኗን መስክሯል፡፡

ይኸውም ጌታ ከእመቤታችን ከመወለዱ አስቀድሞ የአንድነት የሦስትነት ምስጢር እምብዛም በጕላ በተረዳ ነገር አይታወቅም ነበር፤ ወአልቦ ዘአእመሮሙ ለሥሉስ ቅዱስ መኑሂ ዘእንበለ እምድኅረ ተሠገወ ወልድ ዋሕድ እምቅድስት ድንግል እንዳለ ሊቁ አንድነት ሦስትነት በጕላ በተረዳ ነገር የታወቀው ጌታ ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲኽ ነው (ሉቃ ፩፥፴፭፤ ዕብ ፩፥፩- ፱)፡፡ ከዚኽም ምስጢር የተነሣ አብርሃምም ሳራን ሦስት መስፈሪያ የተሠለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ፤ ለውሺውም እንጎቻም አድርጊ በማለት የተገለጸለትን የሦስትነት የአንድነት ምስጢርን አጕልቶ ተናግሯል፡፡

ጌታም አብርሃምን «የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለኊ፤ ሚስትኽ ሳራም ልጅን ታገኛለች» በማለት ዘመኑ ሲፈጸም ከቤተ አብርሃም ከተገኘች ከእመቤታችን የመወለዱንና፤ በሳራ የተመሰለች ወንጌል ምእመናንን እንደምታስገኝ በምስጢር ገልጾለታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስም አካላዊ ቃል በሰጠው ተስፋ መሠረት ከነገደ አብርሃም የመወለዱን ነገር ለዕብራውያን ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ላይ (በሕይወታቸው ኹሉ ስለ ሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ኹሉ ነጻ እንዲያወጣ፤ በሥጋና በደም እንዲኹም ተካፈለ፤ የአብርሃምን ዘር ይዘአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም) በማለት ገልጾታል (ዕብ ፪፥፲፭-፲፮)፡፡

ይኸቺ ሥላሴ የገቡባት ኀይመተ አብርሃም (የአብርሃም ድንኳን)

68. አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 2
69. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 46



www.ethiopianorthodox.org

የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፤ ይኸውም ሥላሴ ወደ አብርሃም ድንኳን እንደገቡ ኹሉ፤ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምም፤ አብ ለአጽንኦ፣ መንፈስ ቅዱስ ለአንጽሖ፣ ወልድ በተለየ አካሉ ሥጋን ለመዋሐድ አድረዋል (ሉቃ ፩፥፴፭)፤ በመኾኑም አማናዊቷ የሥላሴ ማደሪያ የአብርሃም ድንኳን እመቤታችን ብቻ ናት።

ሊቁም በነገረ ማርያም ይኽንን ምስጢር ሲገልጽ «ወይእቲ ኀይመት ትትሜሰል በድንግል ወዕደው አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እመንትሄ፤ አብ አጽንአ፣ ወወልድ ተሰብአ እምኔሃ፤ ወመንፈስ ቅዱስ ቀደሳ ከመ ትጸርር አምላክ በከርሣ» (ያቺ ድንኳንም በድንግል ትመሰላለች፤ ሰዎቹም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ናቸው። አብ አጸናት፣ ወልድም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው ኾነ፣ መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ቃል አምላክን ትሸከም ዘንድ ለያት) በማለት ሲተረጉም፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በሰላምታ መጽሐፉ ላይ መጽሐፉ «ኀይመተ አብርሃም አብ ሰላም ለኪ ፤ዘኮንኪ ከመ ተድባብ ሰላም ለኪ» (እንደ ጥላ የኾንሺው የአባት አብርሃም ድንኳን ሰላምታ ይገባሻል)[70] በማለት አመስግኗታል።

ይኽ አብርሃም የተቀበለውን የተስፋ ቃል ሊቃውንት ሲተረጉሙት «አ አኃውየ በይነ መኑ እንከ ዘይቤ እግዚአብሔር ለአብርሃም አመ ከመ ዮም እገብእ ኀቤከ አኮኑ እግዝእትነ ማርያም ይእቲ ዘወፅአት እምነ ሥርው ለአዳም ወእምነ ሐቌሁ ለኖኅ ወፈለሰት ውስተ ቤተ አብርሃም አበ ብዙኃን ዘበእንቲአሃ ተአንገዱ ሥላሴ ውስተ ቤተ አብርሃም ለዜንዎ ትሥጉተ ወልደ እግዚአብሔር እምነ ዘርዐ ለአብርሃም። ወበእንተዝ ይደልወነ ንለቡ ናእምር ከመ ያስተርኢ እግዚአብሔር ትእምርተ ሥርወ ልደታ ለእግዝእትነ በበጊዜሁ» (ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር አብርሃምን እንደዛሬው ኹሉ ወደአንተ ተመልሼ እመጣለኍ ያለው ስለማን ይመስላችኋል? ከአዳም ሥር ወጥታ፤ ከኖኅ አብራክ ተገኝታ፤ ወደ አብርሃም አብራክ ልትከፈል፤ ሥላሴ በአብርሃም ቤት በእንግድነት ተገኝተው፤ ከአብርሃም ዘር ከእመቤታችን የእግዚአብሔርን ልጅ ሰው መኾን ስለስዋ የተናገሩላት እመቤታችን ድንግል ማርያም አይደለችምን፤ ስለዚኽ እግዚአብሔር ስለ እመቤታችን ጥንታዊ የልደቷን አመጣጥ በየጊዜው

70. አባ ጊዮርጊስ፤ የሕማማት ሰላምታ ፤ገጽ ፻፷፭





ምልክት እንደሚሰጥ ልብ አድርገን ማስተዋል ይገባናል)[71] በማለት አብራርተው ተርጉመዋል።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው በቍ፴፱ ላይ «ተናግዶቱ ለአብርሃም» (የአብርሃም እንግድነቱ አንቺ ነሽ) በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ የገለጠውን ይኽንን ድንቅ ምስጢር፤ ሊቁ በነገረ ማርያም ላይ በስፋትና በጥልቀት «ወዓዲ ኀይመት ዘአብርሃም ዘውስቴታ ተአንገደ እግዚአብሔር አኮ ከማሁ ዘኮነቶ ምጽላለ በአንተ ምዕር አላ ኮነቶ እመ ወተከደነ ሥጋሃ ወረሰዮ አሐደ ምስለ መለኮቱ» (ዳግመኛም እግዚአብሔር (በሦስትነት) በእንግድነት ያረፈባት የአብርሃም ድንኳን አንቺ ነሽ፤ ለጥቂት ጊዜ ብቻ መጠለያን፣ መጠጊያን የኾነቺው አይደለም፤ እናትን ኾናው ሥጋዋን ተዋሕዶ ከመለኮቱ አንድ ዐደረገው እንጂ) በማለት በአብርሃም ድንኳን ብትመሰልም እንኳ ክብሯ ከፍ ያለ፤ ለዘላለም የአምላክ ማረፊያውና እናቱ መኾኗን አብራርቶ ገልጧል።

አምላክን በአንድነት በሦስትነት ለማየት ለበቃ ለደጉ አብርሃም አስቀድሞ «የምድር ነገዶች ኹሉ በአንተ ይባረካሉ»(ዘፍ ፲፪፥፫) በማለት የገባለትን የተስፋ ቃል፤ በድንኳኑ ውስጥም የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመጣለኍ፤ በማለቱ ከእሱ ወገን ከኾነች ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ገልጾለት፤ ያውም ከገረዲቱ ከአጋር ልጅ ከይስማኤል ሳይኾን፤ ከእመቤቲቱ ልጅ ከሳራ ልጅ ከይስሐቅ ዘር ከተገኘች ከድንግል ማርያም አካላዊ ቃል ስለመወለዱ «እስመ እምይስሐቅ ይሰመይ ለከ ዘርዕ» (በይስሐቅ ዘር ይጠራልኻል) ዘፍ ፳፩፥፲፪-፲፫ በማለት አጉልቶ ነግሮታል(ሮሜ ፱፥፯-፲፫ )።

## ዕፀ ሳቤቅ

አምላክን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያም ለይሥሐቅ ቤዛ ኾኖ የተሠዋ ጸዐዳ በግን በያዘችው ዕፀ ሳቤቅ በሚባለው ሐረግ ትመሰላለች (ዘፍ ፳፪፥፩-፲፬)። የእግዚአብሔር ወዳጅ አብርሃም አንድያ ልጁን ይሥሐቅን እንዲሠዋው ከእግዚአብሔር በታዘዘው መሠረት፤ በሞሪያ ተራራ ላይ መሠዊያ ሠርቶ እንጨቱን ረብርቦ ልጁ ይሥሐቅን አስሮ በመሠዊያው ዕንጨት ላይ አጋድሞ፤ ሰይፉን አንሥቶ ሊሠዋው በተዘጋጀበት ቅጽበት «ኢትደይ እዴከ

71 ተአምረ ማርያም፤ገጽ ሄ፩



www.ethiopianorthodox.org

ላዕለ ወልድከ ወኢትግበር ቦቱ ወኢምንተኒ›› (በብላቴናው ላይ እጅኽን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት) የሚለውን ቃል ሰምቶ ዐይኑን አቅንቶ ቢያይ‹‹ እንትዘ አቅርንቲሁ በዕፀ ሳቤቅ›› ይላል ለይሥሐቅ መድኀኒት ሊኾነው በኀቱም ጕንድ ኹለቱ ቀንዶቹ የተያዙ ጸዐዳ በግ ተይዞ አይቶ ልጁ ይሥሐቅን ፈቶ ያን ጸዐዳ በግ ሠውቶታል፡፡

ይኸውም ምሳሌ ነበር ይኽ በግ ከኀቱም ጕንደ ዕፅ ተገኝቶ ለይሥሐቅ መድኀኒት ኾኖ በሞሪያ ተራራ እንደተሠዋ ኹሉ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ በግዕ ወልደ እግዚአብሔርም እመ በግዕ ነባቢ ከተባለች ከቅድስት ድንግል ማርያም በኀቱም ድንግልና ተወልዶ የዓለም ቤዛ ኾኖ በቀራንዮ ተራራ በመስቀል ላይ ተሠውቷል(ኢሳ ፶፫፥፯፤ ፩ ጴጥ ፩፥፲፱፤ ራእ ፯፥፲)፡፡

ለዚኽ ነው ዮሐንስ መጥምቅ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ‹‹የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፤ አንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል ከእኔም በፊት ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ኾኖአል ብዬ ስለ እርሱ ያልኹት ይኽ ነው›› እያለ የምስክርነቱን ቃል የሰጠው (ዮሐ ፩፥፳፱-፴)፤ በመኾኑም ያቺ የታተመች ዕፀ ሳቤቅ ለይሥሐቅ ቤዛ የኾነውን ጸዐዳ በግ ይዛ እንደተገኘች ኹሉ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም የዓለምን ኀጢአት ያራቀ በግዕ ወልደ እግዚአብሔርን በኀቱም ድንግልና ፀንሳ በኀቱም ድንግልና ወልዳ አስገኝታለችና እንወዳታለን፣ እናከብራታለን፣ እናመሰግናታለን፣ እናገናታለን፡፡

አብርሃምም በኋላ ዘመን አማናዊ በግዕ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ዓለምን እንደሚያድን በምሳሌው ተረድቶ ስለመደሰቱ ሊቃውንት ሲተነትኑ *‹‹ወተፈሥሐ አብርሃም በዕለተ ወልደ እግዚአብሔር ዘርዕየ በአምሳለ ወልዱ፡፡ ወአእመረ አብርሃም ከመ ይትወለድ ክርስቶስ እምነ ይሥሐቅ ወልዱ ዘትትከፈል እምኔሁ ወይእቲ እግዝእትነ ማርያም እመ በግዕ ነባቢ በደኃሪ መዋዕል፡፡ ወይቤ ቡሩክ ውእቱ አምላክነ ወእግዚእነ ወመልአከ ሕይወትነ ወሀቤ ፍሥሓ ወበረከት ወሎቱ ይደሉ ስብሐት ወክብር ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡ ወሰብሖ ለእግዚአብሔር በይነ ዘከሠተ ሎቱ ዘተመነየ ምስጢረ ልደቱ ለመድኀኔዓለም በግዐ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኀጢአተ ዓለም፡፡ ወላቲ ይደሉ ዕበይ ወክብር ለእመ በግዕ ነባቢ ወይእቲኒ ድንግል ማርያም ይእቲ››* (አብርሃምም የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ኾኖ ለመሥዋዕት መቅረብ





በልጁ በይስሐቅ አምሳል በተረዳ ጊዜ ፈጽሞ ደስ አለው፡፡ አብርሃምም ከልጁ ከይሥሐቅ ወገን የምትገኝ ወይም ከይሥሐቅ አብራክ የተከፈለች፤ በኋለኛው ዘመን የነባቢ በግዕ እናቱ ከኾነች ከእመቤታችን ማርያም የክርስቶስን መወለድ በዚኽ ነገር ዐወቀ ተረዳ፡፡ የሕይወታችን መገኛ የሚኾን እሱ አምላካችንና ጌታችን ቡሩክ ነው፤ደስታንና በረከትን የሚሰጥ ለሱ እስከ ዘላለሙ ድረስ ክብር ምስጋና ይገባል አለ፤ይመኛት የነበረችውን የዓለሙን ኀጢአት የሚያስወግድ ለመሥዋዕት የቀረበ የእግዚአብሔርን በግ የመድኀኔዓለምን የልደቱን ምስጢር የገለጸለት እግዚአብሔርን ፈጽሞ አመሰገነው፤ ሰባቱን አጽራሐ መስቀል የተናገረ የነባቢ በግ እናቱ ለድንግል ማርያም ክብር ምስጋና ይገባል)[72] በማለት በስፋትና በጥልቀት አስተምረዋል፡፡

ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም ያቺ በሞርያ ተራራ ላይ የበግ ጠቦት ያበረከተችው ዛፍ፤ ያለ ግንኙነት ክርስቶስን የወለደችው የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ሲገልጽ ‹‹Never before, and never again has tree given birth to a lamb…›› (ቀድሞም ወደፊትም አልተደረገም አይደረግም፤ በዚኽ ምድር ዛፍ የበግ ጠቦትን ወለደ፤ የትኛዋም ድንግል ያለ ወንድ ርዳታ አልወለደችም፤ ማርያምና ያ ዛፍ አንድ ናቸው በጉ በቅርንጫፍ ላይ ተሰቅሎ ነበር ጌታ በጎልጎታ እንደተሰቀለ፤ በጉ ይሥሐቅን ከመታረድ አዳነ ጌታ ፍጥረትን ከሞት አዳነ)[73] በማለት የምሳሌውን ፍጻሜ ማግኘትን አስተምሯል፡፡ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ

*‹‹አንተ ውእቱ ለይሥሐቅ ደብረ መዐዛሁ*
*እንተ ፈረይከ በግዐ ዘእኁዝ በዕፀ ሳቤቅ አቅርንቲሁ››*

(ቀንዶቹን በዕፀ ሳቤቅ የተያዘ በግን ያፈራችለት የይሥሐቅ የመዐዛ መሥዋዕትነቱ ተራራ አንቺ ነው)[74] በማለት የነባቢ በግዕ የወልደ እግዚአብሔር እናቱ መኾኗን ሲመሰክር በተጨማሪም በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ*‹‹ይሥሐቅ እንዘ ንጹሕ ወቅልዔሁ አዕረጎ አቡሁ መሥዋዕተ ለእግዚአብሔር ወአውረደ ሎቱ ቤዛሁ በግዓ በሐከ ንጹሐ ኢበሊወ ይሥሐቅ ባዕዳነ ዘእንበለ ዘተቤዘወ በደመ በግዕ ወወልድኪሰ ከዊኖ ከመ በግዕ ቅድው ቤዘወ ኵሎ ዓለመ በንጽሕናተ*

72. ተአምረ ማርያም፤ ገጽ ፶፬-፶፭
73. Bride of Light p 42
74. አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 2



www.ethiopianorthodox.org

*ደመ*›› (ይሥሐቅ ንጹሕና የእግዚአብሔር ወዳጅ ሲኾን አባቱ አብርሃም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው በንድ ወደ ተራራ አወጣው ነገር ግን ቤዛው የሚኾን ንጹሕ በግ በግን አወረደለት፤ ይሥሐቅ ራሱን ከመዳን በቀር ሌሎችን አላዳነም፤ ልጅሽ ግን እንደተወደደ በግ ኾኖ በደሙ ፈሳሽነት ዓለሙን ኹሉ አዳነ)[75] በማለት የዓለምን ኀጢአት ያራቀ የጌታችን እናቱ መኾኗን መስክሯል፡፡

## የአብርሃም እርሻ

እመ አዶናይ ቅድስት ድንግል ማርያም አብርሃም በ ፱፻ ሰቅል ዋጋ በገዛት ኹለት ክፍል ባላት እርሻ ትመሰላለች (ዘፍ ፳፫፥፱-፳)፤ ይቺ አብርሃም ከኤፍሮን የወሰዳት እርሻ በአተ ካዕበትነት የኾነች እንደ እልፍኝ ካዳራሽነት ያላት ኹለት ክፍል ናት፤ አብርሃምም እርሻውን ከላይ ያርሳት፣ ይቆፍራት፣ ያርማት፣ ይኮተኩታት ነበር፤ ምሳሌ ትኹንኝ ብሎ ዘር ግን አልዘራባትም፤ በውስጧም ሰው ይቀብርባት ነበር፤ ይኸውም ምሳሌ ነው አብርሃም የጌታ፣ እርሻ የእመቤታችን ምሳሌ ናት፡፡

ያች እርሻ ድርብ ክፍል ይዛ እንደተገኘች ቅድስት ድንግል ማርያምም ድንግል በ፪ኤ (በኹለት ወገን) ማለትም በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች ናት፡፡ ዳግመኛም እናትነትን ከድንግልና፤ ድንግልናን ከናትነት ጋር አስተባብራ ተገኝታለች፤ በተጨማሪም ያቺ የአብርሃም እርሻ ዘር እንዳልተዘራባት ኹሉ የጌታችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያምም ዘርዐ ብእሲ (የወንድ ዘር) አልተገኘባትም (ሉቃ ፩፥፴፬፤ ማቴ ፩፥፲፰፤ ኢሳ ፯፥፲፬)፤ ያርማት ይኮተኩታት እንደነበር ቅድስት ድንግል ማርያምም ከፍትወታት ከእኩያት ንጽሕት ናትና (መሓ ፬፥፯)፤ ያች እርሻ እንደተጠበቀች ኹሉ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከእናቷ ማሕፀን ገምሮ በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቃ የመኖሯ ምሳሌ ነው፡፡

ይቺ የአብርሃም እርሻ በእውነት የድንግል ማርያምም ምሳሌ መኾኗን ታላቁ የቤተክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በመጽሐፈ ድጓው ላይ ‹‹*እግዝእትየ ገራህቱ ለአብርሃም*›› (እመቤቴ የአብርሃም እርሻው)[76] በማለት ሲያመሰግናት ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በመጽሐፉ

75 አርጋኖን ዘንመስ ፭፥፰
76 ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ፤ ገጽ፫፻፸፱





‹‹*አንቲ ውእቱ ለአብርሃም ማኅተመ ጽድቁ*
*ገራህት አንቲ ዘተማኅፀነ በወርቁ*››

(የአብርሃም የጽድቁ ማኅተም አንቺ ነሽ፤ በወርቁ የገዛውም እርሻ ነሽ)[77] በማለት የምሳሌውን እውነትነት ገልጾታል፡፡

## የርብቃ መታጨት

አብርሃም ከገሊጋዩ ኢያውብር አማካይነት ለልጁ ይሥሐቅ ርብቃን ማጨቱ ብሥራተ ድንግልን ያመለክተናል (ዘፍ ፳፬፥፩-፰፯)፡፡ ለእግዚአብሔር ወዳጅ ለአብርሃም ኢያውብር የሚባል ሎሌ ነበረውና እሱን አስጠርቶ ልጄ ይሥሐቅን ከአገሬ ከወገኖቼ ከአዋልደ ሶርያ (ከሶርያ ሴቶች ልጆች) እንጂ አብሬ ከምኖራቸው ከአዋልደ ከነዓን (ከከነዓን ሴቶች ልጆች) እንዳታጋባው በሰማይና በምድር አለ ላለ በእግዚአብሔር አምልኳለው አለው፤ እሱም ጠንቅቆ ይምላል፡፡ ያቺ ብላቴና አልመጣም ብትል ጎጋሮው ልኺድ አለው ‹‹ዐቀ ኢታግብኦ ለይሥሐቅ ወልድየ እስመ ውእቱ እግዚአብሔር ዘሐፀነኒ ወሴሰየኒ ይፌኑ ለከ መልአኮ›› ልጄን ወደዚያ እንዳትመልስ ተጠንቀቅ ከአባቴ ቤት ከተወለድኹባት ምድርም ያወጣኝ ይኽችንም ምድር እሰጥኻለኍ ብሎ የነገረኝና የማለልኝ የሰማይ አምላክ እግዚአብሔር እርሱ መልአኩን ይሰድዳል አለው፡፡

እሱም ግመሎቹን ጭኖ ዐሥር ወቄት ወርቅ ለእጅ አምባር ኹለት ወቄት ወርቅ ለገሮ ጉትቻ ይዞ ኼደ፤ ከሶርያ አውራጃ ሲደርስ ብዙ ሴቶች ውሃ ሊቀዱ ሲመጡ አይቶ ከእነዚኽ ወገን አንዲቱ መልክ ከደምግባት አስተባብራ ይዛ ተገኝታ የጌታዬ ወገን ኹና ውሃ አጠጭኝ ብያት አጠጥታኝ ግመሎቼን አጠጥታልኝ‹‹ ኪያሃ አስተዳሎከ ለይሥሐቅ ገብርከ›› እርስዋ ለባሪያኽ ለይሥሐቅ ያዘጋጀኻት ትኹን አላለኍ፤ እያለ ሲያስብ ወዘእንበለ ያኀልቅ ተናግሮ ይላል ይኽነን ተናግሮ አስቦ ሳይጨርስ ርብቃ ባጭር ታጥቃ ማድጋዋን ይዛ ውሃ ልትቀዳ መጣች፤ ውሃ ቀድታ ስትወጣ ውሃ አጠጪኝ አላት፤ አጠጣችው፡፡ ግመሎችኽንም ላጠጣልኽ ብላው አጠጣችለት፤ ስትጨርስ የማነሽ ልጅ? አላት፤ ሚልካ ለናኮር የወለደችው የባቱኤል ልጅ ርብቃ ነኝ አለችው፤ ከአባትሽ ቤት የምናድርበት ስፍራ ይገኛልን? አላት የሚያርፍበት

77. አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 30



www.ethiopianorthodox.org

ዙፋን የሚመገበው የሚጠጣው እንዳለ ግመሎቹም የሚታሰሩበት ጋጥ የሚበሉት ገፈራ እንዳለ ነገረችው፡፡

እሱም ፈጣሪውን አመስግኖ ዐሥር ወቄት ወርቅ ለኹለት እጆችዋ አምባር፤ ኹለት ወቄት ለኹለት ጕሮዎቿ ጉትቻ አስጊጦ ሰደዳት፤ እሷም ለቤተሰቦቿ ተናገረች፡፡ ላባ የሚባል ስሱ ወንድም ነበራት እንደሷ የሚያገኝ መስሎት ኼዶ ይዞት መጣ፤ እኽል ቀረበለት፤ እርሱ ግን ጌታዬ የላከኝን ሳልናገር ሌላ ሥራ አልሠራም አለ፤ በል ንገረን አሉት፤ እርሱም እግዚአብሔር ጌታዬ አብርሃምን ከኹሉ በላይ እንዳከበረው ታውቃላችኊ፤ በእርጅና የወለደው ተወራራሽ ተቈራራሽ የሌለው አንድ ልጅ አለው፤ እሱንም ከአዋልደ ሶርያ እንጂ ከአዋልደ ከነዓን እንዳታጋባው ብሎ አምሎኛል፤ ዛሬም ገንዘብ ይገፍ መጥቼ ከውሃ ዳር ዐርፌ ሳወጣ ሳወርድ፤ ይኽቺ ብላቴና መጣች እንደምታይዋት አስጊጩ ሰደድኳት፤ እኹንም ቸርነትንና እውነትን ለጌታዬ ትሠሩ እንደኾነ ንገሩኝ አላቸው፡፡

እነሱም ለመልእክተኛው ነገሩ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለመጣ ይዘኻት ኺድ ካሉ በኊላ ርብቃን ጠርተው ትኼጃለሽ? ብለው ጠየቋት፤ እሷም እኼዳለኊ አለች፤ እነሱም አንቺ እኅታችን እልፍ አእላፋት ኹኚ ፤ልጆችሽ የልጅ ልጆችሽ የጠላቶችን ደጅ ይውረሱ፤ ብለው መርቀው ሰደዷት፡፡ ሎሌውም ለቤተሰቦቿ ለማጫ የሚኾን የከበረ ስጦታ ሰጥቶ ይዟት ኼደ፡፡ ይሥሐቅ ወንበዴ እንዳይጣላቸው ብሎ፤ ብላቴኖቹን አስከትሎ ከአፋፍ ኾኖ እየወጣ እየገባ ሲመለከት ርብቃ አይታ ያ ማነው? አለችው፤ አንቺ የምትኼጂለት የጌታዬ የአብርሃም ልጅ ጌታዬ ይሥሐቅ እንጂ እሱ ነው አላት፤ እርሷም መሸፈኛ ወስዳ ተከናንባ አጊጣ ቆየች ይሥሐቅም ይዟቸው ኼዷል፡፡

ይኽ ኹሉ ምሳሌ ነው አብርሃም የእግዚአብሔር አብ፤ ይሥሐቅ የመለኮት፤ ኢያውብር የቅዱስ ገብርኤል፤ ርብቃ የድንግል ማርያም ምሳሌ ከነዓን የሰማይ፤ ሶሪያ የዚኽ ዓለም ምሳሌ ናቸው፤ አዋልዶ ሶርያ የተባሉት በምስጢር ደቂቀ አዳም (የአዳም ልጆች) ናቸው፤ ከነሱ ወገን አጋባው ማለቱ መለኮት የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ ሥጋውን እንዲዋሐድ ዕወቅ ሲል ነው፤ አዋልደ ከነዓን የተባሉ መላእክት ናቸው ከነሱ ወገን አታጋባው ማለቱ መለኮት የመላእክትን ባሕርይ ገንዘብ እንዳያደርግ ዕወቅ ሲል ነው፡፡





ለዚኽ ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መለኮት የእኛን አካል አካል፤ የእኛን ባሕርይ ባሕርይ አድርጎ መዋሐዱን ለዕብራውያን ሰዎች በጻፈላቸው መልእክቱ ላይ ‹‹በሕይወታቸው ኹሉ ስለሞት ፍርሃት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ኹሉ ነጻ እንዲያወጣ በሥጋና በደም እንዲኹ ተካፈለ፤ የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክት አይደለም›› በማለት የገለጸው (ዕብ ፱፥፲፬-፲፮)፡፡ ይኽ ዓለም የዳነበት በማሕፀነ ድንግል የመለኮትና የትስብእት መዋሐድ በሰርግ ቤት በሚደረግ የመርዓዊና የመርዓት ውሕደት የሚገለጽ መኾኑን በርካቶች የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ቅዱስ ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች የጻፈላቸውን መነሻ በማድረግ አስተምረዋል፤ ከነዚኽም መኻከል እነ ቅዱስ ኤፍሬም፣ እነ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ይገኙበታል፡፡

ታላቁ መምህር ቅዱስ ኤፍሬም ይኽነን ልዩ የተዋሕዶ ምስጢር በረቡዕ ውዳሴ ማርያም ላይ ‹‹ከብካብ ንጹሕ ወመርዓ ቅዱስ›› (ድንግል ማርያም ሙሽራዋ ንጹሕ የሚኾን የሰርግ ቤት ናት) በማለት በድንግል ማሕፀን የተደረገውን የመለኮትና የትስብእትን ተዋሕዶ ነገር አስተምሯል፡፡ ይኸውም በሰርግ ቤት አራት ነገሮች ይደረጋሉ እነሱም፦

ሀ. የመርዓዊ (የሙሽራ) እና የመርዓት (የሙሽሪት) ተዋሕዶ ይደረግባታል(ማቴ ፲፱፥፭-፮፤ ኤፌ ፭፥፳፭-፴፫፤ ዮሐ ፫፥፳፱)

ለ. አዝማደ መርዓዊ (የሙሽራ ዘመዶች) እና አዝማደ መርዓት (የሙሽሪት ወገኖች) ይገናኙባታል፡፡

ሐ. መብል መጠጥ ይገኝባታል፡፡

መ. ተድላ ደስታ ይደረግባታል፡፡

በዚኽች የሰርግ ቤት ውስጥ ከጋብቻ አስቀድሞ ኹለት የነበሩት መርዓዊና መርዓት እንደሚዋሐዱባት፤ አንድ አካል እንጂ ኹለት እንደማይባሉ ኹሉ ድንቅና ልዩ በኾነው የነገረ ሥጋዌ ምስጢር ከተዋሕዶ በፊት ኹለት የነበሩት መለኮትና ትስብእት በተዋሕዶ አንድ የመኾናቸውን ረቂቅ ምስጢር የሚያሳይ ነው (ዮሐ ፩፥፩-፲፬)፡፡ ዳግመኛም በዚኽ በሰርግ ቤት አዝማደ መርዓዊና አዝማደ መርዓት አንድነት እንደሚፈጥሩ ኹሉ፤ በአምላክ ከድንግል ማርያም መወለድ ተራርቀው የነበሩት መላእክትና ሰዎች፤ ሕዝብና አሕዛብ አንድ ኾነው



www.ethiopianorthodox.org

አመስግነዋል (ሉቃ ፩፥፳-፳፤ ገላ ፫፥፳፰-፳፱)።

በተጨማሪም በሰርግ ቤት መብልና መጠጥ እንደሚገኝባት ኹሉ በእመቤታችንም ቃለ እግዚአብሔር ተሰምቶባታል፤ ዳግመኛም አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ኾኖ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለእኛ ሰጥቶናል። በመጨረሻም በሰርግ ቤት ተድላ ደስታ እንደሚደረግ ኹሉ በመለኮት ትስብእትን ተዋሕዶ ሰው መኾን በቤተልሔም ግርግም ትእምርት ተአምራት ተደርጓልና ፤ይኸውም እደ መወልዲት ተኮማትሯል፤ ሰብአ ሰገል እጅ መንሻ ይዘው መተዋልና (ማቴ ፪፥፩-፲፪፤ ሉቃ ፪፥፲፱)፤ ሊቃውንት አባቶቻችን ይኽንን ምስጢር በመረዳታቸው ይሥሐቅን በመለኮት፤ ርብቃን በድንግል ማርያም መስለው በማነጻጸር አስተምረዋል።

ዳግመኛም መልእክተኛው ኢያውብር ከአብርሃም ተልኮ ከከነዓን ወደ ሶርያ መውረዱ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ የአምላክ ሰው የመኾን ብሥራት ይዞ ከሰማይ ወደ ገሊላ የመውረዱ ምሳሌ ነው (ሉቃ ፩፥፳፮)፤ ርብቃ ውሃ ቀድታ ስትወጣ አጠጪኝ ቢላት ብታጠጣው በግራ በቀኝ ገሮዋ የወርቅ ጉትቻ እንደሰጣት፤ ቅዱስ ገብርኤልም ድንግል ማርያምን ውሃ ቀድታ ስትወጣ ‹‹እንሆም ትፀንሻለሽ›› ብሎ አምላክን የመፅነሷን ብሥራት በገሮዋ አሰማት (ሉቃ ፩፥፳፰-፴፯) ፤ርብቃ ብትጠየቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከኾነማ እሽ ማለቷ፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም አምላክን ትፀንሻለሽ ብሎ ቅዱስ ገብርኤል ሲያበሥራት ‹‹ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ›› (እንደቃልኽ ይኹንልኝ) ብላ ብሥራቱን በእምነት የመቀበሏ ምሳሌ (ሉቃ ፩፥፴፰)፤ ርብቃን ቤተሰቦቿ መርቀው አመስግነው መሸኘታቸው ቅድስት ድንግል ማርያምም አምላክን ወልዳ በአራ መላእክት ወሰብእ (በመላእክትና በሰው እንደበት) ስትመሰገን የመኖሯ ምሳሌ ነው (ሉቃ ፩፥፳፰፤ ሉቃ ፩፥፵፪-፵፭፤ ሉቃ ፩፥፵፰-፵፱) ፤ኢያውብር ለቤተሰቦቿ ማጫ እንደሰጠ ቅዱስ ገብርኤልም ለዘመዶችዋ ለነገዷዋ (ለሰው ልጆች) ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ ክብር የሚሰጠውን አምላክን ትወልጃለሽ ብሎ የማብሠሩ ምሳሌ (ሉቃ ፩፥፴፪-፴፭)፤ ኢያውብር የዐሥር ወቄት ወርቅ አንባር ለርብቃ እንደሰጣት ‹‹ወርእያ ደንገፀት እምቃሉ›› (እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና…) ከሚለው ዠምሮ ‹‹ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ›› (ለመንግሥቱ መጨረሻ የለውም)





እስከሚለው ድረስ ቢቈጥሩ ዐሥር ይኾናሉ (ሉቃ ፩፥፳፱-፴፫) ይኽ የብሥራት ቃል ስለ ዐሥሩ ወቄት ወርቅ ተቆጥሮላታል።

በርብቃ በገሮዋ የተደረገላት ኹለት ወቄት ወርቅ ጉትቻ እመቤታችን በገሮዋ የሰማቻቸው ‹‹ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልዕተ ጸጋ›› (ጸጋን የተመላሽ ደስተኛይቱ ሆይ ደስ ይበልሽ) ያለውና ‹‹ቡርክት አንቲ እምአንስት›› (ከሴቶች መኻከል የተባረክሽ ነሽ) የሚለው ኹለት የብሥራት ቃላት ምሳሌ መኾናቸውን (ሉቃ ፩፥፳፰) ጥንታውያን ሊቃውንት አስተምረዋል።

## ሰዋስወ ያዕቆብ

ሰአሊተ ምሕረት ቅድስት ድንግል ማርያም የሰማይ ደጅ በተባለች ያዕቆብ በሎዛ መንገድ ባያት የወርቅ መሰላል ትመሰላለች (ዘፍ ፳፰፥፲-፳፪)። ይኸውም ያዕቆብ ከአባቱ ከይሥሐቅ በረከትን ተቀብሎ ወደ አጎቱ ወደ ላባ ሲኼድ መሸበትና መንገድ እልፍ ብሎ ደንጊያ ተንተርሶ ቢተኛ ‹‹ወሐለመ ወይሬኢ ሰዋሰወ ዘወርቅ ውስተ ምድር ወርእሱ ይጐድዕ ሰማየ›› ይላል በሕልሙ የወርቅ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ፤ መላእክት በእርከኗ ሲወጡባት ሲወርዱባት፤ በላይዋ ላዩ ዙፋን ተነጽፎባት፤ በዚያ ላይ ልዑል እግዚአብሔር ተቀምጦባት አይቷል። በኋላም ያዕቆብ ማልዶ ተነሥቶ ‹‹ይኽ ስፍራ እንዴት ያስፈራል ይኽ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይኽም የሰማይ ደጅ ነው›› በማለት ትንቢት ተናግሮ ተንተርሶት የነበረውን ደንጊያ ተክሎ በላዩ ላይ ዘይት አፈሰሰበት ስሟንም ቤቴል ብሎ ሰይሞታል፤ ትርጕሙም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው (ዘፍ ፳፰፥፲፰- ፲፱)።

ይኽቺ እግዚአብሔር ተቀምጦባት ያዕቆብ ያያት መሰላል ወልደ እግዚአብሔር ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ወርቁ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ እርከኗ ብዙ መኾኑ የሀብቷ የመዓርጓ ምሳሌ፤ ከምድር እስከ ሰማይ ተተክላ ማየቱ የልዕልናዋ፤ ድንጋዩ የትንቢተ ነቢያት፤ መሰላሏ በድንጊያ ላይ ተተክላ ጸንታ ማየቱ ቅድስት ድንግል ማርያምም በትንቢተ ነቢያት ጸንታ የመኖሯ ምሳሌ ነው። ‹‹ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት ዘነቢያት›› (ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢትና ምሳሌ) ብሎ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያሙ በቊ ፴፺ እንዳስተማረ፤ መላእክት ሲወጡባት



www.ethiopianorthodox.org

ሲወርዱባት ማየቱ ጌታ ከድንግል ማርያም ሳይወለድ መላእክት ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መሥዋዕት ለማሳረግ ከመውጣት ከመውረድ ተከልክለው ነበር፤ ጌታ ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ግን ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መሥዋዕት ለማሳረግ የሚወጡ የሚወርዱ ኾነዋልና (ሉቃ ፩፥፲፩፤ የሐዋ ፲፥፫-፬)።

አንድም ያዕቆብ የሐዋርያት፣ ደንጊያው የአሕዛብ ምሳሌ፤ በደንጊያው ላይ መሰላል መኾኑ አሕዛብ በሐዋርያት ስብከት አምነው በእመቤታችን ፍቅር የመጽናታቸው ምሳሌ (መዝ ፺፱፥፱-፲፯፤ ፻፫፥፩-፯፤ ፻፴፩፥፲፫-፲፯፤ ኢሳ ፩፥፱፤ የሐዋ ፩፥፲፬)፤ አንድም ያዕቆብ የጳጳሳት የሊቃነ ጳጳሳት፤ ደንጊያው የታቦት፤ ዘይቱ የሜሮን ምሳሌ፤ በደንጊያው ላይ መሰላል፤ በመሰላሉ ላይ ጌታ መታየቱ የጌታና የእመቤታችን ስም በታቦት ላይ የመጻፉ ምሳሌ፤ ዛሬም በቤተክርስትያናችን ሥርዐት መሠረት የጌታና የእመቤታችን ስም ያልተጻፈበት ታቦት አይቀደስበትምና።

ይኽነን ልዩ ምስጢር ኢትዮጵያዊው የቤተክርስትያናችን ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በኆኅተ ብርሃን መጽሐፉ እንዲኽ ሲል ተርጕሞታል። *«አንቲ ውእቱ ሰዋስው ዘርእየ ያዕቆብ እምድር ዘይበጽሕ እስከ ሰማይ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ ባቲ፤ ሰዋስወ ወርቅ እንከ ተሰመይኪ እስመ ኮንኪ ምዕራገ እምድር እስከ ሰማይ፤ ዘወርቅ እንከ ተሰመይኪ በእንተ ንጽሐ ሥጋኪ ከመ ወርቅ ጽሩይ መፍደይ ዘኢኮነ ተምያነ፤ ወመላእክተ እግዚአብሔር የዐርጉ ወይወርዱ ባቲ ዘይቤ ሥዩማነ ቤተ እግዚአብሔር እሙንቱ ዘቖሙ ጸታ መዓርጊሆሙ፤ የዐርጉሰ ባቲ በአጽጋረ ኀሊና ዘመንፈስ ወእኮ በአጽጋረ ሥጋ ዘነፍስ ሶበ ትትኄለይ ማርያም መኑ ውእቱ ዘተሰብአ እምኔሃ፤ እስመ ይእቲ ሥጋ ዘድንግል ንጽሕት ዐጽፈ ኮነት ለመለኮተ ወልድ ዋሕድ ወነበረት በየማነ አብ ወበእንተዝ ናዐብያ ወናልዕላ ለማርያም እስመ ኮነት ምጥቅተ እስከ አርያም ወኮነት ሰፋኒተ ውስተ ኵሉ ዓለም»* (ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ ያዕቆብ ያየው የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ፤ የእግዚአብሔር መላእክትም ይወጡባታል ይወርዱባታል። ከምድር እስከ ሰማይ መውጫን ኾነሻልና እንግዲኽ ወዲኽ የወርቅ መሰላልን ተባልሽ፤ እንደማይወላውል የወርቅ ሚዛን የጠራ ስለኾነ የሥጋሽ ንጽሕና የወርቅን ተባልሽ፤ የእግዚአብሔር መላእክት ይወጡባታል





ይወርዱባታል ያለውም የማዕርጋቸው ዐይነት በሰባት የሚመደብ ካህናት የቤተ እግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸው (ምሳ ፱፥፩)፤ የሚወጡባት ግን የመንፈስ ቅዱስ በኾነ የኅሊና እግር ነው፤ ነፍስን በተዋሐደ የሥጋ እግሮች አይደለም፤ ማርያም በምትታሰብ ጊዜ ከርሷ ሥጋን ተውሕዶ ሰው የኾነ ማነው? ይኽች ሥጋ የንጽሕት ድንግል የምትኾን ሥጋ ለዋሕድ ወልድ መለኮት ልብስን ኾና በአብ ዕሪና ተቀመጠች (ዮሐ ፩፥፲፬፤ ኢሳ ፱፥፮- ፯፤ ዳን ፯፥፲፫- ፲፬፤ ማር ፲፮፥፲፱)፤ ስለዚኽ ነገር እመቤታችን ማርያምን በፍጹም እናከብራት እናግናት እስከ አርያም የመጠቀች ኾናለችና፤ በዓለም ውስጥ ኹሉ ገናናን ኾናለችና)[78] በማለት አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሣው ሥጋ ከመለኮት ጋር በመዋሐዱ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በመኾኑ፤ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዕሩየ መንበር ኾኖ፤ በየማነ አብ በዘባነ ኪሩብ ተቀምጦ ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሲሠለስ ሲቀደስ መኖሩን በያዕቆብ መሰላል መገለጹን በጥልቅ የነገረ መለኮት አገላለጽ ገልጾታል።

ይኽ ኹሉ ምስጢር ያዕቆብ በሎዛ ባየው ራእይ ተገልጦለታልና ያዕቆብ በፍርሀት በረዐድ በመኾን፤ እግዚአብሔር በስፍራው እንዳለ ተረድቶ፤ ይቺ የሰማይ ደጅ ናት በማለት አጒልቶ ተናግሯል። በመኾኑም እናታችን ድንግል ማርያም ሰውን ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ ያደረገች የሰማይ ደጅ ናት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደጅ ብዙ ምስጢራዊና መንፈሳዊ ትርጓሜዎችን አዝሎ ይገኛል ከነዚኽም ውስጥ በመዝሙር ፳፫፥፯ ላይ «የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ የክብርም ንጉሥ ይግባ ይኽ የክብር ንጉሥ ማነው? እግዚአብሔር ነው» ይላል በመዝ ፺፱፥፬ ላይም «ወደ ደጆቹ በመገባት ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ» ሲል በመዝ. ፻፲፯፥፳ ላይ «ይኽቺ የእግዚአብሔር ደጅ ናት ወደ እርሷ ጻድቃን ይገባሉ» እያለ ተናግሯል፤ ወንጌላዊ ዮሐንስም ስለ ዐዲሲቱ ኢየሩሳሌም ደጃፎች በራእዩ ላይ «ዐሥራ ኹለቱም ደጆች ዐሥራ ኹለት ዕንቈች ነበሩ እየአንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበር» በማለት ተናግሮላታል» (ራእ ፳፩፥፳፩)።

ይኽ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጸው የደጅ ልዩ ምስጢር የአምላክ እናት የድንግል ማርያምም ምሳሌ ስለመኾኑ ታላቁ አባት ዳዊት በመዝ ፹፮፥፩-፪

78. አባ ጊዮርጊስ ፤ኆኅተ ብርሃን ፤ገጽ 130-131



www.ethiopianorthodox.org

ላይ ‹‹መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ውስጥ ናቸው ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል›› በማለት ልዑል እግዚአብሔር ከሌሎች ሴቶች ይልቅ የድንግል ማርያም ሥጋ ለተዋሕዶ መውደዱን ሲናገር፤ ታላቁ ነቢይ ሕዝቅኤልም በትንቢቱ በምዕ ፵፬፥፩-፫ የእመቤታችን የዘላለማዊ ድንግልናዋን ነገር፤ የእስራኤል አምላክ ደጃፏን ሳይከፍታት ገብቶ ሳይከፍታት በወጣ በታላቅ አዳራሽ አምሳል አይቷታል፡፡

በመኾኑም ያዕቆብ ያያት የእስራኤል አምላክ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስ ወደ ዓለም የወጣባት የሰማይ ደጅ እመቤታችን ናትና ‹‹ኆኅተ ምሥራቅ ወእሙ ለብርሃን ሰላም ለኪ›› (የምሥራቅ ደጃፍ የብርሃን እናቱ ላንቺ ሰላምታ ይገባሻል)[79] እያልን እናመሰግናታለን፡፡ ቅዱስ በርናርድም የሰማይ ደጃፍ መኾኗን እንዲኽ በማለት ገልጾታል፤ ‹‹ማንኛውም በንጉሥ የሚላክ የሐላፊነት ግርማ በቤተ መንግሥቱ ደጅ እንደሚያልፍ፤ ከሰማይ ወደ ዓለም የሚላክ የእግዚአብሔር ጸጋም በማርያም እጅ ያልፋል፤ በዚኽም የሰማይ ደጅ ትባላለች፤ ምክንያቱም ማንም በሷ በኩል ሳያልፍ ወደተባረከው መንግሥት አይኼድምና›› በማለት ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝባት መሰላላችን፣ ከእሱ ጋርም በምልጃዋ የምንታረቅባት የሰማይ ደጃፋችን መኾኗን አስተምሯል፡፡

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በያዕቆብ አንደበት የሰማይ ደጅ ተብሎ የተመሰከረላት ስለ መኾኗ በአርጋኖን መጽሐፉ ‹‹ተፈሥሒ ኦ ቤቴል እንተ ተሰምየት ኆኅተ ለሰማይ እምአፈ ያዕቆብ እስራኤል›› (እስራኤል በተባለ በያዕቆብ አንደበት የሰማይ ደጃፍ የተባለች ቤቴል ሆይ ደስ ይበልሽ)[80] በማለት ሲያመሰግናት፤ የመንፈስ ቅዱስ እንዚራ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በቀዳሚት ውዳሴ ማርያም መጽሐፉ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስለኾነችው ያዕቆብ በፍኖተ ሎዛ ስላያት የወርቅ መሰላል ሲገልጽ ‹‹*አንቲ ውእቱ ሰዋስው ዘርእየ ያዕቆብ እግዚአብሔር ላዕሌሁ እስመ ጾርኪ በከርሥኪ ኀቱም ዘኢየትዐወቅ እምኵለሄ ኮንኪ ለነ ሰአሊተ ኀበ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘተሰብአ እምኔኪ በእንተ መድኀኒትነ*›› (እግዚአብሔር በላይዋ ተቀምጦባት ያዕቆብ ያያት መሰላል አንቺ ነሽ፤ በኹሉ በኩል የማይመረመር እርሱን ተፈትሖ

79. ይዌድስዋ መላእክት፤ ቍ ፫
80. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ አርጋኖን ዘነሙስ ፬፥፲፱





በሌለበት ማሕፀንሽ ተሸክመሽዋልና፤ እኛን ስለማዳን ካንቺ ሰው በኾነ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ አማላጅ ኾንሽን) በማለት በምልጃዋ ከልጇ ጋር የምንታረቅባት እውነተኛ መሰላላችን መኾኗን አስተምሯል፡፡

ሊቁ አባ ሕርያቆስም ‹‹ወሰዋስዊሁ ለያዕቆብ›› (የያዕቆብ መሰላል አንቺ ነሽ) ብሎ በቅዳሴው በቍ፴፪ ላይ ሲያመሰግናት፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ሰዋስወ ወርቅ አንቲ ዘብኪ የዐርጉ ወይወርዱ ለልዑል መላእክቲሁ*

*ዘነጸረኪ ያዕቆብ አመ ተኀጥአ እምገጸ እኁሁ››*

(ያዕቆብ ከወንድሙ ፊት በኮበለለ ጊዜ የልዑል መላእክቱ ባንቺ ሲወጡ ሲወርዱ ያየሽ የወርቅ መሰላል አንቺ ነሽ)[81] በማለት ምስጢሩን አጉልቶ ተናግሯል፡፡

## የበረሓ እንኮይ

የኹላችን እናት ቅድስት ድንግል ማርያም የስንዴ አዝመራ በሚታጨድበት ወራት ከዱር ሮቤል ያገኛት እንኮይ ምሳሌዋ ነው (ዘፍ ፴፥፲፬-፲፰)፡፡ ይኸውም የያዕቆብ የበኵር ልጅ የኾነው ሮቤል ስንዴ በሚታጨድበት ወራት በእርሻ ውስጥ እንኮይን አግኝቶ መውለድን ላቆመች ለእናቱ ለልያ አመጣላት፤ ራሔልም አይታ እኅቷ ልያን ልጇ ሮቤል ያመጣላትን እንኮይ እንድትሰጣት ስትጠይቃት ልያ ልትሰጣት ፈቃደኛ ባለመኾኗ፤ ያን ጊዜ ራሔል እኅቷ ልያን ወደ ያዕቆብ እንድትኼድና በባሏ ምትክ እንኮዩን እንድትሰጣት ጠየቀቻት፤ እሷም በቀረበላት ምርጫ ተስማምታ እንኮዩን ከሰጠቻት በኋላ ወደ ያዕቆብ ኼዳ ተስፋዋን ያለመለመ ሐዘኗን ወደ ደስታ የለወጠ ወንድ ልጅ ፀንሳ ወልዳለች፤ ልጇም በእንኮይ የተገዛ ዋጋ በመኾኑ ስሙን እግዚአብሔር ዋጋዬን ሰጠኝ ስትል ይሳኮር ብላዋለች፡፡

ልጅ መውለድን አቁማ ፍሬ በማጣት በሐዘን የነበረችው ይኸቺ ልያ፤ በእንኮዩ ምክንያት ተስፋዋ ለምልሞ፤ የእንኮይ ዋጋ ብላ ስም ያወጣችለት ደስ የምትሰኝበትን የማሕፀኗ ፍሬ ልጅን እንዳገኘች ኹሉ፤ ለኆሺሕቷ ዘመን ከልጅነት ጸጋ ተለይተው፤ በመንጸፈ ደይን ወድቀው፤ በእግረ አጋንንት

81. እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 2



www.ethiopianorthodox.org

ተረግጠው፤ የሃይማኖት የምግባር ፍሬ ከማፍራት ርቀው፤ በሐዘን በቀቢጸ ተስፋ ለነበሩ ለሰው ልጆች፤ አምላከ ነዳያን ወተስፋ ቅቡጻን የተባለ አካላዊ ቃል ክርስቶስ በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ ንጽሕት ከኾነች ከቅድስት ድንግል ተወልዶ ልጅነትን በመመለሱ፤ ምእመናን ከገኑ በፈለሰ ማየ ገቦ በጥምቀት ተወልደው የሃይማኖት የምግባር ፍሬን የሚያፈሩ ኾነዋልና ቅድስት ድንግል ማርያምን፤ ሊቃውንት ሮቤል ባገኛት በእንኮይ ዕንጨት መስለው አስተምረዋል።

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተባለው ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኸነን ልዩ ምስጢር ሲያብራራ ‹‹ዕፀ ኮል እንከ እሰምየኪ፤ እስመ አጽለልኪ ታሕተ ጽላሎትኪ ፈቲውየ፤ ወጽጌ ድንግልናኪ ምዕዞ ለአንፍየ፤ ወፍሬ ንጽሕኪ ጥዕሞ ለጉርዔየ፤ ከመ ዐስበ ኮል ዘአዕተወ ሮቤል እምሐቅል ለልያ እሙ ተፀንሰ ይሳኮር ወልደ ያዕቆብ እስራኤል፤ ወስመ ይሳከር ዐስብየ ብሂል፤ ወከማሁ በዐስበ ደመ ፍሬ ከርሥኪ ዘዐጸርዎ ዕብራውያን በሊቶስጥሮስ መካን፤ ተፀንሱ መሃይምናን እምቅድስት ቤተክርስቲያን ዘተመርዐዋ ወልድኪ እግዚእ ወመድኅን›› (እንግዲኽ የእንኮይ ዕንጨት እልሻለኁ፤ ወድጄ በጥላሽ ሥር ተጠልያለኹና፤ የድንግልናሽ አበባ ኢየሱስ ክርስቶስም ለአፍንጫዬ ሽተተው፤ የንጽሕናሽ ፍሬ አካላዊ ቃልሃ˙ ለጉሮሮዬ ጣፈጠው፤ ሮቤል ለእናቱ ለልያ ከበረሓ እንዳገባው እንኮይ ዋጋ፡ እስራኤል የተባለ የያዕቆብ ልጅ ይሳኮር ተፀነሰ፤ የይሳኮር ስም ትርጓሜው የእንኮይ ዋጋ ማለት ነው። እንዲኹም ሊቶስጥራ በሚባል ቦታ አይሁድ በጠመቁት በማሕፀንሽ ፍሬ ደም ዋጋ ጌታችን መድኀኒታችን ልጅሽ ከተሞሸረባት ቅድስት ቤተክርስቲያን ምእመናን ተፀነሱ)[82] በማለት በጥልቀት አብራርቷል።

ይኸው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ምንም ዐይነት የኀጢአት ምክንያት ያላገኛት በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ የነጻች ቅድስት ድንግል ማርያም ብቻ ናትና፤ ዋዕየ ፀሓይ ባላቃጠላት ነፋስ ባላበላሻት የሮቤል እንኮይ መስሎ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ እግዝእትየ ማርያም ኮለ ሐቅል ሥምርት ዘሀገረ ላባ*
*በኵረ እስራኤል ሮቤል በመዋዕለ ማእረር እንተ ረከባ*
*ዘኢያውዓያ ዋዕይ ወኢያድወያ ነፋስ ሰልቢ ባ››*

82. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ ፮፥፩





(እመቤቴ ማርያም ሆይ የባሕር ነፋስ ያላሰማማት ዋዕየ ፀሓይም ያላቃጠላት፤ የ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል አለቃ (የያዕቆብ የበኵር ልጅ) ሮቤል በአዝመራ ዘመን ያገኛት፤ የስመረች የላባ ሀገር የበረሓ እንኮይ ነሽ)[83] በማለት አመስግኗታል።

## የያዕቆብ በትር

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ያዕቆብ በገንዳው አጠገብ ባስቀመጣቸው በትሮች ትመሰላለች (ዘፍ ፴፥፴፯-፵፪)።ይኸውም ያዕቆብ በጎቹን ከላባ በጎች ለመለየት የራሱ ለማድረግ በማሰብ ልብን፣ ለውዝ፣ ኤርሞን የሚባሉ ሦስት በትሮች ወስዶ ኹሉቱን ጨርሶ ልጦ፤ አንዱን ዝንጉርጉር አድርጎ፤ በጎቹ ውሃውን በሚጠጡበት በገንዳው ውስጥ አድርጓቸዋል። ከዚያም በጎቹ ውሃ ሲጠጡ በመጡ ጊዜ በትሮችን አስመስለው ፀንሰው ሽመልመሌ መሳይና ዝንጉርጉር ነቍጣም ያለበቱን ወልደዋል። ይኸውም በፀሓይ ብርሃን አማካይነት የበትሩ ጥላ ውሃው ላይ ያርፋል፤ በጎቹም ያነን እያዩ ሲጠጡ እንስሳዊ ፈቃድ ይነሣባቸዋል፤ ያን ጊዜ አውራዎቹን ይለቃቸዋል፤ እነዚያም በዚያ አምሳል ፀንሰው በዚያ በትር አምሳል ወልደዋል። ከዚያም ያዕቆብ ሽመልመሌ መሳይ፣ ዝንጉርጉር፣ ነቍጣም ኹነው የተወለዱትን የበጎቹን መንጋ ለብቻቸው እየለየ አቆማቸው እንጂ ከላባ በጎች ጋር አላገናኛቸውም፤ ዳግመኛም በጎቹ በሚፀንሱበት ወራት በበትሮቹን አምሳል ይፀንሱ ዘንድ እሊያን በትሮቹ በገንዳው ውስጥ በበጎቹ ፊት ለፊት ሲያኖራቸው፤ በጎቹ ከወለዱ በኋላ ግን እነዚያን በትሮች በገንዳው ውስጥ አያኖራቸውም ነበር፤ በመጨረሻም ምልክት ያላቸው ብርቱዎቹ በጎች ኹሉ ለያዕቆብ ሲኾኑ ምልክት የሌላቸው ደካሞቹ በጎች ግን ለላባ ኾነዋል።

ይኽም ለጊዜው ቢደረግም፤ ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር። ሦስቱ በትሮች የሥላሴ፤ የተላጡት የአብና የመንፈስ ቅዱስ፤ ቅጥልጥል የኾነው የወልድ አምሳል አምላክ ወሰብእ ነውና (ዮሐ ፩፥፲፬፤ ዕብ ፪፥፲፯)፤ በጎቹ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ የምእመናን፤ ውሃው የጥምቀት፤ አውራዎቹ የመምሕራን የቀሳውስት ምሳሌ ሲኾኑ፤ በጎቹ በትሮቹን እየመሰሉ እንደተወለዱ ኹሉ ምእመናንም በጥምቀት ምክንያት ከሥላሴ ይወለዳሉ (ማቴ

83. እንዚራ ስብሐት ገጽ 38



www.ethiopianorthodox.org

፳፰+፲፱፤ ማር ፲፮+፲፯፤ ዮሐ ፫+፫- ፰፤ ፲+፩- ፲፯፤ ፳፩+፲፭- ፲፯)፤

ይኸነንም አባ ስብሐት ለአብ በመጽሐፉ ሲገልጽ ‹‹በአብትረ ያዕቆብ በርሀ ሥላሴክሙ ፀሐይ፤ ወተመሰሉ ሰብአ ዐይን አባግዐ ላባ ወማይ ለኀበ አባግዐ ዘዮም ወጥምቀት ዐባይ›› (አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ ፀሐይ ሦስትነታችኹ በያዕቆብ በትሮች ላይ በራ፤ የላባ በጎችና ውሃም በስለላ ሰዎች ተመሰሉ፤ በምእመናን በሚመሰሉ በዛሬዎቹ በጎችና በታላቂቱ ጥምቀት ዘንድ)[84] በማለት ገልጾታል። ዳግመኛም በትር የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ሦስቱን በትሮች አይተው ፍሬ ያፈሩ በጎች በሦስት ወገን ማለትም ንጹሐ ሥጋን፤ ንጹሐ ነፍስን፤ ንጽሐ ልቡናን አስተባብራ በያዘች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን አማላጅነት የጽድቅ ፍሬን የሚያፈሩ የክርስቲያኖች ምሳሌ ናቸው (መዝ ፺፩+፱- ፲፯፤ መዝ ፹፯+፩- ፯፤ መዝ ፻፴፩+፲፫- ፲፯፤ ኢሳ ፩+፱፤ ዮሐ ፲፱+፳፭- ፳፯)።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኸነን ምስጢር በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ሲያብራራ

*‹‹አንተ ውእቱ ዕፀ ከርካዕ ወበትረ ልብነት*
*ዘአንበረኪ ያዕቆብ በውስተ ገብላት፤*
*ከመ ይፅንሳ አባግዕ ወይለዳ በትእምርት››*

(በጎች ፀንሰው በምልክት እንዲወልዱ ያዕቆብ በገንዳዎቹ ውስጥ ያኖረሽ የሎሚ ዕንጨትና የልብን በትር አንቺ ነሽ)[85] በማለት አባግዕ ምእመናን በምልጃዋ ከሞተ ነፍስ የሚጠብቁባት የጽድቅ ፍሬን የሚያፈሩባት አማናዊት በትርነቷን አጒልቶ ገልጾታል።

በዚኽም ያዕቆብ በጌታ ሲመሰል ላባ በዲያብሎስ ተመስሏል፤ ይኸውም ብርቱዎችና ምልክት ያላቸው በጎች ለያዕቆብ እንደኾኑ፤ በሥላሴ ስም ተጠምቀው ሀብተ ውልድና ስመ ክርስትና ያላቸው በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን አማላጅነት ያመኑ ምእመናን ኹሉ ለእግዚአብሔር ናቸው (መዝ ፺፩+፱፤ መሐ ፯+፱-፲፤ ኢሳ ፶፱+፳፫፤ ሚል ፬+፲፪፤ ሉቃ ፩+፵፰)፤ ምልክት የሌላቸው ደካሞቹ ለላባ እንደኾኑ ሀብተ ውልድና ስመ ክርስትና የሌላቸው <u>የቅድስት ድንግል ማርያምን አማላጅነት</u> የሚቃወሙ ፀረ ማርያም መናፍቃን

84. አባ ስብሐት ለአብ፤ መልክአ ሥላሴ፤
85. አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 46





የዲያብሎስ የገሃነመ እሳት ፈንታ ናቸው (መዝ ፻፳፰+፯-፰፤ ራእ ፲፪+፬-፯፤ ፲፫-፲፯፤ ራእ ፲፫+፯)።

ኢትዮጵያዊዉ የዜማ ሊቅ ቅዱስ ያሬድም ይኸቺ የያዕቆብ በትር በእውነት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሊ እንደኾነችና ዳግመኛም በትር እመቤታችን ከነገደ ዕሴይ ተገኝታ ጽጌ ክርስቶስን እንደምትወልድ ኢሳይያስ ከተናገረው የትንቢት ቃል ጋር በማገናኘት በድጓው ላይ ‹‹…መንክር ተአምሪሁ ለመድኀኒነ በከመ ወፅአት በትር እምሥርወ ዕሴይ በአምሳለ በትረ ያዕቆብ በዘይርዒ አባግዒሁ ይእቲኬ ማርያም ይእቲ፤ ወበእንተ ዘይቤ ትወፅእ በትር ወየዐርግ ጽጌ ውእቱኬ ዋሕድ፤ ውእቱኬ ወልደ አምላክ ውእቱ›› (… በጎቹን በሚጠብቅበት ገንዘብ በያዕቆብ በትር አምሳል፤ ከዕሴይ ባሕርይ በትር እንደወጣች የመድኀኒታችን ተአምሩ ድንቅ ነው፤ ያቺውም በትር ርሷ ድንግል ማርያም ናት፤ በትር ትወጣለች አበባም ከእርሷ ይወጣል ብሎ የተናገረው ርሱ አንድ ነው፤ ያውም ወልደ አምላክ ነው)[86] በማለት እየራቀቀና እያመሳጠረ ተንትኖታል።

<u>የያዕቆብ ትግል</u>

የ፲፪ቱ ነገደ እስራኤል አባት ያዕቆብ እስከሚነጋ ድረስ ከጌታ ጋር የታገለው የፍቅር ትግል በኋላ ዘመን አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም የሚወለደውን ልደት ያመለክታል (ዘፍ ፴፪+፳፬-፴)።

ይኸ ያዕቆብ መላ ቤተሰቦቹን ይዞ የያቦቅን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ መላዎቹን ጓዙን ሸኝቶ እሱ ከዚያ ብቻውን ባደረ ጊዜ፤ ጌታ በአምሳለ ብእሲ ታይቶ ሲታገለው ዐደረ፤ ታግሎም እንደማይጥለው ባየ ጊዜ ሊበሉት የተከለከለውን ሥርዐት የተሠራበትን የጭኑን ሹልዳ ቢነካው የያዕቆብ ሹልዳ ደነዘዘ። ሲነጋም ሌሊቱ ሲነጋ አቅላልቶአልና ልቀቀኝ አለው፤ ያን ጊዜ ያዕቆብ ጌታን ካልባረከኝ አልለቅኽም አለ፤ ጌታም የጀግና ስም ይጠየቃልና አከብርኽ እመርቅኽ ዘንድ ስምኽ ማነው? አለው እሱም ስሜንስ ንገረኝ ካልከኝ ያዕቆብ ነው አለ፤ እንግዲኽ ወዲኽ ስምኽ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ጋር መታገልን ከላባም ጋር መከራከርን ችለኻልና ብሎታል።

86. ቅዱስ ያሬድ፤መጽሐፈ ድጓ



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ያዕቆብ ጌታን ስምኽን ንገረኝ ባለው ጊዜ ‹‹ለምንት ለከ ትሴአል ስምየ እስመ መድምም ውእቱ›› (ስሜ ድንቅ ነውና ላታውቀው ስሜን ለምን ትጠይቀኛለኽ) ብሎ ያዕቆብን ባርኮታል፡፡

ይኽ የጌታ ስም ድንቅ እንጂ ሊመረመር የማይችል መኾኑን አረጋዊ መንፈሳዊ በድርሳኑ ላይ ‹‹ምንተኑ እሰምየከ ኦ እግዚእየ ወኢየአምር ዘእብል ለእመ ሰመይኩከ አምላከ፤ ናሁ ትብል አልብየ ስም፡፡ ወይእዜኒ ኵሎሙ አስማት ወባህላት ርሑቃን እምኔከ ኦ ክቡር ወዐቢይ ምንተኑ እሰምየከ ይእዜ ወበመኑ አስተማስለከ ስመ ክሡተ ወሀብከ በዘይትፌሥሑ ኀሣሥያኒከ ወይሰብሑ ዘቦሙ ኵሉ ሰብእ የአምረከ›› (አቤቱ በምን ስም እጠራኻለኹ? አንተን የምጠራበት ስም አላውቀውም፤ አምላክ ብልኽ ስም የለኝም የባሕርይ ስሜ አይታወቅም ትለኛለኽ፤ እነኾም እነዚኽ ኹሉ ስሞችና አባባሎች ከአንተ የራቁ ናቸው፡፡ ክቡር፣ ታላቅ፣ ገናና ሆይ ምን ብዬ እጠራኻለኹ? ፀምንስ እመስልኻለኹ? አንተን የሚሹ የሚፈልጉኽ ደስ በሚላቸው ኹኔታ በሚያመሰግኑኽ ይዞታ የተገለጸ ስምኽን ሰጥተኻል፡፡ በእነዚኽም ሰው ኹሉ ያውቅኻል)[87] በማለት ስሙ ሊታወቅ የማይቿል ድንቅ መኾኑን አስተምሯል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅም የዕብራውያን መልእክትን በተረጐመበት ድርሳኑ ‹‹እስመ ሶበ ኢረከበ ስመ ዘይኤምር ኀበ ባሕርይሁ ብህለ በዝንቱ አስማተ እስመ ዕበይ ወስብሐት ኢይኤምሩ ኀበ ውእቱ ስም ዘፈቀደ ይገብሮ ወባሕቱ ስእነ ረኪቦቶ፡፡ በከመ እቤ ቀዳሚ ከመ ንሕነ ንኔሊ በእንተ ብዙኀ ግብራቲሁ ወንስእን ፈክሮ ወነገረ በእንቲአሃ እወ ካዕበ ወኢገ ስም ዘውእቱ ብሂለ እግዚአብሔር ኢይኤምር ኀበ ውእቱ ባሕርይ ወፍጹም ኢይትከሃል ይርከቡ ስሞ ለዝኩ ባሕርይ፣ ኢታንክር ኦ ፍቁር በእንተዝ ኀድግሰ ለባሕርየ እግዚአብሔር ልዑል፡፡ ለመልአክኒ ጥቀ ኢይትረከብ ስመ ባሕርይሁ ወበእንተ ነፍስኒ ከማሁ ይመስለኒ እስመ ብሂለ ነፍስ ኢይኤምር ኀበ ስመ ባሕርይሃ፡፡ ወአልቦ እንከ ስም ዘይትዐወቅ ለባሕርይሃ›› (ባሕርዩን የሚያመለክት ስም ባላገኘ ጊዜ በእነዚኽ ስሞች ተናገረ፤ ታላቅነትና ክብር ሊያወሳው ወደፈቀደው ወደዚያ ስም የሚያመለክት አይደለምና፤ ነገር ግን ሊያገኘው አልቻለም፤ ከዚኽ አስቀድሜ እንደተናገርኹ ብዙ በኾኑ ሥራዎቹ

87. አረጋዊ መንፈሳዊ፤ ድርሳን ፵፫ ገጽ ፻፶፱





እንደምናስብና መተርጐሙን ኾነ ስለዚያው መናገር እንደሚሳነን ኹሉ ነው፡፡አዎን ይኽም ስም እርሱም እግዚአብሔር የማለት ስም ወደዚኽ ባሕርይ አያመለክትም፤ ጨርሶም የዚኽን ባሕርይ ስም ያገኙት ዘንድ አይቻልም፡፡ አዎን ወዳጄ ሆይ ስለዚኽ አታድንቅ፤ የልዑል እግዚአብሔርንስ ባሕርይ እናቆይና የመልአክስ እንኳ የባሕርይ ስሙ ሊገኝ አይችልም፤ የነፍስንም ነገር እንደዚኹ ይመስለኛል፤ ነፍስ የማለት ትርጉም የባሕርይዋን ስም አያመለክትምና ፈጽሞም ለባሕርይዋ የሚታወቅ ስም የለም)[88] በማለት በጥልቀት የስሙን ነገር አስተምሯል፡፡

በመኾኑም ልዑል አምላክ ለያዕቆብም ‹‹ስሜን ለምን ትጠይቀኛለኽ›› ማለቱ ይኽነን ምስጢር የሚያመለክት ነበር፤ ስለኾነም ያዕቆብ እግዚአብሔር የተገለጸበትን ያንን ቦታ፤ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየኹት ሲል፤ ራእየ እግዚአብሔር (ጵኒኤል) ብሎ ጠርቶታል፡፡

ይኽ ለጊዜው ቢደረግም ለኋላው ግን ምሳሌ ነው፤ ይኸውም ጌታ ከያዕቆብ ጋር መታገሉ በረድኤት እቀርብኻለው አልለይኽም ሲሰው ሲኾን፤ በውስጥ ኾኖ ጌታ ያዕቆብን ማስጨነቁ እኔን ብትጥል እኔም አንተን አስጨንቅኻለኹ ማለቱ ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን መታገል ደረት ለደረት ገጥሞ እንደኾነ ኹሉ ከሥጋኽ ሥጋ ከነፍስኽ ነፍስ ነሥቼ አካልኽን አካል ባሕርይኽን ባሕርይ አድርጌ አድንኻለኹ ብሎ በአብራኩ ካለች ከቅድስት ድንግል ማርያም የመወለዱን ምስጢር ሲገልጽለት ነበር፡፡

ሊቃውንት ይኽነን ምስጢር ሲገልጹ ‹‹ርእዩኬ ወነጽሩ ዘከመ ሠጽአ ነገረ ሥጋዌሁ ለወልደ አምላክ ዐረፍተ በዲበ ዐረፍት ወዘከመ ተዐገሎ ለያዕቆብ ዘሀሎ ይሠግ እምኔሁ፡፡ ወዘከመ ይቤሎ እንከሰ ኢይኩን ስምከ ያዕቆብ አላ ይኩን ስምከ እስራኤል አእማሮ ከመ ትወጽእ እምሐቌሁ ወለተ እስራኤል እንተ ይእቲ እግዝእትነ ማርያም ዘተሰብአ እምኔሃ ቃለ አብ እስመ ኵሉ ዘተነግረ በእንተ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል በክልኤ ማርያም ወላዲተ አምላክ›› (የአምላክ ልጅ ሰው የመኾኑ ነገር ደረጃ በደረጃ መምጣቱንና ከዚኽ ከያዕቆብ ወገን ሰው መኾኑን ያጠይቀው ዘንድ ያዕቆብን እንደታገለው ተመልከቱ፡፡ የአብ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስ ነሥቶ ሰው የኾነ በእውነት ወለተ እስራኤል የተባለች እመቤታችን ድንግል ማርያም ከእሱ

88. ድርሳን ዘዮሐንስ አፈ ወርቅ ፤ምዕ ፴፱፥፵



www.ethiopianorthodox.org

አብራክ የምትከፈል መኾኑን ሲያስረዳው፤ እንግዲኽ ወዲኽ ስምኽ እስራኤል ይባላል እንጂ ያዕቆብ አይባል ብሎ የሠየመውን አምላካዊ ሥያሜ አስተውሉ፤ ይኽ ኹሉ የተነገረው ትንቢት የተሰጠው ተስፋ አምላክን በወለደች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ድንግል ማርያም ይፈጸም ዘንድ አለውና)[89] በማለት በስፋትና በጥልቀት ምስጢሩን ተንትነውታል(ሮሜ ፱፥፲፩-፲፪)።

ይኽ በእግዚአብሔር የተባረከ የዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል አባት በመጨረሻው ዘመን ልጆቹን ሰብስቦ በኋለኛው ዘመን የሚኾኑትንና የሚያገኛቸውን ነግሮ ባርኳቸዋል (ዘፍ ፵፱፥፩-፳፱)። በተለይ ክብር ይግባውና ቅድመ ዓለም ከአብ አካል ዘእም አካል ባሕርይ ዘእምባሕርይ የተወለደ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው አካላዊ ቃል፤ በኋለኛው ዘመን ከነገደ ይሁዳ ከተወለደች ከድንግል ማርያም የመወለዱን ነገር «… በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መኻከል ገዢ የኾነው እስኪመጣ ድረስ…» በማለት ጌታን በአንበሳ ደቦል እየመሰለ ሰፊ ትንቢት ተናግሯል (ዘፍ ፵፱፥፰-፲፪)። ይኸውም የተናገረው ሊፈጸም ዐማኑኤል ከነገደ ይሁዳ ከተወለደች ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ፤ ዲያብሎስን ድል ነሥቶ ለኹላችን ነጻነትን ሰጥቶ ናል፤ ይኽነንም ዮሐንስ በራእዩ ሲገልጽ «እነሆ ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቶታል» ሲል የሊቃናቱን ምስክርነት ተናግሯል (ራእ ፭፥፭)።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽ ትንቢት በእውነት ስለመፈጸሙ በመጽሐፉ ላይ «ያዕቆብ እስራኤል ምስለ ይሁዳ ወልዱ ይዌድሰኪ እስመ በላዕሌሁ ለወልድኪ ተፈጸመ በረከተ ዚኣሁ ዘባረኮ ለይሁዳ እንዘ ይብል፤ ይሁዳ ዕጓለ አንበሳ ዕርግ ወልድየ እምሕዝአትከ ሰከብከ ወኖምከ ከመ አንበሳ ወከመ ዕጓለ አንበሳ ተንሣእከ ወአልቦ ዘያነቅሖከ፤ እደዊከ ዲበ ዘባኖሙ ለጸላእትከ… (እስራኤል ያዕቆብም ከልጁ ከይሁዳ ጋር ያመሰግንሻል ፤እግዚአብሔር እንዲኽ ሲል የባረከው የርሱ በረከት በልጅሽ ተፈጽሟልና፤ የአንበሳ ደቦል ልጄ ሆይ ከዋሻኽ ወጣኽ፤ እንደ አንበሳ ፊጽመኽ ተኛኽ፤ እንደ አንበሳ ደቦልም ተነሣኽ፤ የሚያነቃኽ የለም፤ ክንድኽ በጠላቶችኽ ዣርባ ላይ ነው…)[90] በማለት የያዕቆብ ትንቢት በእውነት መፈጸሙን መስክሯል።

89. ተአምረ ማርያም፤ ገጽ ፷፰
90. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ ፲፱፥፲፰





በመኾኑም ከያዕቆብ ዘር የኾነችው የቅድስት ድንግል ማርያምን ሥጋ ይዋሐድ ዘንድ አካላዊ ቃል መውደዱንና ምእመናንን ለርስቱ ለመንግሥተ ሰማያት መምረጡን ክቡር ዳዊት በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝቶ በመዝ ፵፮፥፬ ላይ «ለርስቱ እኛን መረጠን፤ የወደደውን የያዕቆብን ውበት» በማለት ሲናገር የቢዖር ልጅ በለዓምም መርገሙ ወደ በረከት ተለውጦ አካላዊ ቃል ከያዕቆብ ወገን ከተገኘች ከቅድስት ድንግል ማርያም የሚወለድ መኾኑ ተገልጾለት «ኮከብ ይሠርቅ እምያዕቆብ» (ኮከብ ከያዕቆብ ይወጣል) ዘኍ ፳፬፥፲፯ በማለት ትንቢት ተናግሯል። ስለኾነም የሚያበራ የንጋት ኮከብ አምላካችንን ክርስቶስን የወለደችልን ናትና፤ እኛም እንደ አባታችን እንደ ቅዱስ ኤፍሬም «አንቲ ውእቱ ምሥራቅ ዘወጽአ እምኔኪ ኮከብ ብሩህ ዘነጸርዎ ቅዱሳን በፍሥሐ ወበሐሤት» (ቅዱሳን በፍጹም ደስታ ያዩት ኮከብ ካንቺ የተወለደ ምሥራቅ አንቺ ነሽ)[91] በማለት እናመሰግናታለን (ራእ ፳፪፥፲፮)።

## የያዕቆብ ጥንካሬና በረከት

ከአምላኩ ጋር የፍቅር ትግልን የታገለው እስራኤል የተባለው ያዕቆብ ልጁ ዮሴፍ ሲመጣ ተጠናክሮ ጸንቶ በርትቶ መነሣቱና ለልጆቹ የተናገረው ትንቢት ልዩ የዘመነ ሐዲስ ምስጢርን የያዘ መኾኑን ብዙ ሊቃውንት አስተም ረዋል (ዘፍ ፵፰፥፩-፪፤ ፵፱፥፩-፳፯)። ይኸውም ወንድሞቹ ዮሴፍን አባትኽ ያዕቆብ ደክሟል ብለው በነገሩት ጊዜ ወደ አባቱ ኼደ፤ ያን ጊዜ ለያዕቆብ ልጅኽ ዮሴፍ ወደ አንተ መጣ ብለው በነገሩት ጊዜ ወተንሥአ እስራኤል ወተንሥአ ነበረ ዲበ ምስካቡ ይላል ጥንካሬን አግኝቶ ተጽናንቶ ተነሥቶ ከአልጋው ላይ ተቀመጠ።

ይኸውም ምሳሌ ነው ያዕቆብ የአዳም፤ ዮሴፍ የወልደ እግዚአብሔር፤ እስራኤል የተባለ ያዕቆብ ዮሴፍ እስኪመጣ ድረስ መድከሙ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም እስኪወለድ ድረስ ድካመ ነፍስ አዳምን የማግኘቱ ምሳሌ ሲኾን፤ ኋላ ግን ያዕቆብ ዮሴፍ መጣ ባሉት ጊዜ ተበራትቶ መነሣቱ የዓለም መድኅኒት ክርስቶስ ከእመቤታችን በተወለደ ጊዜ ጽንዐ ነፍስን አግኝቶ የመጽናቱ የመበርታቱ የመዳኑ ምሳሌ መኾኑን መተርጕማን ገልጸውታል።

91. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘዐርብ



www.ethiopianorthodox.org

ከዚኽ በኋላ ያዕቆብ ልጆቹን፤ በኋላ ዘመን የሚያገኛቸኹን እንድነግራችኍ ተሰብሰቡ ብሎ ወደፊት የሚመጣውን ነገር ተናግሮ መውረሱ (ዘፍ ፵፱፥፩-፴፫)። ያዕቆብ የተናገራቸው ትንቢቶች እጅግ በጣም ብዙ የነገረ ሥጋዌ ምስጢርን የያዙ መኾናቸውን በርካቶች ሊቃውንት አስተምረዋል፤ በትምህርታቸውም እነዚኽን የያዕቆብ ትንቢቶች አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ የፈጸማቸው መኾኑን በጥልቀት ተንትነዋል፤ ኾኖም ግን ሊቃውንቱ ኹሉ ያመሰጠሩትን ምስጢር እጅጉን ከመብዛቱ አንጻር በዚኽ ጽሑፍ ማካተት ባልችልም ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ምስጢሩን ጠቅልሎ ያስተማረውን ትምህርት ብቻ ጠቅሼዋለኍ፤

*«ኦ ድንግል ኀሣሢቱ ለሮቤል እሞተ መርገም*
*አስተጋባኢተ ዝርወቶሙ ለስምዖን ወሌዊ እለ መተሩ ሥረዊሁ ለምድረ ሴኬም*
*ብዕለ ምስፍናሁ ለይሁዳ እጓለ አንበሳ ግሩም*
*ርስተ ዕረፍቱ ለይሳኮር ዐሰበ ኮለ ሐቅል ዘገዳም*
*መርሶ ማኅደር ዘዛብሎን ወበቀልተ ዕፍረት ዘንፍታሌም*
*ቅብዐ እገሪሁ ለአሴር ወዕበየ ጸጋሁ ለዮሴፍ በብሔረ ካም*
*ርሕበ በረከቱ ለጋድ ወማእምንተ ምድሩ ለብንያም*
*መብዝኂተ አዕላፊሁ ለምናሴ ወሀብተ ቡራኬሁ ለኤፍሬም»*

(ከመርገም ሞት የሮቤል ፈላጊው መሻቱ ድንግል ሆይ፤ የሴኬም ምድር ወገኖች ሥሮችን የቆራረጡ ሌዊንና ስምዖንን ከመበተን የምትሰበስቢ ነሽ፤ የሚያስፈራ የአንበሳ ደቦል የኾነ የይሁዳ የምስፍናው የንግሥናው ክብር ነሽ፤ የበረሓ እንኮይ ዋጋ የተባለ የይሳኮር የዕረፍቱ ርስት ነሽ፤ የዛብሎን የወደብ ማደሪያ፤ የንፍታሌም የሽቱ ዘንባባ ነሽ፤ የአሴር የእግሩ መቀባሻ ቅባት፤ በካም ርስትም የዮሴፍ የጸጋው ገናንነት ነሽ፤ የጋድም የበረከቱ ስፋት፣ የብንያም የታመነች (አስተማማኝ) ምድሩ ነሽ፤ የምናሴም የሰራዊት ብዛት፤ የኤፍሬምም የቡራኬው ጸጋ ነሽ)[92] በማለት እጅግ ጥልቅ የቅዱሳት መጻሕፍት ዕውቀት የነበረው ይኽ የነገረ መለኮት ምሁር፤ ታላቁን ምስጢር እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ

92 አባ ጊዮርጊስ፤እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 16





ጠቅልሎ ያስተማረው የነገረ ማርያም ትምህርት እጅግ አድርጎ የሚያስደንቅ ነው።

እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እርሱ ባለቤቱ ስለ እናቱ ከሥነ ፍጥረቱ አንሥቶ እስከ ያዕቆብ ድረስ የገለጸውን አምሳል እንዳየን፤ ከዚኽ ቀጥለን ከሙሴ ዠምሮ ሥጋዌውን እንዴት በብዙ ሕብረ ትንቢት እንዳናገረ በብዙ ሕብረ አምሳል እንደገለጠ እናያለን።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ኹለት
## ነገረ ማርያም በኦሪት ዘፀአት

### ዕፀ ጳጦስ

ሊቀ ነቢያት ሙሴ በደብረ ሲና የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነች ቊጥቋጦን ተመልክቷል። ይኸውም በዘፀ ፫፥፩-፫ ላይ ሙሴ በደብረ ኮሬብ የአማቱ የዮቶርን በጎች ሲጠብቅ ነበልባል ከሐመልማል ጋር ሐመልማል ከነበልባል ጋር ተውሕዶ፤ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥለው፤ ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው አይቷል። ይኸንንም ምስጢር ለመረዳት ወደዚያ ሲጠጋ እግዚአብሔር ከቊጥቋጦው ውስጥ እርሱን በመጥራት «ወደዚኽ አትቅረብ አንተ የቆምኽባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና፤ ጫማኽን ከእግርኽ አውጣ» (ዘፀ ፫፥፭፤ የሐዋ ፯፥፴-፴፬) በማለት አዞታል።

ለጊዜው ሐመልማል የእስራኤል ነበልባል የመከራቸው ምሳሌ ነው፤ ይኸውም ሐመልማሉ ነበልባሉን ያለማጥፋቱ እስራኤልም መከራውን ግብር ገብተን ቀኖና ይዘን እናርቀው ያለማለታቸውን፤ ነበልባሉ ሐመልማሉን ሳያቃጥል ማየቱ የግብጽ መከራ እስራኤልን ጨርሶ አላጠፋቸውምና ይኸንን ሲገልጽለት ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን ሙሴ ያየው የነበልባልና የሐመልማል ተዋሕዶ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ ምሳሌ መኾኑን ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስ በማብራራት አስተምሯል።

ይኸውም ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው ኹሉ፤ መለኮት ምልአቱን ስፋቱን ርቀቱን ሳይተው፤ ሥጋም ግዙፍነቱን ጠባቱን ሳይተው የመዋሐዳቸው አንድ አካል አንድ ባሕርይ የመኾናቸው ምሳሌ መኾኑን አስተምሯል።

ኢትዮጵያዊው ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽንን ምስጢር





ሲገልጽ «ኦ ዕፀ ጳጦስ መንፈሳዊት እንተ አግመረቶ ለእሳት እሳትኒ ዘእንበለ ጥፍአት፤ ወዕፅኒ ዘዕንበለ ውእየት፤ ፍኳሬ ዝ አምሳል ለትስብእተ ወልድ እንተ እምኔኪ ነሥአ ዘእንበለ ሚጠት ወወልጦት» (እሳቱን የቻለችው መንፈሳዊት ዕፀ ጳጦስ ሆይ እሳትነቱም ሳይጠፋ ዕንጨትነቷም ሳይቃጠል የዚኽም ትርጓሜው ሚጠት፤ ውላጤ ሳይኖርበት ወልድ ከአንቺ ለነሣው ትስብእት ምሳሌ ነው)[93] በማለት አመስጥሮታል።

ሶርያዊው ቅዱስ ኤፍሬምም ሙሴ በደብረ ሲና ያየው፤ ነበልባሉ የጌታችን፤ ሐመልማሉ የእመቤታችን ምሳሌ መኾኑን አስተምሯል። ይኸውም ነበልባሉ ሐመልማሉን እንዳላቃጠለው ኹሉ እሳተ መለኮት ጌታም ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ ባደረ ጊዜ ድንግል ማርያምን ባሕርየ መለኮቱ አላቃጠላትም፤ ሐመልማሉ ነበልባሉን እንዳላጠፋው ኹሉ ጌታም ከእመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው ቢኾንም ባሕርየ መለኮቱ አልተለወጠም፤ ይኽነንኑ ምስጢር ቅዱስ ኤፍሬም በነሙስ ምስጋናው ላይ «ዕፀ እንተ ርእየ ሙሴ በነደ እሳት ውስጥ ገዳም ወአዕጹቂሃ ኢትውዒ ትመስል ማርያም ድንግል ዘእንበለ ርኩስ ተሰብአ እምኔሃ ቃለ አብ ወኢያውዐያ እሳተ መለኮቱ ለድንግል እምድኅረ ወለደቶ ድንግልናሃ ተረክበ ወመለኮቱ ኢተወለጠ ኮነ ወልደ ዕጓለ እመሕያው አምላክ ዘበአማን መጽአ ወአድኅነነ» (መለወጥ የሌለባት ድንግል ማርያም ሙሴ በበረሓ በነደ እሳት ጫፎቿ ሳይቃጠሉ ያያት ዕፅን ትመስላለች፤ የአብ ቃል በርስዋ ሰው ኾኗልና ፤እሳተ መለኮቱ አላቃጠላትምና፤ ከወለደችውም በኋላ ድንግልናዋ አልተለወጠምና፤ ሰውም ቢኾን መለኮቱ አልተለወጠም በእውነት አምላክ ነውና፤ በእውነት አምላክ የኾነ እርሱ መጥቶ አዳነን) ሲል ገልጾታል።

ዳግመኛም ይኽ ሊቅ ለሙሴ በቊጥቋጦ መኻከል የተናገረው እሳተ መለኮት ጌታ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በጨርቅ ተጠቅልሎ ለሰብአ ሰገል መታየቱን ሲገልጽ «To carry the flame and how the flame dwelt in a moist womb...» (ነበልባሉን ለመሸከም በእርጥብ ማሕፀን ዐደረ፤ ነገር ግን ማሕፀኗ አልተቃጠለም፤ በኮሬብ የነበረው ቊጥቋጦ እግዚአብሔር ያደረባትን ነበልባል ሳይቃጠል እንደተሸከመ ኹሉ... ሙሴ በቊጥቋጦው መኻከል እሳቱን

93. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፲፩፥፲፬



www.ethiopianorthodox.org

ሲመለከት ምሳሌውን አይቶ ነበር፤ ይኸም ምሳሌ በሰብአ ሰገል ተብራራ ፤እሳትን በመጠቅለያ ተጠቅልሎ በተመለከቱት ጊዜ፤ ድምፅ ከቊጥቋጦው ውስጥ ወደ ሙሴ መጣ፤ የእግሩን ጫማ ያወልቅ ዘንድ ተናገረው፤ እንዲኹ የኮከብ ዝምታ ወደተቀደሰው ስፍራ ሰብአ ሰገልን መራቸው… ሙሴ እግዚአብሔርን ሲመለከት አልቻለም መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ነገር ግን ሰብአ ሰገል ሰው የኾነውን አምላክ ተመለከቱ፣ ዋሻው ሰማያትን ይወክላል፤ ሙሴም ሰብአ ሰገልን፤ ሰሚ (አድማጭ) በነቢያት (አለቃ) በሙሴና በፐርሺያ አለቆች በሰብአ ሰገል መኻከል ያለውን አንድነት ቢጠይቅ በዚኽ ሊያውቅ ይችላል)[94] በማለት ምስጢሩን በማራቀቅ አስተምሯል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በተመሳሳይ መልኩ ምስጢሩን ሲያብራራ ‹‹ዕፀ ጳጦስ እንኪ እሰምየኪ፤ እስመ እምዕፀ ጳጦስ አስተርአዮ ለሙሴ አምላከ አብርሃም አምላከ ይሥሐቅ ወያዕቆብ ወፈነዎ ኀበ ደቂቀ እስራኤል ከመ ይስብክ ሎሙ ግእዛነ እምቅኔ ግብርናተ ፈርዖን ወቃለ እግዚአብሔር ዘአስተርአየ እምኔኪ ፈነዎሙ ለሐዋርያት ውስተ ኵሉ አጽናፈ ዓለም ከመ ይስብኩ ሎሙ ግእዛነ እምቅኔ ግብርናተ ሰይጣን›› (ዕፀ ጳጦስ ብዬ እጠራሻለኊ፤ የአብርሃም የይሥሐቅና የያዕቆብ አምላክ ለሙሴ በዕፀ ጳጦስ ኾኖ ተገልጦለት ከፈርዖን ባርነት ነጻ የሚወጡበትን የምሥራች ይነግርላቸው ዘንድ ወደ እስራኤል ልጆች ልኮታልና፤ ከአንቺ የተገኘ የልዑል እግዚአብሔር አካላዊ ቃል ግን ሐዋርያትን ወደ ዓለም ኹሉ ዳርቻች ላካቸው ከሰይጣን ባርነት ነጻ መውጣትን ያስተምሯቸው ዘንድ)[95] በማለት ዕፀ ጳጦስንና ቅድስት ድንግል ማርያምን እያነጻጸረ አስተምሯል።

ከሊቃውንት መኻከል አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

*‹‹ተአምርኪ ማርያም ተሰብከ በኦሪት*
*አመ ተሰነሀውኪ ጳጦስ ምስለ መለኮት*
*ዘርእየኪ ሙሴ ሊቀ ነቢያት*
*ጸልልኒ በአዕጹቅኪ ሐመልማላዊት ዕፀት*
*ሦከ ኀጢአትየ ያውዒ ጽጌኪ እሳት››*

94. Bride of Light pp141-142
95. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘሰኑይ ፩፻፲፰-፲፱





(ጳጦስ ከመለኮት ጋር አንድ በኾነሽ ጊዜ ማርያም ሆይ ተአምርሽ በኦሪት ተሰበከ፤ ሊቀ ነቢያት ሙሴ ያየሽ ለምለሚቱ ቊጥቋጦ በቅርጫፎችሽ ጋርጂኝ፤ ሽፍኚኝ፤ እሳት አበባሽ እሾኽ ኀጢአቴን ያቃጥል ዘንድ)[96] በማለት ሙሴ በደብረ ሲና ያያት እሳተ መለኮት ጌታን የተሸከመች የአምላክ እናት ምሳሌ የመኾኗን ምስጢር አጕልተው አሳይተዋል።

ኢትዮጵያውያን ሊቃውንትም በነገረ ማርያም ስለዚኽ ምስጢር በስፋት ሲተነትኑ ‹‹ኦ እኁየ እስኩ ሀልዩ መኑ ዛቲ ይእቲ ዕፅ እንተ ርእየ ሙሴ በነደ እሳት ውስተ ገዳም ወአዕጹቂሃ ኢትውዒ ዘእንበለ እግዝእትነ ማርያም ድንግል ወላዲተ አምላክ ዳእሙ ዛቲ ይእቲ በጥይቅና። ወነበልባልሂ ዘእሳት ውእቱ ወልደ እግዚአብሔር ዘተሰብአ እምኔሃ እንተ ኢያውዐያ እሳተ መለኮቱ። ርእዩ ምስጢረ ምጽአተ ሥጋዌሁ ለወልደ እግዚአብሔር እስመ ከመዝ ትኳት ተአገሎ ለያዕቆብ በአርአያ ብእሲ ወሬዛ ይእዜኒ አስተርአየ አምሳለ ነበልባል በኀበ ዕፀ ጳጦስ ሐመልማላዊት ዘሲና (ወንድሞቼ ሆይ እስኪ አስተውሉ፤ ነደ እሳት ሰፍሮባት በነደ እሳት ተከባ ጫፎቿ ሳይቃጠሉ ሙሴ ያያት ያቺ ዕፅ አምላክን ከወለደች ከድንግል ማርያም በስተቀር በማን ትመሰላለች፤ በጎላ በተረዳ ነገር በእመቤታችን በድንግል ማርያም ትመሰላለች እንጂ። በእሷም ላይ የሰፈረው ነደ እሳት የመለኮቱ እሳትነት ሳያቃጥላት ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ ሰው የኾነ የእግዚአብሔርን ልጅን ይመስላል። እኹንም የወልደ እግዚአብሔርን ሰው የመኾን ምስጢር እንመልከት፤ አስቀድሞ ያዕቆብን በጎበዝ ሰው አምሳል እንደታገለው ኹሉ ዛሬም ደግሞ በለመለመች በሲና በረሓ እንጨት ላይ በነደ እሳት አምሳል ሰፍሮ ታይቷልና)[97] ሲሉ በጥልቀት አስተምረዋል።

ሊቁ ዮሐንስ ዘደማስቆ (፯፻፯-፯፻፵፱) ስለዚኽ ልዩ ምሳሌ ሲያብራራ ‹‹The burning bush was an image of God's mother…››( ዕፀ ጳጦስ የአምላክ እናት አምሳል ነበረች፤ ሙሴም ወደ እርሷ ሲቀርብ ሲል እግዚአብሔር ‹‹ወደዚኽ አትቅረብ አንተ የቆምኽባት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማኽን ከእግርኽ አውጣ›› አለው፤ እንግዲኽ ሙሴ የወላዲተ አምላክን ምሳሌ ያየባት መሬት የተቀደሰች ከኾነች፤ ምሳሌዋ ራሷ ምን ያኽል የተቀደሰች ትኾን፤

96. አባ ጽጌ ድንግል፤ ማሕሌተ ጽጌ፤ ቍ ፳፫
97. ተአምረ ማርያም፤ ገጽ ፳፪



www.ethiopianorthodox.org

ቅድስት ብቻ ሳትኾን ቅድስተ ቅዱሳን ናት ለማለት እደፍራለኹ)[98] በማለት ምስክርነቱን ሰጧል።

## ደመና ግብጽ፤ ደመና ሙሴ

ኹሉ የሚቻለው ልዑል እግዚአብሔር በግብጻውያን ላይ ከሃሊነቱን ለማሳየት «ወይረውድ እሳቱ ዲበ በረዱ ወበረዱ ዲበ እሳቱ» (በረዶም ነበር በበረዶም መኻከል እሳት ይቃጠል ነበር) (ዘፀ ፱፥፳፬)፤ በማለት እንደተጻፈ ድንቅ በኾነ ምስጢር እሳቱ በረዱን ሳያቃጥለው በረዱ እሳቱን ሳያጠፋው ኹለት ተቃራኒዎች ነገሮችን እሳትና በረድ እንደ ሰምና ፈትል ተስማምተው እንዲወርዱ አድርጓል፤ በተመሳሳይ መልኩ በዘመነ ሐዲስም እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምን ድንግልናዋ እናትነቷን፤ እናትነቷ ድንግልናዋን ሳይለውጠው እንደ እሳትና በረዶ ውሕደት ኹለቱን መስተፃርራን (የሚቃረኑ ነገሮችን) ማለትም እናትነትን ከድንግልና ድንግልናን ከእናትነት ጋር እንድታስተባብር አድርጓታል።

ታላቁ የቤተክርስትያን መምሕር ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ ለማንም ሴት ያልተሰጠ ለድንግል ማርያም ብቻ የተሰጠ ድንግልና ከእናትነት ጋር አስተባብራ ስለመገኘቷ ሲገልጽ «… ወሶበሂ ወለደቶ ዐቀበ ድንግልናሃ ዘእንበለ ርኩስ ከመ በዕንሳ መንክር ትኩን መራሂተ ለሃይማኖት ዐባይ» (…ክድንግል ተወለደ በወለደችውም ጊዜ ድንግልናዋን ያለመለወጥ አጸና፤ ድንቅ በሚኾን ዕንሷ ለደገኛው ሃይማኖት መሪን ትኾን ዘንድ)[99] በማለት ቅድስት ድንግል ማርያም አምላክን ስትወልድ ማኅተመ ድንግልናዋ እንዳልተለወጠ ጌታም ሰው ሲኾን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ፤ እሷ ድንግል ወእም (ድንግልም እናትም) ስትባል እንደምትኖር አካላዊ ቃል ክርስቶስም አምላክ ወሰብእ (ሰው የኾነ አምላክ) ሲባል የሚኖር የመኾኑን የተዋሕዶ ልዩ ምስጢርን ያወቅንባት የተረዳንባት እሷ ብቻ መኾኗን አስተምሯል።

ይኽ ብቻ ሳይኾን ቅድስት ድንግል ማርያም እናትነትን ከአገልጋይነት ጋር ደርባ መገኘት እና በድንግልና ሳለች ወተትን በማስገኘት ለማንም ሴት ያልተሰጠ ኹለቱን ተቃራኒዎች (መስተፃርራን) ነገሮች አስተባብራ በመገኘቷ

98. John of Damascus, On the Divine Image
99. ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ፤ ሃይማኖተ አበው፤ ምዕ ፷፯





የበረዶና የእሳት ውሕደት ምሳሌዋ መኾኑን በይበልጥ እንረዳለን።

ይኸውም እናትነትን ከአገልጋይነት የሚለውን ምስጢር ስንመለከት ድንግል ማርያምን መልአከ ብርሃን ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ አምላክን እንደምትወልድ የብሥራትን ቃል ባሰማት ጊዜ ነገሩን በእምነት ተቀብላ «ነየ ዓመተ እግዚአብሔር ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ» (እንሆኝ የጌታ አገልጋይ እንደቃልኽ ይኹንልኝ) ሉቃ ፩፥፴፰፤ በማለት የጌታ አገልጋይ መኾኗን መስክራለች፤ ኾኖም ግን እመቤታችን ፍጥረትን የሚገዛ፤ ፍጥረት ኹሉ የሚገዛለት የጌታ አገልጋይ ብቻ ሳትኾን እናቱ ልትኾነው ችላለችና፤ ይኽነን ኹለት ጸጋ አስተባብራ መገኘቷ «ምልዕተ ጸጋ» ያሰኛታል፤ ይኽነንም ምስጢር የቤተክርስቲያናችን የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድ «እንዘ ዓመቱ እሞ ረሰያ» (አገልጋዩ ስትኾን እናቱን አደረጋት)[100] በማለት እናትነትን ከአገል ጋይነት አስተባብራ የተገኘች መኾኗን አስተምሯል። ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በማግሰኞ ምስጋናው «ተፈሥሒ ኦ ማርያም እም ወዓመት» (እናትና አገልጋይ ማርያም ሆይ ደስ ይበልሽ) ሲል የተሰጣትን ጸጋ አድንቋል።

ዳግመኛም ለማንም ሴት ያልተሰጠውን የማይሰጠውን ወተትን ከድንግልና ጋር አስተባብሮ የመገኘትን ለድንግል ማርያም ብቻ ተደርጎላታል፤ ይኸውም መአስባትን (የወለዱ፤ ያገቡ) ሴቶች በመግቧቸው ወተትን ያስገኛሉ፤ ደናግልን ግን በመግቧቸው ወተት አያስገኙም፤ እመቤታችን ግን በድንግልና እያለች ከድንግልና ጡቶቿ ወተት ተገኝቷል፤ ይኽ ከድንግል ጡቶች ወተት መገኘት ዕፁብ ድንቅ ብሎ የጌታን ሥራ ከማድነቅ በስተቀር ቃል ከቶ ሊገልጸው አይቻለውም፤ ይበልጥ እጅጉን የሚደንቀው ግን ይኽ የድንግልና ጡቶቿን የጠባው (የተመገበው) ፍጥረትን ኹሉ በገዘናብ አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግበው የዓለም አስገኝ ፈጣሪያችን ክርስቶስ መኾኑ ነው፤ ስለዚኽም ቅድስት ድንግል ማርያም መጋቢዋንና ፍጥረታትን የሚመግብ አምላክን በክንዷ ታቅፋ የድንግልና ጡቶቿን የመገበች መኾኗ እጅግ አስደናቂ ነው።

ይኽነን ምስጢር ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በልደት ድርሳኑ በአድናቆት ኹሉን ለሚመግብ ለልጇ እናቱ ናትና ጡቶቿን መመገቧ እሱም ፈጣሪዋ ነውና ለድንግል እናቱ ወተትን መስጠቱን በሰፊው እያብራራ አስተምሯል።[101] ሊቁ

100. ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ፤ ገጽ ፻፶፫፪
101. Ephrem the Syrian, On the Nativity



www.ethiopianorthodox.org

አባ ሕርያቆስም ኹለት ተቃራኒዎች ነገሮችን ማለት እመቤትነት ከአገልጋይነት፣ አገልጋይነት ከእናትነት፣ ድንግልናና ወተትን ባንድ ላይ አስተባብራ መገኘቷ ከኀሊና ኹሉ የራቀ አድናቆት የሚገባው መኾኑን በቅዳሴው ላይ ‹‹ኦ ከዊነ እም ዘምስለ ዓመተ ጽበተ ከርሥ ዘምስለ ርሕብ ዕንስ እንበለ ሩካቤ ከመ ንህብ ዘእምቃል ንባብ ሐሊብ ምስለ ድንግልና ዕሙር፤ ወሶበ እኄሊ ዘንተ ይፈቅድ ኀሊናየ ይጽብት ዕሙቀ አብሕርቲሁ ለወልድኪ ወያመዐብሎ መዋግደ ምስዋራቲሁ ለፍቁርኪ›› (ከገረድነት ጋር እናትነት እንደምን ያለ ነው? ከስፋት ጋር የኾድ መጥበብ፤ እንደ ንብ ያለሩካቤ ከቃል ድምፅ የተገኘ ዕንስ፤ ከድንግልና ጋር አንድ የኾነ ሐሊብ (ወተት)፤ ይኽነንም ባሰብኩ ጊዜ ኀሊናየ የልጅሽን የባሕሩን ጥልቅነት ሊዋኝ ይወዳል፤ የወዳጅሽ የመሰወሪያው ማዕበልም ያማታዋል)[102] በማለት ለድንግል ማርያም የተሰጣት ይኽ ልዩና ድንቅ ጸጋ ከአእምሮ በላይ መኾኑን ገልጿታል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በዚኽ ምስጢር ደመና ግብጽ ተብላ እንደተጠቀሰች ኹሉ ዳግመኛም ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን የሕይወት ምግብ መና ወልደ እግዚአብሔርን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን በመኾኗ ለእስራኤል ልጆች መናን ይዛ በተገኘች ደመና በርካቶች ሊቃውንት በመመሰል ደመና ሙሴ የሚል ሥያሜን ሰጥተዋታል (ዘፀ ፲፮፥፲፫-፳፫)።

ኾኖም ግን ያቺ በምድረ በዳ መና የያዘች ደመና እስራኤልን ከሞት ልታድን ከቶ አልተቻላትም፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የወለደችው ግን ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የዘላለም ሕይወት ሊኾነን የሰጠን አምላካችን ክርስቶስን ነው። ራሱ ጌታም በዮሐንስ ወንጌል ምዕ ፮፥፵፰-፶፩ ላይ ‹‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ አባቶቻችኹ በምድረ በዳ መናን በሉ ሞቱም፤ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አኹን የወረደ እንጀራ ይኽ ነው፤ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚኽ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ስለዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው›› በማለት አስተምሯል።

የመናፍቃን መዶሻ የተባለው ሊቁ ቅዱስ ቄርሎስም ይኽነን ቃል

102. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤ ቊ፲፫





በጥልቀት ሲተረጕመው ‹‹ወአማንሰ ኢወረደ እምሰማይ ሥጋሁ አላ እምድንግል ውእቱ ዘከመ ጽሑፍ ወቃልኒ ኢይትበላዕ አላ በአሐቲ ትድምርት አስተጋቢዖ ምስጢረ ያርኢ ከመ ይነግረነ በእልፍ ትእልፊት›› (በእውነት ሥጋው ከሰማይ የወረደ አይደለም እንደተጻፈ፤ ከድንግል ባሕርይ የተገኘ ነው እንጂ፤ ቃል በባሕርዩ አይበላምና፤ በእልፍና ትእልፊት ምሥክር እንደሚነግረን በአንዲት ተዋሕዶ አዋሕዶ ምስጢርን ያሳየን ዘንድ ነው እንጂ)[103] በማለት አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የዘላለም ምግብ ሊኾነን መስጠቱን አስተምሯል።

ታላቁ የቤተክርስትያናችን ሊቅ የዜማ አባት ቅዱስ ያሬድም በመጽሐፈ ድጓው ላይ ‹‹ዓይ ይእቲ ዛቲ ቀሊል ደመና ፤እንተ ትፀውር መና፤ ማርያም ይእቲ ንጽሕት በድንግልና አልባቲ ሙስና›› (መናን የተሸከመች ፈጣን ደመና የትኛዪቱ ናት? ነውር ነቀፋ የሌለባት በድንግልና ንጽሕት የምትኾን ማርያም ናት!)[104] በማለት ደመናነቷን ሲተረጕመው፤ሌላው ኢትዮጵያዊ የቤተክርስትያናችን የነገረ መለኮት ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹አንቲ ውእቱ ደመና ዘአዝነምኪ ጊዜ ርደተ ኀቦ*

*አያየተ ኵሉ መፍቅድ መጣዕመ ፍትታት ዘቦ››*

የፍላጎት ኹሉ ወለላ ማርንና የነበረ የመና ቁርስራሽ ጣዕምን፤ ውርጭ በሚወርድበት ጊዜ ያዘነምሽ ደመና አንቺ ነሽ)[105] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ አስተምሯል።

## ሥርጕት (የተሸለመች) ደመና ፤ የሙሴ በትር

የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም እስራኤላውያንን በመራች ደመና እና ሙሴ የኤርትራን ባሕር በከፈለባት በትሩ ትመሰላለች (ዘፀ ፲፫፥፳፩፤ ዘፀ ፲፬፥፩-፴፩)። እስራኤላውያን ለ፬፻፴ ዓመት መከራን ከተቀበሉባት ከግብጽ ወጥተው ወደ ምድረ ርስት ሲጓዙ በሰባት ደመና ተጋርደው ወጥተዋል። አንደኛው ደመና በፊታቸው አንደኛው ደመና በኋላቸው፤ አንደኛው ደመና

103. ቅዱስ ቄርሎስ ዘእስክንድርያ፤ ተረፈ ቄርሎስ
104. ቅዱስ ያሬድ፤ መጽሐፈ ድጓ፤ ገጽ ፫፻፺፱
105. አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 40



www.ethiopianorthodox.org

በቀኝ፤ አንደኛው ደመና በግራ ፤አንደኛው ደመና ከላይ እንደጥላ ኾኖ የቀን ሐሩር የሌሊት ቍር እንዳያገኛቸው እየከለለ፤ አንዱ ደመና ከሥር እንደ ጫማ ኾኖላቸው እሾኽ እንቅፋት እንዳያገኛቸው እየቃደገ፤ ሰባተኛው ደመና የሦስት ቀን ጎዳና ተቀድሞ እየሔደ ዛፉን እየነቀለ ድንጊያውን እየፈነቀለ ዝቅ ያለውን ከፍ፤ ከፍ ያለውን ዝቅ እያደረገ ይደለድላቸው ነበር፤ ይኽ ቀን ዐምደ ደመና ኾኖ ሲመራቸው የነበረ ደመና ሌሊት ዐምደ እሳት ኾኖ ሲያበራላቸው ያድር ነበር።

ያቺ ለእስራኤላውያን ከእግዚአብሔር የተሰጠቻቸው ደመና እስራኤል ዘሥጋን ከፊት መርታ ከኋላ ተከትላ በቀኝ በግራ ከልላ ርስታቸው ወደምትኾን ምድረ ርስት ኢየሩሳሌም እንዳደረሰቻቸው ኹሉ፤ ከፈጣሪያችን ከልጇ ከክርስቶስ በመስቀል ሥር እናት እንድትኾነን ልጆቿ እንድንኾን በአደራ የተሰጠችን ቅድስት ድንግል ማርያምም እስራኤል ዘነፍስ ምእመናንን በምልጃዋ በቃል ኪዳኗ ከልጅዋ አስታርቃ፤ በፍቅሯ፣ በጣዕመ ፍቅሯ፣ በምግባር በሃይማኖት እየመራች እየመከረች የዘላለም ርስታቸው ወደምትኾን ኢየሩሳሌም ሰማያዊት መንግሥተ ሰማያት ታደርሳቸዋለችና በደመናዪቱ ተመስላለች።

ይኽም መሪነቷ በመቅድመ ተአምር ላይ «ማርያም ብሂል መርሒ ለመንግሥተ ሰማያት» (ማርያም ማለት መንግሥተ ሰማያት መርታ የምታገባ ማለት ነው)[106] በማለት እንደተገለጸው ያለ እሷ ቃል ኪዳን መንግሥተ ሰማያትን የሚወርስ ማንም የለም፤ ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ «አንቲ ዐምደ ደመና ሥርግው ዘመርሆሙ ለዕብራውያን» (ዕብራውያንን የመራቸው ብርሃንን የተሸለመ የደመና ምሰሶ ነሽ)[107] በማለት አመስግኗታል።

ይኽ የነገረ ማርያም ሊቅ በዚኽ ብቻ ሳይኾን በሙሴ በትርም መስሏት አስተምሯል። ይኸውም እስራኤላውያን ቀን በደመና ዐምድ ሌሊት በእሳት ዐምድ እየተመሩ ከባርነት ነጻ ወጥተው ጉዞ ከጀመሩ በኋላ፤ ሕዝቡም እንደኮበለሉ ለፈርዖን ነገሩት፤ እሱም ፮፻ የተመረጡ ሠረገሎችንና፤ የግብጽን ፈረሶች በማዘጋጀት ሰራዊቱን አስከትሎ እስራኤላውያን ላይ ደረሰባቸው። እነሱም

106 መቅድመ ተአምር
107 አባ ጊዮርጊስ አርጋኖን





አይተው እጅግ ፈሩ፤ ሙሴ ግን ለሕዝቡ አትፍሩ፤ ዛሬ የምታዩአቸውን ግብጻውያንን ለዘላለም አታዩአቸውምና፤ ቁሙ ዛሬ ለእናንተ የሚያደርጋትን የእግዚአብሔርን ማዳን እዩ፤ እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል፤ እናንተም ዝም ትላላችኁ፤ አላቸው።

ያን ጊዜ ጌታ ለሙሴ በትርኽን አንሣ፤ እጅኽንም በባሕሩ ላይ ዘርጋ፤ ክፈለውም አለው። ሙሴም በታዘዘው መሠረት ባሕሩን በበትሩ ቢመታው ባሕሩ ደረቀ ውሃውም ተከፈለ፤ የእስራኤል ልጆች በመላ ተሻግረው ግብጻውያን የፈርዖን ፈረሶችና ሠረገሎች ወደ ባሕሩ በገቡ ጊዜ፤ እግዚአብሔር ሙሴን እጅኽን በባሕሩ ላይ ዘርጋ፤ ውሃውም በግብጻውያን በሠረገሎቻቸውም በፈረሶቻቸውም ላይ ይመለስ አለው፤ ሙሴም እንደታዘዘው እጁን በባሕሩ ላይ ሲዘረጋ ውሃው ተመልሶ ፈርዖንና ሰራዊቱን አሰጠመ፤ ያን ጊዜ ሙሴና ያእስራኤል ልጆች ፈጣሪያቸውን አመሰገነዋል(ዘፀ ፲፬፥፳፮-፴፩ ፤ዘፀ ፲፭፥፩-፳፩)።

ይኸቺ ሙሴ ባሕረ ኤርትራን የከፈለባት በትር የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምና የመስቀል ምሳሌ መኾኗን ሊቃውንት አስተምረዋል። ይኸውም በዘመነ ብሉይ ለሙሴ እግዚአብሔር ባመለከተው በትሩ እስራኤል ከፈርዖን ባርነት ተላቀው ጠላታቸው ፈርዖንና ሰራዊቱ በባሕረ ኤርትራ ሰጥመውላቸው እንደቀሩ ኹሉ በዘመነ ሐዲስም ለእስራኤል ዘነፍስ ምእመናን በመስቀል ሥር እናት ትኾነን ዘንድ ለዮሐንስ ባመለከተው በቅድስት ድንግል ማርያም ጸሎትና ቃል ኪዳን ከዲያብሎስና ከሰራዊቱ ከአጋንንት ግዞት የምንሰወር ኾነናል (ዮሐ ፲፱፥፳፮-፳፯)።

ዳግመኛም በበትሯ አማካይነት እስራኤል ባሕሩ ተከፍሎላቸው ከኀሣር ወደ ክብር፣ ከባርነት ወደ ነጻነት፣ ከግብጽ ወደ ርስታቸው ከነዓን እንደተጓዙ ኹሉ ምእመናንም በወላዲተ አምላክ በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ከኀሣር ወደ ክብር፤ ከዘላለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት፤ በግብጽ ከተመሰለች ከሲኦል (ከገሃነመ እሳት) በከነዓን ወደተመሰለች ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት ያሻግራሉና፤ ለሙሴ በትር ተመስላለች። ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በትርነቷን በአንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ፤

*«በትረ ረድኤቱ ለሙሴ ለባሕረ ኤርትራ ዘሠጠቃ*
*እመ ተሀጉለ ግብጽ ለወርኀ ኒሳን በኅጽቃ»*



www.ethiopianorthodox.org

(በሚያገዩ ግማሽ ወር ግብጻች በጠፉ ጊዜ፤ የኤርትራን ባሕር የከፈለባት የሙሴ የረድኤት በትሩ አንቺ ነሽ)[108] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ አስቀምጦታል፡፡

## መሶበ ወርቅ

የዘላለም ሕይወት ሊኾነን ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን ዐማኑኤልን የወለደችልን ቅድስት ድንግል ማርያም መና ይዛ በደብተራ ኦሪት በተቀመጠችው የወርቅ መሶብ ትመስላለች (ዘፀ ፲፮፥፴፫-፴፬)፡፡ ልዑል እግዚአብሔር አገልጋዩ ሙሴን መሶበ ወርቅን ሽምሽር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቀርጸኽ አብጅ *ወንሣእ ቈጽለ ወርቅ ረቃቀ ወግለ ባቱ* ወርቁን እንደ ቅጠል አሳስተኽ ውጪውን ውስጡን በወርቅ ለብጠው፤ በውስጧም ጊዜ ሳትወስን ጎሞር ሙሉ መና አኑርበት ብሎታል፡፡

ይኽውም ለጊዜው ቢደረግም ለኋላው ምሳሌ ነበር፤ መና የያዘችው መሶበ ወርቅ አማናዊ መና ወልደ እግዚአብሔርን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ መና የጌታ ምሳሌ ነው፡፡

ዳግመኛም ጌታ ለሙሴ ጊዜ ሳትለካ አንድ ጎሞር ሙሉ መና አኑርበት ማለቱ ለጊዜው ለአዘክሮተ ፍቅርና ለአዘክሮተ በቀል ነው፤ ለአዘክሮተ ፍቅር ማለት አባቶቻችንን ቢወዳቸው መና ከደመና አውርዶ ይመግባቸው ውሃ ከጭንጫ አፍልቆ ያጠጣቸው ነበር ለማለት፤አዘክሮተ በቀል አባቶቻችን መና ከደመና አውርዶ ውሃ ከጭንጫ አፍልቆ ቢመግባቸው ካዱት ብለው ውሉድ አበውን መፈረጃ እንዲያደርጓቸው ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን ያ ብዙ ዘመን ሲኖር ጣዕሙ እንዳልተለወጠ ጌታም ሰው ሲኾን ባሕርየ መለኮቱ ላለመለወጡ ምሳሌ ነው፤ እስራኤል ከየሰበሰቡ ከቤታቸው የሚያኖሩት መና ሲሸት ሲለውጥ፤ በደብተራ ኦሪት ውስጥ በመሶበ ወርቅ ያለው መና ግን ያለመሽተቱ ያለመለወጡ ጌታ አምላክ ወሰብእ ሲኾን አምላክነቱ ሰውነቱን ሰውነቱ አምላክነቱን ያለመለወጡ ምሳሌ ነው (ሚል ፫፥፮፤ ዕብ ፲፫፥፰) ፡፡

ይኽውም ምሳሌነት ያለው መና ከዘመነ ሙሴ እስከ ዘመነ ሥጋዌ በመሶበ ወርቅ ተቀምጦ ሲኖር ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን ምግብ

108. አባ ጊዮርጊስ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 32





ርትባን ስቱ ጽሙአን እውነተኛው መና ወልደ እግዚአብሔር በአማናዊት መሶብ በማሕፀነ ማርያም ባደረ ጊዜ ያ እንደ ሰም ቀልጦ ጠፍቷል፤ አማናዊ ኅብስተ ሕይወት ጌታ እኔ ተተካኹላችኋ ሲለን ነው (ዮሐ ፮፥፴፯)፤ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በሰንበት ክርስቲያን የእመቤታችን ምስጋናው ላይ *‹‹አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኵሉ ዓለም›* (የተሠወረ መና ያለብሽ የንጹሕ ወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ፤ መናም ከሰማይ የወረደውና ለዓለም ኹሉ ሕይወትን የሚያድለው ኅብስት ነው) በማለት ኅብስተ ሕይወት ክርስቶስን ያስገኘችልን በንጽሕና የተጌጠች አማናዊት መሶበ ወርቅ ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አስተምሯል፡፡

በተመሳሳይ መልኩ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ላይ *‹‹አስተማሰልናኪ ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት በመሶብ ዘወርቅ ዘውስቴታ ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ወሃቤ ሕይወት ለኵሉ ዘየአምን ቢያሁ ወይበልዕ እምኔሁ በአሚን ወበልብ ሥሙር ምስለ አለ በየማነ››* (የተለየሽና ደግ የኾንሽ የተመሰገንሽ የተባረክሽ የከበርሽና ከፍ ከፍ ያልሽ ሆይ የሕይወት ኅብስት ባለበት በወርቅ መሶብ መሰልንሽ፤ የሕይወት ኅብስትም በቀኙ ካሉ ጻድቃን ጋር ርሱን ለሚያምን በሃይማኖትና ፈቃደኛ በኾነ ልብ ከእርሱ ለሚበላም ኹሉ ሕይወትን የሚሰጥ ከሰማይ የወረደ ነው)[109] በማለት ከሰማይ የወረደ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ያለ፤ ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን የሕይወት ምግብ ክርስቶስን የወለደችልን አማናዊት የወርቅ መሶብ ድንግል ማርያም መኾኗን ተንትኖ ሲተረጕመው፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ምስጢሩን በመጠቅለል *‹‹ኦ መሶብ ቤተልሔማዊት ዘወለደቶ ለኅብስተ ሰማይ ዘኢያብቈልዎ ገራህት ወዘኢሐፀንዎ አየራት››* (ገራህት ያላበቀሉትን አየራት ያላሳደጉትን የሰማዩን እንጀራ የወለድሺው ቤተልሔማዊት መሶብ ሆይ)[110] በማለት የሕይወት እንጀራ አካላዊ ቃል ክርስቶስን ያለ ወንድ ዘር በቤተልሔም የወለደችልን አማናዊት መሶብ መኾኗን መስክሯል፡፡

109. ቅዱስ ያሬድ፤ አንቀጸ ብርሃን ቁ ፮
110. አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፳፥፲፪



www.ethiopianorthodox.org

## የኮሬብ ቦታ

እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ቸርነት ከግብጽ ባርነት ወጥተው በገዳ ላይ ሳሉ ራፊዲም ደረሱ፤ ያን ጊዜ የምንጠጣውን ውሃ ስጠን በማለት በሊቀ ነቢያት ሙሴ ላይ ያንጐራጐሩ ገርመር፤ ያን ጊዜ ሙሴ ይኽነን ነገራቸውን ወደ እግዚአብሔር አመለከተላቸው፤ ጌታም ለሙሴ « በኮሬብ በዐለት ላይ በፊትኽ እቆማለኍ፤ ዐለቱንም ትመታለኽ፤ ሕዝቡም ይጠጣ ዘንድ ከእርሱ ውሃ ይወጣል» ባለው መሠረት የእስራኤላውያንን ሥጋዊ ጥማቸውን ያበረደ ውሃ ከኀቱም ዐለት ተገኝቷል (ዘፀ ፲፯፥፩-፯) ።

እንደዚኹም ኹሉ በዘመነ ሐዲስ ለእስራኤል ዘነፍስ ለምእመናን ዘላለማዊ ጽማቸውን ያራቀ የሕይወት ውሃ ጌታ ከእመቤታችን በኀቱም ድንግልና ተገኝቷልና በኮሬብ ዐለት ተመስላለች(ዮሐ ፬፥፲፫-፲፬፤፯፥፴፯)። ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም የሕይወት ውሃ ጌታ በኀቱም ድንግልና ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፳፻ሕ፳፰ ዓመት ከፈጣሪዋ ረድኤት ተለይታ ከልጅነት ተጠምታ የነበረች የሰው ልጅ ሰውነትን በልዩ ጸጋው እንዳረካው በመጽሐፉ ሲገልጽ «On Horeb the rock marked out your type, o virgin…» (ድንግል ሆይ በኮሬብ ዐለቱ ያንቺን ምሳሌ ኾነ፤ ያለ መሠንጠቅ ለተጠሙት በሞት አፋፍ ለነበሩት እስራኤውያን ውሃን ሰጠ፤ ምልክቱ አንቺን አብራራ፤ ያሰማይ ውሃ ካንቺ ፈልቋልና፤ ከርሱም በጸጋ ፍጥረት ኹሉ ጠጣና ረካ… ሙሴ ከዐለቱ ጋር ተነጋገረ፤ ውሃም ሰጠ ነገር ግን የሚያጠፋ ኀርፍ አልነበረም፤ ያ ምንጭ የሕዝቦቹ መሪዎች ያመለከቱት ዐለት በበትር አማካይነት ተከፈተ ምሳሌም ኾነ፤ ለተጠማ ይኽ ምልክት መልካም ነበር፤ ከዳዊት ሴት ልጅ ጋር ሙሴ ቆመ፤ ከእርሷም ጋር ስለዚኽ መንፈሳዊ ኹኔታ ተነጋገረ፤ ሙሴ ከዐለቱ ጋር እንደተነጋገረ እርሷም ፀነሰች በድንግልናም ወለደች፤ በምልክቶቹም ሙሴ እነዚኽና ረቂቅ ነገሮች አሰረዳ)[111] በማለት ሙሴ በኮሬብ የሠራው ሥራ ቤሐዲስ ኪዳን ለተገለጠው ልዩ ምስጢር ጥላ እንደነበረ አጕልቶ አስተምሯል።

ብርሃነ ዓለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የእስራኤልን ጽም ስላበረደው ከዐለት ስለፈለቀው ውሃ በ፩ኛ ቆሮ ፲፫-፬ ላይ ሲመሰል « ኹሉም ያን

111 Bride of light, pp.59,142





መንፈሳዊ መብል በሉ፤ ኹሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ድንጋይ ጠጥተዋልና፤ ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ» በማለት በኮሬብ ከተመሰለች ከቅድስት ድንግል ማርያም በኀቱም ድንግልና ተወልዶ የነፍሳትን ጥም ያበረደ ስቴ ጽሙአን ማየ ሕይወት ክርስቶስ መኾኑን መስሎ አስተምሯል።

የቤተክርስትያናችን ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን በመጽሐፉ ሲተረጉም «አንቲ ውእቱ መካነ ኮሬብ ኀበ ይቀውሞ እገሪሁ ለእግዚአብሔር ወሀየ ኰኲሕ ዘይውሕዙ እምኔሁ ዐሥርቱ ወክልኤቱ አንቅዕተ ማይ ጥዑም ዘይሰትዩ ሕዝብ ለጽምዖሙ ወነበ የሐውሩ የሐውር ምስሌሆሙ፤ ወኰኲሕ ክርስቶስ ውእቱ» (የእግዚአብሔር እግሮች የሚቆሙባት የኮሬብ ቦታ አንቺ ነሽ፤ ሕዝብ ለጥማታቸው የሚጠጡትም የጥፍጥ ውሃ፤ ዐሥራ ኹለት ምንጮች ከርሱ የሚፈሱ ዐለት በዚያ አለ፤ ወደሚኼዱበትም ከነርሱ ጋር ይኼዳሉ፤ደንጊያውም ክርስቶስ ነው)[112] በማለት የሕይወት ዐለት ጌታን ያገኘንበት የኮሬብ ቦታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መኾኗን አስምሯል።

የሚላኑ አምብሮስም የቅድስት ድንግል ማርያምን ድንግልና በዐለቱ መስሎ ሲያስረዳ «ድንጋዩ ውሃ ማፍለቁንና የባሕሩ ሞገዶች እንደ ግድግዳ ጸንተው እንዲቆሙ መደረጋቸውን ብናነብ፤ ድንግል በድንግልና መውለዷ ለማመን የሚከብድ ነገር አይኾንም»[113] በማለት ሲተነትን ልክ እንደ አምብሮስ ኢትዮጵያዊው ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፈ ምስጢር ላይ «ነቅዐ ሐሊብ እም አጥባቲሃ ለድንግል እንተ ኢተአምረ ብእሴ። ወበዝ አእመርነ ከመ እምነዘ ውእቱ ዘተወልደ እምኔሃ እስመ አልቦ ዘይክል አንቅዖ ሐሊብ እም[illegible] ድንግል ዘእንበለ ዘአንቅዐ ማየ እምኰኲሐ ኮሬብ፤ ወአልቦ ካዕበ ዘይት[illegible] ሐሊበ ድንግል ዘእንበለ እግዚአብሔር ባሕቲቱ» (ወንድ ከማታውቀው ከድንግል ጡቶች ወተት ፈሰሰ፤ በዚኽም ከእርሷ የተወለደው አምላክ እንደኾነ ዐወቅን፤ ከኮሬብ ዐለት ውሃንካፈለቀው በቀር ከድንግል ጡቶች ወተት ማግኘት የሚቻለው የለምና። ዳግመኛም በድንግል ማሕፀን ካደረ ከእግዚአብሔር ብቻ በቀር በድንግልና ወተት የሚሰጥ የለም)[114] በማለት ከኀቱም [illegible]

112 አባ ጊዮርጊስ፤ አርጋኖን ውዳሴ [illegible]
113. Ambrose of Milan, letter 15
114 አባ ጊዮርጊስ፤ መጽሐፈ ምስጢር ገጽ ፪፻፺



www.ethiopianorthodox.org

ያፈለቀ ጌታ፤ ከእናቱ የድንግልና ጡቶች ላይ ወተትን አፍልቆ ፍጥረትን የሚመግብ ጌታ የተመገበው መኾኑን በጥልቀት አስረድቷል።

## የሙሴ ክንድ

በመስቀል ተሰቅሎ ሲቃነ አጋንንትን ሰራዊተ አጋንንትን ድል የነሣ አምላካችን ክርስቶስን የወለደችልን ድንግል ማርያም አማሌቃውያንን ድል በነሣች በሙሴ ክንድ ትመሰላለች (ዘፀ ፲፯፥፰-፲፯)። ይኸውም እስራኤላውያንና አማሌቃውያን በሚዋጉበት ጊዜ ሙሴ ኢያሱን ወደ ጦር ሜዳ በመላክ እሱ እጆቹን ያጥፍ፤ በመስቀል አምሳል ይዘረጋ ነበር፤ ሙሴ እጆቹን ባጠፈ ጊዜ አማሌቃውያን እስራኤላውያን ላይ በመበርታት ድል ሲነሧቸው፤ሙሴ ግን በመስቀል ምልክት እጆቹን በዘረጋ ጊዜ ግን እስራኤላውያን ድል ያደርጉ አማሌቃውያን ድል ይነሡ ነበር፤ ያን ጊዜ አሮንና ሖር የሙሴን እጆች አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ ተሸክመው ሙለው ሲደክማቸው ደንጊያውን ከበው እንደ ዐምድ አድርገው ፀሓይ እስኪጠልቅ ድረስ በእዚያ ላይ አኑረውት ኢያሱም ከእስራኤል ጋር ኾኖ ጦሩን አሰልፎ አማሌቃውያንን ድል ነሥተዋል።

ይኸውም ምሳሌ ነው ሙሴ የክርስቶስ፤ ደንጊያው የመስቀል፤ አሮንና ሖር የፈያታዊ ዘየማንና የፈያታዊ ዘጸጋም፤ እስራኤል የነፍሳት፤ አማሌቅ የአጋንንት ምሳሌ ናቸው (ማቴ ፳፯፥፴፰)፤ ይኸውም ሙሴ እጁን ባጠፈ ጊዜ እስራኤል ድል መነሣታቸው፤ መድኀኒታችን ክርስቶስ እጁን ዘርግቶ በመልዕልተ መስቀል እስከሚሰቀል ድረስ ነፍሳት በመንጸፈ ደይን ወድቀው በእግረ አጋንንት ተጠቅጥቀው የመኖራቸው ምሳሌ ሲኾን፤ ሙሴ እጆቹን በዘረጋ ጊዜ ግን አማሌቃውያን ድል መነሣታቸው፤ ጌታ በዕለተ ዐርብ እጁን ዘርግቶ በመልዕልተ መስቀል በተሰቀለ ጊዜ አጋንንት ድል የመነሣታቸው ምሳሌ ነበር (ዮሐ ፫፥፲፬-፲፭፤ኤፌ ፪፥፲፮፤ቆላ ፪፥፲፬)፤ ዳግመኛ የሙሴ እጆች ፀሓይ እስኪገባ ድረስ ተዘርግተው እንደዋሉ ኹሉ መድኀኒታችን ክርስቶስም እጆቹን ዘርግቶ በዕለተ ዐርብ ከስድስት ሰዓት እስከ ዘጠኝ ሰዓት በተሰቀለ ጊዜ ዓለም ኹሉ ጨለማ ኾኖ ውሏል (ማር ፲፭፥፴፫)።

ሰማዕቱ ጀስቲን ይኽነን ሲያስተምር ‹‹In truth it was not because Moses prayed that his people were victorious...›› (በእርግጥ ሕዝቡ፡ ባለድል (አሸናፊ) የኾኑት ሙሴ ስለጸለየ አልነበረም፤ የኢየሱስ (የኢያሱ) ስም በጦርነቱ ቦታ ከፊት ኾኖ ሳለ ሙሴ የመስቀል ምልክት በመሥራቱ እንጂ፤ከለቅሶ እና ከዕንባ ጋር የሚቀርብ ጸሎት ለእግዚአብሔር በጣም አስደሳች እንደኾነ የማያውቅ ከእናንተ መኻከል ማን አለ? በዚኽ አጋጣሚ ላይ ግን ሙሴ ወይም ከእርሱ ጋር ካሉት ማናቸውም በዚኽ ኹኔታ አልጸለየም፤ በድንጋይ ላይ ቁጭ ብሎ ነበር እንጂ፤ ድንጋዩ ራሱ የጌታ ምሳሌ መኾኑን አሳይቻለኊ፤ በተጨማሪም ነቢዩ ሙሴ እስከ ምሽት ድረስ እጆቹ በአሮንና በሖር ተይዘውለት በመስቀል ቅርጽ መቆየቱ በዚኽ ምልክት አምሳል የኾነ ነው፤ ጌታም እስኪቀበር ድረስ በመስቀል እስከ ምሽት ቆይቷልና፤ ከዚያም በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ)[115] በማለት የምሳሌው እሙንነትና ኢያሱ በጦር ሜዳ ሲኖር የስሙ ትርጉም መድኀኒት በመኾኑ የኢየሱስ የስም ትርጉም በስሙ በመኖሩ ምክንያት በጦርነቱ ቦታ ድል መንሣታቸውን በጥልቀት አስተምሯል።የመልክአ ኢየሱስ ደረሲ ለዚኽ ነው፤

*‹‹ሰላም ለዝክረ ስምከ ስመ መሐላ ዘኢይሔሱ*
*ዘአንበረ ቅድመ እግዚአብሔር በአትሮንሱ*
*ኢየሱስ ክርስቶስ ለዳዊት ባሕርየ ክርሡ*
*አክሊለ ስምከ እንዘ ይትቄጸል በርእሱ*
*አሕጉረ ፀር ወረሰ ኢያሱ››*

በማለት እስራኤላውያንን ዘገር ነጥቆ ጦር ነቅንቆ አማሌቃውያንን ድል ነሥቶ ከሥጋዊ ጠላታቸው አድኖ መድኀኒት የተባለ ኢያሱ፤ ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ ምእመናንን ከመከራ ሥጋና ከመከራ ነፍስ በኀጢአታቸው ከመጣባቸው ፍዳ አድኖ መድኀኒት የተባለ ከዳዊት ባሕርይ የተወለደው የኢየሱስ ክርስቶስን የስሙን ምሳሌ በመያዙ የጠላትን ሀገር ኹሉ ድል ነሥቶ መውረሱን አስተምሯል (ማቴ ፩፥፳፩፤ሉቃ ፪፥፲፩)።

ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅም የዮሐንስን ወንጌል በተረጐመበት ክፍል ላይ ይኽነን ሲገልጽ ‹‹see how the type was given through Moses...›› ( ምሳሌው በሙሴ በኩል እንደተሰጠ፤ እውነታው ግን በጌታችን በኩል እንደመጣ ተመልከቱ፤ በድጋሚ በሲና ተራራ ላይ አማሌቃውያን

115. Justin the Martyr, Dialogue with Trypho pp 90,97




www.ethiopianorthodox.org

በዕብራውያን ላይ ጦርነት ባወጁ ጊዜ የሙሴ እጆች በግራና በቀኝ በቆሙት በአሮንና በሖር ተደግፈው ተዘርግተው ነበር። ጌታ ሲመጣ ግን እጆቹን በራሱ ኀይል በመስቀሉ ላይ ዘረጋቸው፤ ምሳሌው እንዴት እንደተሰጠና እውነታው እንዴት እንደመጣ ተመለከታችኍ)[116] በማለት የሙሴ የክንዱን የመዘርጋት ምስጢር በማብራራት ተርጕሞታል።

ኢትዮጵያዊው ሊቅ ዐጤ ዘርአ ያዕቆብም በምስጢር በመራቀቅ በመጽሐፈ ብርሃን ላይ የሙሴ ቀኝ እጁን በቅዱስ ኢያቄም ግራ እጁን በቅድስት ሐና መስሎ ሰፊ ትንታኔ ሰጥቷል፤ ይኸውም ሙሴ እጁን ሲዘረጋ አማሌቅ ደክመው እንደተሸነፉ ኹሉ ቅዱስ ኢያቄምና ቅድስት ሐናም ዲያብሎስን በቅዱስ መስቀሉ ድል የነሣ አምላካችን ክርስቶስን የወለደች ቅድስት ድንግል ማርያምን በወለዱ ጊዜ ዲያብሎስ ከሰራዊቱ ጋር የመድከሙ የመሸነፉ ምሳሌ መኾኑን ሲያብራራ *‹‹በእማንቱ አዕዳዊሁ ለሙሴ መዋእያት ይትሜሰሉ ኢያቄም ወሐና እለ ፈረይዋ ለማርያም ድንግል በክልኤ ለዘወለደቶ ለኀይል ዘመልዕልተ ኵሉ። ሙሴ በሰፊሐ እደዊሁ ክልኤሆን ሞአሙ ለአሜሌቅ ወለሕዝቡ ኢያቄምኒ ወሐና በወሊደ ማርያም ምእምሙ ለሰይጣን ወለአጋንንቲሁ ኢያቄም ይትሜሰል በእዴሁ ለሙሴ ዘየማን ወሐና ትትሜሰል በእዴሁ ዘጸጋም››* (እሊያ ከኹሉ በላይ የሚኾን ኀይልን (ጌታን) የወለደችው በኹለት ወገን ድንግል የኾነች ማርያምን ያፈሩ (የወለዱ) ኢያቄምና ሐና አሸናፊዎች በኾኑ በነዚያ በሙሴ እጆች ይመሰላሉ። ይኸውም ሙሴ ኹለቱን እጆቹን በመዘርጋት አማሌቅና ሠራዊቱን አሸነፋቸው፤ ኢያቄምና ሐናም ማርያምን በመውለዳቸው ሰይጣንና አጋንንቱን አሸነፉት። ኢያቄም በሙሴ ቀኝ እጅ ሲመሰል ሐናም በግራ እጁ ትመሰላለች)[117] በማለት አመስጥሮታል።

ይኸነንም በጥልቀት ስናየው ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ለ፳፻ሺሕ፰፻ ዘመን የነበረውን የዲያብሎስን ምርኮ የማረከ የኀያላን ጌታ የአምላካችን የክርስቶስ እናት የቅድስት ድንግል ልደቷ ለዲያብሎስ የሽንፈት ኾርማሮ መኾኑን በርካቶች ሊቃውንት አስተምረዋል። አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም ስለዚኽ ምስጢር በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ፤

*‹‹ተፈሥሐት ምድር ወሰማይ አንፈርዐፀ*
*በዕለተ ጸገዩኪ አብላስ ወአውዕኡ ሠርጸ*
*ተአምረ ሕይወት ማርያም ዘአልብኪ ቢፀ*
*እስከ ፈርሀ መልአከ ሞት ወሰይጣን ደንገፀ*
*ዜና ልደትኪ ነጐድጓድ እስከ ሲኦል ደምፀ››*

(በለሶች (ኢያቄምና ሐና) አንቺን ባስገኙሽ ጊዜ ምድር ደስ አላት ሰማይም ደስ አለው። ጓደኛ (ምሳሌ) የሌለሽ የድኅነት ምልክት ማርያም፤ መልአከ ሞት እስኪፈራና ሰይጣንም እስኪደነግጥ ድረስ የመወለድሽ ዜና እስከ ሲኦል ድረስ ተሰማ)[118] በማለት የእመቤታችን ልደት በምድር በተመሰሉ በሰው ልጆችና በሰማይ በተመሰሉ በመላእክት ዘንድ ደስታ የፈጠረ ሲኾን በአንጻሩ ግን ዲያብሎስንና ሰራዊቱን ያስደነገጠ ግሩም ዜና መኾኑን አስረድቷል።

በተመሳሳይ መልኩ ሊቁ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ *‹‹ወፈድፋደሰ ይትመዐዕ ወየሐቂ ስነኒሆ ሶበ ይሰምዕ ዜና ውዳሴኪ እስመ ሰሚዐ ውዳሴኪ ጕድብ ውእቱ በኀቤሁ ወይሰብር ቀኖጺሁ ወሰይፍ ውእቱ ዘይመትር ርእሶ ወእምዘከረ ስምኪ ይደነግፅ ከመ ዘርእየ ንጉረ መብረቅ ዘይበርቅ በኀይል፤ ወእም ከመ ተወለድኪ አንቲ ኢረከበ ዕረፍተ ወኢናህየ ሐመ ብኪ ወተጽዕረ በወልድኪ ወረከቦ ሥቃይ በመስቀሉ ለዋሕድኪ››* (ይልቁንም የምስጋናሽን ነገር በሚሰማ ጊዜ ጥርሶቹን እያፋጨ ይበሳጫል፤ የአንቺን ምስጋና መስማት በርሱ ዘንድ መራጃ ነውና ጭኖቹንም ይሰብረዋል፤ ራሱንም የሚቆርጥ ሰይፍ ነው። ከስምሽ አጠራር የተነሣ በኀይል የሚበርቅ የመብረቅ ነጸብራቅ እንደ ተመለከተ ይደነግጣል፤ አንቺ ከተወለድሽ ገርምሮም ፍጹም ዕረፍትን አላገኘም፤ በአንቺ ታመመ በልጅሽም ተጨነቀ በአንድ ልጅሽ መስቀልም ሥቃይ አገኘው)[119] በማለት የደረሰበትን ሽንፈት አስተምሯል።

## ደብረ ሲና

እመ አደናይ ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ልዑል እግዚአብሔር በገናና ክብር የታየባት የሲና ተራራና፤ በተራራው ላይ የታየው ግሩም ደመና ምሳሌዎቿ እንደኾኑ ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን አስተምረዋል (ዘፀ ፲፱ ፥ ፲፰)።

116. John Chrysostom, Homilies on the Gospel of John 14
117. ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ብርሃን ገጽ ፳

118. አባ ጽጌ ድንግል ፤ ማሕሌተ ጽጌ ፤ ቁ 47
119. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አርጋኖን ዘሠሉስ ፤ ምዕ. ፬ ፥ ፲፱-፳፩






www.ethiopianorthodox.org

ከነዚኽ መኻከል የሶርያ ፀሓይ የተባለው ቅዱስ ኤፍሬምና ታላቁ መምህር ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ይገኙበታል፡፡ ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር በሲና ተራራ ሕግንና ሥርዐትን ከመሥራቱ በፊት እስራኤል ከሙሴ ጋር ሲነጋገር እንዲሰሙት በሲና ተራራ በከባድ ደመና እንደሚመጣና ሕዝቡ ኹሉ በንጽሕና በቅድስና ተዘጋጅተው እንዲቆዩ ለሙሴ ከነገረው በኋላ ልክ በሦስተኛው ቀን ሙሴና አሮን በተራራው ጫፍ፤ ሌዋውያን ካህናት በተራራው መኻከል፤ ሕዝቡ ከተራራው ሥር ሳሉ ልዑል እግዚአብሔር የሲናን ተራራ ራስ በጭጋግ፣ በእሳት፣ በነፋስ፣ በጨለማ ሸፍኖ ሰባት የእሳት መጋረጃ ጋርዶ የነጋሪት ድምፂ እያሰማ በታላቅ ግርማ በተገለጸ ጊዜ ኹሉም ተርበድብደው በድንጋ... ወድቀዋል፡፡ ይኸውም በዘፀ ፲፱፥፲፰ ላይ ‹‹እግዚአብሔርም በእሳት ስለወረደበት የሲና ተራራ ኹሉ ይጤስ ነበር፤ ከእርሱም እንደ እቶን ጢስ ያለ ጢስ ይወጣ ነበር፤ ተራራውም ኹሉ እጅግ ይናወጥ ነበር›› በማለት ጌታ በሲና ተራራ በከባድ ደመና የመገለጡን ነገር ይናገራል፡፡

ይኽቺ ልዑል እግዚአብሔር በዐበየ ግርማ የተገለጠባት ደብረ ሲና በኋለኛው ዘመን ወልደ እግዚአብሔር ከሷ ተወልዶ የተገለጠባት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ቅዱስ ኤፍሬም በስሩትና በጥልቀት ሲያስተምር፤ ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ በበኩሉ በሲና ተራራ የታየው ደመና፤ የቅድስት ድንግል ምሳሌ መኾኗን አስተምሯል፡፡

ይኽ አባት ቅዱስ ኤፍሬም በማግሰኞ ዕለት ውዳሴ ማርያም ላይ‹‹ ቃለ አብ ሕያው ዘወረደ ውስተ ደብረ ሲና...›› ወደ ደብረ ሲና የወረደ ለሙሴ ሕግን የሰጠ፤ የተራራውን ራስ በጭጋግ በጢስ፣ በጨለማና በነፋስ የሸፈነ ፈርተው የቆሙትንም በነጋሪት ድምፅ የገሠጸ የአብ አካላዊ ቃል ነው... በትሕትና የተናገርሽ ተራራ ሆይ ወደ አንቺ የወረደው እኮ ያው ነው፤ ሰውን የወደደ እርሱ ያለመለወጥ ሰው ኾነ፤ እንደ እኛ በሚናገር ሥጋ ፍጹም ሰው ኾነ፤ አምላክ በግብረ መንፈስ ቅዱስ በማሕፀኗ ዐደረና፤ ፍጹም ሰው ኾነ፤ አዳምን ያድነው ዘንድ ኀጢአቱንም ይቅር ይል ዘንድ በሰማያት (በሰማያዊ ማዕርግ) ያኖረው ዘንድ፤ በቸርነቱና በይቅርታው ብዛት ወደ ቀድሞ ቦታው ይመልሰው ዘንድ) በማለት በሲና ተራራ ላይ ለእስራኤላውያን የተገለጸው አካላዊ ቃል፤ የሰው ልጆችን ለማዳን ፭ሺሕ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ደብር ነባቢት ከተባለች ከቅድስት





ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ተውሕዶ ለዓለም የመገለጡን ምስጢር ያሳየ መኾኑን ገልጿል፡፡

ይኸውም ደብረ ሲና የቅድስት ድንግል ማርያም፤ እሳት የመለኮት፤ ጽልመት የትስብእት ምሳሌ ኾኖ የተገለጠ ስለመኾኑ ይኸው ቅዱስ ኤፍሬም በሃይማኖተ አበው ላይ *"እምደብረ ሲና ወፅአ እሳት ወጽልመት፤ ወእምኔኪ ወፅአ ለነ አምላክ ወሰብእ"* (ከደብረ ሲና እሳትና ጨለማ ወጣ፤ ከአንቺ ግን ሰው የኾነ አምላክ ተገኘልን)[120] በማለት የምሳሌውን እሙን መኾን አስተምሯል፡፡ በተጨማሪም በዘፀ ፳፥፲፰ ላይ ‹‹ሕዝቡም ኹሉ ነጐድጓዱንና መብረቁን የቀንደ መለከቱን ድምፅ፤ ተራራውም ሲጤስ አዩ፤ ሕዝቡም ባዩ ጊዜ ተርበድብደው ርቀውም ቆሙ›› ሲል ጌታ በደብረ ሲና በዐበየ ግርማ በንጉሥ አምሳል ሲገለጽ፤ በተራራው ላይ የታየው ታላቅ ግርማ ሲጮኽ የተሰማው የቀንደ መለከት ድምፅ እስራኤላውያንን ጽኑ ድንጋጤ እንዳስደነገጠ ኹሉ በደብረ ሲና የተገለጠው የነገሥታት ንጉሥ አካላዊ ቃል ክርስቶስ ደብር ነባቢት ከተባለችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በተወለደ ጊዜ ‹‹የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው? ኮከቡን በምሥራቅ አይተን ልንሰግድለት መጥተናልና›› (ማቴ ፪፥፪) የሚለው የሰብአ ሰገል ድምፅ በንጉሥ ሄሮድስና በሠራዊቱ፤ በዲያብሎስና በአጋንንት ላይ ታላቅ ጽኑ ድንጋጤ ማሳደሩን ቅዱስ ኤፍሬም በሃይማኖተ አበው ላይ ‹‹*እምደብረ ሲና ወፅአ ድንጋፄ ወሀውክ ላዕለ አይሁድ ወእምኔኪ ወፅአ ሁከት ወድንጋፄ ዐቢይ ላዕለ አይሁድ ወሄሮድስ ወዲያብሎስ ምስለ አጋንንቲሁ*›› (በደብረ ሲና በአይሁድ ላይ ድንጋፄ ሀውክ ተደረገ፤ በአንቺም በአይሁድና በሄሮድስ በዲያብሎስና በአጋንንቱ ላይ ጽኑ ድንጋጤ ተደረገ)[121] በማለት ጌታ በደብረ ሲና በተገለጠ ጊዜ ከሩቅ የተሰማው የነጋሪት የቀንደ መለከት ድምፅንና አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በተገለጠ ጊዜ ከሩቅ ሀገር የመጡት የሰብአ ሰገልን ቃል፤ በተጨማሪም የአይሁድን ድንጋጤ ከዲያብሎስና ከሄሮድስ ድንጋጤና ፍርሃት ጋር እያነጻጸረ አስተምሯል፡፡

ዳግመኛም ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ጌታ በደብረ ሲና የተገለጠባት ደመናንና በዘመነ ሥጋዌ ከሷ ተወልዶ የተገለጠባት ቅድስት ድንግል ማርያምን

120. ሃይማኖተ አበው ዘኤፍሬም፤ ምዕ.፴፰ ክፍል ፪፥፲ ፤ገጽ ፻፶፩
121. ዝኒ ከማሁ ገጽ ፻፶፩



www.ethiopianorthodox.org

በማነጻጸር በጥልቀት አስተምሯል። ይኸውም በብሉይ ኪዳን ልዑል እግዚአብሔር በብዛት በደመና እየተገለጠ ቃሉን ያሰማቸው እንደነበር መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እናገኛለን (ዘፀ ፲፱፥፲፮-፲፰)። እስራኤላውያንም ይኸንን የደመናውን ዐምድ ሲመለከቱ የእግዚአብሔር ሀልዎቱን በመረዳት ኹሉም እየሰገዱ ፈጣሪያቸውን ያመልኩ ነበር (ዘፀ ፴፫፥፱-፲)። እንደዚኹም ኹሉ በዘመነ ሥጋዌ አምላክ ሰው ኾኖ ለመገለጥ በእውነተኛዪቱ ደመና በቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ባደረ ጊዜ አረጋዊው ዮሴፍ አምላኩ በማሕፀነ ማርያም መኖሩን ተረድቶ የፈጣሪውን እናት በሚገባ አገልግሏታል።

ይኸውም በቅዱስ ወንጌል እንደተጻፈ የጌታ መልአክ ለሱ ተገልጾ ነቢዩ ኢሳይያስ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ዐማኑኤልን የምትወልድ መኾኗን ትንቢት የተናገረላት፤ ዐማኑኤል ማለትም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት መኾኑን፤ ልጇ የባሕርይ አምላክ እሷ የአምላክ እናት መኾኗን አስረድቶታል (ማቴ ፩፥፲፰-፳፭)። ቅዱስ ያዕቆብ ይኸንን ሲገልጥ ‹‹He was loving her and marveling her...›› (ዮሴፍ ወደዳት፣ አከበራት፣ ታዘዛት፣ አገለገላት፣ በሲና ተራራ እንዳለው ደመናም ያከብራት ነበር፤ በእርሷ የእግዚአብሔር ኀይል ዐድሯልና)[122] በማለት ዮሴፍ የአማልክትን አምላክ፣ የጌቶችን ጌታ፣ የነገሥታትን ንጉሥ በማሕፀኗ የተሸከመች ቅድስት ድንግል ማርያምን እንዳገለገለ አስተምሯል።

ይኽ ነገር አረጋዊ ዮሴፍን ብቻ ሳይኾን ቅድስተ ቅዱሳኑን የሚያገለግል ሊቀ ካህናቱ ዘካርያስ በደብረ ሲና በታላቅ ግርማ የተገለጠውን አምላክ በማሕፀኗ የተሸከመች የአምላክ ዙፋን ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ሚስቱ ኤልሳቤጥን ለመጐብኘት ወደ ቤቱ በመጣች ጊዜ በታላቅ ፍርሃት እንደተዋጠ ሲገልጽ ‹‹When the high priest, Marveling looks on you...›› (ሊቀ ካህናቱ (ዘካርያስ) ተመልክቶሽ ሲያደንቅሽ አንደበት የለውም ነበር፤ በአንቺ ተገርሞ ነበርና፤ ልዑል ዐድሮብሻል፤ ኹለንተናሽ በሲና እንደተገለጠው ጥቁር ደመና ግሩም ነው፤ ሽማግሌው ካህን ሲመለከትሽ ይርዳል)[123] በማለት የቅድስት ድንግል ማርያም ማሕፀን ከሲና ደመና ይልቅ የማያርድ የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ መኾኑን በስፋትና በጥልቀት ገልጾታል።

122. Jacob of Serugh, On The Annunciation, ET by M. Hansbury, p.59
123. ibid, p.54





ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በተገለጠ ጊዜ ተራራው ይጤስ፤ ፈጽሞ ይናወጥ ይንቀጠቀጥ ነበር፤ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በኪሩቤል በሱራፌል ዐድሮ ሰፍሮ የሚኖረውን ከግርማው የተነሣ የሲና ተራራ እቀልጥ እፈርስ እናድ ያለችለት ሰማያዊ መለኮትን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ ተሸክማ፤ ኹሉን የያዘ አምላክን በክንዷ ታቅፋ፤ የፈጠረውን ፍጥረት በዝናብ አብቅሎ በፀሓይ አብስሎ የሚመግበውን ጌታን ከድንግልና ጡቶቿ ወተትን ያጠባች መኾኗ ምን ይደንቅ! ምን ይረቅ።

ሊቃውንትም በዚኽ በጠለቀ ልዩ ትምህርታቸው ‹‹Mary's bosom is like the cloud over mount Sinai...›› (የማርያም ዕቅፍ በሲና ተራራ ላይ ያለን ደመና ይመስላል፤ የልዑላን ጌታ በዚያ ውስጥ የሚኖርበት (ደመና) ታላቅ ድንቅ ነበር፤ ተራራው ይንቀጠቀጥ ነበርና፤ የማርያም ዕቅፍ ግን ፈጽሞ አልታወከም (አልተነቃነቀም)[124] በማለት ደብረ ነባቢት ተብላ ክብሯ ዘወትር የሚነገርላት ከሲና ተራራ ይልቅ ያማረች፣ የከበረች፣ የተዋበች ለአምላክ ማደሪያነት የበቃች መኾኗን አስተምረዋል።

ኢትዮጵያዊ ቂርሎስ የተባለ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ምስጢር በጥልቀት ሲገልጥ "ኦ ድንግል ደብረ መቅደሱ ለእግዚአብሔር እንተ በላዕሌሃ አስተርአየ አርአያ ሁሩኒ ከመ ንደተ እሳት ዘያንበለብል በቅድሜሆሙ ለእስራኤል ወደብሩ ይበርት ከመ ብርሃን ዘለንጻስ የዐውዳ መሲ ያወሥእ ወእግዚአብሔር ይሰጠም" (በእስራኤል ፊት እንደ እሳት ከነዳድ ከሚያንበለብል የብርሃን አምሳል በላይዋ የተገለጠ ድንግል ሆይ የእግዚአብሔር የመቅደሱ ተራራ ነሽ፤ ተራራውም የእሳት ላንቃ ብርሃን እንደሚዘረው (እንደሚከበው) ይበርቃል ብልጭ ብልጭ ይላል፤ ሙሴ ይናገራል እግዚአብሔርም ይመልስለታል)[125] በማለት በደብረ ሲና ጌታና ሙሴ ተነጋገሩባት እንጂ ተራራዋ አልተነጋገረችም እመቤታችን ግን ተናግራ በምልጃዋ ለጻድቃን ዕሴት ለኃጥአን ስርየት ታስጣለችና ደብር ነባቢት (የምትናገር ተራራ) ለምን እንደተባለች በማብራራት አስተምሯል።

124. Bride of light, p. 98
125. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፻፶



www.ethiopianorthodox.org

## የቃል ኪዳን ታቦት

የአምላክ ማደሪያ ቅድስት ድንግል ማርያም በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ ጥበብና ማስተዋል በተሰጠው በባስልኤል እጅ በተሰራችው የቃል ኪዳን ታቦት ትመሰላለች (ዘፀ ፳፭፥፱-፳፤ ፴፯፥፩-፲፭)፡፡ ይኸቺ የእግዚአብሔር የጌትነቱ መገለጫ የኾነችው የቃል ኪዳን ታቦት ባሕረ ዮርዳኖስን የከፈለች (ኢያ ፫፥፲፬-፲፯) ዳጎን የተባለ በፍልስጥኤም ይመለክ የነበረ ጣዖትን ቀጥቅጣ ያጠፋች (፩ሳሙ ፭፥፩-፭፤ ፪ቆሮ ፮፥፲፮)፤ በድፍረት ሊነካት የሞከረ ኦዛን የቀሰፈች (፪ሳሙ ፮፥፯)፤ በታላቅ ክብር ወደ ሀገሯ ስትመለስ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ በፊቷ የዘመረላት (፪ሳሙ ፮፥፲፬-፳፫)፤ ልጁ ሰሎሞንም ታላቅ ቤተ መቅደስ ሠርቶ በክብር ያኖራት ናት (፩ነገ ፰፥፩-፲፩)፡፡

ጌታ የታቦቷን አሠራር ሲነግረው ሽምሽር ሰጢን ከሚባል፤ ከማይነቅዝ ዕንጨት ቀርጸኽ አብጅ፤ ከታች እንደ ዙፋን አራት እግር አውጣለት ሞላልነቱን ኹለት ክንድ ከስንዝር፣ ቁመቱ ክንድ ከስንዝር፣ ወርዱን ክንድ ከስንዝር አድርግ፤ ኹለት ክንድ ከስንዝር ምስሃል ለዚኽ ቁመት የለውም፤ አራት ቀለበት፤ ኹለት ሙሎጊያ አብጅለት አፍአውን ውስጡን በንጹሕ ወርቅ ለብጠው፤ በምስማኩና በምስማኩ ኹለቱን ኪሩቤል እንደሚናተፉ አውራ ዶሮዎች አንገታቸውን ደፋ አድርገኽ ክንፋቸውን ዘረር አድርገኽ በላይ ሣልበት፤ ዙሪያውን ፈለግ አውጣለት፤ ብጽብጽ ወርቅ አፍስበት፤ ጽላቶቹን በውስጡ አኑር ብሎታል፡፡

ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ታቦት የእመቤታችን፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ታቹ መቀመጫው የንጹሐት እንስት፤ ላዩ መግጠሚያው የንጹሓን አበው፤ ግራ ቀኙ የሐና የኢያቄም፤ ወደ ውስጥ የገባችው የድንግል ማርያም፤ ያቺ በመኻከላቸው እንደኾነች እመቤታችንም ከሐና ከኢያቄም ለመገኘቷ ምሳሌ ነው፤ ኹለት ክንድ ከስንዝር ሞላልነቱ ከአዳም እስከ ኖኅ ባለው ዘመን ይመሰላል፤ ይኸውም ፪ሺ.ሕ ከ፪፻፶፮ ይኾናል፤ ይኸ በኾነ በ፪ሺ.ሕ ከ፪፻፶፮ ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ኖኅ ለመገኘቷ ምሳሌ፡፡

ክንድ ከስንዝር ቁመቱ ከኖኅ እስከ ሙሴ ባለው ዘመን ይመሰላል፤ ይኸውም ሺ.ሕ ከ ፯፻ ይኾናል፤ ይኸ በኾነ በሺ.ሕ ከ፯፻ ዘመን አርአያ ድንግል ጽላተ ሙሴ ለመገኘቷ ምሳሌ፡፡ ክንድ ከስንዝር ወርዱ ከሙሴ እስከ እመቤታችን





ባለው ዘመን ይመሰላል፤ ይኸውም ሺ.ሕ ከ፯፻፵፬ ይኾናል፤ ይኸ በኾነ በሺ.ሕ ከ፯፻ ፵፬ ዘመን አርአያ ድንግል ታቦተ ኖኅ አርአያ ድንግል ጽላተ ሙሴ ምሳሌዎቿ የሚኾኑ አማናዊት ድንግል ለመገኘቷ ምሳሌ ነው፡፡

አራቱ ቀለበት የአራቱ ወገን ንጽሕናዋ ምሳሌ ይኸውም ከርእይ (ኀጢአትን ከማየት)፣ ከሰሚዕ (ኀጢአትን ከመስማት)፣ ከገሲስ (በእጅ ዳስሶ ኀጢአትን ከመሥራት)፣ ከአጼንዎ (የኀጢአት መዐዛን ከማሽተት) እመቤታችን ከነዚኽ ኹሉ ተጠብቃለችና (መሓ ፬፥፯)፤ ኹለቱ ቀለበት የፍቅረ እግዚአብሔርና የፍቅረ ቢጽ ምሳሌ፤ ኹለቱ ሥዕለ ኪሩቤል የጠባቂ መልአክ የቅዱስ ሚካኤልና የአብሣሪ መልአክ የቅዱስ ገብርኤል ምሳሌ ናቸው፤ ይኸውም የብሉይ ሊቀ ካህናት ባመት አንድ ቀን ገብቶ ከኹለቱ ኪሩቤል መኻከል ቃል ሰምቶ ይወጣ ነበር፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም በሊቀ መላእክት በቅዱስ ሚካኤል ተጠብቃ ከቅዱስ ገብርኤል ቃል ሰምታ አካላዊ ቃልን በግብረ መንፈስ ቅዱስ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ ፀንሳ ተገኝታለችና ( ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰)፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ይኽነን መንፈሳዊ ምስጢር በጥልቀት በመመርመር ድንግል ማርያምን በምስጢር የተመላች ታቦት፣ እሳትን የተመላች ታቦት፣ የቅዱስ ቃል ታቦት፣ የቃል ኪዳን ታቦት በማለት ገልጿታል፤ የዚኽ አባት ይኽነን ጥልቅ ትምህርቱን ወደፊት በመጽሐፈ ሳሙኤል ላይ በስፋት ተንትነናዋለኊ፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ በመጽሐፈ ምስጢር ላይ የታቦትን ነገር ሲተረጕም "እምቅድመ የሀብ እግዚአብሔር ለሙሴ ኦሪተ በጽላተ ሰማይ አዘዘ ለሙሴ ከመ ያስተዳሉ ላቲ ታቦተ ለሙዳዩ፡፡ ከማሁ አስተዳለዋ ለድንግል ከመ ትኩን ስርጉተ በቅድስና ወበንጽሕ ወዘይቤሰ ወትቀፍላ ወርቀ ንጹሐ እንተ ውስጣ ወእንተ አፍአሃ፡፡ ወለዝሰ ፍካሬሁ ይትመየጥ ኀበ ድንግል እንተ ውስጣ ዘይቤ በጾም ወበጸሎት ወበንጽሐ ሥጋ ዘይኤድሞ ለመንፈስ ቅዱስ" (እግዚአብሔር በሰማይ ጽላት ኦሪትን ለሙሴ ከመስጠቱ አስቀድሞ ለመኖሪያዋ ታቦትን እንዲያዘጋጅ አዘዘው፤ እንዲኹ ድንግልን በቅድስናና በንጽሕና ያጌጠች ትኾን ዘንድ አዘጋጃት፤ በውስጥና በውጪዋ በንጹሕ ወርቅ ለብጣት ያለው የዚኽስ ትርጕም በድንግል ይተረጐማል፤ በውስጧ ያለው በየዋህነትና በማስተዋል ይተረጐማል፤



www.ethiopianorthodox.org

በውጪዋም ያለው በጾምና በጸሎት መንፈስ ቅዱስንም ደስ በሚያሰኘው በሥጋ ንጽሕና ይተረጐማል)[126] በማለት ይኸቺ የቃል ኪዳን ታቦት ትመጣ ዘንድ ያላት የአምላክ ታቦት (ማደሪያ) የኾነችው በንጽሕና፣ በቅድስና የተጌጠችው የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን በስፋት ገልጦታል።

## ማዕድ

የኅብስተ ሕይወት የክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ኅብስተ ገጹን በያዘችው ማዕድ (ገበታ) ትመሰላለች (ዘፀ ፳፭፥፳፫-፴)። ማዕድንም ጌታ ሽምሽር ሰጢን ከሚባል ከማይነቅዝ ዕንጨት ቁርጠኽ ሥራ ብሎታል፤ ይኸውም አቈልቋዩ ኹለት ክንድ፤ ወርዱ ክንድ፤ ቁመቱ ክንድ ከስንዝር ይኹን፤ በዙሪያውም ጋት ሙሉ ክንፈር አብጅለት፡፡አፍኣው ውስጡን በወርቅ ለብጠው፤ እግሩን እንደ ዙፋን አልጋ ሽንኮር ለብቻው ቀረጸው፤ በዙሪያው አራት ቀለበት አበጅለት፤ እግሩና ክንፈሩ በአራቱ ማእዘን አድርገው፤ ኹለቱ መሎጊያን ሠርተኽ በወርቅ ለብጣቸው፤ መሎጊያዎቹን ከቀለበት አግባ፤ ዘወትር ኅብስቱን ከማዕድ ላይ አድርገው ብሎታል፤ ጢት ስድስት አምጥተው ስድስቱን ሰውተው ስድስቱን ያኖሩ ነበርና የጢት ለማታ የማታው ለጢት ይኹን ብሏቸዋል።

ይኽም ምሳሌ ነው ማዕድ የመስቀል፤ ኅስስት የጌታ፤ ስድስቱ ጠዋት ስድስቱ ማታ ይቀርብ እንደነበር ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን የሠራ ጌታ ጢት ማታ እየተሠዋ ስንቀበለው የመኖራችን ምሳሌ፤ ዳግመኛም ማዕድ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ኅብስት የኅብስተ ሕይወት የክርስቶስ ምሳሌ ነውና፤ የሕይወት ኅብስት ጌታን በድንግልና ሀንሳ በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን አማናዊት ማዕድ (ገበታችን) ቅድስት ድንግልን ዘወትር እናመሰግናታለን።

ሊቁ አባ ሕርያቆስም ፭ሺሕ፭፻ ዘመን በረሃበ ነፍስ ሲሰቃዩ ለነበሩ ለሰው ልጆች ኹሉ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም፤ የሕይወት ውሃ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይጠማም ብሎ እውነተኛ መብል ክብር ሥጋውን እውነተኛ መጠጥ የክበረ ደሙን የሰጠን ኢየሱስ ክርስቶስን በመውለዷ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ *‹‹ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ*

126. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ መጽሐፈ ምስጢር ገጽ ፪፻፩





*ሕይወት ዘበአማን›* (ማርያም ሆይ ስለዚኽ ነገር እንወድሻለን፤ ከፍ ከፍም እናደርግሻለን፤ እውነተኛውን መብልን እውነተኛውን የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናንና)[127] በማለት የኅብስተ ሕይወት የክርስቶስ እናት አማናዊት ገበታ ቅድስት ድንግልን አመስግኗል።

የእመቤታችን ፍቅሯ ምስጋናዋ የበዛላት አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫም በምስጋናው ላይ *‹‹ተፈሥሒ ኦ ማዕደ ወርቅ እንተ ትፀውር መዐዛ ሠናየ ዘውኩፍ ቅድመ ልዑል››* (በልዑል እግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያለውን በጎ መዐዛን የምትሸከም የወርቅ ማዕድ (ገበታ) ሆይ ደስ ይበልሽ)[128] በማለት የምሳሌውን እውነትነት አስተምሯል።

## መቅረዝ

እውነተኛው የዓለም ብርሃን ክርስቶስ አባታችንን የወለደችልን የብርሃን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ሰባት አዕጹቅ ባሏት የወርቅ መቅረዝ ትመሰላለች (ዘፀ ፳፭፥፴፩-፵)።. ጌታ ለሙሴ የተቅዋምን አሠራር ሲነግረው አንዱን መክሊት ወርቅ መቅረዝ አብጅ፤ ከታች እንደ ጽዋ እግር አውጣለት ከፍ ብለኽ አንድ መሸቢያ ቃትተኽ ተወው፤ ከፍ ብለኽ ሦስት መሸቢያ አዙርበት፤ ኹለት ኹለት አጽቅ አውጣለት፤ ስድስት ይኾናል፤ መኻከሉ ሥረ ወጥ ይኹን አትቀጥልበት፤ ሰባት ሰባት ምንባረ ፈትል አበጅለት፤ በመኻከሉ ገንቦ ሙሉ ዘይት ቅዳበት፤ በመኻከሉ የተቀዳው በአዕጹቁ ኹሉ እንዲበራ ብሎታል።

ይኸውም ምሳሌ ነው፤ ተቅዋም የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ወርቅ መኾኑ ወርቅ ከሰባቱ መዓድናት በላይ እንደኾነ የብርሃን እናቱ እመቤታችንም መትሐተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን (ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ) ናትና (መሐ ፯፥፲፤ ራእ ፲፪፥፩)፤ ታቹ የኃምስ ጠባባት (የዐምስቱ ልባሞች) ማቱ ፳፭፥፬፤ ከፍ ብለኽ ሦስት መሸቢያ አዙርበት አለው፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም በሦስት ነገር ንጽሕት ናትና (በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና)፤ሰባት አዕጹቅ የፍጹም ክብሯ፤ እስመ ትልቀ ሳብዕ በነበ ሰብራውያን ፍጹም ውእቱ እንዲል ሰባት በዕብራውያን ፍጹም እንደኾነ እመቤታችንም በክብር ፍጽምት ናትና የዚያ ምሳሌ፤ምንባር የማሕፀኗ፣ ፈትል የአራቱ

127. አባ ሕርያቆስ፣ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፲፪
128. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አርጋኖን ዘነሙስ ፴፥፲፯



www.ethiopianorthodox.org

ባሕርያት፤ ዘይት የነባቢት ነፍስ፤ ፋና የመለኮት፤ ማፈኛ መግጠሚያ ወለባ የማኅተመ ድንግልናዋ ምሳሌ፤ይኸነኑ ሰባት ሰባቱን ምንባረ ፈትል አንድ አድርጐ አገናዝቦ ቢቈጥሩት ፵፱ ይኾናል። (፯ x ፯=፵፱) ይኸውም እመቤታችን የዓለም ብርሃን ክርስቶስን ከወለደች በኋላ በዚኽ ዓለም የኖረችዉ ዕድሜዋ ፵፱ ዘመን መኾኑን የሚያሳይ ነውና፤ በርካቶች የነገረ መለኮት ምሁራን በስፋትና በጥልቀት ቅድስት ድንግል ማርያምን በመቅረዝ መድኀኒታችን ዐማኑኤልን በብርሃን እየመሰሉ አስተምረዋል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ለ፭ሺ.ሕ፭፻ ዘመን በሞተ ሥጋ ላይ ሞተ ነፍስ በርደት መቃብር ላይ ርደተ ሲኦል ተፈርዶብን በጽኑ ጨለማ ለነበርነው ለሰው ልጆች ይኽነን ጽኑ የጨለማና የሞት ጥላ አስወግዶ የጣለ እውነተኛውን ብርሃን ኢየሱስ ክርስቶስን ፱ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች አማናዊት መቅረዝ መኾኗን በእሑድ ውዳሴ ማርያም ላይ *«አንቲ ውእቱ ተቅዋም ዘወርቅ እንተ ጾርኪ ማኅቶተ ጸዳል ኵሎ ጊዜ ዘውእቱ ብርሃኑ ለዓለም...»* (ኹል ጊዜ ብርሃንነት ያለውን ፋና የተሸከምሽ የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ፤ ይኸውም ፋና የዓለም ብርሃን ነው፤ ጥንት ከሌለው ብርሃን የተገኘ ብርሃን ነው፤ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ እውነተኛ አምላክ ነው፤ ያለመለወጥም ከአንቺ ሰው የኾነው ነው ፤በመምጣቱም (ሰው በመኾኑንም) በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ ለምንኖር ለኛ አበራልን)[129] በማለት አስተምሯል (ኢሳ ፱፥፩-፪፤ ማቴ ፬፥፲፬-፲፮)።

ታላቁ የዜማ አባት ሊቁ ቅዱስ ያሬድም እውነተኛውን የዓለም ብርሃን ክርስቶስ አምላካችንን የወለደችልን እውነተኛዪቱ የወርቅ ተቅዋም ስለኾነችው ስለ ቅድስተ ቅዱሳን ንጽሕተ ንጹሐን ቅድስት ድንግል ማርያም በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ *«አንቲ ውእቱ ተቅዋም ዘወርቅ ዘኢገብራ እደ ኬንያ ዘሰብእ...»* (የብልኀተኛ እጅ ያልሠራት በወስጧም መብራት የሚያበሩባት የወርቅ መቅረዝ አንቺ ነሽ፤ ራሱ የአብ ብርሃን ያበራባታል እንጂ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን ወደ አንቺ መጥቶ ዐደረ፤ በአምላክነቱም በዓለም ኹሉ አበራ፤ ጨለማን ከሰዎች ላይ አራቀ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ በብርሃኔ እመኑ ብርሃን ሳለላችኁ ተመላለሱ ብሎ በሚያድን ቃሉ አዳነን)[130] ዮሐ ፲፪፥፴፭፤ ፩ኛዮሐ

129. ቅዱስ ኤፍሬም፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስትያን ቅድስት
130. ቅዱስ ያሬድ፤ አንቀጸ ብርሃን፤ቍ ፫





፩፥፭ ፤በማለት ምስጢሩን እያራቀቀ ተርጕሞታል።

## ደብተራ ኦሪት

ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሰማያዊት ድንኳን አምሳል በተሠራች በውስጧም ብዙ ንዋያተ ቅድሳት በያዘችው የምስክሩ ድንኳን ትመሰላለች (ዘፀ ፳፮፥፩-፴)። ልዑል እግዚአብሔር አገልጋዩ ሙሴ ደብረ ሲና ላይ አውጥቶ የብርሃን ድንኳንን ካሳየው በኋላ በዚያ አምሳል ሥራ በማለት አዞታል። ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በአርያም ዜማው *«ቀዳሚሁ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበግዳም አርአዮ ለሙሴ ዘከመ ይገብር ግብራ ለደብተራ»* (ከጽዮን አስቀድሞ ሰማይን ፈጠረ፤ ዳግመኛም ለሙሴ እንደምን እንደሚሠራ የድንኳኗን አሠራር አሳየው)[131] በማለት ደብተራ ኦሪት በሰማያዊቷ ደብተራ ብርሃን አምሳል መሠራቷን ገልጿል።

ይኽቺ ደብተራ ኦሪት እስራኤላውያን አምላካቸው ከነሱ የማይለይና በመኻከላቸውም ዐድሮ የሚኖር መኾኑን የሚረዱባት ልዩ ምልክታቸው ነበር። ድንኳኗም የተሠራችው የእስራኤል ልጆች ባመጡት ስጦታ ሲኾን ከስጦታቸው ብዛት የተነሣ ተጨማሪ ስጦታ እንዳይመጣ በእስራኤላውያን ሰፈር ዐዋጅ ተነግሯል (ዘፀ ፴፯፥፲፯-፳፬)። ኦሪት ዘፀአት ምዕራፍ ፳፭፤ ፳፮፤ ፳፯፤ ፴፭፤ ፴፮፤ ፴፯፤ ፴፱ እና ፵ የደብተራ ኦሪት አሠራርን በስፋት ይገልጻል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ለደብተራ ኦሪት ሦስት የተለያዩ ሥያሜ ተሰጥቷታል፤ ይኸውም የመገናኛ ድንኳን (ዘፀ ፴፱፥፴፪፤፵፥፪-፮፤፩ዜና ፮፥፴፪) የምስክሩ ማደሪያና ዘኍ ፩፥፶፫፤፲፥፲፪)፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ ትባላለች (ዘኍ ፴፩፥፴፤ ፴፩፥፵፯፤፩ዜና ፳፩፥፳፱፤ ፪ዜና ፩፥፭)፤ ይኽቺውም ደብተራ ኦሪት ወርዷ ፴ ክንድ ሲኾን በሦስት ክፍሎች ትከፈላለች፤ የመገናኛዪቱ አሥራቱ ክንድ ቅድስተ ቅዱሳን ስትኾን ሊቀ ካህናቱ በዓመት አንድ ጊዜ ስለራሱና ስለሕዝቡ ኀጢአት የሚረጭ ደም ይዞ ይገባባታል (ዕብ ፱፥፯)፤ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥም ጽላተ ሕግ ያለበት እና ኪሩቤል ክንፋቸውን የሚጋርዱት ታቦት፤ መናውን የያዘች መሶበ ወርቅ፤የለመለመች የአሮን በትርና የወርቅ ማዕጠንት ነበሩ(ዕብ ፱፥፫-፭)።

131. ቅዱስ ያሬድ፤ጾመ ድጓ ፤ገጽ ፲፰



www.ethiopianorthodox.org

ኹለተኛዪቱ ሃያይቱ ክንድ ቅድስት ስትኾን ሌዋውያን ካህናት ዘወትር እየገቡ ይጸልዩባታል፤ መሥዋዕት ይሠዉባታል፤ በቅድስት ውስጥም መቅረዝ፣ ኅብስተ ገጽ ያለባት ማዕድ (ገበታ)፣ የዕጣን መሠዊያና ለማቃጠል መሥዋዕት የሚኾን መሠዊያ ይገኝ ነበር፡፡ ሦስተኛዪቱም ዐጸደ ደብተራ ኦሪት (ዐደባባይ) ስትኾን ካህናቱ ሕጻቸውን እግራቸውን የሚታጠቡባትና፣ ተረፈ መሥዋዕት የሚበላባት ናት (ዘፀ ፳፮፥፴፩፤ ፴፥፲፰፤ ዘሌ ፲፥፳፯)፡፡

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልዕክቱ በምዕ ፱፥፩-፭ ስለመገናኛ ድንኳኒቱ አገልግሎትና በውስጧ ስላሉት ንዋያተ ቅድሳት ከዘረዘረ በኋላ ይኽቺ ድንኳን በዘመነ ሥጋዌ ሊገለጽ ስላለው ታላቅ ነገር ምሳሌ እንደነበረች ሲገልጽ በዚኹ ምዕራፍ በቍጥር ፱-፲ «ይኽም ለአኹኑ ጊዜ ምሳሌ ነው» ሲል ገልጾታል፡፡

ይኸውም ደብተራ (ድንኳኗ) የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ፤ ቅድስት የነፍሷ፤ ቅዱሳን የሥጋዋ፤ ታቦት የመንፈስ ቅዱስ፤ ጽላት የልቡናዋ፤ ቃሉ በመንፈስ ቅዱስ የተገለጸላት ምስጢር (ሉቃ ፩፥፲፱፤፴፩)፤ አንድም ቅዱሳን የሥጋዋና የነፍሷ፤ ቅድስት የልቡናዋ፤ ታቦት የማሕፀኗ፤ ጽላት የትስብእት፤ ቃሉ የመለኮት (ዮሐ ፩፥፲፬)፤ ምሳሌ መኾኑን መተርጕማን አስተምረዋል፡፡ ዳግመኛም በዚያች በደብተራ ኦሪት ሙሴ አሮን አምልኮቱን ይመሰክሩባት እንደነበር በቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያምም አንድነትና ሦስትነት ታውቆባታል፤ ይኸውም ጌታ ከእመቤታችን ከመወለዱ አስቀድሞ እንደዛሬው የሥላሴ አንድነት ሦስትነት በገሃ በተረዳ አልታወቀም ነበር፤ ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲኽ የአንድነት የሦስትነት ምስጢር በገሃ በተረዳ ነገር ታውቋልና፤ ዳግመኛም ሊቀ ካህናቱ ሲገባ ከምስሐል አዕናቍ ድምፅ ይሰማ እንደነበር እመቤታችንም እውነተኛውን ሊቀ ካህናት ጌታን ሀንሳ ሳለ መላእክት በማሕፀኗ ዐድረው ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ሲያመሰግኑ አንገቷን ዘለስ አድርጋ ትሰማ ነበርና «ወታደንን ድንግል ርዕሳ መንገላ ከርሣ ወትሰምዕ ቃለ እመላእክት ከመ ወላዲተ እግዚአብሔር ይእቲ» (ድንግል አንገቷን ወደ ኾዷ ዘንበል አድርጋ የእግዚአብሔር እናት እንደኾነች ከመላእክት ቃልን ትሰማ ነበር)[132] እንዲል፡፡

132. መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡና ትርጓሜው፤ ገጽ ፹፫





ታላቁ አባት ቅዱስ ኤፍሬምም ወልደ እግዚአብሔርን ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች አማናዊት ደብተራ መኾኗን በውዳሴ ማርያም ሲያመሰጥር «አንቲ ውእቱ ደብተራ እንተ ተሰመይኪ ቅድስተ ቅዱሳን ወውስቴታ ታቦት በወርቅ ልቡጥ እምኵለሄ ወውስቴታ ጽላተ ኪዳን መሶበ ወርቅ እንተ መና ኅቡእ ዘውእቱ ወልደ እግዚአብሔር መጽአ ወኀደረ ኀበ ማርያም ድንግል» (ቅድስተ ቅዱሳን (ከተለዩ የተለየች) የተባልሽ የኪዳን ጽላት ያሉብሽ የተሰወረ መና ያለበት የወርቅ መሶብ ያለብሽ ደብተራ ድንኳን አንቺ ነሽ፤ ይኸውም መና የተባለው መጥቶ በድንግል ማርያም ማሕፀን ያደረው የእግዚአብሔር ልጅ ነው)[133] በማለት በስፋት ገልጾታል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ የተናገረላት ደብተራ ኦሪት፤ የመለኮት ማደሪያ የኾነችው የቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን «ተፈሥሒ ኦ ደብተራ ብርሃን ማኅደሩ ለዐቢይ ሊቀ ካህናት » (የታላቁ ሊቀ ካህናት ማደሪያ የብርሃን ድንኳን ሆይ ደስ ይበልሽ)[134] በማለት የሊቀ ካህናት የባሕርይ አምላክ የክርስቶስ እናት አማናዊት ድንኳን መኾኗን መስክሯል፡፡

ይኽቺ በብሉይ ኪዳን በእመቤታችን ምሳሌ የተገለጸች ኦሪታዊት ድንኳን ኋላ በሐዲስ ኪዳን በቅድስት ድንግል ማርያም ተተክታ ሐዋርያው ጳውሎስ በዕብ ፱፥፫-፭ ላይ ስለ እሷ በመጻፉ በርካቶች ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት የጳውሎስ ድንኳን በማለት ቅድስት ድንግል ማርያምን አመስግነዋታል፡፡ ከነርሱም መኻከል ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*«ኦ እግዝእትየ ማርያም ደብተራ ሳውል መምህረ ቲቶ*
*ሊቀ ካህናት ሰማያዊ ዘረሰየኪ ምብያቶ*
*አመ ደመረ ውስተ ሥጋኪ ዘኢይትነገር መለኮቶ*
*ዘኢይክሉ ማኅበራነ ሱራፌል ለኪፎቶ*
*ወኢሰራዊተ ኪሩቤል ነጽሮቶ*
*ዘብከ ከሠተ ሣህሎ ወምሕረቶ*
*ወበእንቲአኪ አርአየ ቅድመ አድኅኖቶ»*

133. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘቀዳሚት
134. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ አርጋኖን ዘኀሙስ ፬፥፲፪



www.ethiopianorthodox.org

(ስለአንቺ የማዳንን ሥራ አስቀድሞ ያሳየ ምሕረቱንና ይቅርታውን በአንቺ የገለጠ፤ የሱራፌል አንድነት መዳሰሱን፤ የኪሩቤል ሰራዊትም ማየቱን የማይችሉ፤ የማይመረመር መለኮቱን ከሥጋሽ ጋር ባዋሐደ ጊዜ፤ ሰማያዊ የካህናት አለቃ ማደሪያውን ያደረገሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ የቲቶ መምህር የሳውል (የጳውሎስ) ድንኳን ነሽ)[135] በማለት ምስጢሩን በማራቀቅ ገልጾታል፡፡

## ልብሰ አሮን

ትውልድ ኹሉ የሚያመሰግኗት አምላክን የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሊቀ ካህናቱ በአሮን በልብሰ ተክህኖው ላይ ባለች ሻኩራ ትመሰላለች(ዘፀ ፳፰፥፮-፴፭፤ ፴፱፥፩-፳፱)፡፡ ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር ሙሴን ወደመገናኛው ድንኳን ሲገባ የተቀደሰውን ልብስ ለክብርና ለጌጥ እንዲኾን ለወንድምኽ ለአሮን ሥራለት ብሎታል፤ እሱም ዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል በየነገዳቸው የተጻፉባቸው እንደ ዕንቍ ፈርጥ ያለ በፊቱ ስድስት በኋላው ስድስት በድምሩ ዐሥራ ኹለት ሻኩሮች ያሏት ልብስ አሠርቶ አልብሶታል ሲሔድ ሿ ሿ ትላለች፤ሕዝቡም ድምጿን እየሰሙ አኹን ለማዕጠንት አኹን ለመሥዋዕት ገባ እያሉ ለጸሎት የሚተጉ ኹነዋል፡፡

ድምፅ መሰማቱ መላእክት እንዳይቀስፉት ሲኾን ይኸውም ከንጉሥ እልፍኝ ብላቴና ሳይናገርለት ወይም ድምፅ ሳያሰማ ቢገባ ቅጣት እንደሚያገኘው በዚያ ልማድ አሮን እንዳይቀሰፍ ይኽነን ሥርዐት ሠርቶለታል (ዘፀ ፳፰፥፴፭)፤ ዳግመኛም በድምፁ አማካይነት ደዌያት እንዲከለከሉ ነበር፡፡

ይኸውም ምሳሌ ነው ልብስ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ዐሥራ ኹለት አዕናቍ የዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት፤ ከዚያ ድምፅ መሰማቱ ሐዋርያት ወላዲተ አምላክ ብለው የማስተማራቸው ምሳሌ ነው (መዝ ፵፬፥፱-፲፯፤ ፵፯፥፩-፯፤ ገላ ፬፥፬፤ ራእ ፲፪፥፩-፫)፡፡ አንድም ሻኩራ የንጹሐን አበው ምሳሌ፤ ከዚያ በሚሰማው ድምፅ ደዌያት ይከለከሉ ይርቁ እንደነበር አካላዊ ቃልም ከእመቤታችን ሰው ከኾነ በኋላ ፍዳ መርገም ጠፍቷልና፡፡ አንድም ልብስ የእመቤታችን ፤ጸናጽል ጌታችን ከእርሷ የነሣው ሥጋ፤ ድምፁ የአካላዊ ቃል ምሳሌ መኾኑን መተርጉማን በማረቀቅ ተርጉመውታል፤ ከነዚኽ መኻከል እነ

135. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ እንዚራ ስብሐት ገጽ 48





ጎርጎሬዎስ ዘእንዚናዙ፣ እነ አባ ሕርያቆስ፣ እነ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ይገኙበታል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ይኽነን ምስጢር እያረቀቀ ሲተረጉም ‹‹ኦ ልብሰ ቅድስና ዘዐቢይ ሊቀ ካህናት ዘእምጸዴር ወዘእሜላት ዘእምቢሶስ ክቡብ ወእምሕብረ ያክንት ዕስቅት ዘበፈትለ ወርቅ ዘምስለ ደርከኖ ሠናየ ግብረት ወውስቴታ ሰርጕ ዘበዐሥርቱ ወክልኤቱ ባሕርያት እለ ጽሑፋት በበአስማቲሆሙ ለዐሥርቱ ወክልኤቱ ነገደ እስራኤል እለ ተሰምዩ ዕፀወ ዘይት፤ ወፍካሬሆሙሰ ዘበአማን ለዐሥርቱ ወክልኤቱ ባሕርያት ይተረጐም በዐሥርቱ ወክልኤቱ ሐዋርያት፤ ወእሉ እሙንቱ ደቂቀ ባሕርየ መለኮት፤ ወውስቴታ ካልዕ ልብሰ ሄጳዴጤን ወጸናጽላት ወርቅ ከመ ፍሬያተ ሮማን ዘውእቶሙ ቅዱሳን ሰማዕት ሰርጎ ትርሲታ ለመርዓት ወመኃትዊሃ ቅዱሳን ዘእንበለ ጥፍኢት›› (አሠራረ መልካም ከሚኾን ደርከኖ ከሚባል ልብሰ ተክህኖ ጋር በወርቅ ፈትል የሮማን ፍሬ ቅርጽ ካለው ዕንቍ በወርቅ ፈትል የተጠለፈች ከለስላሳ የልብስ ክታን ፈትል ከሐርና ከካባ በድርብ የተሠራች የታላቅ ሊቀ ካህናት ልብስ ሆይ፤ ዐሥራ ኹለቱ ነገድ እስራኤል በየስመ ነገዳቸው የዘይት ዕንጨቶች የተባሉ የዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል በየነገዳቸው በተጻፉባቸው ምሳሌም የዐሥራ ኹለት አዕናቍ ጌጥ በውስጧ አለ፤ የዐሥራ ኹለት አዕናቍ አማናዊ ትርጓሜዉንም በዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት መስሎ ይተረጉመዋል፤ እሊኹም የመለኮት ባሕርይ (የባሕርያዊ አምላክ) ደቀ መዛሙርት ናቸው፡፡ በውስጧም እንደ ሮማን ፍሬ ያለ የወርቅ ሻኩራ እጅጌ ሰፊ ልብስ ተክህኖ ያለባት እነዚያም ሻኩራዎቿ የተባሉ የሙሽራዪቱ (የቤተክርስትያን) የጌጥ ሽልማት ቅዱሳን ሰማዕት ናቸው፤ ያለመጥፋት የሚበሩ ልዩዎች ፋናዎቿ ናቸው)[136] በማለት ሲያስተምር፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስ ምስጢሩን በመጠቅለል በቅዳሴው በቍ፴፫ላይ ‹‹ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን ካህን›› (በአሮን በልብሱ ላይ ያለች ጸናጽል አንቺ ነሽ) በማለት አመስግኗታል ፡፡

## የወርቅ ማዕጠንት

መለኮታዊ እሳትን በማሕፀኗ የተሸከመች ቅድስት ድንግል ማርያም

136. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፲፩፥፲፬



www.ethiopianorthodox.org

እሳታዊ ፍሕምን በያዘው የወርቅ ማዕጠንት ትመስላለች (ዘፀ ፴፥፩-፫)። ልዑል እግዚአብሔር ሊቀ ነቢያት ሙሴን የወርቅ ማዕጠንትን ከማይነቅዝ ዕንጨት ቀርጾ እንዲያበጅ ቁመቱን ኹለት ክንድ ከስንዝር፤ አቆልቋዩን አንድ ክንድ፤ ወርዱን አንድ ክንድ እንዲያደርገው፤ ክንዱን ሙሉ ወደ ላይ እንዲፈለፍለው፤ ክንዱን ሙሉ ወደታች እንዲተወው፤ አፍኣውን ውስጡን በወርቅ እንዲለብጠው፤ ሕለተ ወርቅ አበጅቶ ስኂን ሰንድሮስ የሚባለውን ነጭ ዕጣን ደቁሶ ፍሕሙን በዛ አድርጎ ጢስ ቅታሬው አምሮ እንዲወጣ በሕለተ ወርቁ እንዲያዋሕደው፤ ወርቅ አይችልምና እንዳይቀልጥ መጤስ ሲዠምር ፈጥኖ በብርት እንዲገለብጠው አዞታል።

ይኸውም ምሳሌ ነው ማዕጠንት የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ወርቁ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ክንዱን ሙሉ ወደ ላይ ፈልፍለው ክንዱን ሙሉ ወደታች ተወው አለው እመቤታችን ድንግል ወእም እየተባለች ስትመሰገን ለመኖሯ ምሳሌ፤ አቅርንት የሥልጣነ እግዚአብሔር፤ ፍሕም የመለኮት፤ ዕጣን የትስብእት፤ ሕለተ ወርቅ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው(.ሉቃ ፩፥፴፭፤ዮሐ ፩፥፲፬)።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ኪሩቤል ሱራፌል እሳተ መለኮቱ እንዳያቃጥላቸው በፍርሃት ክንፋቸውን የሚጋርዱለት እሳተ መለኮት ጌታን የቻለች አማናዊት የወርቅ ማዕጠንት መኾኗን በእሑድ ውዳሴ ማርያም ላይ *‹‹አንቲ ውእቱ ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ጾርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ ዘይሠሪ ኀጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ ዝ ውእቱ ዘእግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ››* (ቡሩክ ከቤተ መቅደስ ይዞሽ የወጣ እሳትነት ያለውን ፍሕም የተሸከምሽ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ፤ ፍሕም የተባለውም ኀጢአትን ይቅር የሚል በደልን የሚደመስስ ነው፤ ይኸውም ካንቺ ሰው የኾነና ለባሕርይ አባቱ ራሱን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ያሳረገ የእግዚአብሔር ቃል ነው)[137] በማለት ምሳሌውን ተርጕሞታል።

137. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት





## ጣፋጭ ሽቱ

ለእግዚአብሔር ወልድ እናትነት ብቻዋን የተመረጠች ቅድስት ድንግል ማርያም ለጌታ ብቻ በተለየ ጣፋጭ ሽቱ ትመስላለች (ዘፀ ፴፥፴፬-፴፰)። ይኸውም ልዑል እግዚአብሔር አገልጋዩ ሙሴን ሚዓ የሚባል የጣፈጠ ያማረ የተወደደ ሽቱና ዐይን የሚበዘብዝ ስኂን የሚባል ነጭ ዕጣን አምጣ ብሎታል፤ የዚኽ ኹሉ ሚዛኑ ትክክል ይኹን፤ ብልኀ ሰው ዕጣኑን ያማረ የተወደደ የጣፈጠ አድርጎ ይሥራው ንጹሕ ልዩ ሥራ አድርገው፤ ከዕጣኑ አድቀኽ ፈጭተኽ እኔ በምገለጽበት በደብተራ ኦሪት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ አኑረው፤ ይኽ ዕጣን ከተለዩ የተለየ ከከበሩ የከበረ ይኹን *‹‹ወበዝ ግብረት ኢትግበሩ አርዓያ ዝ ዕጣን ኅሩመ ለይኩንክሙ ዝንቱ ወቅዱሰ ለእግዚአብሔር››* ይላል በዚኽም አምሳል ሌላ ዕጣን አታድርጉ፤ ይኽም ለእናንተ ታደርጉት ዘንድ የማይገባ ለእግዚአብሔር የተለየ ገንዘብ ይኹን፤ ይኽነንም ሊያሸተው ያኖረ ሰው ቢኖር ከወገኖቹ ተለይቶ ይጥፋ ብሎታል።

ይኽም ለጊዜው ለእግዚአብሔር የምናቀርበው መሥዋዕት ነውር ያልተቀላቀለበት የተለየ፣ የነጻ፣ የተቀደሰ መኾን እንዳለበት ሲያስረዳ ፍጻሜው ግን ከንጹሓን ይልቅ የነጻች ከተለዩት የተለየች ቅድስት ድንግል ማርያም ለልዑል እግዚአብሔር እናትነት ከአንስተ ዓለም ኹሉ ተመርጣ በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና አጊጣ፤ ሽቱው በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ እንደተቀመጠ ኹሉ ርሷም በቤተመቅደስ ዐሥራ ኹለት ዓመት በቅድስና ቆይታ፤ አካላዊ ቃል በግብረ መንፈስ ቅዱስ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና የመወለዱን ታላቅ ምስጢር የሚያሳየን ነው።

ሃገራችን ኢትዮጵያ ካፈራቻቸው ታላላቅ ሊቃውንት አንደኛው አባ ጊዮርጊስ ይኽነን ሲተረጉም *‹‹አንቲ ውእቱ ዕፍረት ዘኢያጸዐጦ እደ ጸዓጢ ዘተገብረ ለቅብዐ ክህነት ወመንግሥት ዘአሕረመ እግዚአብሔር ከመ ኢይግበር ባዕድ ዝ ጽዒጠ ይቤ እመቦ ዘገብረ በአምሳለ ዝ ጽዒጥ ለተቀብዖ ሞተ ለይሙት፤ ዕፍረትኬ አንቲ ወዘተቀብዖስ ሥጋ ዚአኪ ሊቀ ካህናት ወንጉሠ ነገሥተ ኢየሱስ ክርስቶስ፤ እስመ ክርስቶስ ብሂል ቅቡዕ በከመ ተርጕመ ቄርሎስ በከመ አሕረመ እግዚአብሔር ተቀብዖ ዕፍረት ዘደብተራ ስምዕ ዘእንበለ ካህናት ወነገሥት፤*



www.ethiopianorthodox.org

*ወከማሁ ሕሩም ልደትኒ እምድንግል ዘእንበለ ቃለ አብ»* (ለክህነትና ለመንግሥት ቅባት የተሠራ ይኸነን ሽቱ ሌላ እንዳይሠራ እግዚአብሔር ያስከለከለውና እንዲኸም ያለ ለመቀባት በዚኸ ሽቱ (ቅባት) አምሳል የሠራ ቢኖር ሞትን ይሙት ብሎ ሕግን የሠራላት የቀማሚ እጅ ያልቀመመው ሽቱ አንቺ ነሽ ፤ ቅባት ሽቱ የተባልሽም አንቺ ነሽ፤ የአንቺን ሥጋ የተቀባው (የተዋሐደው) የካህናት አለቃ የነገሥታት ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፤ ክርስቶስ ማለት ቅቡዕ ማለት ነውና ቄርሎስ እንደተረጐመው፤ ካህናትና ነገሥታት ካልኾኑ በቀር የምስክሩን ድንኳን ቅባት መቀባትን እግዚአብሔር እንዳስከለከለ እንዲኹ ከድንግል የሚኾን መወለድም የአብ አካላዊ ቃል ካልኾነ በቀር ዕርም ነው፤ ፍጹም ክህነትና ንጹሕ መንግሥት የርሱ ብቻ ነውና)[138] በማለት ከሊቅ ቃል ጠቅሶ በማራቀቅ ተንትኖታል።

## የሙሴ ጽላት

ማኅደረ ቃል አብ የኾነች ቅድስት ድንግል ማርያም በአጻብዐ እግዚአብሔር የተጻፉ ፲ቱ ቃላት ባሉባት ጽላት ትመሰላለች (ዘፀ ፴፪፥፲፭-፲፱ ፤፴፬፥፩-፭፤ ጃ፱-፴):: ይኸውም እስራኤል ከግብጽ ከወጡ በኋላ ሊቀ ነቢያት ሙሴ አሮንና ሖርን ከተማ አስጠብቆ እሱ ኢያሱን አስከትሎ ወደ ደብረ ሲና ኼደ ፤ ከዚያም ኢያሱን ከተራራ ሥር ትቶ እሱ ወደ ላይ ቢወጣ ሰባት የእሳት መጋረጃ ተጋርዶ ቆይቶታል፤ ጌታም ስድስቱን ዕለት ከዕለተ እሑድ እስከ ዕለተ ዐርብ የተፈጠሩትን ኻያ ኹለቱን ሥነ ፍጥረት በልቡናው ሲስልበት ሰንብቷል፤ ሠላሳ አራቱን ቀን ቃል ለቃል እየተነጋገሩ ዐምስት መቶ ሰባ ዐምስቱን ወነበበ አጽፎታል፤ ከዚያም ዐሥሩ ቃላትን በኹለት ዕንቍ ጽላት ጽፎ ሰጥቶት ያን ይዞ ወደ ሕዝቡ ሲመለስ አምልኮተ እግዚአብሔርን ትተው በዚያ ፈንታ ጣዖት አቁመው ተረፈ መሥዋዕቱን በልተው ለጣዖቱ ሲወድቁ ሲነሡ ሲዘፍኑ፣ ሲያጨበጭቡ፣ ሲሰግዱ፣ ሲረበረቡ ቢያያቸው ደንግጦ ጽሌዎቹ ከእጁ ወድቀው ተሰበሩ። ከዚኸ በኋላ እነዚያ የሰጠኸኝ ጽላት ተሰበሩ ብሎ ወደ ጌታ ቢያመለክት *ቀር ከመ ቀዳምያት* እንደቀደመው አድርገኸ ቀርጸኸ አምጣ አለው፤ እንዳለው አድርጎ ይዞ ሲኼድ ቃሉ በግብር አምላካዊ በጽላቱ ላይ ተጽፎ ተገኝቷል።

138. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፲፱፤ ስምዐት ዘቄርሎስ ፪፳፩፥፴፤፪፳፬፥፲፬





ይኸውም ምሳሌ ነው የቀደመው ጽላት የአዳም፤ ኹለት መኾኑ የነፍስ የሥጋው ምሳሌ፤ ያ እምኀበ አልቦ እንደተገኘ አዳምም ከኀቱም ምድር ያለ ዘር የመገኘቱ ምሳሌ፤ ያ በጣዖት ምክንያት እንደተሰበረ አዳምም በዲያብሎስ ምክንያት ወደ ስሕተት ወድቋል( ዘፍ ፫፥፩-፯)፤ የኋለኛው ጽላት የእመቤታችን ኹለት መኾኑ የነፍስ የሥጋዋ፤ ያ ቀር ከመ ቀዳምያት ብሎት በሙሴ እጅ እንደተቀረጸ እመቤታችንም በዘር በሩካቤ ከሐና ከኢያቄም የመገኘቷ ምሳሌ፤ የኋላዎቹ ጽላት መሰበር መሰንጠር እንዳላገኛቸው እመቤታችንም ጽነተ ሥጋ ጽነተ ነፍስ አላገኛትምና፤ ቃሉ የአካላዊ ቃል፤ ያ በግብር አምላካዊ እንደተገኘ አካላዊ ቃልም በዘር በሩካቤ ከተገኘች ከእመቤታችን እንበለ ዘርዕ እንበለ ሩካቤ የመወለዱ ምሳሌ(ማቴ ፩፥፲፰፤ ሉቃ ፩፥፴፭፤ ዮሐ ፩፥፲፬፤ ገላ ፬፥፬) ሲኾን፤ የዐሥሩ ቃላት አጻጻፋቸው ወደ ላይም ሳይተርፉ ወደታችም ሳይሰጥሙ ነው፤ ይኸም ወደላይ አለመትረፉ ሥጋ ለሥላሴ አራተኛ፤ ለቃል ኹለተኛ ያለመኾኑን አምሳል ሲያስረዳ፤ ወደታች አለመስጠሙ ከእመቤታችን ሲወለድ በመንበረ ጸባኦት የመሠለሱ፣ የመቀደሱ አምሳል ነው::

በተጨማሪም ይቺ የሙሴ ጽላት ያማረች ናት፤ ዐሥሩ ቃላት ተጽፎባታል፤ ሕጓን የጠበቀ ከመቅሠፍት፣ ከዔዋዌ፣ ከመከራ ሥጋ ትጠብቃለች፤ አራት ማዕዘን ነበራት፤ ፍጻሜው ግን ያቺ ጽላት ያማረች እንደኾነች ቅድስት ድንግል ማርያምም ባማረ ባማረ ነገር ይመስላታል፤ ያቺ ዐሥሩ ቃላት እንደተጻፉባት ቅድስት ድንግል ማርያምም ማኅደረ ቃለ አብ ናትና (ሉቃ ፩፥፴፭፤ ዮሐ ፩፥፲፬፤ )፤ ያቺ ሕጓን የጠበቀውን ከመቅሠፍት እንደምትሰውር ቅድስት ድንግል ማርያምም በቃል ኪዳኗ በምልጃዋ የሚታመነውን ከሞተ ነፍስ በምልጃዋ ትታደጋለችና፤ ያቺ ጽላት አራት ማዕዘን እንዳላት ቅድስት ድንግል ማርያምንም በአራቱ ማዕዘን ሰአሊ ለነ ቅድስት (ቅድስት ሆይ ለምኝልን) ሳይላት የሚውል የለምና በጽላቷ ትመሰላለች፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ላይ ምስጢሩን በመጠቅለል *«ጽላት ዘሙሴ»* (የሙሴ ጽላት አንቺ ነሽ )[139] በማለት አመስግኗታል::

ኢትዮጵያዊዉ አጼ ዘርዐ ያዕቆብም በመጽሐፈ ብርሃን ላይ ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባት ጽላት በእውነት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን

139. አባ ሕርያቆስ ፤ ቅዳሴ ማርያም ፤ ቍ፴፫



www.ethiopianorthodox.org

እንዲኽ ሲል ተንትኖታል ፤ ‹‹ወአብላቅሰ እንዘ እኅዝት በእደ እሳት ኢውዕዮት ወኢረስነት ወኢሐለለት በአምሳለ ማሕፀና ለማርያም ወማሕፀናሰ ለማርያም ድንግል በክልኤ ይትሜሰል በጽላት ዘተጽህፈ ውስቴታ ፲ቃላት፤ ወ፲ቃላት ቀዳሜ ስሙ ለወልዳ ውእቱ ዘውእቱ የውጣ ዘተሰምየ በኍልቈ ፲ቃላት፤ ወታቦትሰ አምሳለ ከርሣ ለማርያም ውእቱ፤ ወደብተራኒ አምሳለ ኵሉ ምልአ ሥጋሃ ውእቱ፤ ወይእቲሰ አብላቅ ሶበ ተመጠዋ በእዴሁ እሳተ መለኮት እምአፅዳወ ሙሴ ወሶበኒ አኃዛ ወገሠሣ ወሶበኒ ጸሐፋ በቀሪጽ ኢውዕየት ወኢሐለለት አርአያ ወአምሳል ይእቲ ለማርያም ድንግል በክልኤ። ወባሕቱ ቲዓቢ ወትከብር ማርያም ድንግል በክልኤ ዘኢውዕየ ማሕፀና በእሳተ መለኮት በጸዊር ኪያሁ ፱አውራኀ ወለብሰ ሥጋሃ ወተወልደ እምኔሃ፤ ወደብረ ሲናሰ ሶበ ወረደ ውስቴታ እግዚአብሔር ስእነት ጸዊሮቶ ለእሳተ መለኮት ኦላ ጤሰት ወነደደት ኵለንታሃ ምስለ ዕፀዊሃ ወእበኒሃ፤ ወሙሴኒ ዘረከበ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር እመ ወረደ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና በቃለ መብረቅ ወደመና ወጊሜ ወቃለ መጥቅዕ ዐቢይ ድምፅ በእሳት ወጽልመት ወዓውሎ ወጣቃ ዘቦ ህየ ኃበ ኀሎ እግዚአብሔር ዘተውህበ ሎቱ አምሳሊሃ ለማርያም ድንግል በክልኤ፤ ጽላት አምሳለ ማሕጸና፤ ወታቦተ ሕግ አምሳለ ከርሣ፤ ወደብተራ መርጡል አምሳለ ኵሉ ምልአ ሥጋሃ ወዘተርፈሂ ብዙኀ አምሳሊሃ ዘተውህበ ሎቱ›› (ታቦት ግን በእሳት እጅ ተይዛ ሳለች በማርያም ማሕፀን አምሳል ፈጽማ አልተቃጠለችም፣ ደግሞም አልተቃጠለችም፣ አልጋለችም፣ አላረረችም፤ በኹለት ወገን ድንግል የምትኾን የማርያም ማሕፀንስ ዐሥሩ ቃላት በውስጧ በተጻፈ ጽላት ይመሰላል። ዐሥሩ ቃላትም የልጇ የኢየሱስ የመዠመሪያ ስሙ ነው፤ ያውም የውጣ በዐሥሩ ቃላት የተጠራ ነው። ታቦትም የማርያም የማሕፀኗ አምሳል ነው፤ ድንኳኑም ከራስ ጸጒሯ እስከ እግር ጥፍሯ ያለው የመላው ሰውነቷ ምሳሌ ነው። ይኽቺንም ታቦት መለኮታዊ እሳት በእጁ ከሙሴ እጅ በተቀበላት ጊዜ፤ ይዞም በዳሰሳት ጊዜ በመቅረጽም በጻፋት ጊዜ ፈጽሞ አልተቃጠለችም፣ ደግሞም አልተቃጠለችም፣ አልጋለችም፤ አላረረችም፣ አልከሰለችም፤ በኹለት ወገን ድንግል ለምትኾን ለማርያም አርአያና አምሳል ናት፤ ነገር ግን ሥጋዋን ለብሶ በተወለደ ርሱንም ዘጠኝ ወር በመሸከም በመለኮት እሳት ማሕፀኗ ያልተቃጠለ (ያልተለወጠ) በኹለት ወገን





ድንግል የኾነች ማርያም ትልቃለች ትከብራለች። የሲና ተራራ ግን እግዚአብሐር በርሷ ላይ በወረደ ጊዜ መለኮታዊ እሳትን መሸከም አልቻለችም ከደንጊያዎቿና ከዕፀዋቷ ጋር ኹለንተናዋ ጤሰች ነደደች እንጂ። እግዚአብሔር በመብረቅ፣ በደመና፣ በጉም ቃል፣ የደውል በሚኾን ታላቅ ድምፅ በእሳትና በጨለማ በነፋስና በጭጋግ ወደ ሲና ተራራ በወረደ ጊዜ ጽላት የማሕፀኗ አምሳል፣ የሕግ ታቦትም የኾዷ አምሳል፣ የአዳራሽ ድንኳንም የመላ ሰውነቷ ኹሉ አምሳል፣ የተቀረውም ብዙ ምሳሌዋም በኹለት ወገን ድንግል የምትኾን ማርያም ምሳሌዋ የተሰጠለት እግዚአብሔር ወዳለበት ከእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን ያገኘ ሙሴ ገባ)[140] ሲል አስተምሯል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባት ጽላትን የቀረጹ የሙሴ እጆች የአብ አካላዊ ቃልን የወለደችልን ቅድስት ድንግል ማርያምን ያስገኙ የሐና የኢያቄም ምሳሌ መኾናቸውን ሲተነትን ‹‹ወበእደዊሁ ቅዱሳት ወቀረ ጽላተ በከመ ተአዘዘ እምኀበ እግዚአብሔር። ወበእደዊሁ ቅዱሳት መጠዎ ውእተ ጽላተ እደ ሣዕር ለእደ እሳት ወኢውዕየ፤ ወይእቲሰ ጽላት ሶበ ተመጠዋ እግዚአብሔር በእደዊሁ ኢውዕየት ወኢረሰነት ወኢሓለለት ወኢማሰነት እምእሳተ መለኮት ወሶበ ጸሐፈ ውስቴታ በቀሪጽ ፲ቃላተ እስመ አምሳለ ማሕፀና ለማርያም ይእቲ ዘኢውዕየት ወኢሐለለት በጸዊረ እሳተ መለኮት። ማሕፀና ለማርያም ቅዱስ ፤ ማኅደረ መለኮት፤ ወይእተ ጽላተ ተመጠወ ሙሴ እምእደ እግዚአብሔር በእደዊሁ ቅዱሳት ፤ ወበእማንቱ አእዳዊሁ ቅዱሳት እለ ፈረያ ጽላተ እምእደ እግዚአብሔር ጸባኦት ይትሜሰሉ ሐና ወኢያቄም ቅዱሳን ወንጹሓን እለ ፈረይዋ በሩካቤ ንጽሕ ለማርያም ድንግል በክልኤ እመ እግዚአብሔር ክብርት ወልዕልት እምኵሉ ፍጥረት ዘአልቦ ዘከማሃ ወአልቦ ዘይትማሰላ›› (ከእግዚአብሔር ዘንድም በታዘዘ መጠን በቅዱሳት እጆቹ ጽላትን ቀረጸ፤ ያንን ጽላትም የሣር እጅ ለእሳት እጅ በቅዱሳት እጆቹ በሰጠው ጊዜ አልተቃጠለም፤ ያቺም ጽላት እግዚአብሔር በእጁ በተቀበላት ጊዜ ፈጽማ አልተቃጠለችም፣ ደግሞም አልተቃጠለችም፣ አልጋለችም፣ አላረረችም ፣አልከሰለችም፤ ዐሥሩ ቃላትን በውስጧ ቀርጾ በጻፈ ጊዜ ከመለኮታዊ እሳት የተነሣ አልተለወጠችም፤ መለኮታዊ እሳትን በመሸከም ያልተቃጠለች ያላረረች

140. ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ ፤ መጽሐፈ ብርሃን ገጽ 67-68



www.ethiopianorthodox.org

የማርያም ማሕፀኗ የመለኮት ማደሪያ ነው። ያነን ጽላትም ሙሴ በቅዱሳት እጆቹ ከእግዚአብሔር እጅ ተቀበለ፤ እንደርሷ ያለና ርሷንም የሚመስል የሌለ ከፍጥረት ኹሉ የከበረችውንና የገነነችውን የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናትን በኹለት ወገን ድንግል የኾነች ማርያምን በንጽሐ ሩካቤ የወለዷት ያስገኟት ቅዱሳን ንጹሓን የሚኾኑ ሐናና ኢያቄም፤ ከአሸናፊ እግዚአብሔር እጅ ጽላትን በተቀበለ ጊዜ ከመለኮታዊ እሳት የተነሣ ባልተቃጠሉና ጽላትን በቀረጹ በእሲያ በእጆቹ ይመሰላሉ)[141] በማለት አስተምሯል።

ይኽ ምሑር እጅግ በሚያስደንቅ በዚኽ ሃይማኖታዊ ትንታኔው ቅድስት ድንግል ማርያም ዐሥሩ ቃላት በተጻፉባት ጽላት የምትመሰል ብቻ ሳትኾን በጽላቱ ላይ የተጻፉትን ዐሥሩ ቃላትን በሙሉ የፈጸመች እሷ ብቻ መኾኗን ሲያስረዳ ‹‹ወጽላትሰ ዘተጽሕፈ ወስቴታ ፲ቃላት አምሳለ ማርያም ይእቲ ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ ወንጽሕት በነፍሳ እምሰብእ ወእመላእክት ይፈደፍድ ንጽሓ አልቦ ዘይትዔረያ በንጽሕ ወበቅድስና በክብር ወበልዕልና ከምከርሠ እማ አንጽሓ ወቀደሳ ለሐኬ አዳም ፈጣሪሃ ከመ ይልበስ ሥጋሃ ወነፍሳ ወኅሊናሃ ድልው ከመ ይልበሶሙ ወልደ እግዚአብሔር እስከ ረሰዮሙ አሐደ ምስለ መለኮቱ፤ ሥጋሃኒ ወነፍሳኒ ወኅሊናሃ ለማርያም ንጽሕ ውእቱ፤ ለማርያምሰ ንብላ ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ፤ እስመ ፈጻሚተ ፲ቃላት ይእቲ በኢፈቲው በኅሊናሃ ወበገቢረ ኵሉ ፲ቃላት ዘጸሐፈ እግዚአብሔር በእደዊሁ ከመ ይግበሩ ትእዛዛቲሁ ሕዝብ መምለክያኒሁ፤ ወባሕቱ አልቦ ዘፈጸመ ፲ቃላት በገቢር በእንበለ ማርያም ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ፤ ይቤ በእንተ ኢፈቲው በኅሊና በኦሪት ዘፀአት በውስተ ፲ቃላት ኢትፍቱ ብእሲተ ካልእከ ኢተፍቱ ቤቶ ለካልእከ ወኢገራህቶ ወኢገብሮ ወኢአመቶ ወኢላሕሞ ወኢብዕራይሁ ወኢኵሎ በውስተ እንሰሳሁ ዘአጥረየ አጥርዮ ቢጽከ ፤ ዘንተ ዘፈጸመ ተደንገለ በኅሊናሁ፤ ወዘንተኒ አልቦ ዘፈጸመ ዘእንበለ ማርያም ባሕቲታ እስመ ተደንግሎ ኅሊና ተውህበ ለባሕቲታ፤ ወእለ ተርፉኒ ቃላተ አልቦ ዘፈጸመ በገቢር ዘእንበሌሃ ኢአምቅድሜሃ ወኢአምድኅሬሃ፤ ወሶበ ረሰያ ፍጽምተ በድንግልና ኅሊና ወበድንግልና ሥጋ ወስርጉተ በፈጽሞ ፲ቃላት ለብሰ አምላክ ፍጹመ ትስብእተ እምኔሃ፤ ወለእመሰ ኢፈጸመት ፲ቃላተ እምኢደለዎ ለአምላክ ይልበስ ሥጋሃ እስመ ኮነ ንትጋ እም፲ቃላት ውስተ ምግባራቲሃ፤ ወበእንተዝ ንብላ ለማርያም ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ እስመ ፈጻሚተ ፲ቃላት ይእቲ ወባሕቱ ፍጽምት ሰብእ ይእቲ በጠባይዒሃ ዘእንበለ ኀጢአት ባሕቲታ እስመ ወለተ አዳም ወሔዋን ይእቲ። ወተደንግሎታሰ በኅሊናሃ ሕሩም ውእቱ እምካልኣን ኢእምተባዕት ወኢእምአንስት፤ ወተደንግሎታኒ በሥጋ ፍጹም ውእቱ ዘእንበለ ዐቅም እምካልኣን ደናግል ኢእምተባዕት ወኢእምአንስት ወእመሰ ቦ ዘይቤ ኢፈጸመት ማርያም ፲ቃላተ ወንሕነኒ ንብሎ አየ፦ ቃለ እም ፲ቃላት ዘኢገብረት ማርያም ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ ይምጻእኬ ማእከለ ጉባኤ መሃይምናን ከመ ናዕቅጾ በኀይለ እግዚአብሔር ወበቃለ መጻሕፍት›› (በውስጧ ዐሥሩ ቃላት የተጻፉ ጽላት ግን በኅሊናዋና በሥጋዋ ድንግል በነፍሷም ንጽሕት የምትኾን የማርያም አምሳል ናት።ይኽቺ ማርያምም ከሰውና ከመላእክት ይልቅ ንጽሕናዋ ይልቃል፤ በንጽሕናና በቅድስና በክብርና በልዕልናም የሚተካከላት ማንም የለም። አዳምን የፈጠረ ፈጣሪዋ ከእናቷ ማሕፀን ገሮምሮ ፈጽሞ አነጻት፤ ሥጋዋን ይለብስ (ይዋሐድ) ዘንድ ሥጋዋ ነፍሷና ኅሊናዋ የተገቡ ናቸውና፤ ወልደ እግዚአብሔር ይዋሐዳቸው ዘንድ ከመለኮቱ ጋር አንድ እስኪያደርጋቸው ድረስ የማርያም ሥጋዋ ከነፍሷና ኅሊናዋ ጋር ንጹሕ ነው። ማርያምንስ በኅሊናዋና በነፍሷ ድንግል እንላታለን፤ ዐሥሩ ቃላትን የፈጸመች ናትና፤ በኅሊናዋ ሥጋዊ ነገርን ባለመሻት፤ የሚያመልኩት ወገኖች ትእዛዛቱን ይሠሩ ዘንድ እግዚአብሔር በእጆቹ የጻፋቸው ዐሥሩ ቃላትን ኹሉ በመሥራት። ነገር ግን በኅሊናዋና በሥጋዋ ድንግል ከኾነች ከማርያም በቀር ዐሥሩ ቃላትን ሠርቶ (በመሥራት) የፈጸመ የለም። በኅሊና ስላለመመኘት በዐሥሩ ቃላት በኦሪት ዘፀአት የጓደኛኽን ሚስት፤ ቤቱንም፤ ርሻውንም፤ የወንድ ሎሌውንም፤ የሴት አገልጋዩንም፤ ላሙንም፤ በሬውንም፤ በእንስሳቱ ውስጥ የገዛውን ኹሉ አትመኝ አለ። ይኽነን የፈጸመ በኅሊናው ድንግልን ኾነ፤ ይኽነን ግን ከብቻዋ ከማርያም በቀር ያለማርያም የፈጸመ የለም፤ የኅሊና ድንጋሌ ለብቻዋ ተሰጥቷታልና (ስለተሰጣት)፤ የቀሩትንም ቃላት ከርሷ አስቀድሞ ከርሷም በኋላ ያለ ርሷ በመሥራት የፈጸመ የለም፤ በድንጋሌ ኅሊና በድንጋሌ ሥጋ የጸናች ዐሥሩ ቃላትን በመፈጸምም ያጌጠች ባደረጋት ጊዜ

141. ገዘኒ ከማሁ ገጽ 68-69







www.ethiopianorthodox.org

አምላክ ባሕርይዋን ተዋሐደ። ዐሥሩ ቃላትን የፈጸመች ባትኾን ኖሮ አምላክ ሥጋዋን ይለብስ ዘንድ ባልተገባውም ነበር፤ ከዐሥሩ ቃላት ውስጥ በሥራዎቿ የጎደለ አለና። ስለዚኽ ማርያም በድንጋሌ ኅሊና፣ በድንጋሌ ሥጋ የጸናች ናት እንላታለን ዐሥሩ ቃላትን ፈጽማለችና። ነገር ግን ከብቻዋ ከኀጢአት በቀር በባሕርይዋ ፍጽምት ሰው ናት፤ የአዳምና የሔዋን ልጅ ናትና። በኅሊናዋ ድንግል መኾኗ ግን ከሌሎች ከወንድም ከሴትም ቢኾን የተለየ ነው። በሥጋ ድንግል መኾኗም ከሌሎች ደናግል ከወንድም ከሴትም ከመጠን በላይ ፍጹም ነው። ማርያም ዐሥሩ ቃላትን አልፈጸመችም የሚል ካለ በድንጋሌ ኅሊና በድንጋሌ ሥጋ የጸናች ማርያም ከዐሥሩ ቀላት ያልሠራችው የቱን ነው? እንለዋለን። በእግዚአብሔር ኀይልና በመጻሕፍ ቃል እናሰነካክለው (እንረታው) ዘንድ ወደ ምእመናን ጉባኤ እስኪ ይምጣ?)[142]

በማለት በድንጋሌ ነፍስ በድንጋሌ ሥጋ የጸናች የአማናዊት ጽላት የቅድስት ድንግል ማርያም ንጽሕናዋ ቅድስናዋ እጅግ የሚያስደንቅ መኾኑንና በዚኽም ንጽሕናዋን ቅድስናዋን የሚጠራጠሩ ኹሉ በመጽሐፍ ቃል እንደሚረቱ አስተምሯል።

ለዚኹም ምስክር ከቅዱሳት መጻሕፍት እየጠቀሰ በመተንተን ካስረዳ በኋላ በንጽሕናዋ በቅድስናዋ ምክንያት አምላክ ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ መወለዱን ሲያብራራ «ወወልዳሰ ለድንግል በሥጋሃ ወድንግል በኅሊናሃ አእሚሮ ከመ አልብነ ድንግልና ኅሊና እንዘ ይኤምረነ ከመ ንትዐቀብ በቃልነ ይቤ በወንጌለ ማቴዎስ ኵሉ ሰብእ ዘነበበ ንባበ ፅሩዐ በከመ ረከበ ያገብኡ በእንቲአሁ ቃለ ወይፄነነን ባቲ በዕለተ ደይን እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን ወኅሊናሃሰ ለማርያም ኢኮነ ከመ ኅሊናነ ዘአልቦ ተደንግሎ፤ ወኅሊናነሰ ይኄሊ ሠናየ ወእኩየ ወንገብር ሠናየ ወእኩየ በከመ ኅለይነ እስመ አልቦቱ ተደንግሎ ለኅሊናነ፤ ወማርያም ድንግል በኅሊናሃ ወድንግል በሥጋሃ አልቦ አመ ኀለየት ዘኢያሠምሮ ለእግዚአብሔር ወአልቦ አመ ገብረት ዘኢያሠምሮ ለእግዚአብሔር፤ ኀለየት ዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር ወገብረት ዘያሠምሮ ለእግዚአብሔር፤ እስመ እምከርሠ እማ ቀደሳ ወአንጽሓ ከመ ትኩኖ እመ ለፈጣሪሃ፤ ወሶበ ርእየ ወልደ እግዚአብሔር ድንግልና ኅሊናሃ

142. ገፀ ከማሁ፤ ገጽ 70-72





ወድንግልና ሥጋሃ ፍጹመ ኀደረ ላዕሌሃ በዕለተ ወረደ እምአርያም ለቢሶ ሥጋሃ ወኢያጽንሐ ክልኤ ወሠለሰ ወረቡዐ ወኀሙሰ ወሰዱሰ መዋዕለ እምአመ ወረደ እምአርያም እስከ ይጸወር ውስተ ማሕፀና በከመ አጽንሐ ለሙሴ አመ ወረደ እግዚአብሔር ውስተ ደብረ ሲና ከመ ይትናገሮ ወከመ ያርእዮ ገጸ ወኢተናገሮ ዘእንበለ በሳብዕት ዕለት›› (በድንጋሌ ኅሊና በድንጋሌ ሥጋ የጸናች የማርያም ልጇ ግን የኅሊና ድንግልና እንደሌለን ዐውቆ በቃላችን እንጠበቅ ዘንድ ሲያመለክተን በማቴዎስ ወንጌል እንዳገኘ የማይገባ ብላሽ ነገርን የሚናገር ሰው ኹሉ በፍርድ ቀን ስለርሱ መልስን ይሰጡበታል ከአነጋገርኽ የተነሣ ትጸድቃለኽና፤ ከአነጋገርኽም የተነሣ ትኰነናለኽና አለ (ማቴ ፲፪፥፴፮)። የማርያም ኅሊና ግን ተደንግሎ እንደ ሌለው እንደ እኛ ኅሊና አይደለም። ኅሊናችንስ መልካሙንና ክፋውን ያስባል፤ እንዳሰብንም መልካሙንና ክፋውን እንሠራለን፤ ኅሊናችን ድንግልና (ጽናት) የለውምና። በድንጋሌ ኅሊና የጸናች ማርያም ግን እግዚአብሔርን ደስ የማያሰኝ ነገርን ያሰበችበትና ደስ የማያሰኘውንም የሠራችበት ጊዜ የለም። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ዐስባ ደስ የሚያሰኘውን ሠራች። ለፈጣሪዋ እናትን ትኾነው ዘንድ ከእናቷ ማሕፀን ገርምሮ ለይቶ አንጽቷታልና።
ወልደ እግዚአብሔርም የኅሊናዋንና የሥጋዋን ድንግልና ባየ ጊዜ፤ ከአርያም በወረደ ቀን ሥጋዋን ለብሶ (ተዋሕዶ) በርሷ ዐደረ ። እግዚአብሔር ወደ ደብረ ሲና በወረደ ጊዜ ይናገረው ዘንድ ፊቱንም ያሳየው ዘንድ ሙሴን እንደቆየው፤ በኦሪት ዘፀአትም እንደተነገረ ያለሰባተኛዪቱ ቀን እንዳልተናገረው በማሕፀኗ እስኪወሰን ከአርያም ገርምሮ ኹለትና ሦስት አራት ዐምስትና ስድስት ቀናት የቆየ አይደለም)[143]

በማለት በሙሴ ጽላት መስሎ ያስተማረውን ይኽነን ጥልቅ የነገረ ማርያም ትምህርት ስንመረምር ቤተክርስቲያናችን ምን ያኽል ታላላቅ የነገረ ማርያም ምኹራን የነበሯት መኾኗን ያሳየናል።

## ገራህተ ሙሴ

ሊቀ ነቢያት ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ጥልቅ ግንኙነት የተነሣ እባክኽ ክብርኽን አሳየኝ ብሎ ልመናን አቀረበ፤ እግዚአብሔርም እኔ መልካምነቴን ኹሉ በፊትኽ አሳልፋለኍ፤ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን

143. ገፀ ከማሁ፤ገጽ 72 -73



www.ethiopianorthodox.org

ማየት አይቻልኽም ብሎታል። ይኸውም ፈጣሬ ዓለማት ጌታን በአምላካዊ ባሕርዩ፤ በመለኮታዊ ክብሩ ማንም ሊያየው አለመቻሉን ሲገልጽለት ነው፤ ይኽነን ካለው በኋላ ይገለጽ ዘንድ ስላለው ምስጢር ሲገልጽለት «ናሁ መካነ ኀቤየ ሀሎ» (እንሆ ስፍራ በኔ ዘንድ አለ)፤ «ወትቀውም ውስተ ኰኵሕ» (በዐለቱም ላይ ትቆማለኽ)፤ «ወአነብረከ ውስተ ስቍረተ ኰኵሕ ወእከድን እዴየ በላዕሌከ እስከ አኀልፍ» (በሰንጣቃው ዐለት አኖርሃለኊ፤ እስካልፍ ድረስ እጄን በላይኽ እጋርዳለኊ፤ ካለፍኊ በኋላ እጄን አንሥቼልኽ ገርባዬን ታያለኽ፤ ፊቴ ግን አይታይም) ብሎታል (ዘፀ ፴፫፥፲፯-፳፫)።

ይኸውም ገርባ በስተኋላ እንደሚገኝ ኹሉ በኋላ ዘመን አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በታቦር ተራራ ላይ እንደሚገለጽለት ሲያመለክተው ነው። ይኸውምን ጌታ ለሙሴ «እንሆ ስፍራ በኔ ዘንድ አለ» ማለቱ የሞት፣ የመቃብር ሥልጣን በኔ ፈቃድ ነውና ሲለው ነው። «በዐለቱም ላይ ትቆማለኽ» ማለቱ ፭ሺሕ ፭፻ ዘመን ሲፈጸም ሰው ኾኜ ሥጋ ለብሼ በደብረ ታቦር እስክገልጽልኽ ድረስ አንተ በመቃብር ትኖራለኽ ማለቱ ሲኾን «እስካልፍ ድረስ እጄን በላይኽ እጋርዳለኊ» ያለው በታቦር ተራራ የባሕርይ ልጅነቴን እስክገልጽ ድረስ ሥልጣኔን በአንተ ላይ አጸናለኊ ማለቱን ሲያመለክት «እጄንም ፈቀቅ አደርጋለኊ» ማለቱ ሰው ኾኜ ሥጋ ለብሼ በዚኽ ዓለም በተገለጽኊ ጊዜ የሞትን ሥልጣን ከአንተ አርቃለኊ ሲለው ነው፤ «ገርባዬንም ታያለኽ» ማለቱ ያን ጊዜ በደብረ ታቦር በክበበ ትስብእት ታየኛለኽ ሲለው ነበር፤ ይኽም ያለው አልቀረም አካላዊ ቃል ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በዚኽ ዓለም ከተገለጸ በኋላ የሰጠውን ቃል ሲፈጽምለት ከሦስቱ ባለሟሎቹ (ከጴጥሮስ፣ ከያዕቆብ፣ ከዮሐንስ) ጋር በሎኾን በደብረ ታቦር ላይ ተገልጾለታል (ማቴ ፲፯፥፩-፯ ፤ ማር ፱፥፪-፰፤ሉቃ ፱፥፳፰-፴፮)።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብም ስለ ታቦር በሚተነትነው መጽሐፉ ሙሴ በቃዴስ ባለው በመሪባ ውሃ ከእስራኤል ጋር በበደለው በደል ምክንያት ምድረ ርስት ኢየሩሳሌም እንዳይገባ አይቷት ብቻ በናባው ተራራ ላይ እንዲያርፍ ኾኗል (ዘዳ ፴፪፥፶፪፤ ዘዳ ፴፬፥፩-፰)። ይኽ ለሙሴ አሳዛኝ ቢኾንም በኋላ ዘመን አካላዊ ቃል ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሙሴ በፊት በሩቁ ያያት ግን





ያልገባባት በምድረ ርስት በኢየሩሳሌም ያለች ታቦር ተራራ ላይ አምጥቶት በዘመነ ብሉይ በአካለ ሥጋ ያልገባባትን ርስት እንዲገባባት አድርጎታል፤ ይኸውም አዳምና ልጆቹ በአካለ ሥጋ ያጡትን ርስታቸው ገነትን በአካለ ነፍስ ዳግመኛ ሊያገባቸው እንደመጣ የሚያመለክት መኾኑን በስፋት አስተምሯል።[143]

በመኾኑም ቅድስት ድንግል ማርያም ቀደምት አበው ሊያዩት ይመኙት የነበረን መድኀኒታችንን ወልዳ ያስገኘች በመኾኗ ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ካም፣ ትውልደ ያፌት በመላ ያመሰግኗታል (ሉቃ ፩፥፵፱)። ስለእነዚኽ አበው ናፍቆት ጌታ ለሐዋርያት ሲገልጽላቸው «እውነት እላችኊለኊ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም የምትሰሙትን ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም» በማለት አበው ሊያዩት ወደው ሳለ አረፍተ ዘመን ገትቷቸው እንዳለፉ አስተምሯቸዋል (ማቴ ፲፫፥፲፯ ፤ ዮሐ ፰፥፶፮ ፤ ፰፥፶፯፤ ዕብ ፩፥፩-፪፤ ፩ዮሐ ፩፥፩-፪)። ለሙሴ ፊቴን አይቶኝ ማንም አይድንም ፊቴን ማየት አይቻልኽም ያለ አምላክን የማየት ምኞት የአበው ብቻ ሳይኾን የመላእክትም ነበር፤ ይኸውም ሥጋዌውን ለነቢያት ተልከው የሚነግሩ መላእክት ነበሩና ከዚኽ የተነሣ የሰውን ሥጋ ተውሕዶ አይተነው እያሉ ሲመኙ፤ ዘመኑ ሲፈጸም ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በጎል ተጥሎ በጨርቅ ተጠቅልሎ የድንግልና ጡቶቿን ሲጠባ አይተውት «ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይኹን፤ ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃድ» (ሉቃ ፪፥፲፬)በማለት ፈጣሪያቸውን አመስግነውት በምስጋና ላይ ምስጋና፣ በጣዕም ላይ ጣዕም ተጨምሮላቸው ደስ ብሏቸዋል።

እረኞችም፡ ሙሴ በዐይኑ ሊያየው የተመኘውን የዓለም ጠባቂ እውነተኛ እረኛ ጌታቸውን አይተው ምስጋና ሲያቀርቡ፤ ሰብአ ሰገልም ከሩቅ ምሥራቅ ኮከብ እየመራቸው መጥተው ፈጣሪያቸው ክርስቶስን ከእናቱ ከማርያም ጋር አይተውት ወድቀው በመስገድ ወርቅ፣ ዕጣን፣ ከርቤ እጅ መንሻ አቅርበውለታል (ማቴ ፪፥፩-፲፩ ፤ሉቃ ፪፥፰-፳)። ይኽነን እጹብ ድንቅ ምስጢር ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም ሲያመሰጥር Moses was unable to see the God head, as scripture tells, but the magi entered and saw... (ሙሴ እግዚአብሔርን

143. Jacob Of Serug, On Transfiguration P 217



www.ethiopianorthodox.org

ሲመለከት አልቻለም መጽሐፍ እንደሚነግረን፤ ግን ሰብአ ሰገል ሰው የኾነውን አምላክ ተመለከቱ፤ ዋሻው ሰማያትን ይወክላል፤ ሙሴም ሰብአ ሰገልን፤ ሰሚ በነቢያት አለቃ በሙሴና በፐርሺያ (በፋርስ) አለቆቻ በሰብአ ሰገል መኻከል ያለውን አንድነት ቢጠይቅ በዚኽ ሲያውቅ ይችላል፤ እግዚአብሔር በቀደሙት ጊዜያት ምስጢሩን እንዲያውጁ ጠቢባንን ባይመርጥ ኖሮ ካልተቀደሱ እጆች ስጦታን ባልተቀበለ ነበር፤ ሙሴ ምሳሌዎችን አመለከተ ጌታ ግን ፈጸማቸው)[144] በማለት የሙሴ ምኞት መፈጸሙን መስክሯል።

መተርጕማን ሲቃውንት በውዳሴ ማርያም ትርጓሜ ላይ ሲያዩት ጌታ ለሙሴ ፊቴን ልታይ ከወደድኽ ዘር ካልወደቀባት እርሻ የበቀለ ስንዴ አምጥተኽ ብትሠዋልኝ እገልጽኻለኍ አለው፤ ሙሴስ የዋህ እምኵሉ ፍጥረት ይላል ሙሴ የዋህ ነበርና አገኛለኍ መስሎት በራእየ ሌሊት ሲባክን አድሯል። ጌታ ግን እንዲኽ ማለቱ በዘር በሩካቤ ከተወለደች ድንግል ያለ ዘር ያለ ሩካቤ ተወልጄ መሥዋዕት ኾኜ በምቀርብበት ጊዜ እገለጽልኻለኍ ሲለው ነው፤ ይኽም አልቀረ ከሦስቱ ባለሟሎቹ ጋር በደብረ ታቦር ታይቶኋል በማለት የሙሴ እርሻነቷን ሲገልጹ ፤ በትርጓሜ ቤት ታሪካቸው በስፋት የሚነገርላቸው ታላቁ የጉባዔ ሊቅ መምህር ኤስድሮስ ግን ሙሴ የብረት መደብ አስበጅቶ በዚያ ላይ አፈር አስደልድሎ ውሃ እያጠጣ ይበቅልልኛል መስሎት ዐርባ ዘመን ይዞ ዙሯል ብለው ተርጕመውታል።

144. Bride of Light P 142





## ክፍል ሦስት
## ነገረ ማርያም በኦሪት ዘኍልቍ

### የወይን ሐረግ

የሕይወት መብል የሕይወት መጠጥ ጌታችንን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የእስራኤል ልጆች በተቆረጧት የወይን ሐረግ ትመሰላለች (ዘኍ ፲፫፥፩-፳፱)። ይኽውም ልዑል እግዚአብሔር ለነቢዩ ለሙሴ የሚያወርሳቸው ምድረ ርስትን ይሰልሉ ዘንድ ከዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል አውጣጥቶ ምድሪቱን እንዲሰልሉ ከፍሬዋም እንዲያመጡ አገዘ ሰደዳቸው። ከእነሱ መኻከል ኢያሱና ካሌብ ይገኛሉ፤ እነሱም ምድሪቱን በመላ ሲሰልሉ ሰንብተው ሲመለሱ የስንዴው ዛላ እፍኝ ይመላ የወይኑ ዘለላ ጽዋ ይመላ ሲሉ «*ወበጽሐ እስከ ቈላተ ዐጽቅ ወርእይዎ ወገመዱ እምህየ ሐረገ ወይን ወውስቴቱ አሐዱ አስካል ወጾርዎ በምዝላል ወእምሮማንሂ ወእምበለስሂ* » ይላል የወይን ሐረግ እስካለበት ቆላ ደርሰው፤ ከወይኑ ሐረግ ዘለላውን ከስንዴው ዛላውን ቈርጠው፤ በባጢ (በቀፎ) አድርገው ከሮማን ከበለስ ጨምረው፤ ስድስቱ በፊት ስድስቱ በኋላ ኾነው የሳንሳ ተሸክመው መጡ፤ የእስራኤል ልጆች ከዚያ የወይን ሐረግ ስለቈረጡባት ያን ቦታ የወይን ሐረግ ያለበት የተገኘበት ሲሉት ስሙንም የኤሽኮል ሸለቆ ብለው ጠርተውታል (ዘኍ ፲፫፥፩-፳፬)።

ይኽውም ምሳሌ ነው ሐረግ የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ፍሬ የሕይወት ፍሬ የክርስቶስ አምሳል ነው፤ በፊት ያሉት የነቢያት ምሳሌ



www.ethiopianorthodox.org

ናቸው፤ ይኸም በፊት ያሉት የወይን ሐረጉን ተሸክመዋል ኾኖም ግን የተሸከሙትን እንዳያዩት ነቢያትም የሕይወት ፍሬ አምላክ ይወርዳል ከአማናዊት ሐረግ ከቅድስት ድንግል ማርያም ይወለዳል ብለው ትንቢት ቢናገሩም ወርዶ ተወልዶ አላዩም። በኋላ ያሉት የሐዋርያት ምሳሌ ናቸው፤ ይኸውም ተሸክመዋል የተሸከሙትን የወይን ሐረግ ያዩታል ሐዋርያትም አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወረደ ከቅድስት ድንግል ተወለደ ብለው አስተምረዋል ወርዶ ተወልዶ አይተዋል (ዮሐ ፩፥፲፬፣ ፩ዮሐ ፩፥፩)። ክብር ይግባውና ጌታችን አምላካችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነቢያት የሕይወት ፍሬ እሱን ሊያዩት ወደው ግን እንዳላዩት ሐዋርያት ግን ወርዶ ተወልዶ እንዳዩት በማቴ ፲፫፥፲፮-፲፯ ላይ «የእናንተ ግን ዐይኖቻችሁ ስለሚያዩ ጆሮቻችኹም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው፤እውነት እላችኋለኹ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም» በማለት አስተምሯል።

በመኾኑም *ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠን የርኁባን ምግብ የተጠሙት መጠጥ የሕይወት ወይን ክርስቶስን ያገኘንባት አማናዊት ሐረግ* እሷ ብቻ ናትና ሊቁ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴው ላይ *«ኦ ማርያም በእንተዝ ናፈቅረኪ ወናዐብየኪ እስመ ወለድኪ ለነ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘበዐማን»* (ማርያም ሆይ ስለዚኽ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን፤ እውነተኛ የጽድቅ መብልንና እውነተኛ የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና)[145] በማለት አመስግኗታል።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ልዩ ምስጢር በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *«አንቲ ውእቱ ቈጽለ ሐረግ ዘገመዱ ደቂቀ እስራኤል እምውስቴቱ አስካለ ወጸርዋ በመዝለል ዝ ውእቱ ፍሬ ድንግልናኪ ኢየሱስ ክርስቶስ»* (የእስራኤል ልጆች ፍሬን ከውስጡ ቈርጠው በ*መሎጊያ* (በባጢ ቀፎ) የተሸከሙላት የወይን ሐረግ አንቺ ነሽ ፤ ይኸውም የድንግልናሽ ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው)[146] በማለት ሲተረጉሙው፤ *ዳግመኛም* ለእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ የወይን ቦታነቷን በጉልሕ ሲያስረዳ፤

145. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፶
146. አባ ጊዮርጊስ ዘ*ጋሥጫ*፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፲፩





*«ኦ እግዝእትየ ማርያም ዐጸደ ወይን ዘጽድቅ ወአኮ ዐጸደ ወይን ዘሱባማ*

*ዘተኀረይኪ ለምድር እምነ ኵሉ አፅዋማ*

*በደመ አስካልኪ ተስዕረ ለሔዋ መርገማ*

*ወተፈትሐት ለተርኅዎ ኆኀተ ገነት እማኅተማ»*

(ከምድር ዛፎች ኹሉ የተመረጥሽ የሱባማ የወይን ቦታ ያይደለሽ የእውነተኛ የወይን ቦታ የኾንሽ እመቤቴ ማርያም ሆይ፤ የማሕፀንሽ ፍሬ በኾነ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የሔዋን መርገም ተሻረ፤ የገነት ደጃፍም ለመከፈት ከቁልፏ ተፈታች)[147] በማለት በማሕፀኗ ፍሬ በወልደ እግዚአብሔር የተደረገውን የድኅነት ምስጢር አድንቋል።

## የአሮን የወርቅ ማዕጠንት

ፍዳ መርገምን ያራቀ መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የወለደችልን ቅድስት ድንግል ማርያም አሮን ከቤተ መቅደስ ይዟት በወጣ የወርቅ ማዕጠንት ትመሰላለች (ዘኍ ፲፮፥፴፰-፶)። ይኸውም እስራኤልን አባር ቸነፈር ቢፈጃቸው ሙሴ ወደ ደብተራ ኦሪት ገብቶ ወደ ጌታ አመለከተ፤ያን ጊዜ ጌታ ለሙሴ ወንድምኽ አሮን ልብሰ ተክህኖውን ለብሶ ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ሕሙማኑ ባንድ ወገን ሕያዋኑን ባንድ ወገን አድርጎ እሱ በመኻከል ቁሞ ይጠንላቸው፤ ጢስ ቅታሬው በመኻከላቸው ይጋደማል፤ ከዚያ በኋላ ደዌ ከሕሙማን ወደ ሕያዋኑ አይተላለፍም አለው፤ ሙሴም አሮንን ጥናኽን ውሰድ ከመሠዊያው ላይ እሳት አድርግበት፣ ዕጣንም ጨምርበት ወደ ማኅበሩም ፈጥነኽ ወስደኽ አስተስርይላቸው፤ከእግዚአብሔር ፊት ቁጣ ወጥቶአልና መቅሠፍት ዠምሮአል አለው። አሮንም ሙሴ እንደተናገረው ማዕጠንተ ወርቁን ይዞ ዕጣኑን ጨምሮ ሕያዋኑን ባንድ ወገን ሕሙማኑን ባንድ ወገን አድርጐ እሱ በመኻከላቸው ቆሞ ቢያጥንላቸው ጢስ ቅትሬው በመኻከላቸው ተጋደመ፤ ከዚያ በኋላ ደዌ ከሕሙማኑ ወደ ሕያዋኑ ሳይተላለፍ ቀርቷል።

ይኸውም ምሳሌ ነው ማዕጠንት (ጥና) የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ደዌ የፍዳ የመርገም ምሳሌ፤

147. እንዚራ ስብሐት ገጽ 15



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያ በኋላ ደዌ ከሕመማን ወደ ሕያዋን እንዳልተላለፈ ጌታችን ከእመቤታችን ሰው ከኾነ ወዲኽ ፍዳ መርገም መውረድ ቀርቶአልና ፤ቀድሞ ግን ፍዳው ይወርድ እንደነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕ ፭፥፲፪-፲፬ ላይ ‹‹ስለዚኽ ምክንያት ኀጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ፤ በኀጢአትም ሞት እንደዚኹም ኹሉ፤ ኀጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ኹሉ ደረሰ፤ ሕግ እስከመጣ ድረስ ኀጢአት በዓለም ነበርና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኀጢአት አይቈጠርም ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኀጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ገምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ›› በማለት አባቱ ሲሠራው የነበረውን ኀጢአት ልጁ ቢሠራውም ባይሠራውም አባቱ በተቀጣበት መቅሠፍት ይቀጣ እንደነበር ገልጾታል፤ ዛሬ ግን በዘመነ ሐዲስ ጌታ ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲኽ ሰው ኀጢአቱን ቢሠራው እንኳ በንስሐ የሚድን ኾኗል፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ይኽቺ አሮን ከቤተመቅደስ ይዟት የወጣ ጽና (ማዕጠንት) የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን በሰንበተ ክርስቲያን ምስጋናው ላይ ‹‹ቡሩክ ዘንሥአ እመቅደስ›› (ቡሩክ ከቤተ መቅደስ ይዟት የወጣ የወርቅ ማዕጠንት አንቺ ነሽ )[148] በማለት አመስግኗታል፡፡

## <u>የአሮን በትር</u>

ያለ ዘር ያለ ሩካቤ አምላክን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች ድንግል ማርያም ሳይተክሏት በቅላ፣ ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ ፣ አብባ ፣ የበሰለ ለውዝ አፍርታ በተገኘች በአሮን በትር ትመሰላለች (ዘኍ ፲፯፥፩-፲)፡፡ ይኸውም በሙሴና በአሮን ሹመት ላይ በጠላትነት ተነሥተው የነበሩ አቤሮና ዳታን፣ ቆሬና ኹለት መቶ ሃምሳ ደጋፊዎቹ በኀጢአታቸው ምድር ተከፍቶ ሲውጣቸው፤ እኩሌቶቹን እሳት ዐመድ ካደረጋቸው በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን ከእያንዳንዱ ከዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል ዐሥራ ኹለት በትር ውሰድ፤ የእያንዳንዱን ስም በየበትሩ ላይ ጻፍ፤ በሌዊ በትር ላይ የአሮንን ስም ጻፍ፤ እኔ ከአንተ ጋር በምገናኝበት በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በምስክሩ ፊት አኑራቸው፤ የመረጥኹት ሰው በትር ታቈጠቊጣለች አለው፤ እሱም እንዳለው ዐሥራ ኹለት በትሮች ሰብስቦ የአሮንን በትር በመኻከላቸው አድርጎ

148. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት





እንዳይሳሳት ስማቸውን በየበትራቸው ጽፎ በምስክሩ ድንኳን በመገናኛው ሰዓተ ሌሊት አግብቶ ሲጸልይባቸው ዐድሮ፤ በመገናኛው ሰዓተ መዓልት ቢያወጣቸው የአሮን በትር ከሌሎች በትሮች ተለይታ ሳይተክሏት በቅላ፣ ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ፣ አብባ፣ የበሰለ ለውዝ አፍርታ ተገኘች፤ ከዚኽ በኋላ ጌታ የአሮን በትር ምልክት ኹና እንድትጠበቅ አዘዘ ፡፡

ይኸውም ምሳሌ ነው የአሮን በትር ከሌሎች በትሮች ተለይታ ለምልማ፣ አብባ፣ ፍሬ አፍርታ እንደተገኘች ኹሉ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከሌሎች የእስራኤል ሴቶች ተለይታ በንጽሐ ሥጋ፣ በንጽሐ ነፍስ፣ በንጽሐ ልቡና አብባ፣ አጊጣ ያለዘር ያለሩካቤ ጥዑም የሕይወት ፍሬ ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ ተገኝታለችና በእውነት የአሮን በትር የወላዲተ አምላክ ምሳሌ ናት (ኢሳ ፯፥፲፬፤ማቴ ፩፥፲፰-፳፫፤ ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰)፡፡ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ላይ ይኽነን ሲገልጽ ‹‹በትረ አሮን እንተ ሠረጸት ዘእንበለ ተክል ወኢሰቀይዋ ማየ ከማሁ አንቲኒ ኦ ወላዲተ ክርስቶስ አምላክነ ዘበአማን ዘእንበለ ዘርእ መጽአ ወአድኀነነ›› (ሳይተክሏትና ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር ነበረች፤ ያለ ዘር ሰው ኾኖ ያዳነን እውነተኛ አምላካችንን ክርስቶስን የወለድሽልን ሆይ አንቺም እንደርስዋ ነሽ)[149] በማለት የአሮን በትር ያለ ዘር ያለ ሩካቤ አምላክን በድንግልና የወለደች የድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ተርጒሞታል፡፡

ዳግመኛም ይኽቺ የአሮን በትር ወደ ምስክሩ ድንኳን በገባች በዐሥራ ኹለተኛው ሰዓት ሳይተክሏት በቅላ ውሃ ሳያጠጧት ለምልማ ለውዝ ገውዝ አፍርታ እንደተገኘች፤ እመቤታችን ቅድስት ማርያምም ዐሥራ ኹለት ዓመት በቤተ መቅደስ ተቀምጣ፤ የሕይወት ፍሬ ጌታን ያለ ዘር ያለ ሩካቤ በግብረ መንፈስ ቅዱስ በድንግልና ወልዳ ተገኝታለችና አማናዊት የአሮን በትር ናት፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በመጽሐፋ ይኽነን ሲተረጒም ‹‹ዕፀ ክርካዕ እንከ እሰምየኪ እስመ ክርካዕ ሠናየ ይጸጊ፣ ወሠናየ ይፈሪ፣ ወሠናየ ይጼኑ፣ ወከመ በትር ይቡስ ዘቦ ኅዕሌሁ ወዕአ ዑፃዊ ክህነት አሥረጸ አዕጹቀ ወአቍጸለ ክርካዐ ምዑዘ፣ ወከማሁ አንቲኒ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ ዐሠርተ ወክልኤተ ክራማተ ወፀነስኪዮ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘእንበለ ዘርዐ

149. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘሰንበተ ክርስቲያን ቅድስት



www.ethiopianorthodox.org

*ብእሲ››* (እንግዲኽ የሎሚ ዕንጨት ብዬ እጠራሻለኍ፤ ሎሚ መልካሙን ያብባል፣ መልካሙን ፍሬ ያፈራል፣ በጐ በጐ ይሸታልና፣ ዕጣ እንደወጣበት ደረቅ በትር ሳይተክል በቤተ መቅደስ ለምልሞ፣ ቅንጣት አውጥቶ፣ አብቦ ተገኝ፣ ሽታው ያማረ የተወደደውን ሎሚ አፈራ፤ እንዲኹም አንቺ በቤተ መቅደስ ዐሥራ ኹለት ዓመት ተቀምጠሽ፤ ያለ ወንድ ዘር መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፀነስሺው)[150] በማለት አብራርቶ አስተምሯል፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያሬድም በአንቀጸ ብርሃን መጽሐፉ ላይ *‹‹በትረ አሮን እንተ ሠረጸት ዘእንበለ ተክል ወኢሰቀይዋ ማየ በቤተ መቅደስ ወረሰያ ድሉተ ለካህናት ከማሁ አንቲኒ ነበርኪ ውስተ ቤተ መቅደስ በቅድስና ወበንጽሕ ወወፃእኪ እምቤተ መቅደስ በክብር ወበዐቢይ ፍሥሓ ወሠረጸ እምኔኪ ፍሬ ሕይወት ዘበአማን እግዚእነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ አ ቅድስት ዘ፡ የበለ ሩካቤ ረከብኪ ወልደ በከመ ተጠየቂዮ ለመልአክ ወይቤለኪ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ››* (ሳይተክሏትና ውሃ ሳያጠጧት የለመለመች የአሮን በትር በቤተ መቅደስ ነበረች፤ ለካህናት ዝግጁ ያደረጋት ነበረች፤ አንቺም በቅድስናና በንጽሕና ጸንተሽ እንደርስዋ በቤተ መቅደስ ኖርሽ፤ ከቤተመቅደስም በክብር በታላቅ ደስታ ወጣሽ፤ በእውነት የሕይወት ፍሬ የኾነ ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ካንቺ ተገኘ፡፡ ቅድስት ሆይ ከመልአኩ እንደተረዳሽው ከወንድ ያለመገናኘት ልጅን ነገኘሽ፤ መልአኩ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ ያድርብሻል፤ የልዑል ኀይልም ይጋርድሻል ብሎ ነግሮሽ ነበርና)[151] በማለት የድንግል ምሳሌ አስቀድሞ በአሮን በትር የተገለጸ መኾኑን አስተምሯል፡፡

ይኽቺ ሳይተክሏት የበቀለች የአሮን በትር ለኹሉ ምልክት እንድትኾን ከጌታ እንደታዘዘ ኹሉ ቅድስት ድንግል ማርያምም ያለ ዘር ያለ ሩካቤ በድንግልና አምላክን በመውለዷ ከአምላክ የተሰጠችን ልዩ ምልክታችን መኾኗ ኢሳይያስ በትንቢቱ በምዕ ፯፥፲፬ ላይ ‹‹ስለዚኽ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፤ እንሆ ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም ዐማኑኤል ብላ ትጠራዋለች›› በማለት ገልጾታል፡፡

150. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ አርጋኖን ዘሰኑይ ፳፥፲፪
151. ቅዱስ ያሬድ፤ አንቀጸ ብርሃን፤ ቍ ፲፭





# ክፍል አራት
# ነገረ ማርያም በኦሪት ዘዳግም

## ንጽሕት መስኩ

ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ በመንፈሰ እግዚአብሔር እየተቃኘ በኦሪት ዘዳግም ፴፪፥፩-፪ ላይ በእስራኤል ጉባኤ ኹሉ ፊት በዝማሬ የተናገራቸው የምስጋና ቃላት ብሥራተ ድንግልን የሚያመለክት ትንቢት ነው፡፡ ምስጋናውንም ሲዠምር *‹‹አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ››* (ሰማይ አድምጥ ልንገርኽ) በማለት በትንቢት አጕሊ መነጽርነት የራቀው ቀርቦለት የረቀቀው ጐልቶለት ብሥራትን የምትነግር ቅዱስ ገብርኤል ስማኝ ልንገርኽ ሲል ነው፤ *‹‹ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ››* (ምድርም የአፌን ቃሎች ትስማ) ሲል ደግሞ ድንግል ማርያም በአንተ አድሬ የምነግራትን ብሥራትን ትስማ የሚለውን ምስጢር አጕልቶ ያመለክታል፡፡

‹‹ትምህርቴ እንደ ዝናም ትፈስሳለች›› ሲል ምድር በላይዋ የሚፈስሰውን ዝናም እንድትቀበል ድንግል ማርያምም ነገሬን ትቀበለው ማለቱ ሲኾን *‹‹ወይረድ ከመ ጠል ነቢብየ››* (ነገሬ እንደ ጠል ትንጠባጠብ) ሲል የሚንጠባጠብ (የሚወርድ) ጠል ሳይሰማ ከሰማይ እንዲወርድ ኹሉ አካላዊ ቃልም ሳይሰማ ሰው የመኾኑን ምስጢር ያመለክታል፤ ‹‹በሣርም ላይ እንደ ካፊያ›› ማለቱ ይኽ የሚዘንም ዝናም ለስ ብሎ ሳይሰማ እንዲወርድ ኹሉ አካላዊ ቃልም ሳይሰማ ሰው ይኾን ሲል ነው፡፡ ይኸውም ሙሴ አስቀድሞ በመንፈሰ



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር እየተቃኘ የተናገረው የትንቢት ቃል ከቶ አልቀረምና አካላዊ ቃል ከእመቤታችን ሰው የኾነበት (የተፀነሰበትን) ምስጢር ማንም ከቶ አላወቀም ከሰውም ከመላእክትም ዕውቀት እጅግን የራቀና የመጠቀ ነው።

ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ይኽነን የሙሴን የምስጋና ቃል ሲተረጉም *‹‹ወነሐበ ይቤ እስመ ሙሴ ነቢይ ይብል ይረድ ከመ ጠል ነቢብየ ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር እስመ ይወርድ ከመ ጠል ውስተ ፀምር ወፀምርሂ ይትዌከፎ ለጠል ወያነውኅ ሥረዊሁ ወገራህትሂ ትትዌከፍ ዝናመ እንተ ይሴፈውዋ መስተገብራን ወያልህቆ ለዘርዕ ሶበ ተወክፎ በትእዛዘ እግዚአብሔር ወይሁብ ፍሬሁ በተመጥዎቱሂ ይትረከብ ትምህርት ፈድፋደ››* (ዳግመኛ ነቢይ ሙሴ ዝናም በእርሻ ላይ ጉምም በመስክ ላይ እንዲወርድ ቃልም እንደ ጠል ይውረድ አለ። ጠል በመስክ ላይ ከወረደ መስክም ጠልን የሚቀበለው ሥሩንም የሚያሳድገው ከኾነ፤ ገበሬዎች ተስፋ የሚያደርጉት እርሻም ዝናምን የምትቀበል ከኾነ፤ በእግዚአብሔር ትእዛዝም በተቀበለው ጊዜ ፍሬውንም የሚሰጥ ከኾነ፤ ዝናም ለእርሻ ጠል ለመስክ በመስጠቱ ፍጹም ትምህርት ይገኛል) *‹‹ወዝንቱ ይትሜሰል በእግዝእትነ ማርያም ድንግል ሶበ ትቤ እፎ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ ወሰምዐት እንዘ ይብል እስመ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ ወበእንተ ዝንቱ ዘትወልዲዮ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ልዑል። እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናገረ በመልአክ እንዘ ለሊሁ ለሐኬሁ ወፈጣሪሁ እግዚእ ነሥአ አርአያ ገብር ወእግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ተወክፈቶ ለቃል ኀቤሃ ከመ ትፅንሶ ዘከመ ይትዌከፍ ፀምር ጠለ፤ ወገራህት ዝናመ ወውእቱ ኀደረ ውስቴታ ወነሥአ እምኔሃ ሕላዌ እጓለ እመ ሕያው መዋቲ ወከመዝ አስተርአየ ፍሬ ንጹሕ››* (ይኽም (ፀፃ፦ርና እርሻ) ወንድ ሳላውቅ እንደምን ይኾንልኛል? በአለች መንፈስ ቅዱስ ያድርብሻል፤ የልዑል ኀይልም ይጸልልሻል፤ ስለዚኽም ከአንቺ የሚወለደው የባሕርይ አምላክ ነው፤ የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ይባላል፤ ሲል በሰማች በቅድስት ድንግል ማርያም ይመሰላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመልአኩ ቃል ተናገረ፤ እርሱ ፈጣሪ ሲኾን ጌታ የአዳምን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ ፤መስክ ጠልን፣ እርሻ ዝናምን እንድትቀበል ትፀንሰው ዘንድ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አካላዊ ቃልን በባሕርይዋ ተቀበለችው፤





እርሱም በማሕፀንዋ ዐደረ፤ ፈራሽ በስባሽ የነበረ የሰውን ባሕርይ ከእርሷ ተዋሕዶ ንጹሕ ፍሬ (ጌታ) እንዲኽ ተገለጠ)[152] በማለት የሕይወት ጠል የሕይወት ዝናም ክርስቶስን በማሕፀንዋ የተሸከመች ንጽሕት መስክ መኾኗን ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ አስቀድሞ የተናገረላት መኾኗን የቆጵሮሱ ኤጲስ ቆጶስ ቅዱስ ኤጲፋኒዮስ መልሕቅ በሚባል መጽሐፉ ላይ በጥልቀት ተርጉሞታል።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም በመጽሐፉ ላይ ሙሴ በኦሪት ዘዳግም ላይ የተናገረው ይኽ የትንቢት ቃል መፈጸሙን ሲያብራራ *‹‹ሙሴ ወኩሎሙ ማኅበረ እስራኤል ይዌድሱኪ እስመ ይቤ እግዚአብሔር በኦሪተ ሙሴ በእንቲአኪ አጽምዕ ሰማይ ወእንግርከ ወትስማዕ ምድር ቃለ አፉየ ወትሰፈዎ ከመ ዝናም ለነገርየ ወይረድ ከመጠል ነቢብየ ወከመ ዝናም ውስተ ገራህት ወከመ ጊሜ ውስተ ፀምር ገራህተ እንከ ሰመየኪ ወጠለ ሰመዮ ለወልድኪ››* (ሙሴና የእስራኤል አንድነት ያመሰግኑሻል፤ እግዚአብሔር በሙሴ ኦሪት ስለ አንቺ እንዲኽ ይላልና፤ ሰማይ አድምጥ ልንገርኽ፤ ምድርም የአንደበቴን ነገር ትሰማ ዘንድ ነገሬንም እንደ ዝናም ተስፋ ታድርገው፤ ትምህርቴም እንደ ካፊያ ይውረድ ፤እንደ ዝናምም በርሻ ላይ እንደ ጉምም በብዙት መጐናጸፊያ ላይ ይኹን፤ እንግዲኽ አንቺን እርሻ ብሎ ጠራሽ፤ ልጅሽንም ጠል አለው)[153] በማለት የጠለ ሕይወት የጌታ እናቱ አማናዊት እርሻ መኾኗን መስክሯል።

152. ሃይማኖተ አበው፤ ዘኤጲፋንዮስ፤ ምዕ ፶፮ ክፍል ፯፣ ገጽ ፻፷፰-፻፷፱
153. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፬፲፪



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ኹለት
## ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ኢያሱ እና በመጽሐፈ መሳፍንት

## ክፍል አንድ
## ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ኢያሱ

### <u>የካሌብ ርስት</u>

ምድረ ርስትን ለእስራኤል ልጆች ይከፍሉ ዘንድ አስቀድመው በእግዚአብሔር ከታዘዙት መኳከልና ከዐሥራ ኹለቱ ሰላዮች አንዱ የነበረው የዮፎኒ ልጅ ካሌብ፤ መስፍኑ ኢያሱ ምድር ርስትን በሚያካፍልበት ጊዜ ኬብሮንን ዐይቶ መጥቶ፤ ኢያሱን የእግዚአብሔር ባርያ ሙሴ ምድርን እሰልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ የአርባ ዓመት ሰው ነበርኍ፤ ከእኔ ጋር የወጡ ወንድሞቼ ግን የሕዝቡን ልብ አቀለጡ፤ እኔ ግን አምላኬን ፈጽሜ ተከተልኍ፤ሙሴም በዚያ ቀን አምላኬን እግዚአብሔርን ፈጽመኽ ተከትለኻልና እግርኽ የረገጠው ምድር ለአንተና ለልጆችኽ ለዘላለም ርስት ይኾናል ብሎ ምሏል፤ እርሱ እንደተናገረኝ እግዚአብሔር አርባ ዐምስት ዓመት በሕይወት አኖረኝ፤ አኹንም ሰማንያ ዐምስት ኾኖኛል፤ ሙሴም በላከኝ ጊዜ እንደነበርኍ ዛሬም ጕልበታም ነኝ መውጣት መውረድ እችላለኹ፤ በማለት ሀገሪቱን እንዲሰጠው ጠየቀው፤ ኢያሱም ነገሩን ከሰማ በኋላ ካሌብን ባርኮ ኬብሮንን ሰጥቶታል (ዘኍ ፲፫፥፲-፲፪ ፤ ፲፬፥፳፬ ፤ ኢያ ፲፬፥፮-፲፬ ፤ ፲፭፥፲፫ ፤ ፳፩፥፲፪)።





ካሌብም ኬብሮንን አጅ ካደረገ በኋላ አዙባ የምትባል ሴት አገባ ከጠላቶቹ ወገን ነበረችና ሃገሪቷን በስዋ ስም አልጠራትም። ቀጥሎ ከብታ የምትባል አገባ በከብታ ሀገሪቱ ተጠርታለች፤ ቀጥሎ ኤፍራታ የምትባል አገባ በኤፍራታ ኤፍራታ ተብላለች፤ እሷን አግብቶ ወንድ ልጅ ወለደ በዚያ ወራት እንጀራ እገባ እገባ ብሎለት ነበርና የልጁን ስም ልሔም አለው፤ በእብራይስጥ ኅብስት (ዳቦ፣ እንጀራዬ) ማለት ሲኾን በልሔም ሀገሪቱ ቤተልሔም (የእንጀራ ቤት) ተብላ ተጠርታለች። የዚኽች የካሌብ የርስት ሀገሩ የተለያየ የስም አጠራር ልዩ የነገረ ማርያም ምስጢርን የያዘ በመኾኑ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት ላይ

*«መክፈልተ ርስቱ ለካሌብ ወብዕለ ምስፍናሁ ለአውሴ*
*ሀብተ በረከቶሙ አንቲ ለሕዝበ ኤፍሬም ወምናሴ »*

(የካሌብ የርስቱ ዕጣ፤ የአውሴም የምስፍናው ብልጽግና፤ ለምናሴና ለኤፍሬም ወገኖችም የበረከታቸው ሀብት አንቺ ነሽ)[154] በማለት አስተምሯል። ይኸውም ከብታ ማለት ቤተ ስብሐት (የምስጋና ቤት) ማለት ሲኾን በአንድነት በሦስትነት ሲመሰገኑ ከሚኖሩ ከሦስቱ አካል አንዱ አካል ወልደ እግዚአብሔርን በማሕፀኗ የተሸከመች ናትና <u>ቤት</u> በእሷ <u>ስብሐት</u> በልጇ ተመስሏል (ማቴ ፪፥፱-፲፩ ፤ ሕ፩፥፱-፲፮፣ ሉቃ ፪፥፲፫-፲፬ ፤ ራእ ፳፥፮-፲፬)። ዳግመኛም ሀገሪቱ ኤፍራታ ተብላለች፤ ይኸውም የኤፍራታ ትርጓሜ ጸዋሪተ ፍሬ (ፍሬን የምትሸከም) ማለት ሲኾን፤ የሕይወት ፍሬ ክርስቶስን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች በኋላም ድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን ናትና <u>ፍሬ</u> በጌታ <u>ፀዋሪት</u> በእመቤታችን ይመሰሳል (ሉቃ ፩፥፴፪ ፤ዮሐ ፲፫፥፩-፲፩)። በተጨማሪም በልሔም ቤተልሔም (የእንጀራ ቤት) የተባለች ይኸቺ ሀገር በእውነት ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠውን የሕይወት ኅብስት ክርስቶስን የወለደች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ በመኾኗ <u>ቤተልሔም</u> (የእንጀራ ቤት) ተብላ ተጠርታበታለች (መዝ ፻፴፩፥፮ ፤ዮሐ ፮፥፵፱-፶፩) ። ሊቁ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ሲያይ

*«አንቲ ውእቱ ቤተልሔም ምድረ ኤፍራታ*
*ንጉሠ እስራኤል ዐቢይ እንተ አስተርአየ እምውስቴታ*
*ዘያበርሃ ለጥበብ ወለተነብዮ ዘይከሥታ »*

154. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 27



www.ethiopianorthodox.org

(ጥበብን የሚያበራትና ትንቢትንም የሚገልጣት ታላቁ (አማናዊው) የእስራኤል ንጉሥ በውስጧ የተገለጠ የኤፍራታ ዕጣ የኾንሽ ቤተልሔም አንቺ ነሽ)[155] በማለት አስተምሯል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በሰኞ ምስጋናው የቀደመ ሰው አዳምን ከኀሳር ወደ ክብር፣ ከሲኦል ወደ ገነት ለመመለስ የሕይወት እንጀራ ክርስቶስ የነቢያት የትንቢት ሀገራቸው ቤተልሔም (የእንጀራ ቤት) ከምትባል ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ መወለዱን በምስጢር ሲያይ *«ተፈሥሒ ኦ ቤተልሔም ሀገሮሙ ለነቢያት እስመ በኀቤኪ ተወልደ ክርስቶስ ዳግማይ አዳም »* (የነቢያት ሀገራቸው ቤተልሔም ሆይ ደስ ይበልሽ፤ ዳግማዩ አዳም ክርስቶስ ባንቺ ተወልዷልና)[156] በማለት ሲገልጽ ፤ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት ላይ

> *«አንቲ ውእቱ ደብረ መንግሥት እንተ ተሐንጸት እምቅድመ ጣ/ ዘተዋረሳ ላቲ ካሌብ ወልደ ዮፎኒ »*

(የዮፎኒ ልጅ ካሌብ የወረሳት ከጣኒ አስቀድሞ የተሠራች የመንግሥት ተራራ አንቺ ነሽ)[157] በማለት የካሌብ ርስትነቷን አጉልቶ አስተምሯል።

## ምድረ ርስት

አስቀድሞ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል የገባለት ማርና ወተት የምታፈሰው፤ ማለት ተድላ ደስታ የሚደረግባትና አሪት ወንጌል የሚነገርባት ዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው የወረሷት ሀገረ እግዚአብሔር የተባለችው ሀገረ ሰላም ኢየሩሳሌም በእውነት ፀወር ከ፭ቀን ሰማይና ምድር የማይወስነውን ወልደ እግዚአብሔርን በማሕፀኗ በመሸከሟ የእግዚአብሔር ሀገር ለተባለችው ለእመቤታችን፤ ዳግመኛም ልጅነትን ሥጋውን ደሙን ሰጥቶ ለኹሉ ሰላምን የሰጠ ዘላለማዊ ርስታችን ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ያዘጋጀልን ወሃቤ ሰላም ጌታን በመውልዷ ኢየሩሳሌም (ሀገረ ሰላም) ምድረ ርስት ተብላ የተጠራች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌዋ ናት (መዝ ፹፯፥፫፤ ፩ቆሮ ፪፥፱፤ ገላ ፬፥፳፮፤ ዕብ ፲፪፥፳፪፤ ራእ ፳፩፥፩-፬)።

155. ዝኒ ከማሁ ገጽ 44
156. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ውዳሴ ማርያም ዘሰኑይ
157. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 52





ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ ላይ *«ተፈሥሒ ኦ ኢየሩሳሌም ሀገረ እግዚአብሔር እንተ ታውሕዝ ሐሊበ ወመዓረ»* (ማርንና ወተትን የምታመነጭ የእግዚአብሔር ሀገር ኢየሩሳሌም እመቤታችን ሆይ ደስ ይበልሽ)[158] በማለት አመስግኗታል።

ዳግመኛም የአብርሃም ልጆች ነገደ እስራኤል በአርባ አራተኛ ጉዞአቸው ሰጢን ሰፍረው ርስታቸውን አይተው እንዳደሩ እንደዚኹ ኹሉ ምእመናንም ከአብርሃም ዠምሮ ቢቆጠር ከአርባ አራተኛዪቱ ትውልድ ከኾነችው ከእመቤታችን ተወልዶ ርስታቸውን የሚያወርሳቸውን ጌታን አይተዋል፤ ይኸውም ከትውልድ ኤልያቄምን አውጥቶ እመቤታችንን አግብቶ ሲቈጥር ሲኾን፤ በአርባ ዐምስተኛው ጉዞአቸው እስራኤል ዘሥጋ እየርስታቸው እንደገቡ ኹሉ ለእስራኤል ዘነፍስ ለምእመናንም አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቤተ አብርሃም ከተገኘች ከእመቤታችን ተወልዶ ወደ ርስታቸው ገነት መንግሥተ ሰማያት እንዲያገባቸው ያጠይቃልና በማለት መተርጕማን አፍታተው ያመስጥራሉ። የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛለት ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በአርጋኖን መጽሐፉ *«አንቲ ውእቱ ምድረ ርስት ዘአሰፈዎሙ እግዚአብሔር ለአበዊነ ምድር ስፍሕት ወሥምርት እንተ አበኒሃ ኀጻውንት ወእንተ አድባሪሃ ይኤልድዋ ለብርት ወለወርቅ»* (እግዚአብሔር ለአባቶቻችን ተስፋ ያስደረጋቸው ምድረ ርስት፤ የሰፋች የተወደደች ድንጋዮቿ ብረቶች የኾኑላት ተራሮቿም ብረትን ከወርቅ ጋራ የሚያከማቹባት አንቺ ነሽ) [159] በማለት ምስጢሩን ገልጦታል።

ጌታም ለሙሴ በኦሪት ዘኁልቍ በምዕ ፴፭፥፱-፲፬ ላይ ለእስራኤል ልጆች በምድረ ርስት በከነዓን ለእስራኤል ልጆች መማፀኛ ይኾኗቸው ዘንድ ባለማወቅ ነፍስ የገደለ ኹሉ በዚያ ይማፀን ዘንድ ለስደተኛም መማፀኛ ይኾኑ ዘንድ በዮርዳኖስ ማዶ ሦስት፤ በከነዓን ሀገር ሦስት ሀገረ ምስካይ (የመማጠኛ ከተማ) እንዲለዩ አዟቸዋል፤ ቅብዐ ክህነት የተቀባው ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት ድረስ፤ በዚያ እንዲኖርና ነፍስ የገደለው ሰው ከመማፀኛ ከተማ ወጥቶ ቢገኝ ባለደሙም ገዳዩን ከተማፀነበት ሀገር አውራጃ ወጥቶ አግኝቶ ቢገድለው በባለደሙ ዕዳ

158. አርጋኖን ዘኀሙስ ፬፥፲፰
159. ዝኒ ከማሁ፤ ዘዐርብ ፫፥፲፫



www.ethiopianorthodox.org

የሌለበት እንደኾነ፤ ሊቀ ካህናቱ ከሞተ በኋላ ግን ነፍሰ ገዳዩ ወደ ምድረ ርስቱ የሚመለስ መኾኑን አስቀድሞ ገልጾለታል (ዘኍ ፴፭፥፳፭-፳፰)።

ይኸውም ለጊዜው ተደርጓል፤ ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር ይኸውም የመማፀኛ ከተማ የእደ እግዚአብሔር፤ ከዚያ የሚኖሩ በእደ እግዚአብሔር የተጠበቁ የጻድቃን ምሳሌ (ጥበ ፫፥፩)፤ በውጭ ቢገኝ ይሙት ማለቱና ወጥተው የተገኙት መሞታቸው ከእደ እግዚአብሔር በአፍአ ያሉት በሲኦል ሥቃይ የመቀበላቸው ምሳሌ፤ ሊቀ ካህናቱ የጌታ፤ ሊቀ ካህናቱ እስኪሞት በውስጡ ይኑር ማለቱም ጌታ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ተውሕዶ ሰው ኾኖ እስኪሞት ድረስ ደጋጎቹ በእግዚአብሔር ተጠብቀው የመኖራቸውን ምሳሌ ሲያሳይ ፤ሊቀ ካህናቱ ከሞተ በኋላ ወደ ርስት ሀገሩ ይመለስ ማለቱ ሊቀ ካህናት ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋን ተውሕዶ ከሞተ በኋላ ምእመናን ርስታቸው ወደኾነች ወደ ገነት ዳግመኛ የመመለሳቸውን ነገር ሲገልጽለት ነውና (፩ጴጥ ፫፥፲፰-፳)፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በኆኅተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ ይኽነን ምስጢር ጠቅልሎ *‹‹ርስተ ተድላሆሙ ለ፲ወ፪ቱ ደቂቀ ያዕቆብ ምድር እንተ ታውሕዝ መዓረ ምስለ ሐሊብ››* (ወተትን ከማር ጋር የምታፈስስ የያዕቆብ ዐሥራ ኹለት ልጆች የተድላ ደስታ ርስታቸው አንቺ ነሽ)[160] በማለት አመስግኗታል።

<u>የኢያሱ የምስክር ሐውልት</u>

በሙሴ እግር የተተካው መስፍኑ ኢያሱ እግዚአብሔርን ለማምለካቸው በእስራኤል ፊት የተከላት ታላቅ ደንጊያ በቅድስት ድንግል ማርያም ትመሰላለች (ኢያ ፳፬፥፲፬-፳፰) ።

ይኸውም እስራኤል ዮርዳኖስን ተሻግረው ምድረ ርስት ከገቡ በኋላ ኢያሱ ሕዝቡን ሰብስቦ፤ አባቶቻችኍ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኳቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችኹባቸው የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደኾነ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ፤እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን አላቸው፤ ሕዝቡም እኛስ የሞአብን የዐሞንን አምላክ አናመልክም፤ ባሕር ከፍሎ ጠላት ገድሎ ከግብጽ ያወጣንን፤ መና ከደመና





አውርዶ ውሃ ከጭንጫ አፍልቆ አርባ ዘመን የመገበንን ፈጣሪያችን እግዚአብሔርን ነው የምናመልክ አሉት። አኹን መስፍኑ ኢያሱ የአሞራውያንን የሞአብን አማልክት እናመልካለን ቢሉት የሚተዋቸው ኾኖ ሳይኾን አስወድዶ ለማድረግ ነው፤ ከዚያም ኢያሱ ምን ምልክት ይኹንባችኍ? አላቸው፤ አንተ ባወቅኽ ብለውታል፤ ከቆላ የመጣው ዐቀበቱን ከደጋ የመጣው መስኩን ጨርሶ የሚያርፍባት እንደ አፈቄላ ያለች ናት፤ ከዚያች ላይ ሦስት ረድፍ ያላት ታላቅ ደንጊያ ተክለው ተማምለውባታል። ከቈላ የመጣው ዐቀበቱን ከደጋ የመጣው መስኩን ጨርሶ ከዚያች ሲያርፍ የማያውቀው የሚያውቀውን ወንድሜ ይኽቺ ደንጊያ ምንድን ናት? ይለዋል፤ ይቺማ እስራኤልና ኢያሱ የተማማሉባት ናታ፤ እየተባለ አምልኮቱን ስትመሰክርለት ትኖራለች።

ይኽቺውም ለጊዜው ብትደረግም ለኋላው ግን ምሳሌ ነበረች፤ ይኸውም ሐውልት የእመቤታችን ምሳሌ ስትኾን፤ ያቺ ያማረች እንደኾነች ኹሉ እመቤታችንንም ባማረ ባማረ ይመስላታልና (መሐ ፬፥፯)፤ ሦስት ገጽ የሦስቱ ድንግልናዋ(የድንጋሌ ሥጋዋ፣ የድንጋሌ ነፍሷ፣ የድንጋሌ ኅሊናዋ) አንድም ያቺ ከላይ አንድ ከሥር ሦስት እንደኾነች ኹሉ አንድነት ሦስትነትም ተለይቶ የታወቀ ጌታ ከእመቤታችን ከተወለደ ወዲኽ ነው (ሉቃ ፩፥፴፭፤ ዕብ ፩፥፩-፫)፤ ዳግመኛም በዚያች ሐውልት አምልኮት እንደጸናባት በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያምም ወረደ ተወለደ ተብሎ አምልኮት ጸንቶባታል (ማቴ ፪፥፩-፲፪፤ ሉቃ ፪፥፯-፳፤ ዮሐ ፩፥፲፬፤ ሮሜ ፩፥፩-፬፤ ገላ ፬፥፬)። ሊቁ አባ ሕርያቆስ ይኽነን ድንቅ ምስጢር እንደ ወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ በቅዳሴው ላይ *‹‹ሐውልተ ስምዕ ዘኢያሱ››* (የኢያሱ የምስክሩ ሐውልት አንቺ ነሽ)[161] በማለት አመስግኗታል።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ኹለት

## ነገረ ማርያም በመጽሐፈ መሳፍንት

### <u>የባርቅ ኀይል</u>

ይኽ ባርቅ ትውልዱ ከነገደ ንፍታሌም ሲኾን በሱ ጊዜ የነበረው የአሕዛብ ንጉሥ ኢያቢስ ቢትወደዱ ሲሳራ ይባላሉ (መሳ ፬፥፪-፫)። ለቢትወደዱ ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገሎች ነበሩትና ኻያ ዓመት ያኽል እስራኤልን እጅግ አስጨንቋቸው ነበር፤ በዚያን ጊዜ ነቢዩቱ ዲቦራ በተራራማው በኤፍሬም አገር በራማና በቤቴል መኻከል ካለው የዲቦራ ዛፍ ከሚባለው ከዘንባባው በታች ተቀምጣ የእስራኤል ልጆች ወደእሷ እየመጡ ትፈርድላቸው ነበር፤ እሷም ባርቅን ጠርታ ወደ ታቦር ተራራ ውጣ፤ የኢያቢስን የሰራዊት አለቃ ሲሳራን ከሠረገላዎቹ ከሰራዊቱ ጋር እግዚአብሔር በእጅኽ አሳልፎ ይሰጥኻል አለችው፤ ባርቅም አንቺ ከኔ ጋር ብትኼጂ እኔ እኼዳለኍ፤ አንቺ ግን ከእኔ ጋር ባትኼጂ እኔ አልኼድም አላት፤ እኔማ የኼድኹ እንደኾነ ድሉ የሴት ይባልብኻል እንጂ አለችውና ተነሥታ ከባርቅ ጋር ወደ ታቦር ተራራ ወጣች።

ሲሳራም ይኽንን ሰምቶ ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎቹንና ሰራዊቱን ከአሪሶት እስከ ቂሶን ወንዝ ሰብስቦ ለውጊያ አዘጋጀ፤ ዲቦራም ባርቅን እግዚአብሔር ሲሳራን በእጅኽ አሳልፎ የሚሰጥበት ቀን ዛሬ ነውና ተነሣ ብላ ነግራው ከዐሥር ሺሕ ሰራዊት ጋር በመኾን ያን ኹሉ የብረት ሠረገላና የሲሳራን ሰራዊት ኹሉ አጠፉ፤ ንጉሡም በእግሩ ሸሽቶ ኼዶ ኢያኤል ብእሲተ





ኮቦር ቄንያዊ ይላታል፤ በእስራኤልና በአሕዛብ መኻከል ያለች ድንበርተኛ ሴት ናት ኼዶ እንድትሰውረው ጠየቃት፤ በመጐናፀፊያዋ ሰወረችው፤ እርሱም ጠምቶኛልና ውሃ አጠጭኝ አላት፤ እርስዋም የወተቱን አቁማዳ ከፍታ አጠጥታው እንቅልፉን ተኛ፤ ከዚያም የድንኳኑን ካስማ ወስዳ በቀኝ እጅዋ መዶሻ ይዛ በተኛበት *ጸቀወቶ ወደመቀቶ በመትክለ ደብተራ* ይላል በገሮ ግንዱ ካስማውን ቸንከራ ከመሬት ጋር አጣበቀችው፤ ከዚያው ጐስቍሎ ሙቷል፤ወዲያው ባርቅ ደረሰ ኢያኤልም ና የምትሻውን ሰው ላሳይኽ ብላ ግኍ ጥላለታለች (መሳ ፬፥፩-፳፬፤ ዕብ ፲፩፥፴፪)።

ከዚያም ዲቦራና ባርቅ *‹‹ንቂ ንቂ ዲቦራ ሆይ፤ ንቂ ንቂ ዲቦራ ሆይ ን ንቂ ፤ቅኔውን ተቀኚ፤ ባርቅ ሆይ ተነሣ ምርኮኽን ማርክ... የቄናዊዉ የሐቤ ሚስት ኢያኤል በድንኳን ውስጥ ከሚኖሩ ሴቶች ይልቅ የተባረከች ትኹ* እያሉ ቅኔን ተቀኝተዋል፤ ከዚያም ምድሪቱ ዐርባ ዓመት ያኽል ዕረፍት አግኝታለች (መሳ ፭፥፩-፫)።

ይኽ በእስራኤል ዘሥጋ ላይ ከባድ መከራን ያጸናና በጠላትነት የተነሣ ዘጠኝ መቶ የብረት ሠረገላዎችና ብዙ ሰራዊት በሥሩ የነበሩት ሲሳራን በእምነት ባርቅና ዲቦራ ድል እንደነሡትና በኢያኤል እጅ በካስማ ተሸንክሮ ጐስቍሎ እንደሞተ ኹሉ፤ ዛሬም እስራኤል ዘነፍስ በተባልን ክርስቲያኖች ላይ ጽኑ ፍዳ መከራ ሊያጸናብን የሚወድ፤ ጽኑ ረቂቅ ጠላታችን ዲያብሎስን ከሰራዊቱ ከአጋንንት ጋር፤ በምልጃዋ በጸሎቷ አጋዥ ትኾነን ዘንድ በመስቀል ሥር ከአምላካችን በተሰጠችን በወላዲተ አምላክ በቅድስት ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን ድል የምንነሣው ኾነናልና፤ በጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀቱ ኢትዮጵያዊዉ ቄርሎስ የተባለው ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በኆኅተ ብርሃን መጽሐፉ ላይ *‹‹መግረሪተ ፀሮሙ ለባርቅ ወለዲቦራ፤ ወበረከታ ለኢያኤል በእንተ ዘቀተለቶ ለሲሳራ፤ መዐዛ መሥዋዕቱ ለዮፍታሔ መስፍን››* (የባርቅንና የዲቦራን ጠላቶች ድል የምትነሺ ከእግር በታች የምታስገግር፤ ሲሳራን ስለገደለቺው ለኢያኤልም በረከቷ፤ለመስፍኑ ለዮፍታሔም የመሥዋዕቱ መዐዛ አንቺ ነሽ)[162] በማለት ምስጢሩን ጠቅልሎ አስተምሯል።

162. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ ኆኅተ ብርሃን ፤ገጽ 96



www.ethiopianorthodox.org

## <u>የማር ወለላ፤ ኅቱም መንሰከ አድግ፣ የሶምሶን ሹሩባ</u>

ትውልደ ሴም፣ ትውልደ ካም፣ ትውልደ ያፌት በመላ ብጽዕት ነሽ እያሉ የሚያመሰግኗት ቅድስት ድንግል ማርያም፤ ሶምሶን ከአንበሳው አፍ ባገኛት የማር ወለላ፤ ውሃን አስገኝታ ጽሙን ባበረደችለት መንጋጋና፤ ጠላቶቹን ድል በነሣባት ሀጉሩ ላይ ባለች ኀይል እንደምትመሰል ቅዱስ ኤፍሬም፤ ያዕቆብ ዘስሩግ፤ አባ ጊዮርጊስ በስፋት አስተምረዋል (መሳ ፲፬፥፰፤ ፲፭፥፲፱፤ ፲፮፥፲፯)።

ይኸ ሶምሶን ትውልዱ ከነገደ ዳን ሲኾን አባቱ ማኑሄ እናቱ እንትኩይ ይባላሉ፤ መልአከ እግዚአብሔር ለእሷ ተገልጦ ደግ ልጅ ትወልጃለሽና የሚያሰክር ነገር አትጠጪ፤ ልጁም ከእናቱ ማሕፀን ዠምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ ይኾናልና በራሱ ላይ ምንም አይድረስበት አላት፤እሷም ኼዳ ለባልዋ ነገረችው፤ ማኑሄም እንዲገለጽለት ጸሎት አቀረበ፤ ኹለተኛ በተገለጸላት ጊዜ ኼዳ ባሏን ጠራች፤ መልአከ እግዚአብሔርም ደግ ልጅ ትወልዳላችኹና ርኩስ ነገር ከመመገብ ተከልከሉ ብሏቸው፤ ማኑሄ የሠዋውን መሥዋዕት በዘንግ አቃጥሎ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ዐርጓል።

ወዲያው ሶምሶን ተፀነሰ፣ ተወለደ፣ አደገ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በጾርዓና በኤሽታኦል መኻከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ ኀይልን ሰጠው (መሳ ፲፫፥፳፭)። ዐሥራ ፀምስት ዓመት ሲኾነው አባቱና እናቱ ይዘውት ወደ ተምና ወረዱ፤ በተምና ወዳለው ወደ ወይን ስፍራ ሲደርስ የአንበሳ ደቦል አግኝቶ በተሰጠው ኀይል በጡጫ መትቶ ገድሎት ኼዷል (መሳ ፲፬፥፮-፱)። ከጥቂቶች ቀናት በኋላ ተመልሶ ቢያይ ንብ ከአፉ ውስጥ ገብታ ማር ሠርታ አግኝቶ ተመግቦ ለእናትና ለአባቱ ይዞላቸው ኼዷል።

ከሞተው አንበሳ አፍ የተገኘች ይኽቺን ጣፋጭ የማር ወለላ በጥልቅ የነገረ መለኮት ዕውቀቱ ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ከዚኽ መዋቲ ዓለም ውስጥ ብቻዋን ተለይታ በሃይማኖት፣ በምግባር፣ በንጽሕና፣ በድንግልና ጣፍጣ ማርን እንደሚያዘጋጅ እንደ ንብ ድምፅ የቅዱስ ገብርኤልን ብሥራት ሰምታ ቍርባን አሕዛብን መሥዋዕት አሕዛብን የተቀበለ ምግበ ርኁባን ጌታን የወለደች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን በአርጋኖን መጽሐፉ *‹‹ኦ ድንግል ጸቃውዕ እንተ ተቀድሐት እምአፈ አንበሳ በእደ ወልደ*





*ማኑሄ›* (ድንግል ሆይ በማኑሄ ልጅ በሶምሶን እጅ ከአንበሳ አፍ የተቀዳሽ የማር ወለላ)[163] በማለት የምሳሌውን እሙንነት ገልጿል።

በርካቶች ሊቃውንትም በኋላ ዘመን የተገለጸ ይኽነን ድንቅ የጌታ ሥጋዌ በንብ በማር እየመሰሉ አስተምረዋል። ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ ላይ *‹‹ኦ ከዊን እም ዘምስለ አመት ጸበተ ከርሥ ዘምስለ ርሕብ ፅንስ እንበለ ሩካቤ ከመ ንህብ ዘእምቃል ንባብ ሐሊብ ምስለ ድንግልና ጽሙር›* (ከገረድነት ጋራ እናትነት እንደምን ያለ ነው፤ ከስፋት ጋራ የኾድ መጥበብ፤ እንደ ንብ ያለ ሩካቤ ከቃል ድምፅ የተገኘ ፅንስ፤ ከድንግልና ጋር አንድ የኾነ ሐሊብ)[164] በማለት መዓርን ያለ ተራክቦ በአፉራው ድምፅ ብቻ የምታዘጋጀውን ንብንና፤ ያለ ዘር ያለ ሩካቤ ምግበ ርኁባን ጌታን በብሥራተ መልአከ የፀነሰች ቅድስት ድንግል ማርያምን እያነጻጸረ አስተምሯል። የእመቤታችን በረከተ ውዳሴዋ ጣዕመ ውዳሴዋ የበዛላት ሊቁ አባ ጊዮርጊስም እጅግ በሚያስደንቅ ኹኔታ ይኽነን ታላቅ ምስጢር በጥልቀት እንዲኽ በማለት ተንትኖታል፤

*‹‹ኦ እግዝእትየ ቅድስት ድንግል ማርያም ዘበዕብራይስጢ ማሪሃም እንተ ወለድኪ ቃለ ዘእንበለ ዘርዐ ብእሲ ከመ ልደተ ንህብ እምእንቈራ ምፋጣረ ጸቃውዕ፤እስመ ልደተ ዕጌ እምእንቈራ በንቃወ ዜማ ንህብ ይከውን፤ ወጸቃውእኒ ካዕበ እምእንቈራ ትትቀዳሕ ወልደተ ቃልኒ እምኔኪ ከመዝ ኮነ፤ እስመ ይቤ ገብርኤል ተፈሥሒ ፍሥሕት እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ወናሁ ትፀንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ወትቤሊዮ ለመልአክ እፎኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ፤ ወይቤለኪ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኀይለ ልዑል ይጼልለኪ፤ ቃለ አብ ደምፀ ውስተ እዝንኪ በአፈ ገብርኤል ወበእንተዝ ተመሰልኪ በእንቈራ እስመ በሰሚዐ ቃል ፀነስኪ፤ ወህየንተ አክናፈ ንህብ አክናፈ መንፈስ ቅዱስ ጸለለኪ፤ ወህየንተ ጸቃውዐ መዓር ዘይትጌበሮ ንህብ በአስተጋብኦ ጽጌያት ጸቃውዐ ትንቢት ዘተቀስመ እምጽጌ ቃሎሙ ለቅዱሳን ነቢያት ተክዕወ በላዕሌኪ››* (በዕብራይስጥ ማሪሃም የተባልሽ የተመረጥሽ እመቤቴ ድንግል ማርያም ሆይ የንብ ልደት

163. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፰+፰
164. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፹፫



www.ethiopianorthodox.org

ከማር ወለላ መፈጠሪያ ስፈፍ እንዲኾን፤ የወንድ ዘር ምክንያት ሳይኾንሽ (ያለ ዘርዐ ብእሲ) አካላዊ ቃልን የወለድሽ ነሽ፤ የንብ ዕጭ ልደት ከስፈፍ በንብ ዜማ ጩኸት ይኾናልና፤ ኹለተኛም የማር ወለላ ከስፈፍ ቀቀዳለች፤ የአካላዊ ቃል ልደትም ከአንቺ እንዲኹ ኾነ ፤መልአኩ ገብርኤል እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስተኛዪቱ ደስ ይበልሽ ባለ ጊዜ ከሴቶች ኹሉ ይልቅ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤የማሕፀንሽም ፍሬ ቡሩክ ነው፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለሟልነትን አግኝተሻልና እንሆ በድንግልና ፀንሰሽ በድንግልና ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ ትጠሪዋለሽ፤ መልአኩንም እንዲኽ ትይዋለሽ፤ ወንድን ሳላውቅ ይኽ እንደምን ይኾንልኛል? መልአኩም እንዲኽ አለሽ፤ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ በላይሽ ያድራል፤ የልዑል ኀይልም ይጋርድሻል ፤በገብርኤልም አንደበት የአብ ቃል በጆሮሽ ተሰማ (ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰)። ስለዚኽ በንብ እንጀራ ተመሰልሽ፤ ቃልን በመስማት ፀንሰሻልና (ማቴ ፩፥፲፰፤ ዮሐ ፩፥፲፬)። በንብ ክንፎችም ፈንታ (እንደ ንብ ክንፎችም) የመንፈስ ቅዱስ ክንፍ ጋረደሽ፤ አበቦችን በማሰባሰብ ንብ እንደሚሠራው የማር ወለላም (በሚሠራው የማር ወለላ ፈንታም) ከቅዱሳን ነቢያት ቃል አበባ የተለቀመ የትንቢት ወለላ በአንቺ ላይ ፈሰሰ)[165] በማለት ረቂቅና ጥልቅ የኾነ የነገረ ማርያም ትምህርትን አስተምሯል።

ይኽ ኀይል ሥጋዊ የተቀዳጀ ሶምሶን በተሰጠው ኀይል ተጠቅሞ የፍልስጤማውያንን እኽል ክምር በቀበሮዎች አማካይነት በማቃጠሉ፤ ፍልስጤማውያን እስራኤላውያንን ሶምሶንን ይዛችኊ ትሰጡን እንደኾነ ስጡን፤ ያለዚያ ግን ጠባችን ከእናንተ ጋር ነው በማለት አስፈራሯቸው። እነሱም ኼደው ነገሩት፤ እሱም ይዛችኊ ስጡኝ ብሏቸው በኹለት ዐዲስ ገመድ አስረው ሰጡት፤ ፍልስጤማውያንም እንይዘዋለን ብለው ሲኼዱ ገማምዶት ተነሥቶ ዐዲስ የአህያ መንጋጋ አግኝቶ ቢወረውረው ባንድ ጊዜ ሺሕ ሰው ገድሏል፤ ወዲያው ውሃ ጥም ቢሰማው ጌታዬ ኀይል ባደረግኽልኝ ቀን በውሃ ጥም ትገለኝ? ብሎ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት ከኀቱም መንሰከ አድግ ከመንጋጋው ላይ ውሃ መንጭቶለት ጠጥቶ ነፍሱ ተመልሳለት ጥንካሬን አግኝቷል (መሳ ፲፭፥፩-፲፱)።

ይኽ ለጊዜው ቢደረግም ለኋላው ምሳሌ ነበር፤ ይኸውም ጽምአ ሶምሶንን ያበረደ ውሃ ከኀቱም መንሰከ አድግ እንደተገኘ ኹሉ ለጽሺሕ ዘመን

165 አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፩





የሕይወት ውሃዋን ተጠምታ የነበረችውን የነፍሳትን ጥም ያበረደ የሕይወት ውሃ ጌታ በኀቱም ድንግልና ከእመቤታችን የመወለዱን ፍጻሜ ያሳየ መኾኑን፤ ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን በድንግልና በፀነሰችበት ጊዜ፤ ይኽ ከኀሊና ኹሉ በላይ የኾነ ረቂቅ ምስጢር ሳስጨነቀው ለአረጋዊው ዮሴፍ እንዳብራራችለት ታላቁ የነገረ ማርያም መጽሐፍና ከሊቃውንት ቅዱስ ኤፍሬም፣ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ እና አባ ጊዮርጊስ ባንድ መንፈስ ቅዱስ ተገልጾላቸው መስክረዋል (ዮሐ ፬፥፲፫-፲፭፤ ራእ ፳፪፥፩)።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ስለ ጌታችን ልደት በሚናገረው ታላቅ መጽሐፉ ላይ ቅድስት ድንግል ማርያም ስለድንግልናዋ ምስክርነት ለዮሴፍ የነገረችውን እንዲኽ በማለት ገልጾታል፤ Mary said: «If you seek testimony for my words...» (ማርያምም ለዮሴፍ መለሰች «ለቃሌ ምስክር ከፈለግኽ ከመጽሐፍም ከተፈጥሮም ልትረዳ ትችላለኽ፤ አዳምን የወለደች መሬትን ማን በጋብቻ ተገናኝቷት ነው? አዳምስ ሔዋንን ለመውለድ ከማን ጋር ተገናኝቷል? ከዛፍስ ጋር ማን ተገናኝቶ ነው በግን ያስገኘው? (ዘፍ ፳፪፥፲፫)፤ ድንጋዩንስ ማን ዐውቆት ነው ወንዞቹን የወሰደው? (ዘፀ ፲፯፥፩-፯)፤ በማንስ መንፈስ ነው በትሩ ባልተለመደ ኹኔታ የለመለመው? (ዘኁ ፲፯፥፩-፱)፤ በየትኛውስ የጋብቻ አንድነት ነው ሕይወት አልባው መንጋጋ ውሃን ያፈለቀው? (መሳ ፲፭፥፲፱) በእነዚኽ ኹሉ ማሕፀኖች እነዚኽን ኹሉ ልጆች ያስገኘ ማን ነው?...እውነት ቢኾንም ቅሉ በተፈጥሮ ካላመንክ መጽሐፍ ብቻውን ምስጢሩን ሊያስረዳኽ አይችልም...»[166] በማለት ጌታ ከእሷ በድንግልና ለሚወለው ልደቱ አስቀድሞ ብዙ ሕብረ አምሳልን መግለጡን ለአረጋዊው ዮሴፍ አስተምራዋለች።

ከፍልስጤማውያን ወገን ሺሕን ሰው በአንዲት የአህያ መንጋጋ ኀያሉ ሶምሶን ያጠፋባት ጠላቶቹ አሕዛብን ድል ያደረገባት ድንቅ ሥራዎችን የሠራባት ብርታት ኀይል ያገኘባት የጌታ ስጦታ የኾነቺው ከተወለደ ጀምሮ ተቈርጣ የማያውቀውን ይኽቺን ፀጉሩን፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ ጥንተ ጠላታችንን ዲያብሎስን ሠራዊቱ አጋንንትን የእሱን የክሕደት አሠር የሚከተሉ መናፍቃንን በጸሎቷ፣ በምልጃዋ፣ በቃል ኪዳኗ ድል እንነሣ ዘንድ ከጌታ ዘንድ በመስቀል ሥር የተቀበልናት የኀያላን ጌታ የክርስቶስ እናት የቅድስት ድንግል

166. Jacob of Serugh, On the Nativity p 70



www.ethiopianorthodox.org

ማርያም ምሳሌ መኾኗን «ኦ ድንግል ጸቃውዕ እንተ ተቀድሐት እምአፈ አንበሳ በእደ ወልደ ማኑሄ፤ ወኀዕበ ዘዚኣሁ ጽንዕ እንተ ነበረት ዲበ ሥዕርተ ድማኁ» (ድንግል ሆይ በማኑሄ ልጅ በሶምሶን እጅ ከአንበሳ አፍ የተቀዳሽ የማር ወለላ፤ ኹለተኛም በራስ ጠጉሩ ላይ የነበረች የርሱ ኀይል አንቺ ነሽ)[167] በማለት ገልጺታል፡፡

ይኽ ሶምሶን ጌታ እንዲኽ ባለ ኀይል ቢያከብረውም እሱ ግን አምልኮተ እግዚአብሔር ከሌላቸው ከፍልስጤማውያን አሕዛብ ወገን የኾነች በሶሬቅ ሸለቆ የነበረች ደሊላ የምትባል ሴት ለመደ፤ የፍልስጥኤም መኳንንትም ብር እንሰጥሻለንና እርሱን ሸንግለሽ በእርሱ ያለ ታላቅ ኀይል በምን እንደኾነ እኛስ እርሱን ለማዋረድ እናስረው ዘንድ የምናሸንፈው በምን እንደኾነ ጠይቀሽ ንገሪን አሏት፤ እሷም በፍቅር ቃል እየተጠቀመች ሶምሶን ከኀይሉ የሚለይበትን፤ ለፍልስጤማውያን አሳልፎ የሚሰጥበትን መንገድ ለኹለት ጊዜ ሞክራለች፤ ዛሬም ጥንተ ጠላታችን ዲያብሎስ በምልጃዋ ኀይል ጽንዕ ከምትኾነን ከወላዲተ አምላክ ለመለየት እንደ ደሊላ በጥቅማጥቅም የሰከሩ መናፍቃንን ልባቸውን ማደሪያ አንደበታቸውን መናገሪያ በማድረግ እጅግ በለሰለሰ አንደበት ውስጡ ግን ክሕደትና መርዝን በተመላ ቃላት የአማኙን ልብ ለማዳከም ይሮጣልና እጅጉን መንቃትና መጠንቀቅ አለብን (ራእ ፲፪፥፬-፮፤ ፲፪፥፲፫-፲፯፤ ፲፫፥፮)፡፡

ሊቀ ሐዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስም በመልዕክቱ ላይ «በመጠን ኑሩ ንቁም ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ፤በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት» (፩ጴጥ ፭፥፰-፱) በማለት አስጠንቅቋል፡፡ ዳግመኛም ዮሐንስ በራእዩ ላይ ቀድሞ ዘንዶው የተባለ ዲያብሎስ በተንኰሉ በእባብ በተመሰለ በሄሮድስ አድሮ እመቤታችንን ከልጇ ጋር ወደ ግብጽ በረሓ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር እንድትሰደድ እንዳደረገ ኹሉ፤ ዛሬም እንደ ደሊላ ኅሊናቸው በዓለማዊ ጥቅም በመታሰሩና ከእምነት ልቡናቸው በመቀዝቀዙ ምክንያት በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ በተመሰሉት በመናፍቃን ልቡና በማደር፤ የልጇ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የእሷን ወላዲተ አምላክነት የሚያምኑ እውነተኞች ምእመናንን እንደሚዋጋ ሲገልጽ፤

167. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፰፥፰





«ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘሩዋ የቀሩትን ሊዋጋ ቆመ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ» በማለት ገልጾታል (ራእ ፲፪፥፲፯)፡፡

ይኽቺም ደሊላ ሶምሶንን እወድሻለኁ እንዴት ትለኛለኽ? ልብኽ ከእኔ ጋር አይደለም፤ እያለች ነፍሱ እስከሞት ድረስ የተጨነቀች እስክትኾን ድረስ ዕለት ዕለት በቃልዋ ስትነዘንዘው፤ ኅሊናው ተዳክሞ ከተወለድኁ ገምሮ ኀይሌ በጠጉሬ ነው፤ ተላጭቸው አላውቅም፤ እስመ ናዝራዊ ሐዲሱ ለእግዚአብሔር የተባልኩ እኔ ነኝ አላት፤ እሷም ለፍልስጤማውያን መኳንንት የልቡን ገልጦልኛልና ኑ ብላ በስውር ልካባቸው፤ እነሱም ወርቅና ብር ለእሷ ይዘው መጥተዋል፤ እሷም እሱን በጉልበትዋ ላይ አስተኝታ ኀይል የኾነችውን ፀጉሩን በመቀስ እየተቆረጠ እንዲወድቅ ዐደረገች፤ በዚኽ ምክንያት እግዚአብሔር ተለየው፤ከዚኽ በኋላ ፍልስጤማውያንም ኹለት ዐይኖቹን አውጥተው እነሱ ወዳሉበት ወደ ጋዛ አምጥተው በናስ ሰንሰለት አስረው እኽል ያስፈጩት ገመረ (መሳ ፲፮፥፲፭-፳፩)፡፡

ዛሬም ከላይ እንደጠቀስኩት ልክ እንደ ደሊላ የአጋንንትን መልዕክት በመስማት ራሳቸውን ለኀላፊ ወርቅና ብር አሳልፈው በመስጠት፤ እነሱን ያዳመጡ እውነተኛ ሰዎችን በአማላጅነቷ ኀይል ጽንዕ ከኾነቻቸው ከድንግል ማርያም እየለዩ ረድኤተ እግዚአብሔር እንዲለያቸው በማድረግ፤ ኅሊናቸውን አሳውረው፤ በክሕደት የናስ ሰንሰለት አስረው የነሱን ሥራ እንዲሠሩ የሚያደርጉ የሐሰት መልእክተኞች በዙሪያችን መልተዋል፤ ጌታችንም ከነዚኽ እንድንጠነቀቅ «ተዓቀቡኬ እምሐሳውያን ነቢያት እለ ይመጽኡ ኀቤክሙ በአልባሰ አባግዕ» (የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችኁ በውስጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከኾኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ፤ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችኁ) በማለት አስተምሯል (ማቴ ፯፥፲፭-፲፯) ፡፡

ከራሱ ይልቅ ዕለት ዕለት የምእመናን ሕይወት የሚያሳስበው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንደ ደሊላ በሚያቆላምጥ ንግግር ሰውን ከሃይማኖት ከሚለዩ ከመናፍቃን ትምህርት እንድንጠበቅ ሲያስተምር «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችኹትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ



www.ethiopianorthodox.org

አለምናችኋለሁ፤ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤ እንዲኽ ያሉት ለገዛ ኾዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፤ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኰል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ፤ መታዘዛችኹ ለኹሉ ተወርቶአልና፤ እንግዲኽ በእናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋኾች እንድትኾኑ እወዳለኊ፤ የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችኹ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል›› በማለት ከእነዚኽ የሐሰት መልእክተኞች ተለይተው ራሳቸውን በተቀደሰች እምነት የጠበቁ ኹሉ ሰይጣን ከእግራቸው በታች ተቀጥቅጦ የሚወድቅ መኾኑን አስተምሯል (ሮሜ ፲፮፥፲፯-፳)፡፡

ይኽ በብሥራተ መልአክ የተወለደ ሶምሶን በደሊላ ምክንያት ፀጉሩ ተላጭቶ ኀይሉን ቢያጣም ተመልሳ ፀጉሩ እያደገች ኀይሉ እየተመለሰለት መጣ፤ ፍልስጤውያንም ሊዘብቱበት ከግዞት ቤት አስጠርተው በምሰሶና በምሰሶ መኻከል አቆሙት፤ እሱም እጁን የያዘውን ብላቴና ቤቱን የደገፉትን ምሰሶች እጠጋባቸው ዘንድ እባክኽ አስይዘኝ አለው፤ አስያዘው እሱም ‹‹ኦ እግዚኦ አሐተ ስዕለተ እስእለከ ህየንተ ክልኤሆን አዕይንትየ ትባእ ነፍስየ ምስለ ኢሎፍላውያን›› ስለ ኹለቱ ዐይኖቼ ፍልስጤማውያንን አኹን እንድበቀል እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እባክኽ አስበኝ፤ አምላክ ሆይ ይኽነን አንድ ጊዜ ብቻ እባክኽ አበርታኝ፤ ብሎ ስመ እግዚአብሔርን ጠርቶ ምሰሶውን ቢመታው መኳንንቱም ሕዝቡም ኹሉም አልቀዋል፡፡

ብዙ ሊቃውንትም በሶምሶን ዘርያ ብዙ ትንታኔን ሰተዋል፤ ለምሳሌ ያኽል ሊቁ ያዕቆብ ዘስሩግ ‹‹On Samson›› በሚል ርእስ አንድ ትልቅ የሃይማኖት መጽሐፍ ጽፏል፤ በዚኽም መጽሐፉ ደሊላንና ሔዋንን ሶምሶንና አዳምን እያነጻጸረ ያስተማረው ትምህርት የነገረ መለኮት ምሁራንን እጅግ ያስደነቀ ሲኾን፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ምልጃዋ ፈጥኖ በመድረሱ ለኹሉ ኀይል ብርታት የሚኾን፤ ጠላቶቻችንን አጋንንትን ድል የሚነሣ የእመቤታችንን ቃል ኪዳን ጠላቶቹ ፍልስጤማውያን ድል እንዲነሣ ኀይል ጽንዕ በኾነችው በፀጉሩ ኀይል መስለው ‹‹ወኀይል ሀድርት ለሶምሶን በቆናዝወ ርእሱ›› (በሶምሶን በራሱ ሹርባ ያደርሽ ኀይል አንቺ ነሽ)[168] በማለት ያስተማረውን ትምህርት ስንመረምር

168 አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 23





ሊቁ ምን ያኽል የጠለቀ የነገረ ማርያም ዕውቀት እንደነበረው ያስረዳናል፡፡

የትርጓሜ መምህራንም ሶምሶንን በዘመነ ሐዲስ ከተደረገው ከጌታ ሥጋዌ ጋር ሲያነጻጽሩ፤ ሶምሶን በብሥራተ መልአክ እንደተወለደ ጌታም ከቅድስት ድንግል ማርያም በብሥራተ መልአክ ተፀንሷል፤አንድም ሶምሶን በተናቀች መንሰከ አድግ ብዙ ጠላት እንዳጠፋ ጌታም አይሁድ በናቋት በሞቱ ብዙ አጋንንትን አጥፍቷል፤ አንድም ሶምሶን በሕይወት ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው ጠላቶቹ በሞቱ ያጠፋቸው ጠላቶቹ እንዲበዙ ጌታም በሕይወተ ሥጋ ሳለ ካጠፋቸው አጋንንት በሞቱ ያጠፋቸው አጋንንት ይበዛሉ በማለት ይተነትናሉ፡፡

## የጌዴዎን ፀምር

የአምላክ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ጌዴዎን በአውድማው ላይ በዘረጋት ብዝት ግምጃ ትመሰላለች (መሳ ፮፥፴፮-፵)፡፡ ይኸውም የምድያም ሰዎች እስራኤልን በጠላትነት እጅጉን ባጠቋቸው ጊዜ፤ መልአከ እግዚአብሔር ለጌዴዎን ተገልጾ አንተ ጽኑዕ ኀይል ሰው እግዚአብሔር ካንተ ጋር ነው አለው፤ ጌታም ኺድ እስራኤልንም ከምድያም እጅ አድን እንሆ ልኬኻለኊ አለው፤ እሱም ለዚኽ ምልክት አሳየኝ፤ መሥዋዕት ልሠዋ ብሎ ኺዶ መሥዋዕት ሠውቶ ሥጋውን በሌማት መረቁን በምንቸት ውስጥ አድርጎ አቀረበ፤ ደንጊያውን ጸፍጽፎ እንጨቱን ረብርቦ በላዩ አደረገው፤ መልአኩም በዘንግ ቢነካው ተቃጥሏል፤ ይኸውም እሳት የመቅሠፍት እግዚአብሔር፤ ሥጋው የአሕዛብ፤ ዘንግ የጌዴዎን ጦር ምሳሌ ነበር፡፡

ኹለተኛም ጌዴዎን ፀምር ልዘርጋ ጠል ከብዝት ላይ ይውረድ ዳርና ዳሩ ደረቅ ይኹን አለው፤ ይኹንልኽ አለው፡፡ ይኸውም ለጊዜው ፀምር የእስራኤል፤ ጠል የረድኤተ እግዚአብሔር ምሳሌ ሲኾን፤ ጠል ወደ ፀምር መውረዱ እስራኤልን የመርዳቱ ፤በዳርና በዳር አለመውረዱ አሕዛብን ያለመርዳቱ ምሳሌ ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን ፀምር የእመቤታችን፤ ጠል የጌታ፤ ጠል ወደ ፀምር መውረዱ ጌታ በእመቤታችን የማደሩ ምሳሌ (መዝ ፸፪፥፩-፮፤ ፶፴፩፥፲፫-፲፬፤ ኢሳ ፮፥፲፬፤ ሉቃ ፩፥፳፮-፴፰)፤ በዳርና በዳር አለመውረዱ ጌታ በሌሎች ሴቶች ያለማደሩን ምስጢር ሲገልጽለት ነው፡፡

ጌዴዎንም ሦስተኛ ፀምር ልዘርጋ ፀምሩ ደረቅ ይኹን፤ ጠል በዳርና



www.ethiopianorthodox.org

በዳር ይውረድ አለው፤ ይኹንልኝ አለው ኾኖለታል፡፡ለጊዜው ፀምር የእስራኤል፤ ጠል የመቅሠፍተ እግዚአብሔር ምሳሌ ሲኾን ጠል ወደ ፀምር አለመውረዱ እስራኤልን ያለማጥፋቱ፤ በዳርና በዳር መውረዱ አሕዛብን የማጥፋቱ ምሳሌ ሲኾን፤ ፍጻሜው ግን ፀምር የእመቤታችን፤ ጠል የዘር የሩካቤ፤ ፀምሩ ደረቅ መኾኑ እመቤታችን ያለ ዘር ያለ ሩካቤ የመውለዷ ምሳሌ (ሉቃ ፩፥፴፬፤ ማቴ ፩፥፲፰-፳፫)፤ ዳርና ዳሩ የሌሎች ሴቶች፤ ጠሉ በዳርና በዳሩ መውረዱ ሌሎች ሴቶች በዘር በሩካቤ የመውለዳቸው ምሳሌ ነውና እመቤታችን *የጌዴዎን ፀምር ተብላ ትጠራለች፡፡*

ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው ላይ ‹‹ፀምር ዘጌዴዎን›› (የጌዴዎን ፀምር አንቺ ነሽ)[169] በማለት ጠቅልሎ ያመሰገናትን፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በአርጋኖን መጽሐፉ በጥልቀት ሲያብራራው *‹‹ፀምረ ጌዴዎን ትትሜሰል በድንግል እስመ ተረክበት ጥልልተ በነፍኒፈ ዝናም ዘላዕሉ እንዘ ኵላ ምድር በምልአ ይብስት፣ በከመ ድንግል ተወክፈት ጠለ በረከት ዘወረደ እምሕፅነ አብ ሰማያዊ እንዘ ኵሎን አንስት ኢልኩፋት እማንቱ እም ውእቱ ጠል እስመ ኢኮና ድልዋተ ለጸዊሮቱ ወካዕበ ፀምር ተረክበት ይብስታ እንዘ ኵላ ምድር ጥልልት እምነጠብጣበ ዝናም፡፡ በከመ ለድንግል ኢለከፋ ነጠብጣበ ዘርዕ፡፡ እንዘ ኵሎን አንስት ይፀንሳ እምነጠብጣበ ዘርዕ ዘልማድ ወድንግልሰ ኢኀብረት ሥርዐተ ምስሌሆን ብዑደ ኮነ ፀኒሶታ ወብዑደ ኮነ ወሊዶታ››* (የጌዴዎን ብዝት ግምጃ በድንግል ትመሰላለች፤ ምድር በመላዋ ደረቅ ስትኾን በላይኛው ዝናም ካፊያነት ለምልማ ተገኝታለችና፤ ከሰማያዊ አባቱ ዕቅፍ የወረደ የበረከት ጠልን ድንግል እንደተቀበለች፤ ኹላቸው ሴቶች ከዚያ ጠል ሳይነካቸው ለመሸከም ዝግጁ አልነበሩምና፤ ዳግመኛም ብዝቷ ግምጃ ደረቅ ኾና ተገኘች ምድር በመላዋ ከዝናም ካፊያ የተነሣ የለመለመች ስትኾን፤ ኹላቸው ሴቶች ከተፈጥሮአዊ ልማድ ዘር ነጠብጣብ የተነሣ ሲፀንሱ ድንግልን የዘር ነጠብጣብ እንዳልነካት፤ ድንግል ግን በዚኽ ሥርዐተ ተፈጥሮ ከነርሱ ጋራ ስለአልተባበረችም የመፅነሷ ምስጢር ልዩ ነው፤ የመውለዷ ምስጢር ልዩ ነው)[170] በማለት አማናዊት ፀምርነቷን አምልቶ አብዝቶ አጕልቶ አስፍቶ ተርጕሟል፡፡

169. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤ ቍ ፴፬
170. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ፤ ምዕ ፬፥፲፱-፲፭





# ምዕራፍ ሦስት
# ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ሳሙኤል

## ታቦተ ጽዮን

ፈጣሪያችን ክርስቶስን የወለደችልን ቅድስት ድንግል ማርያም በልዑል እግዚአብሔር ትእዛዝ ጥበብና ማስተዋልን በተቀበለ በባስልኤል እጅ በተሠራችው በቃል ኪዳን ታቦት ትመሰላለች (ዘጸ ፳፭፥፱-፳፤ ፴፯፥፩-፲፭)፡፡ ይኸቺ የቃል ኪዳን ታቦት በደብተራ ኦሪት በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ተቀምጣ የኖረች፤ የዮርዳኖስን ባሕር የከፈለች (ኢያ ፫፥፲፬-፲፯)፤ ቅጽረ ኢያሪኮን ያፈረሰች (ኢያ ፮፥፩-፳፩)፤ ዳጎን የተባለ የፍልስጤማውያንን ጣዖት ቆራርጣ ያጠፋች (፩ሳሙ ፭፥፩-፭፤ ፪ቆሮ ፮፥፲፮)፤ በድፍረት ሊነካት የሞከረ ኦዛን የቀሠፈች (፪ሳሙ ፮፥፮-፯)፤ በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ተቀምጣ ቤቱን በበረከት የመላች (፪ሳሙ ፮፥፲፩)፤ ከብዙ ዘመን በኋላ በታላቅ ክብር ወደ ሀገሯ ስትመለስ ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በታላቅ መንፈሳዊ ደስታ በፊቷ የዘመረላት (፪ሳሙ ፮፥፲፬-፳፫፤ ፩ዜና ፲፭፥፳፭-፳፰)፤ ልጁ ንጉሥ ሰሎሞንም ልዩና ውብ የኾነ በወርቅ የተጌጠ ቤተ መቅደስ ሠርቶ በክብር ያኖራት (፩ነገ ፰፥፩-፲፩)፤ የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የኾነቺው ይቺ የእግዚአብሔር ታቦት፤ በንጽሕና በቅድስና የተጌጠችው የእግዚአብሔር ወልድ እናት የኾነቺው የአማናዊት ታቦት የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፡፡

በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ ምዕራፍ ፬ቁጥር ፲፱ትን



www.ethiopianorthodox.org

እንደምናነበው፤ ታቦተ ጽዮንን ያገለግሉ የነበሩት የካህኑ የኤሊ ልጆች አፍኒንና ፊንሐስ በሠሩት ታላቅ ኀጢአት ምክንያት እግዚአብሔር አዘኖባቸው የክብሩ መገለጫ የኾነችው ታቦት በፍልስጤማውያን እጅ እንድትማረክ አደረገ፤ ፍልስጤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ከአቤንኤዘር ወደ አዛጦን በመውሰድ በድፍረት ከዳጎን አጠገብ አኖሯት፡፡ ነገር ግን ዳጎን በእግዚአብሔር ታቦት ፊት ወድቆ ተገኘ፤ እነሱም እንደገና ዳጎንን ወደ ስፍራው መልሰው ኼዱ፤ በነጋታው ለማየት ሲመጡ የዳጎን እጅ እግሩ ተቆራርጠው ደረቱ ለብቻው ወድቆ ተገኘ፤ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይኽንን ታሪክ ይዞ «የእግዚአብሔር ታቦትንስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው?» (፪ቆሮ ፮፥፲፮) በማለት የታቦትን ክብር አስተምሮበታል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅም በሰቈቃወ ድንግል መጽሐፋ ላይ የአምላክ ማደሪያ የኾነችው ታቦት ወደ ፍልስጤም ሀገር ኼዳ ዳጎንን ሰባብራ እንዳጠፋች ኹሉ፤ አማናዊት የጌታ ታቦት ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታን ይዛ ወደ ግብጽ በተሰደደች ጊዜ የግብጽ ጣዖታት ኹሉ እየተሰባበሩ መውደቃቸውን እንዲኽ በማለት ገልጿል፤

*«ታቦተ አምላከ እስራኤል ጽዮን ዘነገደት ምድረ ኢሎፍሊ*
*ወቀጥቀጠቶ ለዳጎን ነፍሳተ ብዙኃን ማህጎሊ*
*አመ ነገደት ቍስቋመ በኀይለ ወልዳ ከሃሊ*
*ወድቁ አማልክተ ግብጽ መናብርተ ሰይጣን ሐባሊ*
*ወተነፍሩ ኵሎሙ ዘበሙ አስጋሊ»*

(ወደ ኢሎፍሊ ምድር ተማርካ የኼደች የእስራኤል አምላክ የቃል ኪዳኑ ታቦት ታቦተ ጽዮን፤ የብዙዎችን ነፍሳት ያጠፋ ዳጎንን ሰባበረችው፤ በዚኽ ታቦት የተመሰለች ድንግል ማርያምም ኹሉን ማድረግ ከሚችል ከልጇ ጋር ግብጽ ወደሚባል አገር በኼደች ጊዜ፤የሐሰተኛ ሰይጣን ዘፋኖች የኾኑ የግብጽ ጣዖታት ፈረሱ፤ጠንቋይ አስጠንቋይ ያላቸው ኹሉ ዐፈሩ)[171]በማለት አነጻጽሯል፡፡

በእግዚአብሔር ታቦት ላይ ስለሠሩት ታላቅ የድፍረት ኀጢአት እግዚአብሔር ቀጣቸው ብዙዎቹ ሞቱ፤ ያልሞቱትም በእባጭ ተመቱ፤ የአይጥ መንጋም ምድራቸውን አጠፋባቸው፤ ያን ጊዜ በእግዚአብሔር ታቦት ላይ ምን

171. ሰቈቃወ ድንግል ቍ ፴፱





እናድርግ? ወደ ስፍራው በምን እንስደደው? ብለው በመማከር፤ የሚያጠቡ ቀንበር ያልተጫነባቸው ኹለት ላሞችን በመውሰድ፤ በዐዲስ ሠረገላ ጠምደው እንቦሶቻቸውን (ጥጆቻቸውን) ከቤት ዘግተው በማስቀረት፤ ታቦተ ጽዮንን እጅ መንሻውን በሠረገላው ላይ ጫኑ፤ ያን ጊዜ እነዚኽ ላሞች ጥጆቻቸውን ሳይናፍቁ ወደቀኝ ወደግራ ሳይሉ እምቧ እያሉ ወደ ቤተ ሳሚስ ወደሚወስደው መንገድ ታቦተ ጽዮንን ይዘው ገሠገሡ፤ ሠረገላውም ወደ ቤትሳሚሳዊው ወደ ኢያሱ እርሻ ሲደርስ ያን ጊዜ ሌዋውያን ታቦት ጽዮንና ዐብሮ የነበረውን የወርቅ ዕቃ አውርደው በታላቅ ደንጊያ ላይ በማኖር፤ ሠረገላውን ፈልጠው ጊደሮቹን ሠውተዋቸዋል፡፡ ይኽም ለጊዜው ቢደረግም ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር፤ ላሞቹ የሰማዕታት፤ ልጆች የልጆቻቸው፤ ሠረገላ የመስቀል፤ ልጆቻቸውን ከወደኋላ እንዳስቀሩ፤ ሰማዕታትም የልጅ የገንዘብ ፍቅር አያስቀራቸውምና፣ ሠረገላውን ፈልጠው እንደሠዋቸው ራሳቸውን በመስቀል ይሠዋሉና በማለት የብሉይ ኪዳን መተርጕማን ያመሰጥሩታል፡፡

የመልክአ ማርያም ደራሲ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ የኾነችውን የኻያ መንፈቅ ማለት ዐሥሩ ቃላት የተጻፉባቸው ጽላት የተቀመጡባትን የእግዚአብሔርን ታቦት ጊደሮቹ ከልጆቻቸው ይልቅ በማስበለጥና በመውደድ ይዘዋት ወደፊት እንደነጎዱ፤ እሱም የልዑል ማደሪያ ለኾነችው ለቅድስት ድንግል ማርያም ያለውን ጥልቅ ፍቅር በድርሰቱ ላይ

*«ማርያም ጽዮን ታቦተ ቃለ ጽድቅ መንፈቀ ዕሥራ*
*ዕጐልተ እምዕጐሊሆን ከመ ኪያኪ አፍቀራ*
*አፍቀርኩኪ አፍቅርኒ እምይእዜ ለግሙራ»*

(የኻያ እኩሌታ የሚኾን የእውነት ቃል ማደሪያ ጽዮን ማርያም ሆይ፤ ጊደሮች ከጥጆቻቸው ይልቅ አንቺን እንደአፈቀሩ፤ ወድጄሻለኹና ከዛሬ ገምሮ ፈጽሞ ውደጅኝ)[172] በማለት ገልጦታል፡፡

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በምስጢር በመራቀቅ «አንቲ ውእቱ ጽዮን ታቦተ አምላከ እስራኤል እንተ ነገደት ምድረ ኢሎፍሊ፤ ወበህየ አውደቀቶ ለዳጎን፤ ወቀሠፈቶሙ ለመጠዓውያን፤ ወበሀአታ ተወፈየት ሞጻ እምሰብአ አዛጦን፤ ወፈነውዋ ምስለ ሞጻሃ ዲበ ዕጎልተ አልሕምት አስተጻዒኖሙ፤ ምስሌሃ

172. መልክአ ማርያም፤ ለመከየድኪ



www.ethiopianorthodox.org

*አፍቃደ ኤርጋብ ወኢሠርዐ ሥርዓተ ቤርሴክታን በገቦሃ ወባሕቱ ፈነውዋ ዘምስለ ቴሜርጋብ ወንዋየ ወርቅ በኀቤሃ ወበእትወታ ባረከ እግዚአብሔር ቤተ አቢዳራ አመ ኀግደታ ሶበ አኀደራ››* (ወደ ኢሎፍሊ ምድር የኼደች የእስራኤል አምላክ ታቦት (ማደሪያ) ጽዮን አንቺ ነሽ፤ በዚያም ዳጎንኻ የጣለችው ጣዖት አምላኪዎቹንም የቀሠፈቻቸው፤በአመጣጧም ከአዛጦን ሰዎች ካሳን የተቀበለች፤ ከካሳዋም ጋር እንቦሳ ባላቸው ላሞች አስጭነው የሸኟት፤ ከርሷም ጋር የወርቅ ሳጥኖችን በጐኗም፤ የበድን ሣጥን ሥርዐትን አልሠሩም፤ ነገር ግን በርሷ ዘንድ ካለ ከወርቅ መሣሪያና ከሣጥን ጋራ ላኳት፤ በእንግድነቷ ወቅትም በአሳደራት ጊዜ ወደ ቤቱ በመግባቷ እግዚአብሔር የአቢዳራን ቤት ባረከ)[173] በማለት የምሳሌዋን እሙንነት በሰፊው ገልጧል።

ይኸቺም የእግዚአብሔር ታቦት በቤተ ዐሚናዳብ ኻያ ዓመት ተቀምጣለች፤ ከዚያም የሳኦል ዘመን ዐልፎ የእግዚአብሔር ወዳጅ ዳዊት በነገሠ ጊዜ በዐዲስ ሠረገላ አድርገው ከቤተ ዐሚናዳብ አውጥተው በበገና፣ በመሰንቆ፣ በከበሮ፣ በነጋሪት፣ በጸናጽል እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይዘዋት ሲመጡ፤ የእግዚአብሔርን ታቦት ኦዛ በድፍረት በመያዙ እግዚአብሔር ቀሥፎት ወዲያውኑ በታቦቷ አጠገብ ሕይወቱ አልፏል፤ ያን ጊዜ ነቢዩ ዳዊት የእግዚአብሔር ታቦት ያደረገችውን ተአምራት ተመልክቶ፤ እግዚአብሔር በእርሷ እንዳደረ በማመን በፍርሃት ተውጦ ‹‹የእግዚአብሔር ታቦት ወደ እኔ እንዴት ይመጣል?›› በማለት ለታቦቷ ያለውን ታላቅ ክብር ገልጧል (፪ ሳሙ ፮፥፱-፲)፤ በዘመነ ሐዲስም በተመሳሳይ መልኩ ጌታን በማሕፀኗ የተሸከመች የልዑል እግዚአብሔር ማደሪያ አማናዊት ታቦት ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በኼደች ጊዜ፤ ኤልሳቤጥ ልክ እንደ ዳዊት መንፈስ ቅዱስ መልቶባት፤ የጌታ ታቦት (ማደሪያው) መኾኗን ተረድታ፤ ድም፧ን አሰምታ ‹‹የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጪ ዘንድ እንዴት ይኾንልኛል?›› በማለት ለቅድስት ድንግል ማርያም ያላትን ታላቅ አክብሮት እንደ ዳዊት ገልጣለች(ሉቃ ፩፥፵፫-፵፬) ።

ከዚያም ዳዊት ይኽነን ታላቅ ቃል ከተናገረ በኋላ የእግዚአብሔር ታቦት በአቢዳራ ቤት ለሦስት ወር ያኽል እንደተቀመጠች (፪ ሳሙ ፮፥፲፩)፤ በተመሳሳይ መልኩ የአምላክ ማደሪያ ቅድስት ድንግል ማርያምም በካህኑ በዘካርያስ ቤት ለሦስት ወር ተቀምጣለች (ሉቃ ፩፥፶፮)። ኦዛ ተቀሥፎ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር ታቦት ወደ አቢዳራ ቤት ገብታ ቤቱ ለሦስት ወር በበረከት እንደተመላ ኹሉ፤ በተመሳሳይ መልኩ ዘካርያስም የመልአኩን ቃል ባለመቀበሉ ከተረገመ በኋላ (ሉቃ ፩፥፳)፤ እውነተኛዪቱ የአምላክ ታቦት ድንግል ማርያም ቤቱ ለሦስት ወር ተቀምጣለች። እግዚአብሔር በታቦቷ ምክንያት የአቢዳራን ቤት እንደባረከ ኹሉ የዘካርያስንም ቤት በእመቤታችን ምክንያት የባረከው መኾኑን ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ በመጽሐፉ ሲገልጽ *‹‹ድንግል በምስጢር የተመላ ታቦትን ኾና ትኖራለች፤ የካህናት ወገኖችም ደስ ይላቸዋል፤ ያከብሯታልም››*[174] በማለት ታቦትነቷን አጉልቶ አስተምሯል።

በተጨማሪም የእግዚአብሔር ታቦት ከቤተ አቢዳራ ወደ ዳዊት ከተማ ስትገባ፤ ነቢዩ እግዚአብሔር ዳዊት ከደስታው ብዛት የተነሣ የጌታ የክብሩ መገለጫ በኾነችው በታቦቷ ፊት እየዘለለ እንዳመሰገነ ኹሉ (፪ሳሙ ፮፥፲፪-፲፭)፤ አካላዊ ቃልን በማሕፀኗ የተሸከመች የአምላክ ታቦት ቅድስት ድንግል ማርያምም ወደ ተራራማው ሀገር ወደ ይሁዳ ከተማ ወደ ኤልሳቤጥ ቤት በኼደች ጊዜ፤ ታላቁ ነቢይ መጥምቁ ዮሐንስ በእናቱ ማሕፀን ኾኖ ከደስታው ብዛት የተነሣ እየዘለለ አመስግኗል (ሉቃ ፩፥፵፩-፵፭)።

ይኽነን ምስጢር ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ሲያብራራ ‹‹She, the palace of flesh, walked and ascended, and the king was in it…›› (የሥጋ ቤተ መንግሥት የኾነች እርሷ (ማርያም) ኼደች፤ ወረደች ንጉሡም በውስጧ ነበረ፤ በደስታ በእናቱ ኾድ ውስጥ ኾኖ ወደ ዘለለው ልጅ ደጃፍ ስትደርስ ቆመች፤ ኀያሉ አንኳኳ፤ ሠራተኛው በአባቱ ቤት ውስጥ ኹኖ ተንቀጠቀጠ፤ ንጉሡ ተናገረ፤ አገልጋዩ ስገደለት አከበረው አመለከውም፤ ፈጣሪ ሲያየው የመካኗ ልጅ በደስታ ዘለለ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ኀይል ሲገለጥ ዕንሱ ዘለለ፤ ሕፃናትን የሚፈጥረውን አምላክ ድምፅ በሰማ ጊዜ ዕንሱ ተነቃቃ፤ የኹሉን ቻይ ጌታ ፈቃድ ማሕፀኗን መልቷልና፤ ያ ዝም ያለው (ጌታ) ተመለከተ፤ ዝም ያለው (ዮሐንስ) አደነቀ፤ በሥጋ ውስጥ የተሰወረው አሏልና፤ ያ ያልተወለደው ድፍረቱን አሳየ፤ የድንግል ልጅ ሲፈቅድ የመካኒቱ ልጅ

173. አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፲፮

174 Jacob of Serugh, On the Announciation, ET by M. Hunsubury p 53





www.ethiopianorthodox.org

ተደመመ፤ የተሰወረው ሲጣራ፤ ዝም ባለው ልጅ ላይም መደነቅ መላበት፤ የአንበሳ ደቦል በእናቱ ውስጥ አ..ገ፤ ያዕቆብ እንደጻፈው፤ ጥጃው የሸመገለው ሰውዬ ልጅ ድምፁን ሲሰማ ተንቀ..ቀጠ፤ ትንሿ ሴት (እመቤታችን) በአሮጊቷ ጕሮሮ (በኤልሳቤጥ) ደስ የሚያሰኝ ቃልን አሰማች፤ ድምፗ በጕሮሮዋ ሲሰማ አንዳች የሚያነሣሣ መንፈስ ዐደረባት፤ ፅንሱም በደስታና በአክብሮት ሊያመሰግን ተነሣሣ፤ በደስታ በታቦት ፊት በደስታ በዘለለው በዳዊት ልጅ ፊት ሳያቋርጥ የእናቱን ማሕፀን ገፋ፤ ሊወጣና ሊያመልክም ፈለገ፤ ሊጐበኘው የመጣው ጌታ በበር እንዳይቆም... አንዱ ሌላኛውን አስቀድሞ ያሳየ ነበርና:: የነቢያትን እና የነገሥታትን በእግዚአብሔር ፊት በደስታ መዘመር እስራኤላውያን ቀድሞውኑ የተለማመዱት ነገር ነበር፤ ንጉሡ ዳዊት በቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት ይዘል ነበር፤ ከልቡ ደስታ የተነሣ ለንጉሣውያኑ ደንብ አልታዘዘም፤ እንዲኹ ዮሐንስ ደግሞ ገና ፅንስ ሣለ ከደስታው የተነሣ ከዳዊትም በላቀ ኹኔታ ዘለለ፤ ፅንስ ቢኾንም የእርሱ ባልኾነው በዚኽ ዕድሜ አልተገታም፤ ድንግል እና ቡርክት የኾነችው እናት የእግዚአብሔር ቤት ምስጢራት ከመሉባት ታቦትም በላይ ውብ ነበረች፤ ዳዊትም በአክብሮት በታቦቱ ፊት ዘለለ፤ ይህም ዮሐንስ በማርያም ፊት ሊዘል እንዳለ አስቀድሞ ያሳይ ነበርና፤ ከዳዊት በቀር ንጉሥ መዝለሉ ተሰምቶ አይታወቅም፤ሕፃን መዝለሉም እንዲሁ፤ ነቢያት ካህናት የእግዚአብሔርን ልጅ መንገድ አስቀድመው አመለከቱ፤ እርሱም በመጣ ጊዜ ይሹት የነበሩትን ምልክቶች ፈጸማቸው፤ የጌታውን የንጉሡን ምልክት ይጠቁም ዘንድ፤ ዳዊት በደስታ በታቦቱ ፊት ዘለለ፤ዮሐንስ በማርያም ፊት የሚያደርገውን ነገር ምሳሌ በመኾን አሳየ፤ ያቺም ብላቴና እንዲኹ የእግዚአብሔር ታቦት ነበረችና፤ የምስጢራት ጌታ በእርሷ ዐደረ፤ ከዚኽም የተነሣ ልክ እንደዚያ ጀግና ንጉሥ ሕፃኑ በእርሷ ፊት በደስታ ዘለለ፤እርሷ በቅዱስ ቃል እንደተመላ ታቦት የተሸከሚት ነገረች፤ የትንቢት ምስጢራት ፍቺ በእርሷ ዐደረ፤ ሞገሷ ከታቦቱ የበለጠ ይኾን ዘንድ፤ በድንቅ ኹኔታ አሸብርቃ ነበርና ሕፃኑ ዘለለ፤ በተዘጋ ማሕፀን ውስጥ ሳለ ሕፃኑ የተሰማው ደስታ ያልተገደበ ነበር፤ እስከዚያን ዕለት በሐዘን በነበረ ማሕፀን ውስጥ ኹኖ በደስታ ፈነጠዘ) [175] በማለት ይኽ የነገረ መለኮት ምሁር ቅድስት

175. Jacob of Serugh, On The Nativity p.63, ibid 53





ድንግል ማርያምን በምስጢር የተመላች የአምላክ ታቦት መኾኗን በማብራራት ገልጦታል::

ዳግመኛም ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በእግዚአብሔር ታቦት ፊት በደስታ ሲያመሰግን አይታ የሳኦል ልጅ ሜልኮል ብትንቀው እግዚአብሔር ተቈጥቷት በሕይወቷ ዘመን ኹሉ የልጅ ጸጋ እንዳታገኝ በምክነት ቀጥቷታል (፪ሳሙ. ፮፥፳-፳፫):: ይኸውም ማደሪያው የኾነች ታቦቷን በድፍረት ሊነካት የሞከረውን አዛን የቀሠፈ፤ ዳግመኛ የጌትነቱ መገለጫ በኾነች በታቦቷ ፊት ያመሰገነ ዳዊትን የናቀች ሜልኮልን በምክነት የቀጣ አምላክ፤ ዛሬም ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመችውን፤ የድንግልና ጡቶቿን የመገበችውን፤ በጀርባዋ ያዘለችውና በደረቷ የታቀፈችውን ቅድስት እናቱን በድፍረት የሚነቅፉ፤ ሔዋንን ያሳተ እባብ መርዝ ክሕደቱን በአፋቸው የረጨባቸው በሩ.ቡናቸው ያሳደረባቸው፤ ነቢያት ሐዋርያት ያስተማሩትን የሚያጣምሙ ፀረ ማርያሞች ለዚኽ ድፍረታቸው ንስሓ ካልገቡ የዘላለም ቅጣትና፤ በዚኽ ዓለምም ከድንግል ማርያም አማላጅነት የሚገኘውን ታላቅ በረከት በማጣት እንደ ሜልኮል የበረከትና የጸጋ ምክነት ያጋጥማቸዋል::

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ጽዮንን የሚጠሉ ኹሉ ስለሚደርስባቸው ዘላለማዊ ምክነት በመዝ ፻፳፱፥፮-፰ ላይ ‹‹ጽዮንን የሚጠሉ ኹሉ ይፈሩ፤ ወደ ኋላቸውም ይመለሱ፤ በሰገነት ላይ እንደበቀለ ሣር ሳይነቀል እንደሚደርቅ ለሚያጭደው እጁን፤ ነዶዎቹን ለሚሰበስብ ዕቅፉን እንደማይመላ ይኹኑ፤ በመንገድም የሚያልፉ የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ ይኹን በእግዚአብሔር ስም እንመርቃችኋለን አይሉም›› በማለት እንደተናገረ ጽዮን የተባለች የድንግል ማርያም አማላጅነት የሚቀዋወሙ የዲያብሎስ የግብር ..ጆች መናፍቃን እንደ ሜልኮል ከእግዚአብሔር ጸጋ የራቁ ናቸው፤ ጥንቱን ..ያብሎስ በሄሮድስ ዐድሮ የአምላክ ታቦት የኾነችውን ቅድስት እናታችንን እንዳሳደደ፤ ዛሬም እንደ ሜልኮል ልባቸው በትዕቢት በተመላ በልበ መናፍቃን ዐድሮ የኢየሱስ ክርስቶስን የባሕርይ አምላክነት የአማናዊት ታቦት የእናቱ የድንግል ማርያምን አማላጅነት በማመን ጸንተው ያሉ ምእመናንን እንደሚቀዋወም ዮሐንስ በራእዩ በምዕ ፲፪፥፲፫-፲፯ ላይ ‹‹ዘንዶውም ወደ ምድር እንደተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት ልጅ አሳደዳት፤ ከእባቡም ፊት



www.ethiopianorthodox.org

ርቃ አንድ ዘመን፣ ዘመናትም፣ የዘመንም እኩሌታ ወደምትመገብበት ወደ ስፍራዋ ወደ በረሓ እንድትበር ለሴቲቱ ኹለት የታላላቅ የንሥር ክንፎች ተሰጣት፣ እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያኽልን ውሃ ከአፉ በስተኋላዋ አፈሰሰ፤ ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፤ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው፤ ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቆጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ኼደ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ›› በማለት ዲያብሎስ በባሕር አሸዋ በተመሰሉ መናፍቃን ልብ ዐድሮ ዘወትር የፈጣሪያችን የክርስቶስን የባሕርይ አምላክነትን፤ የአማናዊት ታቦት የድንግል ማርያምን የአምላክ እናትነት የሚያምኑ ምእመናን ሲቀዋወም እንደሚኖር በራእዩ አስተምሯል።

ከሊቃውንትም አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም በማሕሌተ ጽጌ መጽሐፋቸው ላይ

*‹‹እስከ መኑንቶ ሜልኮል ቅድመ ታቦት ሕግ ከመ ዘፈነ*
*ንጉሠ እስራኤል ኪያኪ ዘጸገየ ሶሥነ*
*ቅድመ ገጸ ሥዕልኪ ድንግል እዘፍን አነ*
*ዘይሜንን ተአምረኪ ወስብሐተኪ ቍርባነ*
*በአፈ መላእክት ወሰብእ ለይኩን ምኑነ››*

(አንቺን ያስገኘ የእስራኤል ንጉሥ ዳዊት ሜልኮል እስከናቀችው ድረስ በእግዚአብሔር የሕግ ታቦት ፊት እንዳመሰገነ፤ ድንግል ሆይ እኔም በሥዕልሽ ፊት እዘምራለኊ፤ ድንቅ ታምርሽንና የቀረበ መንፈሳዊ ምስጋናሽን የሚንቅ በመላእክትና በሰው አንደበት የተረገመ ይኹን)[176] በማለት ሲያስተምሩ በተጨማሪም ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ በምስጢር በመራቀቅ ቅድስት ድንግል ማርያምን *በምስጢር የተመላች ታቦት፣ የቃል ኪዳን ታቦት፣ እሳትን የተመላች ታቦት፣ የቅዱስ ቃል ታቦት* በማለት እያብራራ ያስተማረው የነገረ መለኮት ትምህርት እጅግ ጥልቅ ነው።

ይኸ ሊቅ ድንግልን *በምስጢር የተመላች ታቦት* ሊል የቻለበት ምክንያት በታቦቷ በምሳሌነት ቀድሞ የተገለጠው ምስጢር በእውነት

176. አባ ጽጌ ድንግል ፤ ማሕሌተ ጽጌ ቍ ፴፫





የታወቀባት ስለኾነ ነው፤ ዳግመኛም በምስጢር የተመላች ማለቱ እናትነትን ከድንግልና፤ ድንግልናን ከእናትነት አስተባብራ የተገኘች፤ ዘርዐ ወራዙት ያልወደቀባት፤ እደ ብእሲ ያልዳሰሳት፤ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ሰማይና ምድር የማይወስኑትን ጌታ በተፈትሖ በማይመረመር ማሕፀኗ የቻለች ልዩ ምስጢርን የተረዳችና በምስጢር የተከበበች የምስጢር ታቦት በመኾኗም ጭምር ነው፤ ሊቁ ያዕቆብ ይኽነን ሲገልጥ ‹‹The virgin abides like an ark full of mysteries…›› (ድንግል በምስጢር የተመላ ታቦትን ኾና ትኖራለች፤ የነህናት ወገኖችም ደስ ይላቸዋል ያከብሯታልም)[177] በማለት ምስጢራዊ ታቦትነቷን አጕልቶ አስተምሯል።

ዳግመኛም ይኸው ሊቅ እሳተ መለኮት ጌታን ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች በመኾኗ *እሳትን የተመላች ታቦት* በማለት ገልጿታል፤ ይኸውም ኪሩቤልና ሱራፌል እሱን ከመፍራት የተነሣ፤ በኹለት ክንፋቸው ፊታቸውን ሸፍነው በኹለት ክንፋቸው እግራቸውን ሸፍነው ከፊቱ የሚቆሙለት፤ እሳተ መለኮት ጌታን ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፤የአማናዊት ታቦት የቅድስት ድንግል ማርያም ነገር የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንትን አስደንቋልና ነው፤ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴው *‹‹ድንግል ሆይ እሳተ መለኮት በኾድሽ ባደረ ጊዜ ፊቱ እሳት፣ ልብሱ እሳት፣ ቀሚሱ እሳት ነው እንደምን አላቃጠለሽ ሰባት የእሳት ነበልባል መጋረጃ በኾድሽ ውስጥ ወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተጋረደ? ከጐንሽ በቀኝ ነውን? ወይስ ከጐንሽ በግራ ነውን? ትንሽ አካል ስትኾኚ፤ የሚያንጸበርቅ ነደ እሳት የሚከበው ኪሩቤል የተሸከሙት ዙፋን በኾድሽ ውስጥ በወዴት ተዘጋጀ? ወዴትስ ተተከለ? ታናሽ ሙሽራ ስትኾኚ››*[178] በማለት እሳተ መለኮት ጌታን የተሸከመች የቅድስት ድንግልን ነገር አድንቋል)። ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በድርሰቱ ይኽነን ሲገልጽ ‹‹They looked on her…›› (የእግዚአብሔር መኖሪያ ብለውም ይመለከቷታል፤ በእነርሱም ዘንድ እሳትን የተመላች ታቦት አድርገው ያከብሯታል)[179] በማለት አስተምሯል።

በሦስተኛ ደረጃ ሊቁ በምስጢር በመራቀቅ *የቅዱስ ቃል ታቦት* ሲል ያመስገነበት ምክንያት በብሉይ ኪዳን በአጽባዕተ እግዚአብሔር የተጻፉ ዐሠሩ

177. Jacob of Serugh, On The Annunciation, ET by M. Hansbury, p 53
178. አባ ሕርያቆስ ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፹-፹፪
179. Jacob of Serugh, On The Annunciation, ET by M. Hansbury, p 53



www.ethiopianorthodox.org

ቃላት ያሉባቸው ጽላት በታቦቷ ላይ ይቀመጡ ነበር (ዕብ ፱፥፫-፭)፤ በዘመነ ሐዲስም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አካላዊ ቃልን በማሕፀኗ የተሸከመች ማኅደረ ቃለ አብ በመኾኗ ይኽነን ስያሜ ሰጥቷታል፡፡ የጌታ ወዳጅ የኾነው ቅዱስ ዮሐንስም በወንጌሉ ላይ የክርስቶስን የምስጢረ ተዋሕዶውን ነገር ሲገልጥ ‹‹ቃል ሥጋ ኾነ በእኛም ዐደረ›› (ዮሐ ፩፥፲፬)ብሎ እንደመሰከረ፤ አካላዊ ቃል ከሥጋዋ ሥጋን፤ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ሰው በመኾኑ የእግዚአብሔር ቃል በላይዋ ከተቀመጠባት ከታቦቷ ይልቅ የአካላዊ ቃል የጌታ እናቱ የኾነች የአማናዊት ታቦት የድንግል ማርያም ክብር እጅጉን መላቁን ሲገልጥ ‹‹she was carried as an ark full of scripture…›› (የቅዱስ ቃል ታቦት (ማደሪያ) ኾነች፤ የምስጢራትን ትርጉም ነቢያት የተናገሩለት በርሷ ዐድሯልና፤ በዚኽም ከጠረጴዛው ታቦት ይልቅ ክብሯ የላቀ ኾነ፤ በሚያስደንቅ ክብር አክብሯታልና)[180] በማለት የአማናዊት ታቦት የቅድስት ድንግልን ክብር አድንቋል፡፡

## የሳሙኤል የሽቱ ዕቃ

ዕፍረት ምዕገዘ የተባለ ጌታችንን የወለደችልን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሳሙኤል ነገሥታቱን ሳኦልንና ዳዊትን ቀብቶ ያነገሠባትን ሽቱ ባኖረባት ዕቃ ትመሰላለች (፩ሳሙ ፲፥፩፤ ፩ሳሙ ፲፮፥፲፫)፡፡ ይኸውም በዚኽች በሽቱ ዕቃ አራቱን ሽቱ ዐምስተኛ ዘይት አጣፍጠው ያኖሩባታል፤ ኋላ ከቤተ ሌዊ የተወለደ ለክህነት የተገባ ቀኝ ቀኝ አካሉን ተቀብቶ ክህነትን፤ መንግሥት የሚገባው ከቤተ ይሁዳ የተወለደ ቀኝ ቀኝ አካሉን ተቀብቶ መንግሥትን ገንዘብ ያደርግ ነበር፤ ጌታም ከቅድስት ድንግል ማርያም እንደ አራቱ ሽቱ አራቱን ባሕርያተ ሥጋ እንደ ዐምስተኛ ዘይት ዐምስተኛ ባሕርየ ነፍስን ነሥቶ ክህነቱን መንግሥቱን ገንዘብ አድርጎ ለሌላ የሚያድል ኾኗልና፤ አንድም ይኽ ቅብዕ ሠያሚነት ያለው እንደኾነ፤ ጌታም ሠያሜ ነገሥት፣ ሠያሜ ካህናት ነው (ማቴ ፲፮፥፲፱፤ ሉቃ ፳፬፥፶፤ ዮሐ ፳፥፳፪) ፡፡

180. ibid p. 74





ይኽነን ምስጢርም ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በመጽሐፈ አርጋኖን ላይ ‹‹አንቲ ይእቲ ቀርነ ቅብዕ ዘሳሙኤል ዘምልእት መንፈሰ ትንቢት እስመ ሰሰለት እምቤተ ሳኦል ወአዕረፈት ውስተ ቤተ ዳዊት፤ እስመ እምዘርዐ ዚአሁ ተሠገወ ቃል›› (ከሳኦል ቤት ተወግዳ ወደ ዳዊት ቤት ያረፈች የትንቢት መንፈስን የተመላች የሳሙኤል ቅባት ማሰሮ አንቺ ነሽ፤ ቃል ከርሷ ዘር (ባሕርይ) ሥጋን ተዋሕዷልና)[181] በማለት አመስጥሮታል፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቍ፴፬ ምስጢሩን በመጠቅለል ‹‹ሙዳየ ዕፍረት ወቀርነ ቅብዕ ዘሳሙኤል›› (የሳሙኤል የሽቱ ሙዳይና የዘይት ቀንድ አንቺ ነሽ) በማለት ሲያመሰግናት በተጨማሪም ብዙ ሊቃውንት እመቤታችንን በሽቱ ዕቃ እየመሰሉ በስፋት አስተምረዋል፡፡

ምክንያቱም የሽቱን ዕቃ በወርቅ በብር አስጊጠው ጢስ እንዳይተንባት ትቢያ እንዳይበንባት ቤት ሰፍተው ሰቅለው ተንከባክበው እንደሚያኖሯት፤ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከእናቷ ማሕፀን ገሮምራ በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቃ ኖራለችና (ኢሳ፩፥፱፤ሉቃ ፩፥፳፰)፡፡በየጊዜውም የጸጋ ክብር ይጨመርላታልና (መዝ ፵፬፥፱-፲፫፤ ራእ ፲፪፥፩) ፤በተጨማሪም ይኽ የሽቱ ዕቃ ሽቱው በውስጡ ሳለ በአፍአ ይሸታል፤ ሽቱው ከወጣ በኋላም መዐዛው አይለየውም፤ እመቤታችንም ጌታን ፀንሳ ሳለች ተአምራት ታደርግ ነበር፤ ጌታንም ከወለደች በኋላ መዐዛ ትእምርቱ መዐዛ ተአምራቱ አልተለያትም፤ ይኽ ብቻ ሳይኾን መዐዛ ንጽሕናን መዐዛ ቅድስናን በማስገኘቷ በሽቱ ዕቃ ተመስላለች (ማቴ ፩፥፲፰-፳፭፤ ፪፥፩-፲፪፤ ሉቃ ፩፥፳፮-፶፮፤ ዮሐ ፪፥፩-፲፩፤ ፲፱፥፳፮-፳፯)፡፡

## የዳዊት መሰንቆ

ታላቁ ንጉሥ ዳዊት ከተሰጠው ሀብት ውስጥ አንዱ መሰንቆ መምታት ነበር፤ ይኸውም ዳዊት ቅብዐ መንግሥትን በተቀባ ጊዜ ሰባቱ ሀብታት ኹሉ አድረውበታል፤ እነዚኽም ሀብተ ኀይል፣ ሀብተ መዊእ፣ ሀብተ ክህነት፣ ሀብተ መንግሥት፣ ሀብተ ትንቢት፣ ሀብተ በገናና ሀብተ ፈውስ ነው፡፡

ሀብተ ኀይል የሚለው ታግሎ መጣል፣ ሩጦ መቅደም፣ አንበሳ በቡጢ መግደል ሲኾን፤ ሀብተ መዊእ የሚለው ሰንደቅ በተተከለበት ዐላማ በተዘረጋበት፣ ነጋሪት በተደረደረበት ገብቶ ድል መንሣት ተሰጥቶት ነበር፤

181. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፴፩



www.ethiopianorthodox.org

በሀብተ ክህነቱም መሥዋዕት ይሠዋ ነበር (፪ሳሙ ፳፬፥፲፰-፳፭)፤ በሀብተ መንግሥቱም ከወንድሞቹ መኻከል ተመርጦ ነግሧል(፩ሳሙ ፲፮፥፲፫)፤ በሀብተ ትንቢቱም ስለምርኮ፣ ከምርኮ ስለመመለስ፣ ስለጌታ ሥጋዌ ተናግሯል፤ ሀብተ በገና መደርደሩም እንደ እሱ አድርጎ አስማምቶ አሳምሮ በገና የሚደረድር አልነበረም፤ ድዉይ መፈወስም በዚያው በገናው ሳኦልን ይፈውሰው ነበር፤ ይኸ ሳኦል ጋኔን ዐድሮበት ነበርና ሲጠናበት ዳዊትን በገና ደርድርልኝ ይለው ነበር፤ ዳዊትም መሰንቆውን ሲመታ ወዲያውኑ ሳኦልን የሚጥለው ጋኔን ይተወው ነበር (፩ሳሙ ፲፮፥፳፫) ፡፡

ይኸ ኹሉ ለዳዊት መደረጉ ጌታ እመቤታችን በአብራኩ ስለነበሩ ሲኾን (ማቴ ፩፥፩፤ ሮሜ ፩፥፬)፤ ዳግመኛም መሰንቆው ምሳሌነት ስለነበረው በምሳሌ ፈውሶታል፡፡ ይኸውም መሰንቆ የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ድሕንጻ (መምቻ) የመንፈስ ቅዱስ፤ ድምፁ የመለኮት፤ አውታሩ የትስብእት ምሳሌ ነው፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም ይኸነን ምስጢር ሲያይ በቅዳሴ ማርያም ድርሰቱ *ወመሰንቆሁ ለዳዊት* (የዳዊት መሰንቆ አንቺ ነሽ)[182] በማለት ቅድስት ድንግልን አመስግኗታል (ማቴ ፩፥፲፰፤ ሉቃ ፩፥፴፪፤ ዮሐ ፩፥፲፬)፡፡

በመኾኑም ያ የዳዊት መሰንቆ የድንግል ማርያም ምሳሌ ቢኾን ሕሙማን ተፈወሱበት እንጂ በዛሬ ጊዜ ሲመታም ውሎ ሲመታም ቢያድር ስንኳን ድዉይ ሊፈውስ የተኛም አይቀሰቅስ፤ ይኸ ብቻ ሳይኾን ጌታ እመቤታችን በዳዊት በአብራኩ ስለነበሩ በእሱ የተዘባበቱ እነ ናባል፤ እነ ሜልኮል ተቀሥፈዋል (፩ሳሙ ፳፭፥፴፰-፴፱፤ ፪ሳሙ ፮፥፳፫)፡፡ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በመጽሐፉ ይኸነን ምስጢር በመጠቅለል *‹‹ወመሰንቆሁ ለዳዊት በዘባቱ ይዜምር መሐልየ ስብሐቲሁ ለእግዚአብሔር››* (የእግዚአብሔርን መንፈሳዊ ምስጋና የሚያደርስባት የዳዊት መሰንቆው ነሽ)[183] በማለት አመስግኗታል፡፡

## አውቴዘራማ

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት በዚኽ ሀብቱ በሳኦል ፊት በገና ቢደረድርም ሳኦል ካደረበት ክፉ የቅናት መንፈስ የተነሣ ዳዊትን ለመግደል ጦር እስከ መወርወር ደርሶ ነበር (፩ሳሙ ፲፱፥፱-፲)፡፡ በዚኹ ምክንያት ዳዊት ሸሽቶ

182. አባ ሕርያቆስም፤ ቅዳሴ ማርያም ቁ ፴፬
183. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘረቡዕ ፩፥፴





ሳሙኤል ወዳለበት ወደ አርማቴም ኼዶ ሳኦል በእሱ ላይ ያደረገውን ኹሉ ነገረው፤ ወሖሩ ዳዊት ወሳሙኤል ውስተ አውቴዘራማ ይላል ዳዊትና ሳሙኤል ወደ አውቴዘራማ ኼደው በዚያ ተቀመጡ፤ ሳኦልም ይኸነን ሰምቶ ዳዊትን ይዘው ይመጡ ዘንድ መልእክተኞች ሰደደ፤ እነዚያም ወረከቡ ማኅበሮሙ ለነቢያት ወሳሙኤል ይቀውም ማዕከሎሙ ይላል የነቢያት ጉባኤ ትንቢት ሲናገሩ፤ ሳሙኤል አለቃቸው ኾኖ ሲቆም ባዩ ጊዜ ፤በእነሱ ላይ መንፈሰ እግዚአብሔር ዐድሮባቸው ዳዊት የመንገሡን ሳኦል የመሞቱን ነገር ትንቢት ተናግረዋል፤ ሳኦልም ይኸነን ሰምቶ ሌሎች መልእክተኞች ቢልክም እነርሱም ያንን ትንቢት ተናግረዋል፤ እሱም ተቈጥቶ ሦስተኛ ቢልክም በተመሳሳይ መልኩ ሳኦል የመሞቱን ዳዊት የመንገሡን ነገር ትንቢት ተናግረዋል፤ ሳኦልም እጅግ ከመበሳጨቱ የተነሣ ጠይቆ ሳሙኤልና ዳዊት ወዳሉበት ወደ አውቴዘራማ ቢኼድም በእሱም መንፈሰ እግዚአብሔር ዐድሮ ትንቢት ተናግሮባታል (፩ሳሙ ፲፱፥፲፰-፳፬)፡፡

ይኸ ኹሉ ተመሳሳይ ትንቢት በአውቴዘራማ እንደተደረገ ነቢያት በሙሉ እንደተስማሙባት፤ በዐራቱ ዘመናት ማለት በዘመነ አበው፣ በዘመነ መሳፍንት፣ በዘመነ ነገሥት፣ በዘመነ ካህናት የተነሡት ነቢያት በመላ በአንድ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ኹሉም አምላክ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከዳዊት ዘር ከኾነች ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም የመወለዱን ነገር በትንቢታቸው ተናግረዋልና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ወግረ ትንቢት አንቲ ዘትሠመዪ አውቴዘራማ*
*ማኅበረ ነቢያት ብኪ ሰንቀዉ ነገራተ ምስጢር በኅብረተ ዜማ››*

(አውቴዘራማ የተባልሽ (በአውቴዘራማ የተጠራሽ) የትንቢት ተራራ አንቺ ነሽ፤ የምስጢራት ነገሮችን በተባበረ ዜማ የነቢያት አንድነት ባንቺ አስማምተው ተናገሩ መሰሉ)[184] በማለት በዐበይት ነቢያት በደቂቀ ነቢያት ኹሉ ስለእሷ የተነገረ መኾኑን አስተምሯል፡፡ ይኸነንም በክፍል ኹለት ላይ ባዘጋጀኹት መጽሐፌ በነቢያት ክፍል ውስጥ በስፋትና በጥልቀት ተንትኘዋለኍ፡፡

በአራቱ ክፍለ ዘመን ኹሉ የተነሱ ነቢያት ይኸነን ትንቢት

184. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት ገጽ 15



www.ethiopianorthodox.org

አስተባብረው መናገራቸውን ነገረ ነቢያትን ጠንቅቀው ያስተምሩ የነበሩ ጥንታውያን የቤተክርስቲያን መምህራን በአራት ዘመን የመነገሩን ምስጢር ሲያብራሩ እንዲኽ ብለዋል፤ በአራቱ ኪሩባውያን ላይ ዐድሮ የሚኖር አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ ይወለዳል ሲሉ በአራቱ ክፍለ ዘመን ኹሉ ተናግረዋል፤ አንድም አራቱ መዓዝነ ዓለምን የፈጠረ አምላክ ከእመቤታችን ይወለዳል ሲሉ በአራቱ ክፍለ ዘመን ተናግረዋል፤ አንድም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሲሠለስ ሲቀደስ በአንድነት በሦስትነት የሚኖር እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ አራቱን ባሕርያተ ሥጋ ከድንግል ማርያም ነሥቶ ዐምስተኛ ባሕርየ ነፍስን ተውሕዶ ይወለዳል ሲሉ በአራቱ ክፍለ ዘመን ኹሉ ትንቢት ተናግረዋል ሱባዔ ቈጥረዋል በማለት ያብራራሉ (ማቴ ፲፫+፲፯-፲፯፤ ዮሐ ፬+፴፰፤ ፰+፶፮፤ የሐዋ ፪+፳፭-፴፯፤ ዕብ ፩+፩-፫)።

በመኾኑም ታላቁ ሊቅ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ‹‹ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት ዘነቢያት››(ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢትና ምሳሌ)[185] በማለት በየዘመናቱ የነበሩ ነቢያት ኹሉ ስለንጽሕናዋ ስለ ቅድስናዋ፣ ስለ ዘላለማዊ ድንግልዋ ስለ አምላክ እናትነቷ በተለያየ ሕብረ ትንቢት የተናገሩላት በተለያየ ሕብረ አምሳል የገለጡላት መኾኗን አስተምሯልና ፤አውቴዝራማ ብለን እንጠራታለን።

## የኦርና ዐውድማ

እስራኤል ዘነፍስ ምእመናን በምልጃዋ ከሞተ ነፍስ የሚሠወሩባት ቅድስት ድንግል ማርያም ዳዊትና የእስራኤል ሕዝብ ከቸነፈር መቅሰፍት በዳኑባት መሥዋዕት በተሠዋባት በኦርና ዐውድማ ትመሰላለች (፪ ሳሙ ፳፬+፲፰-፳፭)። ይኸውም ክቡር ዳዊት ቢትወደዱ ኢዮአብን ከዳን እስከ ቤርሳቤህ ያሉትን እስራኤልን ቍጠራቸው አለው፤ ኢዮአብ ግን ሰው ገንዘቡን ቢቈጥሩበት እንደማይወድ ኹሉ እስራኤልም የእግዚአብሔር ገንዘቦች ናቸውና ይኽ ጥሩ አለመኾኑን ቢገልጽለት እንኳ፤ የዳዊት ቃል በመበርታቱ ሕዝበ እስራኤልን ለመቍጠር ኢዮአብና የሰራዊቱ አለቆች በመውጣት በዘጠኝ ወር ከኻያ ቀን ዐሥሩን ነገድ ቈጥረው ቍጥራቸውን አስታወቁት፤በዚኽም ምክንያት ጌታም

185. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፮





በዳዊት ላይ የሚያመጣበትን ሦስት መከራዎች ለነቢዩ ጋድ ገለጸለት። ጋድም ወደ ዳዊት መጥቶ የሦስት ዓመት ራብ በአገርኽ ላይ ያምጣብኽን? ወይስ ጠላቶችኽን እያሳደዱኽ ሦስት ወር ከእነርሱ ትሸሽን? ወይስ የሦስት ቀን ቸነፈር በአገርኽ ላይ ይኹን? አንዱን ምረጥ ብሎኻል አለው፤ ዳዊትም ‹‹ይኄይሰኒ እደቅ ውስተ እደ እግዚአብሔር እስመ ብዙኅ ውእቱ ምሕረቱ ፈድፋደ እምእደቅ ውስተ እደ እጓለ እመሕያው›› (የእግዚአብሔር ይቅርታው ብዙ ነውና ፤በሰው እጅ ከምወድቅ በእግዚአብሔር እጅ ብወድቅ ይሻለኛል) በማለት ቸነፈሩን መረጠ።

የስንዴ መከር ወራት በኾነ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ እደ መዓቱን ከፍ አድርጎ ሰባ ሺሕ ሰው ሞተ፤ ዳዊትም እነሆ እኔ በድያለኍ፤ ጠማማም ሥራ እኔ አድርጌአለኍ፤ እነዚኽ በጎች ግን ምን ዐደረጉ? እጅኽ በእኔና በአባቱ ቤት ላይ እንድትኾን እለምንኻለኍ፤ ብሎ ተናገረ ነቢዩ ጋድም በዚኽች ቀን ወደ ዳዊት መጥቶ በኢያቡሳዊዉ በኦርና ዐውድማ ለጌታ መሠዊያ እንዲሠራ ነገረው፤ ዳዊትም እንደታዘዘው ኼደ፤ ኦርናም በዳዊት ፊት ሰግዶ ንጉሡ ለምን ወደእሱ እንደመጣ ጠየቀ፤ ዳዊትም መቅሠፍቱ ከሕዝቡ ላይ ይከለከል ዘንድ ዐውድማውን ከአንተ ገዝቼ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ልሠራ ነው ብሎ፤ ዐውድማውንና ለመሥዋዕት የሚኾኑ በሬዎችን በሃምሳ ሰቅል ብር ገዝቶ በዐውድማዋ ላይ ሕዝቡን ከንጉሡ ጋር ንጉሡን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስማማ መሥዋዕት አቀረበ፤ ጌታም የለመነውን ልመና ሰምቶ መቅሠፍቱን ከእስራኤል ከልክሎ ምድርን ይቅር ብሏታል።

ይኽቺ ሕዝቡን ከእግዚአብሔር ጋር ያስማማችና መቅሠፍትን ያስቆመች የኦርና ዐውድማ በቅድስት ድንግል ማርያም ትመሰላለች። ይኸውም ዳዊት በኦርና ዐውድማ ላይ የሠዋውን መሥዋዕት እግዚአብሔር ወዶ እንደተቀበለለት ዛሬም በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አምነን የምናቀርበውን ጸሎትና ልመና ጌታ ወድዶ ይቀበልልናልና (ኢሳ ፩+፱፤ ዮሐ ፪+፩-፲፩)፤ ዳግመኛም በኦርና ዐውድማ የተሠዋው መሥዋዕት ሕዝቡን ከመቅሠፍት እንደጠበቀ ኹሉ፤ በእመቤታችንም ጸሎት ዓለም ኹሉ ተጠብቆ ይኖራልና፤ በተጨማሪም በዐውደ ኦርና በተሠዋው መሥዋዕት እስራኤል ዘሥጋ ተጠብቀው እንደኖሩ ሰአሊ ለነ ቅድስት የምንል እስራኤል ዘነፍስ የተባልን



www.ethiopianorthodox.org

ምእመናንም በየጊዜው በጸሎቷ ከመቅሠፍት የምንሰወር ኾነናልና የእመቤታችን ጣዕመ ውዳሴዋ እጅጉን የበዛለት ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹አንቲ ውእቱ ገራህተ ኦርና ዘብኪ ሦዓ ዳዊት መሥዋዕተ*
*መድኀኒት ለፈጣሪሁ*
*መቅሠፍተ ብድብድ ጽኑዕ አመ ኮነ ለሕዘቢሁ››*

(ብሩቱ የቸነፈር መቅሠፍት በሕዝቡ ላይ በመጣ በበዛ ጊዜ፤ ዳዊት የመድኀኒት መሥዋዕት የሠዋብሽ የኦርና አዝመራ ምድር (እርሻ) አንቺ ነሽ)[186] በማለት አመስግኗታል፡፡

186. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ እንዚራ ስብሐት፣ ገጽ 2





# ምዕራፍ አራት
# ነገረ ማርያም በመጽሐፈ ነገሥት

## <u>የሰሎሞን ቤተ መቅደስ</u>

ሰሎሞን በፈቃደ አምላክ በወርቅ የተሠራ ምሳሌነቱ ለእመቤታችን የኾነ ቤተ መቅደስን አሠርቷል፡፡ ሲሠራም ወርቅን ከመጠን በላይ ተጠቅሟል፤ ይኸነን ቤተመቅደስ ርዝመቱን ስልሳ ክንድ፤ ወርዱን ኻያ ክንድ፤ ቁመቱ ሠላሳ ክንድ አድርጎ ሲሠራ ቅድስተ ቅዱሳኑንም ርዝመቱ ኻያ ክንድ፤ ስፋቱ ኻያ ክንድ፤ ቁመቱን ኻያ ክንድ ካደረገ በኋላ በጥሩ ወርቅ ለብጦታል፤ ቤቱን ኹሉ በወርቅ ለብጦታል፤ በቅድስተ ቅዱሳን ፊት የነበረውን መሠዊያ በወርቅ ለብጦታል፤ የቤቱንም ወለል በውስጥና በውጪ በወርቅ አሠርቶታል፤ ዳግመኛም የወርቁን መሠዊያ፣ የወርቅ ገበታ ከጥሩ ወርቅ የተሠሩ መቅረዞች የወርቅ አበባዎች ቀንዲሎች፣ መኰስተሪያዎች፣ ከጥሩ ወርቅ የተሠሩ ጽዋዎች፣ ጉጠጦች፣ የወርቅ ማጠፊያዎችን ኹሉ አሠርቷል (፩ነገ ፮፥፴፰-፶)፡፡

ይቺ የእግዚአብሔር ቤት ኹለንተናዋ በወርቅ እንደሸለመ ኹሉ የእግዚአብሔር እናት ድንግል ማርያምም ኹለንተናዋ በንጽሕና በቅድስና ያጌጠና የተዋበ ነውና የሰሎሞን ቤተ መቅደስ ተብላለች፡፡



www.ethiopianorthodox.org

(መሐ ፬፥፮፤ ሉቃ ፩፥፳፰)፤ ዳሩ ግን ድንግል ማርያም በንጽሕናዋ በቅድስናዋ በዚኽ የወርቅ ቤት ብትመሰል እንኳ የሕያው እግዚአብሔር አማናዊት መቅደስ በመኾኗ ከሰሎሞን ድንቅ ቤት መቅደስ ይልቅ እጅጉን ትልቃለች፤ ትከብራለች (መዝ ፸፮፥፩-፫)። የቤተክርስትያን ሊቃውንትም በዳዊት ልጅ በሰሎሞን የታነጸው የወርቅ ቤተ መቅደስንና፤በዳዊት ሴት ልጅ(ወለተ ዳዊት) በተባለች በቅድስት ድንግል ማርያም የታነጸው በወርቅ ቤት የተመሰለውን የሥጋ፣ የነፍስ፣ የልቡና ንጽሕናዋን በማመሳሰል ልዩ ትንታኔ ሰጥተዋል።

ከሊቃውንቱ መኻከል ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ የጸናች እመቤታችን ሰሎሞን ባሠራት የወርቅ መቅደስ ሲመስላት *«አንቲ ውእቱ መቅደስ ዘሐነጸ ሰሎሞን ወአስተቀጸላ በሜላትሮን ወለበጠ ዳቤራ በውሳጥያተ መቅደስ፤ ምድራሂ ወአረፍታ በወርቅ ጽሩይ ወኪሩበ አሥዐለ በውስቴታ ዕሥራ በእመት ቆሙ ዐሠርቱ ወኀምስቱ በእመት ክንፉ፤ በአሐዱ ክንፉ ይጐድዕ አረፍተ ቤት፤ ወበአሐዱ ክንፉ ይጼልል መልዕልተ ዳቤር፤ ወከማሁ ካልአንኒ እምለፌ ወእምለፌ ሥዑላን ወያስተራክቡ ክነፊሆሙ ዲበ ዳቤረ ቅድስተ ቅዱሳን»* (ሰሎሞን ያሠራት እንደ ዝናር እንደ ዐምድ ባለ ወርቅ የጠፈሯን ዙሪያ ያስጌጣት፤ በመቅደሱ ውስጥ ያለቺውን ቅድስተ ቅዱሳንዋን ዐውደ ምሕረቷን ግድግዳዋን በጥሩ ወርቅ ያስጌጣት፤ ቁመቱ ኻያ ክንድ፤ ክንፉ ዐሥራ ዐምስት ክንድ የሚኾን ኪሩብን በውስጧ ያሣለባት ቤተ መቅደስ አንቺ ነሽ፤ በአንድ ክንፉ የቤቱን ግድግዳ ይመታል፤ በአንድ ክንፉ በቅድስተ ቅዱሳኑ ላይ ይጋርዳል፤ እንዲኹም ሌሎቹ በወዲያና በወዲኽ ተሥለው ክንፎቻቸውን በቅድስተ ቅዱሳኑ ላይ ይገናኛሉ)[187] በማለት ሲገልጽ፤ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በውዳሴ ማርያም መጽሐፉ *«መቅደስ ዘይጼልልዋ ኪሩቤል እለ ሥዑላን በሥዕለ እግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ኦ ንጽሕት ዘእንበለ ውላጤ ኮነ ሠራዬ ኀጢአትነ ወደምሳሴ አበሳነ»* (በእግዚአብሔር ሥዕል የተሣሉ ኪሩቤል የሚጋርዱሽ መቅደስ አንቺ ነሽ፤ ንጽሕት ሆይ ያለመለወጥ ካንቺ ሰው የኾነው አካላዊ ቃል ኀጢአታችን ይቅር የሚል፤ በደላችንን የሚደመስስልን ኾነ)[188] በማለት ኀጢአታችንን የደመሰሰልን አማናዊ ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን በማሕፀኗ የተሸከመች፤ በድንግልና የወለደች፤ በሕያዋኑ ኪሩቤል የተጋረደች

187. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ ፫፥፲፰

188. ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ፤ ውዳሴ ማርያም ዘተዳሚት





እውነተኛዪቱ መቅደስ መኾኗን መስክሯል።

በመኾኑም በመቅደሱ ያለ ኹሉ በወርቅ እንደተለበጠ ኹሉ፤ ኹለመናው የቅድስት ድንግል ማርያም ነፍስም በንጽሕና በቅድስና ያማረና ያጌጠ ነው።

ይኽ ቤተ መቅደስ ሥራው ከተፈጸመ በኋላ በ፩ኛነገሥት ፰፥፲-፲፩ ላይ «ካህናቱም ከመቅደሱ በመጡ ጊዜ፤ ደመናው የእግዚአብሔርን ቤት መላው። የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት መልቶ ነበርና፤ ካህናቱ ከደመናው የተነሣ ለማገልገል ይቆሙ ዘንድ አልቻሉም» በማለት ቤተ መቅደሱ በጌታ ክብር መመላቱን ይገልጻል። ሊቁ ቅዱስ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ቤተ መቅደሱን የመላ ደመና በእውነት ከእናቷ ማሕፀን ጀምሮ በጌታ ክብር የተመላች የአማናዊት ቤተ መቅደስ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስለመኾኑ ሲያስተምር

*«መቅደስ አንቲ ዘሰሎሞን ውስቴትኪ ተመልአ ለእግዚአብሔር ስብሐቲሁ እስመ ስዕኑ ካህናት ገቢረ ግብሮሙ አሜሁ»*

(ካህናቱ የክህነት ሥራቸውን መሥራት ስለአልቻሉ ያንጊዜ የእግዚአብሔር ምሥጋና የተመላብሽ የሰሎሞን መቅደስ አንቺ ነሽ)[189] በማለት በውስጥ በአፍአ በነፍስ በሥጋ በእግዚአብሔር ጸጋ የተመላች መኾኑን መስክሯል።

የእግዚአብሔር ማደሪያ የኾነውን ቤተ መቅደስ ለመሥራት ዳዊት ቢመኝም፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ልጁ ሰሎሞን እንዲሠራው በመኾኑ ከልክሎታል (፪ሳሙ ፯፥፭፤ ፩ነገ ፰፥፲፰-፲፱)። ጠቢቡ ሰሎሞንም የጌታ ማደሪያ የሚኾን ቤተ መቅደስን አስጊጦ ከሠራ በኋላ እጅግ በመደነቅ «እነሆ ሰማይ ከሰማያትም በላይ ያለው ሰማይ ይይዝኽ ዘንድ አይችልም፤ ይልቁንስ እኔ የሠራኹት ቤት እንዴት ያንስ» (፩ነገ ፰፥፳፯)፤ በማለት በሰው እጅ በተሠራው ቤተመቅደስ እንዴት የማይወሰነው አምላክ ሊወሰን ይቻለዋል በማለት ምስጢሩ ረቀበት ተናግሮ ነበር፤ ነገር ግን «በዚያ ስሜ ይኾናል» የሚለውን የጌታ ቃል ኪዳንን በሙሉ ልብ አምኖ ተቀብሎታል (፩ነገ ፰፥፳፱)፤ በተመሳሳይ መልኩ እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል የአምላክ እናት እንደምትኾን ቢነግራት ነገሩ ረቆባት «ወንድ ስለማላውቅ ይኽ እንዴት

189. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 2



www.ethiopianorthodox.org

ይኾናል›› (ሉቃ ፩፥፵፭)፤ ብትልም እንኳ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር እንደሌለ በማመን ራሷን ለአምላክ እናትነት አሳልፋ በመስጠት ‹‹እነሆኝ የጌታ አገልጋዩ እንደ ቃልኽ ይኹንልኝ›› በማለት ተናግራለች (ሉቃ ፩፥፴፯-፴፰)፡፡

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም፤ ሰሎሞን በሠራው ቤተ መቅደስ የጌታ ማደር እጅግ እንዳስደነቀው (፩ነገ ፰፥፳፯) ኹሉ በንጽሕት መቅደስ በእመቤታችን የአምላክ ሰው መኾን ለሰው ኹሉ እጅግ የሚያስደንቅ የሥጋዌ ምስጢር መኾኑን ሲገልጽ ‹‹Blessed is she…›› (በትንሽ እና ዘርን በማይቀበል ማሕፀኗ ኀያሉን የተሸከመች ርሷ ቡርክት ናት፤በርሱም ሰማያት የተመሉ እና ለእሱ ታናሽ የኾነ)[190] በማለት ሰማይና ምድር የማይወስነውን አምላክ የወሰነች፤ ልክ ሰሎሞን ቤተ መቅደሱን በወርቅ በብር በከበሩ ማዕድናት እንዳስጌጠው እሷም ሰውነቷን በሃይማኖት በምግባር በንጽሕና በቅድስና ያስጌጠች ሕያዋዊት መቅደስ መኾኑን አስተምሯል፡፡ ይኸው ሊቅ እመቤታችን ራሷን በቅድስና ያቀረበች ሕያዋዊት መቅደስ በመኾኗ ለጌታ እናትነት እንደተመረጠች በልደት ድርሳኑ ‹‹መላ ሐሳቦችን ከኀሊናዋ አሰባሰበች አራቀች፤ በቅዱሱ ፊት የእሷን ንጹሕ መቅደስ በፍቅር ረጨች)[191] በማለት በመንፈስ ቅዱስ ጥባቆት እስከ መጨረሻው ድረስ ምልዕተ ጸጋ ኹና የመኖሯን ነገር አስተምሯል፤

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም በትርጓሜው ይኽነን ሲገልጽ ‹‹Mary's body…›› (የማርያም ሰውነት የምድር ላይ መቅደስ ነው፤ በእሱም በኀጢአት፣ በሞት፣ በምድር ርግማን ፈንታ የበረከት ዘር የተዘራባት፤ የእግዚአብሔር መልእክተኛም በሰላምታው ይኽነን ዘር ዘራ፤ የኤልሳቤጥም ሰላምታ ይኽነን አረጋገጠ)[192] በማለት መርገመ ሥጋ መርገመ በነፍስ የሌለባት፤ በቅድስና የተጌጠች ቤተ መቅደስ መኾኗን መስክሮላታል፡፡ ልክ እንደ ቅዱስ ኤፍሬም ኹሉ ቅዱስ ያዕቆብም ድንግል ማርያም ለእግዚአብሔር ንጽሕት መቅደስ ኾና መገኘቷን በትምህርቱ ‹‹When the Great king…›› (ታላቁ ንጉሥ ወደ እኛ ቦታ ለመምጣት ባሰበ ጊዜ በምድር ላይ ካሉት ኹሉ በእጅጉ ንጽሕት ወደኾነችው ዐደረ፤ ምክንያቱም እሱን ደስ አሰኝቶታልና፤ በድንግልናና በቅድስና ክብር

190 Jacob of Serugh, On The Virgin,Hansbury p 41; Mariological Thoughts Of Mar Jocob Of Serugh pp 122-124

191 Jacob Of Serugh, On The Nativity Of Our Redeemer p 59

192 Saint Ephrem's Commentary On Tatian Diatessaron, Iv, ET by C.Mccarthy1993,pp 91-92





እንተሳሰብ በተጌጠ በንጹሕ ማሕፀን እሱ ዐደረ)[193] በማለት የእውነተኛው ሊቀ ካህናት የኢየሱስ ክርስቶስ ማደሪያው በንጽሕና በቅድስና በድንግልና ያማረች የተጌጠች፤ ሕያዋዊት ንጽሕት ቤተ መቅደስ ኹና የመገኘቷን ነገር በጥልቀት አስተምሯል፡፡

## የሰሎሞን ዙፋን (አትሮንስ)

ጥበብ ሥጋዊ ጥበብ መንፈሳዊ የተሰጠው የእግዚአብሔርን ቤት ያሠራው ይኽ ሰሎሞን፤ አምላክን ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች የቅድስት ድንግል ማርያምን ምሳሌ የምትኾን ዙፋን የኾነችውን አትሮንስን በጥሩ ወርቅ አሠርቷል (፩ነገ ፲፥፲፰-፳)፡፡ ይኸውም ወገብረ ንጉሥ አትሮንሰ ዘቀርነ ነጌ ዐቢየ ወቀብዖ ወርቀ ንጹሐ ይላል ከዝሆን ጥርስ ታላቅ ዙፋን አሠርቶ በጥሩ ወርቅ ኹለንተናዋን አስለበጠ፤ ወደ ዙፋኗ የሚያስወጡ ስድስት እርከኖች አስደርጎ፤ በስተኋላ ያለው የዙፋኑን ራስ ክብ እንዲኾን አድርጓል፤ ከዚያም ኹለት አንበሶች በዙፋኑ በክንዶቹ መደገፊያ አጠገብ ሲያስቀርጽ በስድስቱም እርከኖች ላይ በቀኝና በግራ ዐሥራ ኹለት አንበሶችን አቁሟል፡፡

ይኽቺውም ዙፋን ንጉሠ ሰማይ ወምድር ኢየሱስ ክርስቶስን ፱ወር ከ፭ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች የድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ሰሎሞን የጌታ ምሳሌ፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ አምሳል ነው፡፡ ይኽ ንጉሥ ሰሎሞን ስድስቷን እርከን ወጥቶ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነገር ሲሰማ ሲፈርድ ይውል ነበር፤ ይኽን ስድስት እርከን በሱባዔ ቢቈጥሩት አርባ ኹለት ይኾናል፡፡ ይኽም የአርባ ኹለቱ አበው ምግብና ሲፈጸም ለመንግሥቱ ፍጻሜ የሌለው ንጉሠ ነገሥት ክርስቶስ ንጽሕት ቅድስት ከኾነች ከእመቤታችን የመወለዱን ምስጢር አስቀድሞ ያሳየ ነው (ኢሳ ፲፩፥፩-፪፤ ዳን ፪፥፴፬-፴፭፤ ሉቃ ፩፥፴፫፤ ፩ጢሞ ፮፥፲፭፤ ራእ ፩፥፭፤ ፲፯፥፲፬፤ ፲፱፥፲፮)፡፡ ኢትዮጵያዊ ቄርሎስ የተባለው የነገረ መለኮት ምሁር ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ይዞ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

‹‹አንቲ ውእቱ ለሰሎሞን አትሮንሱ
ዘይዌድስዋ አናብስተ ወርቅ ነዐበተ ስሱ››

(የስድስት እጥፍ (ዐሥራ ኹለት) የሚኾኑ የወርቅ አንበሶች የሚያመሰግኗት

193 Jacob Of Serugh, On The Virgin, ET by M.Hansbury,p 924



www.ethiopianorthodox.org

የሰሎሞን ዙፋን አንቺ ነሽ)[194] በማለት በዐሥራ ኹለቱ የወርቅ አናብስት የተመሰሉ ዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት የሚያመሰግኗት የሰማያዊ ንጉሥ የክርስቶስ ማደሪያ የኾነች የወላዲተ አምላክ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን ገልጾታል፡፡

ዳግመኛም በዚያች የወርቅ ዙፋን ከንጉሡ በቀር ማንም ያልተቀመጠባት እንደኾነች ኹሉ፤ የፍጥረታት አስገኝ ሰማያዊ ንጉሥ ወልደ እግዚአብሔር ባደረበት በድንግል ማርያም ማሕፀንም ዕሩቅ ብእሲ ከቶ አያድርም፤ ሠዓሌ ሕፃናት በተሣለበት ሰሌዳ በተቀረጸበት ሰፋድል፤ ዘርዐ ብእሲ ቀለም ኹኖ ሊሣልበት ሊቀረጽበት አይቃጣም አይታሰብም፡፡ በተጨማሪም ነገሥታቱ፣መኳንንቱ፣ መሳፍንቱ በታላቁ በሰሎሞን ዙፋን ፊት እጅ በመንሣት ምስጋናን እንደሚያቀርቡ ኹሉ ፤ቅድስት ድንግል ማርያምም ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክትን፤ ደቂቀ አዳምን ፍጥረታትን ኹሉ የፈጠረ ንጉሠ ሰማይ ወምድር ክርስቶስን በመውለዷ፤ የፈጣሪያቸው እናት ናትና ፍጥረታት ኹሉ የሚያመሰግኗት መኾኑን ሊቁ አባ ጊዮርጊስም በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ እግዝእትየ ማርያም ለሰሎሞን ሐዲስ ዓራተ መንግሥቱ*
*አትሮንሱ ዘቀርነ ነጌ ወዘወርቀ ምዕራፍ መዝራእቱ*
*ዘለኪ ይሰግዱ መላእክት ተስዓ ወተስዐቱ*
*እለኒ ይቀርቡ ኀቤኪ ኢይርሕቁ እምኔኪ ወኢይትአተቱ*
*እንዘ ይገንዩ ለክብርኪ ወዕበየኪ የአኵቱ*
*ለኪ ይትቀነዩ ነገሥት መታክፍቲሆሙ እንዘ ያቴሕቱ*
*ወቅድሜኪ ይቀውሙ መኳንንት ሐቌሆሙ እንዘ ይቀንቱ››*

(እመቤቴ ማርያም ሆይ ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት የሚሰግዱልሽ፤ አትሮንሱ የዝኆን ቀንድና ክንዱም የሚያርፍበት የወርቅ የኾነ የሰሎሞን ዐዲስ የመንግሥቱ ዙፋን አንቺ ነሽ፡፡ ለክብርሽ እየተገዙና ገናንነትሽን እያመሰገኑ ወደ አንቺ የሚቀርቡ ከአንቺ አይርቁም አይወገዱምም፡፡ ነገሥታትም ትከሻቸውን ዝቅ ዝቅ እያደረጉ (አድርገው) ለአንቺ ይገዛሉ፤ መኳንንትም ወገባቸውን ታጥቀው (እየታጠቁ) በፊትሽ ይቆማሉ)[195] በማለት በመላእክትና በደቂቀ አዳም የምትመሰገንና የአክብሮት ስግደት የሚገባት መኾኗን አስተምሯል (መዝ

194. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ እንዚራ ስብሐት፤ገጽ 25
195. ዝኒ ከማሁ፤ገጽ 42





፵፬፥፲፱፤ ፵፬፥፲፯፤ መሐ ፮፥፱-፲፤ ኢሳ ፵፱፥፳፫፤ ሚል ፬፥፱፤ ሉቃ ፩፥፳፰-፵፱፤ ፵፩-፭፭፤ የሐዋ ፩፥፲፬፤ ራእ ፲፱፥፩)፡፡

## የቀርሜሎስ መሠዊያና የኤልያስ ደመና

ነቢየ እግዚአብሔር ኤልያስ ባለበት ዘመን የነበረው ንጉሥ አክዓብ ሲባል ንግሥቲቱ ኤልዛቤል ትባል ነበር፤ ለንጉሡ ለአክዓብ ፬፻፶ ለንግሥቲቱ ለኤልዛቤል ፬፻ ነቢያተ ሐሰት፣ ካህናተ ጣዖት ነበሩአቸው፤ ኀጢአት ይሠሩ ጣዖት ያመልኩ ነበር፡፡

ያን ጊዜ ኤልያስ አክዓብን ‹‹በፊቱ የቆምኹት የእስራኤል አምላክ ሕያው እግዚአብሔርን ከአፌ ቃል በቀር፤ በእነዚኽ ዓመታት ጠልና ዝናም አይኾንም›› በማለት ሰማይ ዝናም ለዘር ጠል ለመከር እንዳይሰጥ፤ መሬትም የዘሩባትን እንዳታበቅል የተከሉባትን እንዳታጸድቅ ከለከለ (፩ነገ ፲፯፥፩)፡፡ ከዚያም ከጌታ ታዝዞ ወደ ኮራት ፈፋ ተቀመጠ፡፡ ያዕቆብም በመልእክቱ በነቢዩ ኤልያስ ስለተደረገው ነገር ሲገልጽ ‹‹የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኀይል ታደርጋለች፤ ኤልያስ እንደኛ ሰው ነበር፤ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፤ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ኹለተኛም ጸለየ፤ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ፤ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች›› በማለት የነቢየ እግዚአብሔር የኤልያስን ታላቅነት መስክሯል (ያዕ ፭፥፲፯-፲፰)፡፡

ከዚኽ በኋላ በጌታ ታዝዞ በሲዶና አጠገብ ወዳለችው ወደ ስራፕታ ኼዶ ቤቷ በበረከት እንዲመላ አድርጎ የሞተ ልጇን ከአስነሣላት በኋላ፤ ጌታ ሑር አስተርእዮ ለአክዓብ ኺድ ለአክዓብ ተገለጥ ብሎ በተናገረው መሠረት በቢትወደዱ አማካኝነት አክአብን ተገናኝቷል፤ ኋላም አክአብን ላንተ ፬፻፶ ለኤልዛቤል ፬፻ በድምሩ ስምንት መቶ ኀምሳ ነቢያተ ሐሰት ካህናት ጣዖት አሏችኍ፤ እኔ ነቢያት ካህናት አልቀው ብቻዬን ቀርቻለኍ፤ መሥዋዕት እንሠዋና እነርሱም ጣዖቶቻቸውን በየስማቸው ይጥሩ እኔም የእግዚአብሔር ስም እጠራለኍ፤ ሰምቶም በእሳት የሚመልስ አምላክ እርሱ አምላክ ይኹን አለ፡፡

እነሱም ይኹን አሉ፤ ከጊዜው ነግሁን ከመሥዋዕቱ የሠባውን መርጠው፤ ላሙን ዐርደው አወራርደው ደንጊያውን ጸፍጽፈው፤ እንጨቱን



www.ethiopianorthodox.org

ረብርበው፤ እስከ ቀትር ድረስ በዓል ሆይ ስማን እያሉ ቢጸልዩ ከሰማይ እሳት ወርዶ የማይበላላቸው ኾነ፤ ወሶበ ኮነ ቀትረ አኀዘ ይሣለቅ ላዕሌሆሙ ኤልያስ ቴስብያዊ ይላል ቀትር በኾነ ጊዜ ቴስብያዊዉ ኤልያስ ይዘብትባቸው ገሮመር ፤ አምላካችኍ ምናልባት ዐሳብ ይዞታል፣ ወይም ፈቀቅ ብሎአል፣ ወይም ወደ መንገድ ኼዷል፣ ወይም ተኝቶ እንደኾነ መቀስቀስ ያስፈልገዋል፤ ጩኻችኍ ጥሩት እያለ ዘበተባቸው። እነሱም ደማችንን ሳይቀር ሠዋንልኽ ለማለት ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ገላቸውን በካራ ቢቧጭሩም ድምፅ አልነበረም፤ መሥዋዕተ ሠርክ ሲደርስ የነሱን አንሥቶ ዐሥራ ኹለት ደንጊያ ጸፍጽፎ ዕንጨቱን ረብርቦ ወይፈኑን ዐርዶ አወራርዶ በዚያ ላይ አድርጎ ዙርያውን አጐድጕዶ አራት ጋን ውሃ በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ አፍስሱ አለ፤ ድገሙ አለ ደገሙ፤ ሦስተኛ አድርጉ አለ ሦስተኛ አደረጉ፤ ይኽ በድምሩ ዐሥራ ኹለት ይኾናል።

ከዚያ በኋላ አቤቱ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አምላክ አንተ እንደኾንኽ፤ እኔም ባሪያኽ እንደኾንኍ፤ ይኽነንም ኹሉ በቃልኽ እንዳደረግኍ ዛሬ ይገለጥ በማለት ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክት፤ ከሰማይ እሳት ወርዳ መሥዋዕቱን፣ ዕንጨቱን፣ ድንጋዮቹን አፈሩን በልታ በጕድጓድ ውስጥ ያለውን ውሃ ላሰች፤ ሕዝቡም ኹሉ ይኽነን አይተው በግምባራቸው ተደፍተው እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነው በማለት መሰከሩ ( ፩ነገ ፲፰፥፩-፵)።

ለጊዜው እንዲኽ ተደርጓል፤ ለኋላው ምሳሌ ነው፤ ምሥዋዕ ከነ ዕፁ የእመቤታችን፤ እሳት የመለኮት፤ ሥጋው የትስብእት ይኸውም መዋሐዱን ብቻ ሲያይ፤ ዐሥራ ኹለት ደንጊያ፤ የዐሥራ ኹለቱ ነገደ እስራኤል፣ ዐሥራ ኹለቱ እንስራ የዐሥራ ኹለቱ ሐዋርያት፤ ውሃው የጥምቀት፤ ከድንጋዩ ላይ ማፍሰሱ ሐዋርያት ከዐሥራ ኹለቱ ነገድ የተወለዱ ምእመናንንና አሕዛብን የማጥመቃቸው አምሳል ነው።

ታላቁ የቤተክርስቲያናችን ሊቅ አባ ጊዮርጊስም የቀርሜሎስ መሠዊያ የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ መኾኗን በመጽሐፉ ሲገልጽ «አንቲ ውእቱ ኑድቀ ምሥዋዕ ዘደብረ ቀርሜሎስ ዘበላዕሌሁ አጸነሐሐ ኤልያስ መሥዋዕተ ለአምላክነ እስራኤል ወረደ እሳት ወበልዖ ለሥጋ መሥዋዕት ወለዕፀዊሁኒ ወለማይኒ ዘውስተ ዐውደ ምሥዋዕ» (ኤልያስ ለእስራኤል አምላክ መሥዋዕትን





በላዩ ያሻተተበት የቀርሜሎስ ተራራ መሠዊያ ግንብ አንቺ ነሽ፤ እሳት ወርዶ የመሥዋዕቱን ሥጋ በላ፤ የተረበረበትን ዕንጨቶችና በመሠዊያው ዙርያ ውስጥ ያለውንም ውሃ)[196] በማለት የምሳሌውን እሙንነት ተናግሯል።

ይኽነን ተአምር ኤልያስ ካየ በኋላ፤ ከበዓል ነቢያት አንድ ሰው እንዳያመልጥ ያዙዋቸው፤ በማለት ወደ ቂሶን ወንዝ ወስዶ አሳርዶአቸዋል። ከዚኽ በኋላ ቀርሜሎስ ተራራ ወጥቶ ዐይኑ ሥጋውን ወደ ምድር ዐይነ ኅሊናውን ወደ ሰማይ በማቅናት፤ አንገቱን ከጕልበቱ ላይ አድርጎ ለመነ፤ ከዚያም ብላቴናውን ወጥተኽ ወደ ባሕር እይ አለው፤ ብላቴናውም እየወጣ እየገባ ሲያይ፤ በሰባተኛው እነሆ የሰው እጅ የምታኽል ደመና ከባሕር ወጣች አለው፤ ኤልያስም ወጥተኽ አክዓብን ዝናብ እንዳይከለክልኽ ሠረገላኽን ጭነኽ ውረድ በለው አለው፤ ከዚያ በኋላ ወዲያው ድምንምን ጭልምልም ብሎ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር የቆየ ዝናብ ዘንቦላቸው ደስ ብሏቸው ጠግበው ዐድረዋል (፩ነገ ፲፰፥፵፩-፵፮)።

ይኽም ምሳሌ ነው፤ ደመና የቅድስት ድንግል ማርያም፤ ዝናም የክርስቶስ ምሳሌ ሲኾን ፤ይቺ ዝናምን የያዘች ደመና በአራተኛው ዘመን እንደተገኘች፤የሕይወት ዝናብ የሕይወት ውሃ ክርስቶስን የወለደች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም በአራተኛው ትውልድ በይሁዳ፤ በአራተኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ ካህናት ተገኝታለች። ዳግመኛም ከዝናም በፊት ጽጋበ ሥጋ እንዳልተገኘ እመቤታችንም ጌታን ሳትወልድ ድኅነተ ነፍስ አልተገኘም፤ ከዝናሙ በኋላ ግን ጽጋበ ሥጋ እንደተገኘ እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ ድኅነተ ነፍስ ተገኝቷልና ደመና ኤልያስ ትባላለች (ሮሜ ፭፥፲፱-፳፩) ።

## <u>የኤልያስ የወርቅ መሶብና የወገቡ መታጠቂያ</u>

ንጉሡ አክዓብ ኤልያስ ያደረገውንና፤ የሐሰት ነቢያትን በሰይፍ እንዳስገደለ ለኤልዛቤል ነገራት፤ ያን ጊዜ እሷ ነፍስኽን ከእነዚኽ እንደ አንዲቱ ነፍስ ባላደረጋት ብላ ለኤልያስ መልእክተኛ ላከች፤ ኤልያስም ኤልዛቤልን ያኽል ጠላት ሳለችብኝ በዚኽ እንደምን እቀመጣለኍ ብሎ፤ ሸሽቶ አንድ ቀን የሚያኽል

196. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፣ አርጋኖን ዘሰኑይ ፲፩፥፲፫



www.ethiopianorthodox.org

መንገድ በምድረ በዳ ኺዶ ደክሞት በክትክታ ዛፍ ሥር ተጋደመ፤ እንቅልፍ አንቀላፋ፤ መልአኩ መጥቶ ቀስቅሶት ቢነካ፤ ከራስጌው በመሶብ ኅብስት፣ በማሰሮው ውሃ ተዘጋጅቶ አገኘ፤ ያን ተመግቦ ተመልሶ ተኛ፤ መልአከ እግዚአብሔር ዳግመኛ መጥቶ ቀስቅሶት «ተንሥእ ወብላዕ እስመ ርሑቅ ፍኖትከ» (ጐዳናኽ የራቀ ነውና ተነሥተኽ ብላ) አለው፤ ያን ተመግቦ ወሖረ በኀይለ ውእቱ እክል ዘበልዐ አርብዓ መዓልተ ወአርብዓ ሌሊተ እስከ ደብረ ኮሬብ ይላል በዚያም ምግብ ኀይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ኼዶ፤ ይኸው ጽንዕ ኹኖት ዐርጓል (፩ነገ ፲፱፥፩-፰)።

ይኸውም የኤልያስ ረኀበ ሥጋውን ያስወገደውን ኅብስት የያዘች መሶብ ሥጋውን ቈርሶ ደሙን አፍስሶ ረኀበ ነፍሳችንን ጽምአ ነፍሳችንን ያራቀልን የሕይወት እንጀራ፣ የሕይወት መጠጥ ክርስቶስን የወለደችልን የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ወርቅ የንጽሕናዋ የቅድስናዋ፤ ኅብስት የሥጋው የደሙ፤ ያን ተመግቦ ያረገው ኤልያስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ተቀብለው ወደ ገነት ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚገቡ የምእመናን ምሳሌ ነውና (መዝ ፸፰፥፩-፯፤ ዮሐ ፮፥፴፫-፴፭፣ ፯፥፶-፶፱)፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም ይኽንን ምስጢር በማየት በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ «መሶበ ወርቅ እንተ ኤልያስ» (የኤልያስ የወርቅ መሶብ አንቺ ነሽ)[197] በማለት አመስግኗታል።

ይኽ ታላቅ ነቢይ ኤልያስ ዮርዳኖስን በመጠምጠሚያው ከፍሎ በእሳት ሠረገላ ተነጥቆ የወጣ፤ ባሕታዊ፣ ጻዋዊ፣ ተሐራዊ ጠጕራም ልክ እንደ ዮሐንስ መጥምቅ በወገቡ ጠፍር ታጥቆ የኖረ ንጹሕ ድንግል ነበር (፪ነገ ፩፥፰)፤ በወገቡ የታጠቃት ይኽቺ መታጠቂያው የድንግልናው ምልክት ነበረች። ይኸውም መታጠቂያው ከደመ ነፍስ የተለየች እንደኾነች እሱም ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ተለይቶ ንጽሕ ጠብቆ በድንግልና መኖሩን የሚያመላክት ነበረ፤ ይኽቺ የኤልያስ የድንግልናው ምልክት መታጠቂያው የደናግል መመኪያቸው፣ የንጽሕናቸው መታወቂያ መከበሪያ መሠረት ኾና የምትኖር ከሥጋዊ ከደማዊ ግብር ተለይታ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ በድንጋሌ ኅሊና የከበረች የድንግል ማርያም ምሳሌ ናትና፤ ሊቁ አባ ጊዮርጊስ በኆኅተ ብርሃን ምስጋናው ላይ «ቅናተ ድንግልናሁ ለኤልያስ» (የኤልያስ የድንግልናው መታጠቂያ አንቺ ነሽ)[198]

197. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፫
198. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ ኆኅተ ብርሃን ገጽ 97





በማለት አመስግኗታል።

ድንግል ኤልያስን ካለበት አምጥቶ በታቦር ተራራ ክብሩን ያሳየ (ማቴ ፲፯፥፫)፤ ለሌሎች ንጹሓን ደናግል ክብር የሚሰጠውን አምላክ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና የወለደች በመኾኗ፤ ደናግል ኹሉ እመቤታችን ዐስበ ድንግልናችንን ታስጠናለች ድንግልናችንን ታስፈጽመናለች እያሉ ያመሰግኗታልና ንጽሕት ድንግል እመቤታችን የደናግል መመኪያቸው፤ የንጽሕናቸው መታወቂያ ናት። ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም መጽሐፉ ላይ «ኦ ድንግል አምሳል ወትንቢት ዘነቢያት ሞገሶሙ ለሐዋርያት አሞሙ ለሰማዕት ወእኅቶሙ ለመላእክት፤ ትምክሕቶሙ ለወራዙት ወደናግል ወመነኮሳት እለ ይትግሁ በውስተ አናቅጺሃ መዓልተ ወሌሊተ» (ድንግል ሆይ የነቢያት ትንቢትና ምሳሌ፣ የሐዋርያት ሞገሳቸው፣ የሰማዕታት እናታቸው፣ የመላእክት እኅታቸው አንቺ ነሽ፣ በመዓልትና በሌሊት በበሮችዋ ደጅ የሚጠኑ የወራዙትና የደናግል የመነኮሳትም መመኪያቸው አንቺ ነሽ)[199] በማለት መመኪያነቷን አስተምሯል።

## የኤልሳዕ ማሰሮና ማድጋ

በፍዳ በመርገም የመረረችውን ዓለም ያጣፈጠ የዓለም መድኀኒት ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ወልዳ ያስገኘችልን እናታችን ድንግል ማርያምም የኢያሪኮን ውሃ ምረት ያስወገደውን ጨው በያዘችው በኤልሳዕ ዐዲስ ማሰሮ ትመሰላለች (፪ነገ ፪፥፳)። ነቢየ እግዚአብሔር ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስን ሸኝቶ ዮርዳኖስን ተሻግሮ ኢያሪኮ ደረሰ፤ ወደዚያው ገብቶ ሃናይት ኀብረታ ለዛቲ ሀገር አለ፤ የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕን እነሆ ጌታችን እንደሚታይ የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው ወማየ ብሔሩሰ እኩይ ውእቱ የአገሩ ውሃ ግን ክፉ ነው፤ እንስትኒ ይመክና ወላዶች ሴቶች ሲጠጡት ይመክናሉ ደኽነኛው ሰውም ቢጠጣው በሽተኛ ይኾናል አሉት፤ ኤልሳዕም በውስጡ ጨው ጨምራችው ዐዲስ ማሰሮ አምጡልኝ አላቸው፤ እነሱም አመጡለት፤ ኤልሳዕም ውሃው ወዳለበት ምንጭ ወጥቶ፤ ጨው ጨምሮ ማሰሮውን ከቀበረ በኋላ እግዚአብሔር

199. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም ቍ ፴፯

www.ethiopianorthodox.org

እንዲኽ ይላል ይኽነን ውሃ ፈውሼዋለኍ፤ ከዚኽም በኋላ ሞትና ጭንገፋ አይኾንበትም አለ። ከዚያ ቀን ገሮምሮ ውሃው ከምሬቱ ተለውጦ ጣፍጦ በሽተኛ ቢጠጣው ጤነኛ፤ መካን ብትጠጣው የሚያስወልድ ኹኗል (፪ነገ ፪፥፲፱-፳፪)።

ለጊዜው እንዲኽ ተደርጓል ለኋላው ግን ምሳሌ ነበር፤ የውሃውን ምሬት ያጠፋውን ጨው የያዘችው ዐዲስ ማሰሮ፤ ከዓለም ፍዳ መርገምን ያጠፋ ጌታን የወለደች የቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትኾን፤ ጨዉ የጌታ፤ ውሃው የዚኽ ዓለም፤ ምሬት የፍዳ የመርገም ምሳሌ ነበር።

ኢትዮጵያዊዉ ሊቅ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ልዩ ምሳሌ ሲተረጉም *‹‹ኤልሳዕ ካዕበተ መንፈሱ ለሊቁ ነሥአ ወበዝብጠተ ሐሜለት ሰጠቆ ለማየ ዮርዳኖስ ወለነጺነ ማሕጼ አጽለሎ ዲበ ማየ ወገብረ ተአምረ ብዙኀ አንሥአ ሙታነ፤ ወአንጽሖ ለንእማን ዘለምጽ በማየ ዮርዳኖስ፤ ወምረተ ማይ ዘያመክን በጼው ቀሰመ ከመ ይለዳ መካናት ዘሰብአ ውእቱ ሀገረ ወአንጽሖ ርስሐት ኢክህለ ወኢቀሲመ ልስሐተ ነፍስ፤ ወልድኪሰ አንጽሖሙ ለልሙጻነ ሥጋ ወአንጽሖሙ ካዕበ ለሥኡባነ ነፍስ ወቀሰመ ዓዲ ልስሐተ ዓለም፤ በጼወ መለኮት ወቀሰም ካዕበ ለማይ ወረሰዮ ወይነ›* (ኤልሳዕም በመምህሩ ያደረ መንፈስ ቅዱስን ዕጥፍ ድርብ አድርጎ ተቀበለ፣ በመጠምጠሚያውም ምት የዮርዳኖስን ባሕር ከፈለው፤ የመጥረቢያውን ብረትም በውሃ ላይ አንሳፈፈው፤ ብዙ ተአምርንም ዐደረገ፤ ሙታንን አነሣ፤ በዮርዳኖስ ውሃ ለምጻሙ ንእማንን አነጻው፤ የሚያመክነውንም የውሃ ምሬት በጨው አጣፈጠ፤ መካኖች የሚኾኑ የዚያ ሀገር ሰዎች ይወልዱ ዘንድ (፬ነገ ፪፥፲፱-፳፩፤ ፭፥፲፬፤ ፮፥፮-፯)፤ ከነጢአት ማንጻትን የነፍስንም ምሬት ማጣፈጥን ግን አልቻለም ፤ ልጅሽ ግን የሥጋ ለምጻሞችን አነጻቸው፤ ዳግመኛም የዓለሙን ምሬት በመለኮቱ ጨውነት አጣፈጠ፤ ኹለተኛም ውሃውን አጣፍጦ የወይን ጠጅ ዐደረገው) (ማቴ ፰፥፪-፫፤ ዮሐ ፪፥፰-፱))[200]፤ በማለት ለ፳ሺሕ፭፻ ዘመን ከመድኀኒቷ ተለይታ፤ አልጫ ለኾነችው ዓለም መድኀኒት የኾነ መድኀኔዓለም ክርስቶስን ያስገኘችልን መኾኗን አስተምሯል።

ከ፬፻ በላይ መንፈሳውያት መጻሕፍትን ታላቁ የቤተክርስቲያናችን ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬምም በመጽሐፉ ላይ ይኽነን ሲያብራራ *‹‹አንቺን በሐዲስቱ ማሰሮ ገለጠሽ ፤ልጅሽም ለምንጩ ዐዲስ ሕይወትን የሰጠ ጨው ነው፤ በሱም ሙታ የነበረችው መላዋ ዓለም እንደገና ሕይወትን አገኘች ››* በማለት ለ፳ሺሕ፭፻ ዘመን በመሪር መርገም ሥር ወድቃ ሕይወቷን ላጣችው ዓለም ሕይወት የኾናትን ክርስቶስን ያገኘንባት ዐዲሲቱ ሸክላ ቅድስት ድንግል መኾኗን መስክሯል።

ሊቁ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም በልደት ድርሳኑ ላይ ይኽነንኑ ሲመሰክር ‹‹The new pitcher of Elisha has been explained to us...›› (ዐዲሲቱ የኤልሳዕ ጋን ምሳሌነቷ ምድርን ያረጋጋች የድንግል ምሳሌ እንደኾነች ለእኛ በግልጽ ታወቀ፤ በምንጩ ውስጥ የተጨመረው ጨውም የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ እርሱም ባልጣፈጠው ማንነታችን ላይ ጣዕሙን የጨመረልን ነው)[201] በማለት እመቤታችንን በማሰሮዋ፤ ጌታን ውሃውን ባጣፈጠው ጨው በመመሰል፤ በጌታ ሰው መኾን የሰው ድኅነት እንዳሰኙ በጥልቀት ተናግሯል።

በቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ የነገረ ማርያም አስተምህሮ ላይ ጥልቅ ጥናት ያጠናው የነገረ መለኮት ምሁሩ ጀምስ ይኽነን የቅዱስ ያዕቆብ ቃልን ሲያብራራ ‹‹The symbol of the "New pitcher of Elisha" is the best symbol...›› ዐዲስቱ የኤልሳዕ ጋን ቅዱስ ያዕቆብ የድኅነትን ጭብጥ መልእክት የድኅነትን ተስፋ ካሳየባቸው ምሳሌዎች ዋነኛዋ ናት፤ የጥሩ ውሃ ዕጦትና የፍሬ የለሿ ምድር፤ ኤልሳዕ ይኽነን ተአምር እንዲሠራ ሥር መሠረቱ ነበረች፤ ይኽም ኀጢአትን የተመላ የሰዎችን ኹኔታ ይመስላል፤ በሐዲስቱ ሸክላ ያለ ይኽ ጨው የሕዝቡን ኹኔታ ለወጠ፤ ይኽም ድርጊት ወደፊት ሊመጣ ያለውን የጌታ የሰው ዘርን የማዳን ውጤትን ያሳየ ነው፤ ይኽም ምልክት ድንግል ማርያም በነገረ ድኅነት ያላትን ድርሻ የሚጠቁመን ነው፤ የሕዝቡን አኗኗር የለወጠው ጨው ነው፤ ግን ጨው የተቀመጠው በዐዲስ ሸክላ ነው፤ ቅዱሳት መጻሕፍት ስናነብ ክርስቶስ እኛን እንዳዳነ ይናገራል፤ ይኸውም በሐዋ ሥራ ምዕ ፬፥፲፪ ላይ ‹‹መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና›› ሲል፤ በሕዝቡ የነበረው አኗኗር ኹኔታ የተለወጠው በክርስቶስ (በጨዉ) ሲኾን፤ ማርያምም (ዐዲሲቱ ሸክላ) ለሰው ዘር ኹሉ ያንን ጨው (ጌታን) የሰጠችን (ያስገኘችልን) ናት፤ በመኾኑም ይኽ

200. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘነሙስ ፳፥፵፳

201. Jacob Of Serugh, On The Nativity Of Our Lord, Et by T.Kollampampill,P 115





www.ethiopianorthodox.org

ምልክት ከድንግል ማርያም የአምላክ እናትነት ምስጢር ጋር የሥጋዌና የድኅነትን ምሥጢር በግልጽ ያሳያል) ሲል የሰጡ ዘር ኹሉ ተስፋነቷንና ነገረ ክርስቶስ (Christology) ከነገረ ማርያም (Mariology) ጋር ያለውን ጥብቅ ትስስር ገልጾታል።[202]

መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን ያጠፋ፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን ያደለ ጌታን የወለደችልን እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የውሃውን ምሬት ያስወገደውን ጨው በያዘችው ሸክላ ብቻ ሳይኾን፤የቅጠሉ ምሬት በተወገደባት በኤልሳዕ ማድጋ ትመሰላለች(፪ነገ ፬፡ ፴፰-፵፩)። ይኸውም በዘመነ ረኀብ ደቂቀ ነቢያት ተሰብስበው ወደ ኤልሳዕ ኼዱ፤እሱም ደቀ መዝሙሩ ግያዝን ጠርቶ፤ ታላቅ ማድጋ ጥደኽ ለነቢያት ልጆች ቅጠል ለቅመኽ ቀቅለኽ ስጣቸው አለው፤ እርሱም ክፉና በጎ ሳይለይ ለቅሞ አምጥቶ ሰጣቸው፤ እነሱም በቀመሱት ጊዜ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ በማድጋው ውስጥ ሞት አለ ብለው ጮኹ፤ ከምሬቱም የተነሣ መብላት ተሳናቸው፤ ኤልሳዕም የስንዴ ዱቄት አምጥተኽ አላትነኽ ስጣቸው አለው፤እሱም አላትኖ ቢሰጣቸው ምሬቱ ጠፍቶላቸው ጣፍጧቸው ተመግበዋል፤ ከዚኽ በኋላ በምንቸቱ ውስጥ ምሬት አልተገኘም።

ይኽም ለጊዜው ተደርጓል፤ ለኋላው ግን ምሳሌ ነው ፤ማድጋ የድንግል ማርያም፤ ቅጠል የትስብእት ፤ላቱን የመለኮት፤ ምሬት የፍዳ የመርገም ምሳሌ ነውና፤ ክብር ይግባውና መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን ነሥቶ መርገመ ሥጋ መርገመ ነፍስን በመሻሩ ሊቃውንት ቅድስት ድንግል ማርያምን በኤልሳዕ ማድጋ መስለዋታል፤ ሊቁ አባ ሕርያቆስም በቅዳሴ ማርያም ላይ ይኽነን ምስጢር በመያዝ «መስብክት ዘኤልሳዕ»(የኤልሳዕ ማድጋ አንቺ ነሽ)[203] በማለት አመስግኗታል።

## ዐጽቀ በለስ

በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን እያማለደች የምታሰጥ ቅድስት ድንግል ማርያም ንጉሥ ሕዝቅያስ እስከ ሞት ድረስ ከታመመ በኋላ እንደገና ከደዌው በተፈወሰባት በዐጽቀ በለስ ትመሰላለች (፪ነገ ፳፥፯)።

ይኽ ንጉሥ ሕዝቅያስ የታመመበትን ምክንያት መተርጉማን

202. Mariological Thoughts Of Mar Jacob Of Serugh, James Puthuparampil O.L.C. p 268

203. አባ ሕርያቆስ፤ ቅዳሴ ማርያም፤ ቍ ፴፫





እንደሚገልጹት ነቢያተ ሐሰት ሕዝቅያስን ወልድ የተባልኽ አንተ ነኽ፤ በቀኝ እጅኽ ሳትወረውር በግራ እጅኽ ሳትመክት ጠላት የጠፋልኽ፤ ድንግል የተባለች ኢየሩሳሌም ናት፤ የአሕዛብ አለንጋ ያልጮኸባት እንግዳ ፈረስ ያልረገጣት አለት፤ ሕዝቅያስም በትዕቢት እኽን ይኹናላ ብሎ የተናገረበት ልቡን ወግቶ ይዞታል፤ ያን ጊዜ ነቢዩ ኢሳይያስ ወደ እርሱ መጥቶ እግዚአብሔር ትሞታለኽ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትኽን አስተካክል ብሎኻል አለው፤ ያን ጊዜ ሕዝቅያስን እጅግ አድርጎ እያለቀሰ ጸሎቱን አቀረበ። ያን ጊዜ ጌታ ኢሳይያስን ለሕዝቅያስ ጸሎትኽን ሰምቻለኍ፤ እንባኽንም አይቻለኍ፤ እነሆ እፈውስልኻለኍ፤ በሦስተኛውም ቀን ወደ እግዚአብሔር ቤት ትወጣለኽ፤ በዕድሜኽም ላይ ዐሥራ ዐምስት ዓመት እጨምራለኍ ብለኽ ንገር ብሎ አዘዘው፤ ኢሳይያስም ዐጽቀ በለስ አምጡልኝ ብሎ ደመ በለሱን በእባጩ ላይ ቢአደርጉለት ተፈውሷል።

ያን ጊዜ ሕዝቅያስም ኢሳይያስን እስከ ሦስት ቀን ድረስ ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንድወጣ ከደዌዬም እንድፈወስ ምልክቱ ምንድን ነው? አለው ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደፊት ይኼድ ዘንድ፤ ወይም ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ ዘንድ ትወድዳለኽን? አለው፤ ሕዝቅያስም ጥላው ዐሥር ደረጃ ቢጨምር ቀላል ነገር ነው፤ ነገር ግን ጥላው ዐሥር ደረጃ ወደ ኋላ ይመለስ በማለት ሠርክ የነበረው ተመልሶ ሠለስት እንዲኾን ጠየቀ። ያን ጊዜ ኢሳይያስ ወደ ጌታ ቢአመለክት ጥላው በአካዝ የጥላ ስፍራ ሰዓት ላይ በወረደበት መንገድ ዐሥር ደረጃ ወደኋላ ተመልሶ ሠርክ የነበረው ተመልሶ ሠለስት ኾኗል (፪ነገ ፳፥፩-፲፩፤ ፪ዜና ፴፪፥፳፬፤ ኢሳ ፴፰፥፩-፳፪)።

ይኽቺ ሕዝቅያስ ከሞተ ሥጋ የተጠበቀባት ዐጽቀ በለስ ኹላችንም በምልጃዋ ከሞተ ነፍስ የምንጠበቅባት የቅድስተ ቅዱሳን የድንግል ማርያም ምሳሌ ናት፤ ይኸውም ሕዝቅያስ ከደዌው በዐጽቀ በለሲቱ ተፈውሶ በዕድሜው ላይ ዐሥራ ዐምስት ዓመት ተጨምሮለት በመንበረ መንግሥቱ ጸንቶ እንደኖረ ኹሉ፤ ምእመናንም የመስቀል ሥር ስጦታ በኾነችው በቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት ከሞተ ነፍስ ተጠብቀው በመንግሥተ ሰማያት ለዘላለም ጸንተው ይኖራሉ (መዝ ፺፬፥፱-፲፯፤ ፻፴፩፥፲፫-፲፯፤ ኢሳ ፩፥፱፤ ዮሐ ፲፱፥፳፭-፳፯)።

ሊቁ አባ ጊዮርጊስም ይኽነን ምስጢር በአርጋኖን መጽሐፉ «ኦ ድንግል



www.ethiopianorthodox.org

*ተውሳከ ዓመታቲሁ ለወልደ አካዝ ዘኮነ በትእምርተ ተመይጦተ ጽላሎት ውስተ ዐሠርቱ መዓርጋተ ጽርሕ››* (ድንግል ሆይ ወደ አዳራሹ ዐሥር እርከኖች በጥላው መመለስ ምልክት የኾነ የአካዝ ልጅ የሕዝቅያስ የሕይወቱ ዓመታት ጭማሪ ነሽ)[204] በማለት ሲያመሰግናት፤ በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ ምልጃዋ መድኀኒተ ነፍስ መኾኗን በአጽቀ በለስ መስሎ በማጉላት

*‹‹ርጢነ ሕዝቅያስ አንቲ ለዕፀ በለስ አፅሁቂ*

*አመ አልጸቀ ለመዊት ወደወየ በሕቁ››*

(በብርቱ ታሞ ለሞት በደረሰ ጊዜ የሕዝቅያስ መድኀኒት የበለስ ጫፍ አንቺ ነሽ)[205] በማለት አስተምሯል፡፡

# ማጠቃለያ

## ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር መመስከር እንደሚገባ

ዛሬም ጸሎቷ ቃል ኪዳኗ መድኀኒት የሚኾነን እኛ የተዋሕዶ ልጆች የፈጣሪያችን እናት በሉቃስ ወንጌል ምዕ ፩፥፵፰ ላይ ‹‹እነኾም ከዛሬ ዠምሮ ትውልድ ኹሉ ብጽዕት ይሉኛል›› በማለት የተናገረችውን ቃል በማክበር ከኦሪት ዘፍጥረት አንሥቶ በብዙ ሕብረ አምሳል የተገለፁትን ትንቢቶችና ምሳሌዎች ጠንቅቀን በመረዳት ንጽሕናዋን ቅድስናዋን ዘላለማዊ ድንግልናዋንና ቃል ኪዳኗን ስንመሰክርላት እንኖራለን (መዝ ፵፬፥፲፱-፲፯፤መሐ ፮፥፱፤ኢሳ ፵፱፥፳፫፤ ሚል ፬፥፪)፡፡

በአንጻሩ ግን ጌታችን በማቴ ፳፪፥፳፱ ‹‹መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኀይል አታውቁምና ትስታላችኁ›› በማለት እንዳስተማረ አንዳንዶች ሰዎች እነዚኽ ኹሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ክብሯ የተናገሩትን ባለመረዳት በድንቁርና የክሕደት ባሕር ውስጥ ጠልቀው በቃል ኪዳኗ ከሚገኘው ጸጋና በረከት ርቀው የጨለማ ገዞ በመንዝ ላይ ይገኛሉ(መዝ ፻፳፰፥፭፤ሮሜ ፲፮፥፲፯-፲፱፤ ፩ኛጢሞ ፩፥፯-፯፤፪ኛ ጢሞ ፫፥፩-፱፤፪ጴጥ ፫፥፲፯፤ይሁ ፲፯-፲፱፤ ራእ ፲፪፥፲፫-፲፯፤ ራእ ፲፫፥፯)፡፡

204. አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ አርጋኖን ዘዐርብ፤ ፳፥፱

205. እንዚራ ስብሐት ገጽ 30



ሊቁ ቅዱስ ሳዊሮስም በተረፈ ቄርሎስ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱሳን አበው ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ክብር የተነገሩትን በምሳሌ የተገለጹትን የቅዱሳት መጻሕፍትን ምስጢር ባለማወቃቸው ምክንያት፤ እሳተ መለኮት ቀዳማዊ አምላክን ፱ ወር ከ፭ ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች፤ ኪሩቤል ሱራፌል ከፊቱ ሊቀርቡ የማይቻላቸው እሱን በክንዷ የታቀፈች በዠርባዋ ያዘለች፤ በዝናብ አብቅሎ በፀሐይ አብስሎ የፈጠረውን ፍጥረት የሚመግበው ዐማኑኤልን የድንግልና ጡቶቿን ወተት የመገበችውን የወላዲተ አምላክን ክብር ያልተረዱትን ሰነፎች መናፍቃንን ሲወቅስ *‹‹ወለዛቲ እንተ መጠነዝ ዐባይ ጸረት መለኮተ እፎ ይክልእዎ እምክብራ ለወላዲተ አምላክ፤ ወላዲተ አምላክሰ ቅድስት ድንግል››* (ይኸነን ያኽል ታላቅ ኾና መለኮትን የተሸከመይቱን የአምላክ እናት ክብርን እንደምን ይነፍጓታል ይከለክሏታል፤ የአምላክ እናት ማለት ቅድስት ድንግል ናታ)[206] በማለት እንዳስተማረ፤ ቅድስት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን የኾነቺውን የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብርና ቅድስናን ዐውቃ፤ ከኦሪት ዘፍጥረት አንሥቶ ስለ እሷ በቅዱሳን አበው በቅዱሳን ነቢያት የተነገረውን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል፤በቅዱሳን ሐዋርያት የተበሰከውን፤ በቅዱሳን ሊቃውንት የተመሰጠረውን ምስጢር ዓለም እስከሚያልፍ ድረስ ስትመስክር ትኖራለች፡፡

ታላቁ የቤተክርስቲያን ሊቅ ቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግም የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን ዘላለማዊ ድንግልና በሚያስረዳው ድርሳኑ ትውልድ ኹሉ ብጽዕት የሚላት፤ በመላእክትም በሰው ልጆችም የምትመሰገን፤ በመጻሕፍተ ብሉያት በመጻሕፍተ ሐዲሳት ክብሯ የተነገረላት የቅድስት ድንግል ማርያምን ክብር በእውነት መመስከር እንደሚገባ ሲያስረዳ ‹‹በጽናት ቁም እውነቱንም ያለ ፍርሃት አስተምር ስበክ፤ ከጥርጣሬዎች በላይ የኾነውን እውነት በገሃድና በግልጽ አውጅ፤ አይሁዶችን ገሥጽ፤ አይሁዳዊ ያልኾኑትንም ውቀስ፤ ተቃዋሚዎችንም መልስ፤ የትምክሕተኞችንም ክርክር ቁረጥ፤ እብሪትንም ከነሱ ላይ አንሣ፤ ጠቢባንም ስለዚኽ ስለማይመረመር

206. ተረፈ ቄርሎስ፤ የብራና የእጅ ጽሑፍ ያልታተመ



www.ethiopianorthodox.org

ማሕፀን ከመናገር ገዘም እንዲሉ አርጋቸው፤ በዚኽም ስለወሊዷ በሚያደርጉት ሙግትና ክርክር ኀሊናቸውን እንዳያጡ ታደርጋለኽ፤ ዐዋቂዎች ነን የሚሉትን የዚያች የተባረከች ከኾነቿው ከእመቤታችን ማሕፀን ገለል እንዲሉ አርጋቸው፤ ሙግተኞችን ተሳስታችኊል በላቸው፤ በዚኽም ትጠቅማቸዋለኽ፤ እናም በታላቅ መገረም ወደ መደነቅ አምጣቸው፤ ድንቅ ከኾነቿው ከእመቤታችን የተወለደው ሥሙ ድንቅ ነው (ኢሳ፱፥፮)፤ እናንተ ጠቢባን ሆይ ወደዚኽ ኑና ሳትመራመሩ ተደነቁ፤ እናንተ ተከራካሪዎች ወደዚኽ ቅረቡ፤ የዳዊት ሴት ልጅ በኾነቿው በእመቤታችን ተደነቁ ... በፍቅርና በእምነት የተመላችኊ እና በመልካም ምግባር የታነጻችኊ ልጆች ሆይ፤ ይኽነን የምነግራችኹን በማስተዋል አድምጡኝ፤ የድንግል ማርያም ጉዳይ በጠቢባን የሚገለጽ (የሚብራራ) አይደለም፤ ብርቱ ተናጋሪዎችም በቃላቶቻቸው ሊናገሩት አይቻላቸውም፡፡ ክርክር የሌለበት ፍቅር ግን ስለ እሷ ሊናገር ይቻለዋል፡፡ ቃላቶቹ ቀሊላን ኾኖም ግን ከክርክር ቃላት በላይ ታላቅና ንጹሕ ናቸው)[207] በማለት በፍቅሯ በጣዕመ ፍቅሯ የጸኑ በቀናው ሃይማኖት የሚኖሩ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው ምእመናን እጅጉን ስለሚያስደንቀው ክብሯ፣ ንጽሕናዋ፣ ቅድስናዋ፣ ዘላለማዊ ድንግልናዋ፣ የአምላክ እናትነቷ ሲመሰክሩላት የሚኖሩ መኾኑን መስክሯል፡፡

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ካፈራቻቸው ሊቃውንት መኻከል አንዱ የኾነው አባ ጊዮርጊስም በቅዱሳት መጻሕፍት ስለእሷ የተነገሩት ኹሉ ፈጽመው ሊያበቁ አለመቻላቸውን በእንዚራ ስብሐት መጽሐፉ ላይ

*‹‹ኦ ድንግል ውዳሴ ንጽሕኪ ዕጹበ*
*ልሳንየ ላዕላዕ ኢይክል ነቢበ*
*እመ ተመላእኩ አእምሮ ወአፈድፈድኩ ጥበበ*
*ከመ ሰሎሞን ዘኮነ ላዕለ እስራኤል መኳብበ*
*እመኒ ላዕሌየ መንፈሰ ኤልያስ ተመክዓበ*
*ከመ ኤልሳዕ በቃሉ ነውረ ንእማን ዘሐጸበ*
*እመ ሰተይኩ ከመ ሰቁኤል ዘሕብረ እሳት አስራበ*
*ወዓጽቀ ልቡናየ እስከ አጽናፈ ምድር ለእመ ሰፍሐ ወርኀበ*

207. Jacob of Serugh, On the Perpetual Virginity of Mary



*ኵሉ ሥዕርትየ ወአዕጽምትየ ልሳነ መንፈስ እመ ተውህበ*
*ወእደ ኀሊናየ በሰሌዳ አእምሮ እመ ጠብጠበ*
*ማኀለቅቶ ለውዳሴኪ ኢይክል ረኪበ*
*ፍቅደ ከዋክብት ያንእስ ወዘደመናት ነጠብጣበ*
*አልቦቱ ኊልቍ ወሐሳበ ››*

(ድንግል ሆይ ዕጹብ የኾነ የንጽሕናሽን ምስጋና ለንባዳ አንደበቴ መናገርን አይችልም፤ በእስራኤል ላይ ንጉሥን (መምህርን) እንደ ኾነ ሰሎሞን ዕውቀትን ብመላ ጥበብንም ባበዛ፤ የንእማን ለምጽ በቃሉ እንዳነጻ እንደ ኤልሳዕ በኤልያስ ላይ ያደረ መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ ቢደራረብም (ዕጥፍ ድርብ ቢኾንም)፤ እንደሱቱኤልም የእሳት አምሳል ያለውን ጽዋ ብጠጣም፤ የልቡናዬ ቅርንጫፍ እስከ ምድር ዳርቻ ፈጽሞ ቢሰፋ፤ ጠጕሬና አጥንቴ ኹሉ የመንፈስ ቅዱስ አንደበትን ቢሰጠው፤ የኅሊናዬ እጅ በአእምሮ ሰሌዳ ቢጽፍም፤ የምስጋናሽን ፍጻሜ ማግኘት አይችልም፤ የከዋክብት ቍጥርንና የደመናት ነጠብጣብን ያሳንሳል፤ ፍጹም ቍጥርም የለውም)[208] በማለት እንዳስተማረ፤ ረድኤተ እግዚአብሔርን አጋዥ በማድረግ ከኦሪት ዘፍጥረት አንሥቶ እስከዚኽ ድረስ ስለእርሷ የተነገረውን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳል እንደገለጽኊ፤ ወደፊት በተከታታይ በምጽፋቸው የነገረ ማርያም መጻሕፍት፤ ከመጽሐፈ ነገሥት ቀጥለው የተነገሩትን ሕብረ ትንቢትና ሕብረ አምሳልን በስፋትና በጥልቀት የማቀርባቸው ይኾናል፡፡

## ይቀጥላል

208. እንዚራ ስብሐት፤ ገጽ 63



www.ethiopianorthodox.org

## <u>ዋቢ መጻሕፍት</u>

- *ሃይማኖተ አበው፤* 1982፤ አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
- መሠረት ስብሐት ለአብ፤ 1988፤ *ሥላሴ በተዋሕዶ፤* አዲስ አበባ
- *መጻሕፍተ ነገሥት አርባዕቱ ንባቡና ትርጓሜው፤* 2000፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት
- *መጽሐፈ ቅዳሴ ንባቡ ትርጓሜው፤* 1988፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማሳተሚያ ድርጅት
- ቅዱስ ቄርሎስ እስክንድርያዊ፤ *ድርሳነ ቄርሎስና ተረፈ ቄርሎስ* በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- *ተአምረ ማርያም፤* 1983፤ አዲስ አበባ፤ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት
- አስራደ ባያብል (ሊቀ ጠበብት)፤ 1998፤ *ማሕሌተ ጽጌ ትርጓሜ፤* አዲስ አበባ
- ________ 2001፤ *የሰቆቃወ ድንግል ትርጓሜ፤* አዲስ አበባ፤ ከሃሊ ማተሚያ ቤት
- *አሪት ዘፍጥረትና ኦሪት ዘፀአት ንባቡና ትርጓሜው፤* 1999፤ አዲስ አበባ፤ ትንሳኤ ማሳተሚያ ድርጅት
- *ኦሪት ዘፍጥረትና ኦሪት ዘፀአት ንባቡና ትርጓሜ፤* በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- ነገረ ማርያም፤ በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፤ 1958፤ *መጽሐፈ ሰዋሰው መግሥ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ፤* አዲስ አበባ፤ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
- *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፤* 1983፤ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት





- *ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፤* በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- ዐምደ ወርቅ እስጢፋኖስ (መምህር)፤ 1991፤ *አመቤታችን በቅዱስ ያሬድ ጸዋትወ ዜማ፤* ሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ፤ 7ኛ ዓመት ቁጥር 2
- ዐጤ ዘርዐ ያዕቆብ፤ *መጽሐፈ ብርሃን ፤*በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- ________ ፤1964፤ *መጽሐፈ ብርሃን፤* E.d.c. Conti Rossini corpus Scriptorum Christianorum Qrientulium
- ቅዱስ ያሬድ፤ 1988፤ *መጽሐፈ ድጓ፤* አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት
- ________ ፤*ጾመ ድጓ፤* አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት
- አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ፤ 2001፤ *መጽሐፈ ምስጢር፤* አዲስ አበባ፤ በአባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫና በአባ በጸሎተ ሚካኤል አንድነት ገዳም
- ________ ፤1998፤ *መልክአ ሕማማት፤ መዝሙር ዘዳዊት፤* አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት
- ________ ፤1993፤ *መጽሐፈ ሰዓታት፤* መጽሐፈ ሰዓታት ወመዝገበ ጸሎት፤ አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት
- ________ ፤*መጽሐፈ አርጋኖን፣ ኖኅተ ብርሃን፣ ዕንዚራ ስብሐት* በእጅ ጽሑፍ የሚገኝ ያልታተመ
- ________ ፤1960፤ *ዕንዚራ ስብሐት*: Ed. M.V.D. Oudenrijn In Corpus Scriptorium Christianoroum Orientalium
- አባ ጽጌ ድንግልና አባ ገብረ ማርያም፤ 1998፤ *ማሕሌተ ጽጌ፤ መዝሙር ዘዳዊት፤* አዲስ አበባ፤ አክሱም ማተሚያ ቤት፤ ገጽ 623-656
- Brock,s. 1994. *Bride of Light: Hymns on Mary from the syriac Churches.* Kerla, India: St. Joseph's Press.
- ________.1985. *The Luminous Eye: The Spiritual World Vision of St. Ephrem.*




www.ethiopianorthodox.org

- Ephrem. 1994. *Commentary on Genesis, in St. Ephrem the Syrian: Selected prose Works*, ed., Mc Vey, K., Washington
- ____. 1989. *Hymns on the Nativity, in Ephrem the Syrian Hymns*, ET by Mc Vey,k., New York
- Irenueus. 1995. *Adversus Heresies, ET in Ante Nicean Fathers.*, *Massachusetts*: Hendrickson Publishers
- Jacob of Serugh. 1995. *A Metrical Homily on Holy Mar Ephrem by Mar Jacob of sarug*, ed., J.p., Turnout
- ____.2005. *Homily on the Perpetual Virginity of Mary.*, ET by Puthuparampil O.I.C, India
- ____.1998. *On The Mother of God.*, ET by Hansbury, New York
- ____.1997. *Select Festal Homilies.*, ET by kollamparampil., Rome
- James Puthuparampil O.I.C. 2005. *Mariological Though of Jacob of Scrugh*, **Karla.**




www.ethiopianorthodox.org